# መጽሐፈ ፡ ግብረ ፡ ሕማማት።

## በግእዝና ፡ በአማርኛ።

ይህ ፡ መጽሐፈ ፡ ግብረ ፡ ሕማማት ፡ በብፁዕ ፡ ወቅዱስ ፡ አቡነ ፡ ጳውሎስ ፡ ፓትርያርክ ፡ ርእሰ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ ዘኢትዮጵያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳስ ፡ ዘአክሱም ፡ ወዕጨጌ ፡ ዘመንበረ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ በ፲፮ኛው ፡ ዘመነ ፡ ፓትርያርክነት ፡ ለመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ በግእዝና ፡ በአማርኛ ፡ ታተመ።

__አሳታሚ__ ፡– ትንሣኤ ፡ ማሳተሚያ ፡ ድርጅት፡
አ·አ· ፲፱፻፺ ፡ ዓ·ም

## ምዕራፍ፡፳።

ትእዛዝ ፡ ወይትጋብኡ ፡ ካህናት ፡ በዕለተ ፡ ሠሉስ፡ጊዜ፡ነግህ፡ወይግበሩ፡ጸሎተ፡በከመ፡ ተጽሕፈ ፡ በዕለተ ፡ ሰኑይ ፡ በጊዜ ፡ ነግህ።ወ ይበል፡መራሒ፡በ፫፡ስምዕዎኬ።
ወይበሉ፡ለከ፡ኃይል።

### ክፍል፡፩።
### አሪት፡ዘፀአት።

ምዕ፤፲፱፡፩-፳፤

፩፤ ወበሣልስ ፡ ወርኅ ፡ እምዘወጽኡ ፡ ውሉደ፡

## ምዕራፍ፡፳።

ካህናቱ ፡ ማክሰኞ ፡ በነግህ ፡ ተሰብስበው፡ ሰኞ ፡ በነግህ ፡ እንደ ፡ ተጻፈ ፡ ጸሎት፡ ያድርጉ ፤ መሪውም ፡ በአንድ ፡ ሃሌታ፡ ስምእዎኬ፡ይበል።
ወይበሉ፡ለከ፡ኃይል።

### ክፍል፡፩።
### አሪት፡ዘፀአት።

ምዕ፤፲፱፡፩-፳፤

፩፤ በሦስተኛውም ፡ ወር የእስራኤል ልጆች

Scanned by CamScanner

## በ፩፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘሠሉስ፡ነግህ።

እስራኤል፡እምድረ፡ግብፅ፡በዛቲ፡ዕለት።

፪ ወጽኡ ፡ ወሐሩ ፡ እምራፌድ ፡ ወበጽሑ ፡ ውስተ፡ገዳም፡ዘሲና፡ወኀደሩ፡ህየ፡መንፀረ፡ደብሩ።

፫ ወሙሴ ፡ ዐርገ ፡ ውስተ ፡ ደብረ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወጸውዖ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለሙሴ፡እምዲበ፡ደብር፡ወይቤሎ፡በሎሙ፡ለቤተ ፡ ያዕቆብ ፡ ወዜንዎሙ ፡ ለውሉደ ፡ እሥራኤል።

፬ ወአንትሙ፡ርኢክሙ፡መጠነ፡ገበርክዎሙ፡ለግብጽ፡ወነሣእኩክሙ፡ከመ፡ክንፈ፡ጕዛ፡ወአቅረብኩክሙ፡ኀቤየ።

፭ ወይእዜኒ፡ለእመ፡ሰማዕክሙኒ፡ቃልየ፡ወዐቀብክሙ ፡ ትዕዛዝየ ፡ ትከውኑኒ ፡ ሕዝበ ፡ ዘጽድቅ፡እምኵሉ፡አሕዛብ፡እስመ፡ዚአየ፡ይእቲ፡ኵለንታሃ፡ምድር።

፮ ወአንትሙ ፡ ትከውኑኒ ፡ እለ ፡ መንግሥት ፡ እለ፡ ትሠውዑ ፡ ሊተ ፡ ወሕዝበ ፡ ዘጽድቅ ፡ ዘ ፡ ቃለ ፡ አይድዖሙ ፡ ለውሉደ ፡ እሥራኤል።

፯ ወመጽአ፡ሙሴ፡ወጸውአ፡ሊቃናተ፡ሕዝብ፡ወአይድዖሙ፡ኵሎ፡ቃለ፡ዘአዘዞ፡እግዚአብሔር።

፰ ወአውሥኡ ፡ ኵሎ ፡ ዘአዘዘነ ፡ እግዚአብሔር ፡ ንገብር ፡ ወንሰምዕ ፡ ወአዕረገ ፡ ሙሴ ፡ ቃለ ፡ ሕዝብ ፡ ኀበ ፡ እግዚአብሔር።

ዘኢዮብ፡ጻድቅ፡በረከቱ፡ትኩን፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

ምዕ፡፴፫፡፩–፲፯።

፩ ወእደ ፡ ተናገረ ፡ ኢዮብ ፡ ወተሰጥወ ፡ ወይቤ።

፪ አንሰ፡አእመርኩ፡ከመ፡እምእዴየ፡ውእቱ፡ዘለፋየ ፡ ወአክበደ ፡ እዴሁ ፡ ላዕሌየ ፡ ወአግዐረኒ።

፫ ምንት ፡ ውእቱ ፡ ኃጢአትየ ፡ ዘኢየአምር ፡ ከመ፡ እርከብ ፡ ወእብጻሕ ፡ እስከ ፡ ለዝሉፉ ፡ አእምር።

## ማክሰኞ፡መዓልት፡በ፩፡ሰዓት፡ነግህ።

ከግብጽ፡ምድር፡ከወጡ፡በኋላ፡በዚያች፡ቀን፡ወደ፡ሲና፡ምድረ፡በዳ፡መጡ።

፪ ከራፌድ ፡ ወጥተው ፡ በደብረ ፡ ሲና ፡ ወዳለ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ደረሱ ፤ በተራራውም ፡ ፊት ፡ ለፊት፡ሰፍረው፡አደሩ።

፫ ሙሴም፡እግዚአብሔር፡ወደ፡ተገለጠባት፡ወደ፡ደብረ፡ሲና፡ወጣ።እግዚአብሔርም፡ሙሴን፡በተራራው፡ላይ፡ሁኖ፡ጠራው።የያዕቆብን ፡ ወገኖች ፡ የእስራኤልንም ፡ ልጆች ፡ እንዲህ፡አለ፡ብለህ፡ንገራቸው፡አለው።

፬ በግብጻውያን፡ሰዎች፡ያደረግሁባቸውን፡መጠን፡እናንተ ፡ አያችሁ ፤ እናንተ ፡ ግን ፡ ጭላት ፡ ጫጩቶቿን ፡ በክንፏ ፡ እቅፍ ፡ አድርጋ፡ እንድ ትይዝ፡እኔም፡በረድኤት፡ወደ፡እኔ፡አቀረብኋችሁ።

፭ አሁንም ፡ ቃሌን ፡ ብትሰሙ ፡ ትእዛዜንም ፡ ብትጠብቁ ፡ ምድር ፡ ፈጽማ ፡ የኔ ፡ ገንዘብ ፡ ናትና ፡ ከአሕዛብ ፡ ሁሉ ፡ ተለይታችሁ ፡ እውነተኛ፡ወገን፡ትሆኑኛላችሁ።

፮ የመንግሥት ፡ ወገኖችን ፡ መሥዋዕትንም ፡ የምትሰዉልኝ፡የእውነት፡ወገንም፡ትሆኑኛላችሁ፡ብለህ፡ለእስራኤል፡ልጆች፡ይህንን፡ቃል፡ንገራቸው፡አለው።

፯ ሙሴም፡መጥቶ፡የሕዝቡን፡አለቆች፡ጠርቶ፡እግዚአብሔር ፡ ያዘዘውን ፡ ቃል ፡ ሁሉ ፡ ነገራቸው።

፰ ሕዝቡም ፡ ሁሉ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያዘዘንን ፡ ቃል፡ሁሉ፡ሰምተን፡እናደርጋለን፡ብለው፡በአንድ፡ቃል፡መለሱ።ሙሴም፡የሕዝቡን፡ቃል፡ወደ፡እግዚአብሔር፡አደረሰ።

ጻድቁ፡ኢዮብ፡የተናገረው፡ይህ፡ነው፤በረከቱ፡ከእኛ፡ጋራ፡ለዘላለሙ፡ትኑር፡አሜን።

ምዕ፡፴፫፡፩–፲፯።

፩ ኢዮብ ፡ ከተናገረና ፡ ከመለሰም ፡ ዘንድ ፡ እንዲህ፡አለ።

፪ እኔ፡ይህ፡ያገኘኝ፡መከራ፡ከተናገርኩት፡ነገር፡የተነሣ፡እንደ፡ሆነ፡አወቅሁ፤እጁ፡መዓቱን፡አጸናብኝ፤በመከራውም፡አስጨነቀኝ።

፫ ከሕፃንነቴ ፡ ጀምሬ ፡ እስካረጅ ፡ ድረስ ፡ መርምሬ፡አውቅ፡ዘንድ፡እኔ፡የማላውቀው፡ኃጢአቴ፡ምንድነው?

Scanned by CamScanner

በ፩፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሠሉስ፡ነግህ።

፬፡ ወይንግረኒ፡እመቦ፡ዘገበርኩ፡ወኢያረምም፡ አፉየ፡እንዘ፡እወቅስ።

፭፡ ወአእምር፡ሊተሂ፡ከመ፡ይሁበኒ፡ፈውሰ፡ ወለበውኩ፡ዘይሁበኒ።

፮፡ ወእመሂ፡በብዙኅ፡ኃይል፡ይመጽእ፡ ኢይገብር፡እንከ፡በመዓቱ፡ላዕሌየ፡እስመ፡ ማህል፡ወጽድቅ፡ኅቤሁ።

፯፡ ወያዐርፈኒ፡ለዝሉፉ፡እምዅነኔየ፡እስመ፡ እገብእ፡ኀበ፡ቀዲሙ።

፰፡ ወኢይሄሉ፡እንከ፡ወኢየአምር፡እንከ፡ ደኀሪታ።

፱፡ እገብእ፡እንከ፡መንገለ፡ፀጋም፡ወኢያጸምዕ፡ ወእትመየጥ፡መንገለ፡የማን፡ወአልቦ፡ ዘእሬኢ፡ወድአ።

፲፡ ወእደ፡አእምር፡ፍኖትየ፡ወፈተነኒ፡ከመ፡ ወርቅ።

፲፩፡ ወኢይወጽእ፡እምተግሣፀ፡ወዐቀብኩ፡ ፍናዊሁ፡ወኢተግኅሥኩ።

፲፪፡ ወኢኀለፍኩ፡እምትእዛዙ፡ወኅባእኩ፡ነገሮ፡ ውስተ፡ሕፅንየ።

፲፫፡ ወመኑ፡ውእቱ፡ዘይትዋቀሶ፡በእንተ፡ዅነኔ፡ እስመ፡ውእቱ፡ዘፈቀደ፡ይገብር።

፲፬፡ ወበእንተዝ፡አነሂ፡ጕጓእኩ፡በእንቲአሁ፡ ወተገሣፅየ፡ኀለይክዎ።

፲፭፡ ወበእንተዝ፡ደንገፅኩ፡እምቅድመ፡ገጹ፡ እኄልዮሂ፡ወይጌርመኒ፡እግዚአብሔር።

፲፮፡ መሰዎ፡ለልብየ፡ወዘዅሎ፡ይመልክ፡ አጕጕዓኒ።

፲፯፡ በአይቴ፡አእመርኩ፡ከመ፡ትመ ጽአኒ፡ጽልመት፡ወደፈነኒ፡ቆባር፡ውስተ፡ ገጽየ።

ምዕ፡፹፱፡፩-፳፭።

፩፡ ለምንት፡ይረስዖን እግዚአብሐር፡ለሰዓ ታትየ።

፪፡ ወተዓደዉ፡ኃጥአን፡እምወሰኖሙ፡

ማከሰኞ፡መዓልት፡በ፩፡ሰዓት፡ነግህ።

፬፡ ያደረግሁትም፡ነገር፡ቢኖር፡ይንገረኝ፤ያለ፡ ኃጢአቴ፡መከራ፡መጣብኝ፡እያልኩ፡ ስወቅስ፡አፌ፡ዝም፡አይልም።

፭፡ ድኅነትን፡ለኔ፡እንዲሰጠኝ፡አወቅሁ፤የሚሰ ጠኝንም፡መረመርኹ።

፮፡ ቸርነትና፡ይቅርታ፡በሱ፡ዘንድ፡አሉና፡ በብዙ፡ኃይልም፡ወደኔ፡ቢመጣ፡ተቆጥቶ፡ በእኔ፡ክፉ፡ሥራ፡አይሠራብኝም።

፯፡ ከሚፈርድብኝም፡ፍርድ፡ፈጽሞ፡ያሳርፈኛል፤ ወደ፡ጥንቱ፡ተድላ፡ደስታዬ፡እመለሳለሁና።

፰፡ እንግዲህ፡ወዲያ፡በመከራው፡አልኖርምና፤ ኋላ፡ግን፡የማገኛትን፡ተድላ፡ደስታ፡ ፍጻሜዋን፡አላውቅም።

፱፡ ወደ፡ግራ፡እመለሳለሁ፤ያገኘሁት፡ግን፡ የለም፡ወደ፡ቀኝም፡እመለሳለሁ፤የማየው፡ ግን፡ፈጽሞ፡የለም።

፲፡ ካወቅሁ፡ዘንድ፡ወርቅን፡በእሳት፡እንዲፈ ትኑት፡በመከራው፡ፈተነኝ።

፲፩፡ ነገር፡ግን፡ከሕጉ፡አልወጣሁም፤ሕጉንም፡ ጠበቅሁ፤ከእርሱም፡አልራቅሁም።

፲፪፡ ከትእዛዙም፡አልወጣሁም፤ነገሩንም፡ በልቡናዬ፡አስተዋልሁ።

፲፫፡ እሱ፡የወደደውን፡ያደርጋልና፡ስለሚፈ ርደው፡ፍርድ፡የሚቃወመው፡ማነው?

፲፬፡ መከራ፡ስላመጣበኝ፡ስለዚህ፡ነገር፡እኔም፡ ለመለመን፡ቸኰልሁ፤መከራውንም፡ ተቀብዬ፡እሱን፡አሰብኹት።

፲፭፡ ስለዚህ፡ነገር፡ከገጸ፡መዓቱ፡የተነሣ፡ ደንገጥኹ፤እኔም፡አስበዋለሁ፤እግዚአ ብሔር፡ግን፡ያስፈራኛል።

፲፮፡ ልቡናዬን፡እንደ፡ሰም፡አቀለጠው።ሁሉን፡የሚ ገዛ፡እግዚአብሔርም፡በመከራው፡አጣደፈኝ።

፲፯፡ ጨለማ፡(መከራይቱ)፡እንድትመጣብኝ፡ ወዴት፡አወቅሁ?ጭጋግም፡(መከራውም)፡ ፊቴን፡ሸፈነኝ።

ምዕ፡፹፱፡፩-፳፭።

፩፡ እግዚአብሔር፡ዘመኖቼን፡ለምን፡ይዘነጋ ቸዋል?

፪፡ ኃጥአንም፡ከወሰናቸው፡

በ፫፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሠሉስ፡ነግሀ።

**ወመሠጡ፡ኖላዌ፡ምስለ፡መርዔቱ።**

፫፤ ወሄዱ ፡ አድግ ፡ ዕጓለ ፡ ማውታ ፡ ወአኅዙ ፡ ላሕመ፡ዕቤር።

፬፤ ወሜጥዎሙ ፡ ለድኩማን ፡ እምፍኖተ ፡ ጽድቅ ፡ ወተጋብኡ ፡ ኅቡረ ፡ የዋሃነ ፡ ምድር።

፭፤ ወኮኑ ፡ ከመ ፡ አእዱግ ፡ ውስተ ፡ ገዳም ፡ በእንቲአየ ፡ ወጽኡ ፡ ወኀደጉ ፡ ተግባሮሙ ፡ ወጥዕሞሙ ፡ እክል ፡ እምንእሰሙ።

፮፤ አኮኑ ፡ ገራህተ ፡ ዘኢኮነ ፡ ዚአሆሙ ፡ አረሩ፡እምቅድመ፡ሰዓቱ፡ወቀነይዎሙ፡ለባሕታውያን ፡ ዓፀደ ፡ ወይኖሙ ፡ ዘእንበለ ፡ ዓስብ፡ ወዘእንበለ ፡ ሲሳይ ፡ ተዓገልዎሙ ፡ ኃጥአን።

፯፤ ወለብዙኃን ፡ ዕሩቃን ፡ አቤትዎሙ ፡ ዘእንበለ ፡ ልብስ ፡ ወሰለብዎሙ ፡ አራዘ ፡ ነፍሶሙ።

፰፤ ወያርሕሶሙ፡ነፍኒፍ፡ወጠለ፡ገዳም፡እስመ፡አልቦሙ፡ክዳን፡ወተከድኑ፡ጸላእተ።

፱፤ ወመሰጡ፡ዕጓለ፡ማውታ፡እምውስተ፡ጥቡ፡ወአሕመምዎሙ፡ለፅኑሳን።

፲፤ ወገፍዕዎሙ፡ ለጽኑሳን ፡ ወነጽሕዎሙ ፡ ወሄድዎሙ፡ለርኁባን፡አፍእሞቶሙ።

፲፩፤ ወአሥርኅዎሙ ፡ ለምንዱባን ፡ ወተዓገልዎሙ፡ወኢያእመርዋ፡ለፍኖተ፡ጽድቅ።

፲፪፤ ወሰደድዎሙ ፡ እምአብያቲሆሙ ፡ ወእምአህጉሪሆሙ ፡ ወአግዐሩ ፡ ነፍሰ ፡ ሕፃናት ፡ ፈድፋደ።

፲፫፤ ለምንት ፡ ውእቱ ፡ ኢገሠፆሙ ፡ ለእሉ ፡ አምጣነ፡ሀለዉ፡ዲበ፡ምድር፡ወኢያእመርዋ፡ወኢርእይዋ ፡ ለፍኖተ ፡ ርትዕ ፡ ወኢሖሩ ፡ ውስተ፡መርኅባ።

፲፬፤ ወአእሚሮ፡ምግባሮሙ፡መጠዎሙ፡ውስተ፡እደ፡ጽልመት፡ወተረሲዮሙ፡ሌሊተ፡ከመ፡በረቂ።

፲፭፤ ዓይነ ፡ ዘማዊ ፡ ይጸንሕ ፡ ጽልመተ ፡ ወይብል ፡ አልቦ ፡ ዘይሬእየኒ ፡ ወይሜውር ፡ እምገጽ።

ማክሰኞ፡መዓልት፡በ፫፡ሰዓት፡ነግሀ።

**እረኛውን፡ከመንጋው፡ጋር፡ነጥቀው፡ወሰዱ።**

፫፤ የድኻ፡አደጉን፡ልጅ፡አህያ፡ቀሙ፤የባልቴቲቱንም፡ላም፡ያዙባት።

፬፤ በኃጢአት ፡ የደከሙ ፡ ሰዎችን ፡ ከእውነተኛው፡ ሕግ፡መለሱአቸው፤እነሆ፡የዋሆች፡ችግረኞች፡አንድ፡ሁነው፡ተሰበሰቡ።

፭፤ ስለ፡እኔ፡እንደ፡ምድረ፡በዳ፡አህዮች፡ኾኑ፤ሥራቸውን፡ትተው፡ወጡ፤ከሕፃንነታቸው፡ጀምሮ፡እህል፡ጣማቸው፡(ጨው፡ጨው፡አላቸው)።

፮፤ የነሱ ፡ ያይደለውን ፡ እርሻ ፡ ከመድረሱ ፡ አስቀድሞ፡የለቀሙ፡አይደለምን፡ኃጢአት፤የሚሠሩ ፡ እነዚህ ፡ ድኆችን ፡ ሳያበሉ ፡ ገዙአቸው ፤ ዋጋ ፡ ሳይሰጡ ፡ የወይን ፡ ቦታቸውንም፡ቀሚቸው።

፯፤ የታረዙ፡ብዙ፡ሰዎችን፡ያለ፡ልብስ፡ራቁታቸውን ፡ አሳደሩአቸው ፤ የሚለብሱትንም ፡ ልብስ፡ከሰውነታቸው፡ገፈፉአቸው።

፰፤ የዱር፡ጤዛና፡ካፊያው፡ያርሳቸዋል፤ልብስ፡የላቸውምና፡ዋሻውን፡ልብስ፡አደረጉ።

፱፤ የድኻውንም ፡ ልጅ ፡ ከጡቱ ፡ ለይተው ፡ ወሰዱት፤ችግረኞችንም፡መከራ፡አጸኑባቸው።

፲፤ የተቸገሩትን ፡ ሰዎች ፡ በደሉአቸው ፤ ጣሏቸውም፤የተራቡ፡ሰዎችንም፡እንጐርሰዋለን፡ያሉትን፡ቀሚቸው።

፲፩፤ የተቸገሩትን፡ሰዎች፡አደከሚቸው፤ገንዘባቸውንም ፡ ቀሚቸው ፤ እውነተኛይቱንም ፡ መንገድ፡(ሕግ)፡አላወቋትም።

፲፪፤ ከቤታቸው፡አወጧቸው፤ካገራቸው፡አስወጥተው፡ሰደዱአቸው፤የልጆችንም፡ሰውነት፡ፈጽመው፡አስጨነቁ።

፲፫፤ በዚህ፡ዓለም፡ሳሉ፡እሱ፡እነዚህን፡ለምን፡አልገሠፃቸውም?የቀናችና፡እውነተኛይቱን፡ሕግ ፡ አላወቋትም ፤ አልጠበቋትም ፤ በሥርዓቷም፡ጸንተው፡አልኖሩምና።

፲፬፤ እሱም፡ክፉ፡ሥራቸውን፡አውቆ፡ለመከራ፡አሳልፎ ፡ ሰጣቸው ፤ እንደ ፡ ሌባም ፡ ጨለማውን፡ለብሰው፡ይመጣሉ።

፲፭፤ የዘማዊ፡ዓይን፡ጨለማውን፡ይጠብቃል፤የሚያየኝ፡አይኖርም፡ይላል፤ከሰውም፡ፊት፡ይሠወራል።

Scanned by CamScanner

## በ፩፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሠሉስ፡ነግህ።

፲፮፡ ወይከሪ፡ አብያተ፡ በጽልመት፡ መዐልተሰ፡ ይትኀብኡ፡ወኢይሬእዩ፡ብርሃነ።

፲፯፡ ወእምከመ፡ ጽብሐ፡ ይመስሎሙ፡ ለኵሎሙ፡ ጽላሎተ፡ ሞት፡ እስመ፡ የአምሩ፡ ሀከከ፡ ዘይከውን፡ ወይትሔዘቡ፡ መዊተ።

፲፰፡ ወይጼለል፡ዲበ፡ገጸ፡ማይ፡ርጉም፡መክፈልቶሙ፡ዲበ፡ምድር።

፲፱፡ ወይሬእዩ፡እንዘ፡ይየብስ፡ተክሎሙ፡በዲበ፡ምድር፡ ወበርበርዎሙ፡ ለዕጓለ፡ ማውታ፡ እለ፡ቦ።

፳፡ ወእምዝ፡ ይዜከራ፡ ሎቱ፡ ለኃጢአቱ፡ ወይጠፍእ፡ ከመ፡ ጊሜ፡ ወጠል፡ ወይትፈደይ፡ በከመ፡ ገብረ፡ ወይትቀጠቀጥ፡ ከመ፡ ዕፅ፡ ብኍቡኍ፡ ኵሉ፡ ዓማፂ።

፳፩፡ ለመካንሂ፡ኢያሠነየ፡ወለእንተ፡ትወልድሂ፡ ኢመሐረ።

፳፪፡ ወአንሐሎሙ፡ በመዓቱ፡ ለጽኑሳን፡ ወተንሢኦ፡ኢይትአመና፡ለሕይወቱ።

፳፫፡ ወእመ፡ደወየ፡ኢይሴፎ፡ሐዪወ፡ዳእሙ፡ ይወድቅ፡ውእቱ፡በሕማም።

፳፬፡ ወለብዙኃን፡ አመንደቦሙ፡ በሢመቱ፡ ወይጸመሂ፡ከመ፡መሎኬ፡በውስተ፡ሐሩር፡ ወከመ፡ ሰዊት፡ ዘይወድቅ፡ ለሊሁ፡ እምቀርሙ።

፳፭፡ ወእመ፡አኮ፡መኑ፡ውእቱ፡ዘይብለኒ፡ሐሳዊ፡ አንተ፡ ወይሬስዮ፡ ከመ፡ ወኢምንት፡ ለነገርየ።

### ትርጓሜ፡ኢዮብ።

አእምር፡ከመ፡እምኔሁ፡ዘለፋየ፡እስከ፡ኅበ፡ ይብል፡ወኢምንት፡ለነገርየ።

፩፡ ይቤ፡ መተርጕም፡ አንሰ፡ አእምር፡ ከመ፡ እምኔሁ፡ ዘለፋየ፡ ይብል፡ ዘንተ፡ በእንተ፡

## ማክሰኞ፡መዓልት፡በ፩፡ሰዓት፡ነግህ።

፲፮፡ በጨለማው፡ ወንዳወንዴውን፡ ይነቅላል፡ በቀን፡ግን፡ይሠወራሉ፤ብርሃንንም፡አያዩም።

፲፯፡ በነሱ፡ምክንያት፡የሚሆነውን፡ጸብ፡ክርክር፡ ያውቃሉና፡ሞታቸውንም፡ይጠራጠራሉና፡ ከነጋ፡በኋላ፡ሁሉንም፡ሞት፡የሚአገኛቸው፡ ይመስላቸዋል።

፲፰፡ በፈሳ፡በቀጤማውም፡መካከል፡ተሠውሮ፡ ይኖራል፤ በዚህም፡ ዓለም፡ ዕድል፡ ፈንታቸው፡የተረገመ፡ነው።

፲፱፡ በምድር፡ላይ፡ተክላቸው፡ሲደርቅ፡ያያሉ፡ የድኻ፡ አደጉንም፡ ልጅ፡ ገንዘቡቹን፡ በረበሩት።

፳፡ ከነሱ፡ አንዱም፡ ከዚያ፡ በኋላ፡ የሠራት፡ ኃጢአቱን፡ያስባታል፤እንደ፡ጠልና፡እንደ፡ ጉም፡በንኖ፡ይጠፋል፤እሱ፡በሌላው፡እንዳደረገ፡ በርሱም፡ፍዳ፡ይደረግበታል፤ዐመፀኛም፡ሁሉ፡ እንደ፡በሰበሰ፡እንጨት፡ይጠፋል።

፳፩፡ ልጅ፡ለሌላትም፡ለመካን፡ሴት፡በጎ፡ነገርን፡አላ ደረገላትም፤ለወላድም፡ሴት፡አልራራላትም፡

፳፪፡ የተቸገሩትንም፡ ሰዎች፡ ተቆጥቶ፡ አጠፋቸው፤ ከመኻታውም፡ በተነሣ፡ ጊዜ፡ ደኅንነቱን፡አይተማመናትም።

፳፫፡ በመከራው፡ ተይዞ፡ ይጨነቃል፡ እንጂ፡ ቢታመም፡እድናለሁ፡አይልም።

፳፬፡ በተሾመበትም፡ ወራት፡ ብዙ፡ ሰዎችን፡ አስ ጨነቃቸው፤ አመድማዶ፡ በድርቅ፡ እንዲጠወልግ፡ በመከራው፡ ይጠወልጋል፤ ከቃር ሚያው፡ የወደቀ፡ እሸት፡ እንዲጠወልግ፡ እሱም፡በመከራው፡ይወድቃል።

፳፭፡ ነገርን፡ እንዲህ፡ አድርጌ፡ ሳውቅ፡ አንተ፡ ሐሰተኛ፡ ነህ፡ የሚለኝ፡ ነገሬንም፡ እንደ፡ ኢምንት፡የሚአደርገው፡ማነው?

### የኢዮብ፡ትርጓሜ።

አእምር፡ከመ፡እምኔሁ፡ዘለፋየ፡ከሚለው፡ጀምሮ፡ ወኢምንት፡ለነገርየ፡እስከሚለው፡ድረስ።

፩፡ ተርጓሚው፡እንዲህ፡አለ፤መገሠጼ፡ከእርሱ፡ እንደ፡ሆነ፡አወቅሁ፡ያለው፡በገንዘቡ፡ጥፋት፡

Scanned by CamScanner

## በ፩፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘሠሉስ፡ነግህ።

ዘረከቦ ፡ ውስተ ፡ ንዋዩ ፡ ወደቂ ፡ ወሥጋሁ ፡
ወሰመዮ፡ለውእቱ፡ዘለፋ።
፪ በከመ፡ይቤ፡ጳውሎስ፡ሐዋርያ፡እስመ፡እግዚ
አብሔር፡ይጌሥፆሙ፡ለውሉድ፡ዘአፍቀረ።
፫ ይቤ ፡ ወእዴሁ ፡ ከብደት ፡ ላዕለ ፡ ገዐርየ ፡
ይብል፡እስመ፡ኃይለ፡እግዚአብሔር፡ሞአት፡
ኀሊናተ፡ዘዚአሁ፡ዘላዕሌሁ፡እስመ፡ሰመያ፡
ለኀይለ፡እግዚአብሔር፡እደ።
፬ ይቤ፡ከመ፡ከብደት፡ዘውእቱ፡ተሰውጠት፡
ላዕለ፡ኀሊናት፡ወገዐር፡ከመ፡ከልአቶሙ፡
እምኔሁ።
፭ ይቤ፡ወመኑ፡የአምር፡ከመ፡አነ፡እረክቦ፡
እስመ፡ኢይበጽሕ፡ኀበ፡ተፍጻሜት፡ከሠተ፡
ሎቱ ፡ እግዚእ ፡ ከመ ፡ ኵሉ ፡ ዘታሕተ ፡
አርዐተ፡ ብሊት ፡ ንቱግ ፡ ውእቱ ፡ ወኢይ
በጽሕ፡ኀበ፡ተፍጻሜት፡አሐዱሂ፡ዘእንበለ፡
እግዚእነ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ።
፮ ወበእንተ ፡ ውእቱኬ ፡ ይቤ ፡ መኑ ፡ የአምር ፡
ከመ ፡ አነ ፡ እረክቦ ፡ ዝ ፡ ውእቱ ፡ ዝንቱ ፡
ትዕግሥት፡ዘተዐገሥክዎ፡እስከ፡ይሬስየኒ፡
ድሙረ ፡ ምስለ ፡ እለ ፡ አምኑ ፡ በክርስቶስ ፡
ወፈጸሙ።
፯ ይቤ ፡ አነ ፡ አአምር ፡ ኃይለ ፡ ዘይብለኒ ፡
ያኤምር፡ከመ፡እግዚአብሔር፡ወሀቦ፡ዕሴተ፡
ላዕለ፡ተጋድሎቱ፡ወአሚኖቱ።
፰ ወሶበ፡ጸላኢ፡የሐውስ፡ውስቴታ፡ኀሊናተ፡
ይትሔዘብ፡ኪያሃ፡ከመ፡ሠናይት፡ይእቲ፡
ከመ፡ያስፍጦ፡ባቲ።
፱ ወኮነት፡ኃይል፡እንተ፡ውስቴቱ፡ትኤምሮ፡
ከመ፡እምጸላኢ፡ይእቲ።
፲ ይቤ፡ወኢያመጽእ፡ላዕሌየ፡ኃይለ፡ዐቢየ፡
ወኢይትመዐዕ፡ላዕሌየ፡በመዐት።
፲፩ ዝ፡ውእቱ፡ኢየኀድገኒ፡ከመ፡እትአንተል፡
ወእከሀደ።
፲፪ ይቤ፡ወይመጽእ፡ኵነኔየ፡እስከ፡ለዝሉፉ፡ዝ፡
ውእቱ፡ ከመ ፡ ዝንቱ ፡ ትዕግሥት ፡ ዘተዐገ
ሥክዎ፡ይሰጣሕ፡እስከ፡ማኅለቅቱ፡ለዓለም፤
እስመ ፡ ኵነኔ ፡ ሕማማት ፡ ውእቱ ፡ ዘረከቦ ፡

## ማክሰኞ፡መዓልት፡በ፩፡ሰዓት፡ነግህ።

በልጆቹ፡መቅሠፍት፡በሰውነቱ፡ደዌ፡ስላመ
ጣበት፡ይህን፡ተግሣፅ፡ብሎ፡ጠራው።
፪ እግዚአብሔር፡የሚወዳቸውን፡ልጆች፡ይገሥፃ
ልና፡ብሎ፡ሐዋርያው፡ጳውሎስ፡እንደ፡ተናገረ።
፫ በጫንቃቴ ፡ ላይ ፡ እጁ ፡ ጸናች ፡ አለ ፡ የእግዚአ
ብሔር ፡ ፈቃድ ፡ በእርሱ ፡ ላይ ፡ ያለች ፡
የእርሱን፡ኅሳብ፡ታሸንፋለችና፡ፈቃደ፡እግዚ
አብሔርን፡እጅ፡(ሥልጣን)፡ብሎ፡ጠራት።
፬ እንደ፡ጸናች፡ሲናገር፡ይኸውም፡በልቡናው፡
አድራ ፡ ከእርሱ ፡ ክፉ ፡ ኅሳቦችን ፡ እንደም
ታርቅ፡ያመለክታል።
፭ እኔ፡አገኘው፡እንደ፡ሆነ፡ማን፡ያውቃል?ወደ፡
መጨረሻውም ፡ አልደርስም ፡ አለ ፤ በአራት ፡
ያለው፡ሁሉ፡ጉድለት፡ያለው፡እንጂ፡አንድም፡
ፍጹምነት፡እንደ፡ሌለው፡በጌታችን፡በኢየሱስ፡
ክርስቶስ፡ከሚሆነው፡በቀር፡ማንም፡ከፍጽምት፡
ሕግ፡እንደማይደርስ፡ጌታ፡ገለጠለት።
፮ ስለ፡እርሱም፡እኔ፡አገኘው፡እንደ፡ሆነ፡ማን፡
ያውቃል፡አለ፤ይኸም፡በክርስቶስ፡አምነው፡
ተጋድሎአቸውን፡ከፈጸሙት፡ጋራ፡አንድ፡
እስኪያደርገኝ ፡ የታገሥኩት ፡ ትዕግሥት ፡
ነው።
፯ የሚለኝን፡ኃይል፡አውቃለሁ፡አለ፤በተጋድ
ሎውና፡በማመኑ፡እግዚአብሔር፡ዋጋውን፡
እንደ፡ሰጠው፡ያመለክታል።
፰ ጠላት፡ዲያብሎስም፡በልቡናው፡አሳብ፡ሲጨ
ምርበት፡መልካም፡እንደ፡ሆነች፡አስመስሎ፡
በእርሷ፡ሊአታልለው፡መሆኑን፡ይጠራጠራል።
፱ ያደረችበትም ፡ ኃይል ፡ (ዕውቀት) ፡ እሷ ፡
ከጠላት፡እንደ፡ሆነ፡ታመለክተዋለች።
፲ በቁጣ፡ኃይል፡መጥቶ፡በእኔ፡ክፉ፡ሥራ፡አይ
ሠራብኝም፡አለ።
፲፩ ይኸውም ፡ ቸል ፡ ብዬ ፡ እንድክደው ፡ አይተ
ወኝም።
፲፪ ለዘወትር ፡ መከራው ፡ ይመጣብኛል ፡ አለ፤
ይኸም ፡ የታገሥኩት ፡ ትዕግሥት ፡ እስከ ፡
መጨረሻ ፡ ይገለጣል ፡ ማለቱ ፡ ነው ። ኵነኔ ፡
ያለውም ፡ ያገኘው ፡ መከራ ፡ ነው ። በቅዱስ ፡

Scanned by CamScanner

## በ፩፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሠሉስ/ነግህ።

በከመ፡ይቤ፡በወንጌል፡እስመ፡እምቃላቲከ፡ትጸድቅ፡ወትትኴነን፡ዝ፡ውእቱ፡ተሐምም፡በእንቲአሁ።

፲፫፡ ይቤ፡ኢየአምር፡ደኅሪትየ፡እስመ፡ውእቱ፡ኮነ፡ይደነግፅ፡በእንተዝ፡ኵሉ፡ከመ፡ይብጻሕ፡ለዝሉፉ።

፲፬፡ ይቤ፡እንበእ፡ፀጋመ፡ወኢያደምፅ፡ዘንተ፡ይቤ፡በእንተ፡ጸላዕቱ፡እለ፡ይትቃረንዎ፡በእንተ፡ምግባራት፡እኩያት፡ወባዕዳንሂ፡እስመ፡ይሰመዩ፡እሙንቱ፡ጸጋመ፡ወእግዚእነ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ይቤ፡ያቀውም፡አባግዐ፡በየማኑ፡ወአጣሌ፡በፀጋሙ።

፲፭፡ ዝ፡ውእቱ፡ዲያብሎስ፡ወዘይተሉ፡ፈቃዶ።

፲፮፡ ይቤ፡ወኢያደምፅ፡ይብል፡ከመ፡ውእቱ፡ኢተእኅዘ፡በምግባራቲሆሙ፡ወኢተገመነ፡በፍናዊሆሙ።

፲፯፡ ይቤ፡ወሠወረ፡የማነ፡ወኢይሬኢ፤ይብል፡በእንተ፡መላእክት፡እስመ፡እግዚአብሔር፡ልዑል፡ከበቶሙ፡እምዕጓለ፡እመሕያው፤አላ፡እመ፡በ፡ዘሐረ፡በፍናዊሆሙ፡ወገብረ፡ፈቃዶሙ፡እምከመ፡ኢነጸሮሙ፡ዘበሕዋስ፡ያጸሪ፡እንከ፡ልቡናሁ፡ከመ፡ይርከቦሙ፡ወይሰብሖ፡ከማሆሙ።

፲፰፡ ለእመ፡ኮነት፡ኵነኔሁ፡ከመ፡ዝ፡መኑ፡ይክል፡ይትቃወም፡ወዘይፈቅድ፡ውእቱ፡ዘይገብሮ፡ይብል፡በእንተ፡ውእቱ፡ከመ፡ሉብእሲ፡ለእመ፡መጽአ፡ላዕሌሁ፡ኵነኔ፡እምኵነኔያት፡እግዚእ፡ይትዐገሥ፡ላዕሌሃ፡ወያአኵቶ፡ሎቱ፡ለዝሉፉ።

፲፱፡ ወኢይትቃወም፡ዘበተአንትሎ፡አው፡በኀሊና፡አላ፡ይረሲ፡ህየንተ፡ውእቱ፡ወተማሕልሎ፡ከመ፡የሀቦ፡ህየንተ፡ውእቱ፡ጸሎተ፡ትዕግሥት።

፳፡ እስመ፡ዘይፈቅዶ፡እግዚአብሔር፡ወዘይ ገብሮ፡ውእቱ። ይቤ፡ወበእንተ፡ምንት፡ትትከበት፡ዛቲ፡እከይ፡እምእግዚእ።

## ማክሰኞ፡መዓልት፡በ፩፡ሰዓት/ነግህ።

ወንጌል፡ከቃልህ፡የተነሣ፡ትከብራለህ፤ከቃልህም፡የተነሣ፡ይፈረድብሃል፤እንዳለ፤ይህም፡ስለእርሱ፡መከራ፡ትቀበላለህ፡ማለት፡ነው።

፲፫፡ መጨረሻዬን፡አላውቅም፡አለ፤ስለዚህ፡ሁሉ፡እስከ፡መጨረሻው፡ትዕግሥቱን፡ኢያስፈጽመኝ፡ይሆን፡እያለ፡የሚደነግጥ፡ሁኗልና።

፲፬፡ ወደ፡ግራ፡እመለሳለሁ፡ይህንን፡አላገኝም፡አለ፤ይኸንንም፡በክፉ፡ሥራ፡ስለሚቃወሙት፡ጠላቶቹ፡ተናገረ፤ሌሎቹም፡ግራ፡ተብለው፡ይጠራሉ።ጌታችን፡ኢየሱስ፡ክርስቶስም፡ጻድቃንን፡በቀኝ፡ኃጥአንን፡በግራ፡ያቆማል፡ብሏል።

፲፭፡ ይኸም፡ዲያብሎስና፡ፈቃዱን፡የሚፈጽሙ፡ተከታዮቹ፡ናቸው።

፲፮፡ አላገኝም፡አለ፤እርሱ፡በክፉ፡ሥራቸው፡እንዳልተያዘ፤በኃጢአታቸውም፡እንዳልረከሰ፡ይናገራል።

፲፯፡ ቀኙን፡ሠወረ፡አላየውም፡አለ፤ይኸንንም፡ስለ፡መላእክት፡ይናገራል፤ልዑል፡እግዚአብሔር፡ከሰው፡ልጆች፡ለይቶ፡ሠውሮአቸዋልና፤በመንገዳቸው፡የሚሄድ፡ፈቃዳቸውንም፡የሚፈጽም፡ቢኖር፡በመልክ፡እንኳ፡ባያያቸው፡በመንፈስ፡አግኝቷቸው፡ከእሳቸው፡ጋር፡በአንድነት፡እንደሳቸው፡ያመሰግን፡ዘንድ፡ዕውቀትን፡ገንዘብ፡ያደርጋል።

፲፰፡ ፍርዱ፡እንደዚህ፡ከሆነች፡ሊቃወም፡የሚችል፡ማነው?እርሱ፡ወዶ፡የሚሠራውን፡ማን፡ይቃወማል፡አለ፤ከጌታ፡ከታዘዙ፡መከራዎች፡በሰው፡ላይ፡መከራ፡ቢመጣ፡በትዕግሥት፡ተቀብሎ፡እስከ፡መጨረሻም፡ያመሰግነው፡ዘንድ፡እንዲገባ፡ይናገራል።

፲፱፡ ቸል፡በማለትም፡ሳይቃወም፡ወይም፡በመጠራጠር፡አሳብ፡መከራ፡ስለ፡መቀበሉም፡ትዕግሥትን፡ይሰጠው፡ዘንድ፡በእርሱ፡ፈንታ፡ጸሎትን፡ምሕላን፡ያድርግ፡እንጂ።

፳፡ እግዚአብሔር፡የሚወደው፡የሚያደርገውም፡ይኸ፡ነውና፡ይህች፡ክፋት፡ከጌታ፡ስለምን፡ትሠወራለች፡አለ።

### በ፩፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሠሉስ/ነግህ።

፳፩፡ ወሶበ፡ርዕየ፡ትዕግሥተ፡እግዚእ፡በእንተ፡ኃጥአን፡ወበእንተ፡እለ፡ይወጽኡ፡እምትእዛዛቲሁ፡ተሐዝቦተ፡ጽድቅ፡ከመ፡ምግባሮሙ፡ሥውርት፡እምእግዚእ፡በእንተ፡ዘይትዔገሥሙ፡እግዚእ፡ለኃጥአን፡ወይጸንሐሙ፡እስከ፡ይገብኡ፡ኀበ፡ሠናይ።

፳፪፡ ወይቤ፡ወጽኡ፡እምወሰኖሙ፡ወመሠጡ፡መርዔተ፡ምስለ፡ኖላዊሁ።

፳፫፡ ይብል፡በእንተ፡ደቂቀ፡እሥራኤል፡ከመ፡ወጽኡ፡እምነ፡ምግባራት፡ዘቦቱ፡ብርሃኖሙ፡እግዚአብሔር፡ወገብሩ፡መቃርንቲሁ፡ወተፅዕኑ፡ፈቃዶሙ።

፳፬፡ እስመ፡ፈትሑ፡ላዕለ፡ክርስቶስ፡በሞት፡ዘውእቱ፡ኖላዊ፡ወአሥገርዎሙ፡ለአርድእት፡እለ፡እሙንቱ፡መርዔት።

፳፭፡ ይቤ፡ወኮኑ፡ከመ፡ላሕም፡ውስተ፡ገዳም፤ይብል፡በእንተ፡ውእቱ፡ከመ፡እሙንቱ፡ወጽኡ፡እምወሰናተ፡ልቡና፡ወኮኑ፡ከመ፡እንስሳ፡ዘውስተ፡ገዳም፡ይትበዋሕ፡ለኵሉ፡ዘርከባት፡እንተ፡ትሔውጽ፡ልብ።

፳፮፡ ይቤ፡ወጥዕሞሙ፡ለሙ፡ኀበስቶሙ፡ከመ፡ሕፃናት፡ይብል፡ከመ፡ውእቶሙ፡ኮኑ፡በምግባረ፡ጽድቅ፡እለ፡አልቦሙ፡ልብ፡ወኢነስሑ፡እምድኅረ፡ውእቱሂ፡በእንተ፡ምግባሪሆሙ፡ዳእሙ፡ኮነ፡በኀቤሆሙ፡ኵሉ፡ዘይገብርዎ፡ጥዑመ፡ከመ፡ብልዐተ፡እክል።

፳፯፡ ይቤ፡ጽኑሳን፡ይትጌበሩ፡ውስተ፡ዐጸደ፡ወይን፡ኃጥአን፡ዘእንበለ፡ዐስብ፡ይብል፡በእንተ፡ኃጥአን፡አሕዛበ፡ምድር፡ወጽኑሳን፡በእንተ፡ሐዋርያት፡ትሩፋን፡እስመ፡እሙንቱ፡ወጽኡ፡ከመ፡በከ፡ጽኑሳን፡በውስተ፡ኵሉ፡ዓለም።

፳፰፡ ይቤ፡ውስተ፡ዐጸደ፡ወይን፡ኃጥአን፡ይብል፡በእንተ፡ወይን፡ኃጥአን፡ወለሐቅልኒ፡ሰመዮ፡ወንጌል፡ዓለመ።

፳፱፡ ወውእቶሙኬ፡እለ፡ሰበኩ፡ሐዋርያት፡ውስተ፡ኵሉ፡ዓለም፡ለእለ፡ኢምእመናን፡እስመ፡ተሰምዩ፡ዘኢ፡ምእመናን፡ንፋቃን።

### ማክሰኞ፡መዓልት፡በ፩፡ሰዓት/ነግህ።

፳፩፡ ሥራቸው፡ከጌታ፡እንደምትሠወር፡አድርገው፡ጽድቅን፡ተጠራጥረው፡ከትዕዛዙ፡ስለወጡ፡ስለ፡ኃጢአተኞች፡በንስሐ፡ወደ፡በጎ፡ነገር፡እስኪመለሱ፡ታግሦ፡ስለሚጠብቃቸው፡ኃጢአታቸውንም፡ስለሚሠውርላቸው፡የጌታን፡ትዕግሥት፡ባየ፡ጊዜ፡ስለምን፡ትሠወራለች፡አለ።

፳፪፡ ከተወሰነላቸው፡ተላልፈው፡መንጋውን፡ከእረኛው፡ጋራ፡ነጥቀው፡ወሰዱ፡አለ።

፳፫፡ ስለ፡እስራኤል፡ልጆች፡ይናገራል፤እነርሱ፡ከበጎ፡ሥራ፡እንደወጡ፡ይኸውም፡ብርሃናቸው፡የእግዚአብሔር፡ሕግ፡ሲሆን፡በልባቸውም፡ፈቃድ፡ተገፋፍተው፡መጣላትን፡አደረጉ።

፳፬፡ በእረኛው፡በክርስቶስ፡ላይ፡የሞት፡ፍርድ፡ፈርደዋልና፡መንጋ፡የተባሉ፡ሐዋርያትንም፡ለሞት፡አጥምደዋቸዋልና።

፳፭፡ እንደ፡ዱር፡እንስሳ፡ሆኑ፡አለ፤ስለዚህም፡እነርሱ፡ልቡና፡ከሚወስነው፡አሳብ፡አልፈው፡ልብ፡እንደሌለው፡በዱር፡እንደሚስለጥን፡እንስሳ፡ልቡና፡የምትጎበኘውና፡ለሁሉ፡እንደሚገኝ፡ሆኑ፡ይላል።

፳፮፡ እንደ፡ሕፃናት፡እንጀራቸው፡ጣፈጣቸው፡አለ፤እነርሱ፡በበጎ፡ሥራ፡ላይ፡ምንም፡አሳብ፡የሌላቸው፡እንደሆኑ፡ስለ፡ሠሩትም፡ክፉ፡ሥራ፡ከሠሩት፡በኋላ፡አይጸጸቱም፤ነገር፡ግን፡የሚሠሩት፡ክፋት፡ሁሉ፡ከእህል፡እንደ፡ተዘጋጀ፡ምግብ፡ይጥማቸዋል፡እንጂ፡ይላል።

፳፯፡ ችግረኞች፡በኃጢአተኞች፡የወይን፡አትክልት፡ቦታ፡ያለ፡ደመወዝ፡ያገለግላሉ፡አለ፤ኃጥአን፡ሲል፡በዓለም፡ስለአሉ፡አሕዛብ፡ችግረኞች፡ሲል፡ስለፍጹማን፡ሐዋርያት፡ይላል።እነርሱ፡ወደ፡ዓለም፡ሁሉ፡ያለ፡ደመወዝ፡በብላሽ፡እየተቸገሩ፡ወጥተዋልና።

፳፰፡ በኃጥአን፡የወይን፡ቦታ፡ውስጥ፡አለ፤ስለ፡ወይን፡ኃጥአንን፡ይላል፤በረኻውን፡ወንጌል፡ዓለም፡ብሎ፡ይጠራዋል።

፳፱፡ እነርሱም፡በዓለሙ፡ሁሉ፡ዞረው፡ያላመኑትን፡አስተምረው፡ያሳመኑ፡ሐዋርያትናቸው፤ያላመኑት፡ከሀዲያን፡ይባሉ፡ነበርና።

Scanned by CamScanner

| በ፩፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሠሉስ/ነግህ። | ማክሰኞ፡መዓልት፡በ፩፡ሰዓት/ነግህ። |
| --- | --- |
| ፴፤ ይቤ፡ዘእንበለ፡ዐስብ፡ይብል፡ከመ፡እሙንቱ፡ ወጽኡ፡በከመ፡ይቤሎሙ፡**እግዚእነ፡** በከንቱ፡ ዘነሣእክሙ፡በከንቱ፡ሀቡ። | ፴፤ ያለ ፡ ዋጋ ፡ አለ ፤ እነርሱ ፡ በከንቱ ፡ ያገኛች ሁትን፡ በከንቱ ፡ ስጡ ፡ ብሎ ፡ **ጌታ ፡** እንዳዘዛ ቸውና፡እንደወጡ፡ይናገራል። |
| ፴፩፤ ይቤ ፡ ረሰይዎሙ ፡ ለብዙኃን ፡ ኃጥአን ፡ ይኑሙ፡ዕሩቃነ፡ወነሥኡ፡ዐራዘ፡ነፍሶሙ። | ፴፩፤ ብዙዎችን ፡ ኃጥአንን ፡ ራቁታቸውን ፡ ተኝተው፡እንዲአድሩ፡አደረጓቸው፤የሰውነታ ቸውንም፡መከለያ፡ልብስ፡ገፈፉአቸው፡አለ። |
| ፴፪፤ ይብል፡በእንተ፡ውእቶሙ፡መምህራነ፡ሕግ፡ እንበይነ ፡ ግህደት ፡ ተጋድሎቶሙ ፡ ላእለ ፡ ሰብእ ፡ ወአፍቅሮቶሙ ፡ ሢመተ ፡ ወአጹ ሮቶሙ፡ክበዳተ። | ፴፪፤ ሰዎችን ፡ በግልጽ ፡ ስለሚታገሉ ፡ ለሰዎችም፡ ከባድ ፡ ሸክም ፡ በማሸከማቸው ፡ ሹመትንም፡ ስለመውደዳቸው ፡ በአሪት ፡ ስለነበሩ ፡ መምህራን፡ይናገራል። |
| ፴፫፤ ወያወጽእዎሙ ፡ እምዝንቱ ፡ ዓለም ፡ እንዘ ፡ ውእቶሙ ፡ ዕሩቃን ፡ እምግባራት ፡ ሠናያት ፡ እስመ ፡ ሄድዎሙ ፡ ዐራዘ ፡ ነፍሶሙ ፡ ዘውእቶሙ ፡ ከልእዎሙ ፡ እምነ ፡ ኵሉ ፡ ትሩፋት፡እንተ፡ይእቲ፡ዐራዘ፡ነፍሶሙ። | ፴፫፤ ከበጎ ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ ባዶ ፡ እንደሆኑ ፡ ከዚህ፡ ዓለም፡ያስወጧቸዋልና፡እርሷ፡ለነፍሳቸው፡ ልብስ፡የምትሆን፡በጎ፡ምግባር፡ትሩፋትን፡ እንዳይሠሩ ፡ የከለከሏቸው ፡ እነዚህ ፡ መምህራን፡የነፍሳቸውን፡ልብስ፡(ክብር)፡ አስቀርተውባቸዋልና። |
| ፴፬፤ በከመ ፡ ይቤ ፡ **እግዚእነ ፡ ክርስቶስ ።** አሌ ፡ ለክሙ ፡ እስመ ፡ ነሣእክሙ ፡ መራኁተ ፡ አእምሮ ፡ ወኢቦእክሙ ፡ ወከላእክሙ ፡ እለ ፡ ይበውኡ፡ሂ። | ፴፬፤ ወዮላችሁ ፡ የዕውቀት ፡ መክፈቻን ፡ ወስዳችሁ፡እናንተም፡አልገባችሁም፤የሚገ ቡትንም ፡ ከልክላችኋልና ፡ ብሎ ፡ **ጌታችን፡ ክርስቶስ፡** እንደተናገረ። |
| ፴፭፤ ይቤ፡ወርኀሱ፡በነጠብጣበ፡አድባር፡እስመ፡ አልቦሙ፡ምጽላል፡ጸላዐ፡ተከድኑ፤ይብል፡ እስመ ፡ ዘተከድኑ ፡ ተወክፉ ፡ ትዕዛዘ ፡ ሐዋርያተ፡**እግዚእነ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ።** | ፴፭፤ በተራራዎች፡ካፊያ፡ረሰረሱ፤መጠለያ፡የላቸ ውምና ፡ ዋሻውን ፡ እንደ ፡ ልብስ ፡ አደረጉ፡ አለ፤ ዋሻውንም ፡ ልብስ ፡ ያደረጉ ፡ ትዕዛዙን፡ የተቀበሉ ፡ የጌታችን ፡ **ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ፡** ሐዋርያት፡ናቸው። |
| ፴፮፤ ዝ፡ውእቱ፡ነጠብጣበ፡አድባር፡ትምህርት፡ መሲሐዊት፡ወእሙንቱ፡ያበጽሕዎሙ፡ኀበ፡ ጸላዕ፡ዘውእቱ፡**ክርስቶስ፡** ወይትከደኑ፡ቦቱ። | ፴፮፤ ይኸውም፡የተራራ፡ካፊያ፡ክርስቲያናዊት፡ ትምህርት፡ናት፤ወደ፡ዋሻው፡ያደርሷቸዋል፤ ዋሻውንም ፡ ይለብሳሉ ፡ ይላል ፤ ዋሻውም፡ **ጌታ፡ክርስቶስ፡** ነው። |
| ፴፯፤ ይቤ ፡ ወአግዐሩ ፡ ነፍሰ ፡ ሕፃናት ፡ ፈድፋደ ፡ ወተነበየ ፡ በእንተ ፡ ምጽአቱ ፡ **ለክርስቶስ ፡** ወቅትለተ፡ሕፃናት፡ዘውስተ፡ቤተ፡ልሔም፡ ወዘኮነ ፡ በውእቱ ፡ ጊዜ ፡ እምገዐር ፡ ዐቢይ ፡ ወሰቈቃው፡ዕፁብ። | ፴፯፤ የሕፃናትን፡ሰውነት፡እጅግ፡አስጨነቁ፡አለ፤ ስለ ፡ **ጌታ ፡ ክርስቶስ ፡** በሥጋ ፡ መምጣትና፡ ስለ፡ ቤተ ፡ ልሔም ፡ ሕፃናት ፡ አልቂት ፡ በዚያን፡ ጊዜም ፡ ስለሆነው ፡ ታላቅ ፡ ጩኸትና፡ ዕፁብ ፡ ድንቅ ፡ ስለሆነው ፡ ልቅሶ፡ ትንቢት፡ተናገረ። |
| ፴፰፤ ይቤ ፡ እለ ፡ ይነብሩ ፡ ዲበ ፡ ምድር ፡ ወኢየአ ምርዋ ፡ ለፍኖተ ፡ ጽድቅ ፡ ወኢሖሩ ፡ ውስተ ፡ ፍናዊሃ ፡ ይብል ፡ በእንተ ፡ ውእቱ ፡ እስመ ፡ ሕዝበ፡አይሁድ፡ኮኑ፡ይሬእዩ፡ትእምርታተ፡ ወእለ፡ይትሜሰሉ፡በእንተ፡ምጽአቱ፡ለክር ስቶስ፡ወይክሕዱ፡እሎንተ፡በእንተ፡አፍቅ | ፴፰፤ በምድር፡የሚኖሩ፡የጽድቅን፡ጐዳና፡አያው ቋትም ፤ በመንገድዋም ፡ አልሄዱም ፡ አለ ፡ ይኸን፡ስለአሉ፡ይላል፡የአይሁድ፡ወገኖች፡ ስለ ፡ **ክርስቶስ ፡** በሥጋ ፡ መምጣት ፡ ምልክ ቶችን፡የሚአዩና፡ምሳሌዎችን፡የሚአውቁ፡ ሲሆኑ ፡ ከንቱ ፡ ውዳሴ ፡ በመውደዳቸው ፡ |

| በ፩፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሠሉስ/ነግህ። | ማክሰኞ፡መዓልት፡በ፩፡ሰዓት/ነግህ። |
|---|---|
| ሮቶሙ ፡ ውስተ ፡ ስብሐት ፡ ብጡል ፡ ወኢየ እምኑ ፡ ቃለ ፡ ነቢያት ፡ ወኢ ፡ በእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ እስመ ፡ ሰመያ ፡ ለፍኖተ ፡ ጽድቅ ፡ በዝየ ፡ ሃይማኖተ ፡ ዘበክርስቶስ። | እነዚህን ፡ ይክዳሉ። የነቢያትን ፡ ቃል ፡ አልተቀ በሉም ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስንም ፡ አላመ ኑትም ፤ በዚህ ፡ በክርስቶስ ፡ ያለችው ፡ ሃይማኖ ትንም ፡ የጽድቅ ፡ ጐዳና ፡ ብለው ፡ ጠርቶአታልና። |
| ፴፱፤ ይቤ ፡ ሶበ ፡ እእመረ ፡ ውእተ ፡ ምግባሮሙ ፡ መጠዎሙ ፡ ለጽልመት ፡ ሶበ ፡ እእመረ ፡ ውእቱ ፡ ከመ ፡ ኢይኔስሑ ፡ እሙንቱ ፡ ርኁቀ ፡ እምኔሆሙ ፡ ወአንገሠ ፡ ላዕሌሆሙ ፡ ፀሮሙ ፡ ወመጠዎሙ ፡ ውስተ ፡ አፈ ፡ ሰይፍ። | ፴፱፤ ይኸን ፡ ሥራቸውን ፡ በአወቀ ፡ ጊዜ ፡ ለጨለማ ፡ ሰጣቸው ፡ አለ ፤ እነርሱ ፡ በንስሓ ፡ እንደማይ መለሱ ፡ እርሱ ፡ ስለ ፡ አወቀ ፡ ከእርሳቸው ፡ በረድኤት ፡ ራቀ ፤ ጠላታቸውንም ፡ አሠለጠነ ባቸው ፤ ለጦር ፡ ለሰይፍ ፡ አሳልፎ ፡ ሰጣቸው። |
| ፵፤ ይቤ ፡ ኀደገኒ ፡ መፍቀሬ ፡ ሰብእ። እስመ ፡ እግዚ አብሔር ፡ ልዑል ፡ የዐቅቦ ፡ ለጻድቅ ፡ ወይከብቶ ፡ በጊዜ ፡ መቅሠፍቱ ፡ ላዕለ ፡ ንፉቃን ፡ በከመ ፡ ዐቀቦ ፡ ለሎጥ ፡ ጻድቅ ፡ ወሠወሮ ፡ ከመ ፡ ኢይትሀጐል ፡ ምስለ ፡ ኃጥአን። | ፵፤ ሰውን ፡ የሚወድ ፡ ጌታ ፡ ተወኝ ፡ ተለየኝ ፡ አለ። ልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ በከሃድያን ፡ ላይ ፡ መቅሠፍቱን ፡ ባመጣ ፡ ጊዜ ፡ ጻድቅን ፡ ሰው ፡ ይጠብቀዋል ፤ ከኃጢአተኞችም ፡ ጋራ ፡ እንዳ ይጠፋ ፡ ሎጥን ፡ እንደ ፡ ጠበቀ ፡ ከመከራው ፡ ይሠውረዋልና። |
| ፵፩፤ ይቤ ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ መክፈልቶሙ ፡ ርጉመ ፡ በዲበ ፡ ምድር ፡ ይብል ፡ ዘይተርፍ ፡ እምደቂቀ ፡ እሥራኤል ፡ ወኢየአምን ፡ በክርስቶስ ፡ ይከውን ፡ ምኑነ ፡ እምኵሉ ፡ አሕዛብ። | ፵፩፤ ዕድል ፡ ፈንታቸው ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ የተረገመ ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ አለ ። ከእስራኤል ፡ ልጆች ፡ በጌታ ፡ ክርስቶስ ፡ ሳያምን ፡ የቀረው ፡ በአሕዛብ ፡ ሁሉ ፡ የተጠላ ፡ የተናቀ ፡ ይሆናል። |
| ፵፪፤ ወውስተ ፡ ኵሉ ፡ ሣቅዕ ፡ ወእምኵሉ ፡ ምድር ፡ ጽሉአነ ፡ ወምኑናነ። | ፵፪፤ በሁሉም ፡ ዘንድ ፡ በአራቱም ፡ ማእዘን ፡ የተጠሉና ፡ የተናቁ ፡ እንደሆኑ ፡ ይናገራል። |
| ፵፫፤ ይቤ ፡ ወእመ ፡ አኮሰ ፡ መኑ ፡ ውእቱ ፡ ዘይብለኒ ፡ ሐሳዊ ፡ አንተ ፡ ውእቱ ፡ ወይሬስዮ ፡ ከመ ፡ ወኢምንት ፡ ለነገርየ። | ፵፫፤ አንተ ፡ ሐሰተኛ ፡ ነህ ፡ የሚለኝ ፡ ነገሬንም ፡ እንደ ፡ ኢምንት ፡ የሚአደርገው ፡ ማነው? አለ። |
| ፵፬፤ ይብል ፡ በእንተ ፡ ውእቱ ፡ ኢይትናገር ፡ ወኢም ንተኒ ፡ በኀቤሁ ፡ ዳእሙ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ለእመኒ ፡ ተፈጸመ ፡ ኮነ ፡ ከማሁ ፡ ወለእመኒ ፡ ኢተፈጸመ ፡ ኢኮነ ፡ ውእቱ ፡ ሐሳዌ ። እስመ ፡ ኢኮነ ፡ ውእቱ ፡ ዘይትናገር ፡ በኀቤሁ ፡ ዳእሙ ፡ እግዚአብሔር ፡ በላዕሌሁ ፡ ዘሎቱ ፡ ስብሐት። | ፵፬፤ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ እንጂ ፡ እርሱ ፡ ከራሱ ፡ ምንም ፡ እንደማይናገር ፡ ይገልጣል ፤ ያስረዳል ፤ ነገሩ ፡ ቢፈጸም ፡ እንዲሁ ፡ ሆነ ፤ ባይፈጸምም ፡ እርሱን ፡ ሐሰተኛ ፡ አያደርገውም ፤ እርሱ ፡ ከራሱ ፡ አይናገርምና ፡ በእርሱ ፡ ላይ ፡ ያደረ ፡ የክብር ፡ ባለቤት ፡ እግዚአብሔር ፡ ነው ፡ እንጂ። |
| ፵፭፤ ዓዲ ፡ ይብል ፡ በእንተ ፡ እግዚእነ ፡ በከመ ፡ ስምዐ ፡ ኮነ ፡ ነቢይ ፡ በብሂል ፡ እስመ ፡ ኢገብረ ፡ ኃጢአተ ፡ ወኢተረክበ ፡ ሐሰት ፡ ውስተ ፡ አፉሁ ። ወሎቱ ፡ ስብሐት ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን። | ፵፭፤ ዳግመኛ ፡ ነቢይ ፡ ኀጢአት ፡ አልሠራምና ፡ በአ ንደበቱም ፡ ሐሰት ፡ አልተገኘበትም ፡ በማለት ፡ ስለ ፡ መሰከረ ፡ ስለ ፡ ጌታችን ፡ ተናገረ ፤ ለእርሱም ፡ ክብር ፡ ምስጋና ፡ ለዘላለሙ ፡ ይሁን ፡ አሜን። |
| ዘኢሳይያስ ፡ ነቢይ ፡ በረከቱ ፡ ትኩን ፡ ምስሌነ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን። | የነቢዩ ፡ የኢሳይያስ ፡ ትንቢት ፡ በረከቱ ፡ ከእኛ ፡ ጋራ ፡ ለዘላለሙ ፡ ትኑር ፡ አሜን። |
| ምዕ፤፩፤፳፩–፴፩። | ምዕ፤፩፤፳፩–፴፩። |
| ፳፩፤ እፎ ፡ ኮነት ፡ ዘማ ፡ ሀገረ ፡ ጽዮን ፡ ማእምንት ፡ | ፳፩፤ የታመነች ፡ ፍርድን ፡ የተመላች ፡ በእሷም ፡ |

Scanned by CamScanner

## በ፩፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሠሉስ/ነግህ።

እንተ፡ምልእት፡ፍትሐ፡ወኀደረ፡ውስቴታ፡ ጽድቅ፡ወይእዜሰ፡ፈያት፡ወቀተልት።

፳፪፤ ወርቅኪኒ፡ወብሩርኪኒ፡ተምያን፡ወመያስያ ንኪኒ፡ይቶስሑ፡ማየ፡ውስተ፡ወይን።

፳፫፤ መላእክትኪኒ፡ኃያድያን፡ሱቱፋነ፡ሰረቅት፡ መስተናድአን ፡ ወያፈቅሩ ፡ ሕልያነ ፡ ወይፈቅዱ፡ይሚጡ፡ፍትሐ፡ወኢያጸምኡ፡ ዕቤረ ፡ ብእሲተ ፡ ወኢይፈትሑ ፡ ለዕጓለ ፡ ማውታ።

፳፬፤ በእንተ፡ዝንቱ፡ከመዝ፡ይቤ፡**እግዚአብሔር፡ ጸባኦት፡** አሌ፡ሎሙ፡ለኃያላነ፡እሥራኤል፡ ኢይቈርር፡መዐትየ፡እምላዕለ፡ዐርየ፡ወእትቤ ቀሎሙ፡ለጸላእትየ።

፳፭፤ ወአመጽእ ፡ እዴየ ፡ ላዕሌኪ ፡ ወአረስነኪ ፡ ወእፈትን ፡ ዛህለኪ ፡ በከውር ፡ ወአሴስል ፡ ኵሎ ፡ ናእከኪ ፡ ወአውዕዮሙ ፡ ለከሀድያን ፡ ወአአትቶሙ ፡ እምኔኪ ፡ ለኵሎሙ ፡ ዓማፅያን።

፳፮፤ ወእሠይም፡ለኪ፡መኳንንተኪ፡ከመ፡ትካት፡ ወመማክርተኪ ፡ ከመ ፡ ቀዲሙ ፡ ወእምዝ ፡ ትሰመዪ ፡ ሀገረ ፡ ጽድቅ ፡ ደብረ ፡ አህጉረ ፡ ጽዮን፡ማእምንት።

፳፯፤ እስመ፡በጽድቅ፡ይድኅኑ፡ፂውዋንኪ፡ወበም ጽዋት።

፳፰፤ ወይትቀጠቀጡ ፡ ኃጥአን ፡ ወዓማፅያን ፡ ኅቡረ፡ ወይጠፍኡ፡ኵሎሙ፡እለ፡ኀደግዎ፡ **ለእግዚአብሔር።**

፳፱፤ ወይትኀፈሩ፡በአማልክቲሆሙ፡በዘመከሩ፡ ለሊሆሙ፡ወይትኀፈሩ፡በምሕራማቲሆሙ፡ ዘፈተዉ።

፴፤ ወይከውኑ፡ከመ፡ዕፀ፡ጠርቤንቶስ፡እንተ፡ ነገፈት ፡ ቈጽላ ፡ ወከመ ፡ ገነት ፡ እንተ ፡ አልባቲ፡ማይ።

፴፩፤ ወይከውን፡ኃይሎሙ፡ከመ፡ብርዐ፡ባሕሩስ፡ ወምግባራቲሆሙ፡ከመ፡አፍሐመ፡እሳት፡ ወይውዕዩ ፡ ኃጥአን ፡ ወዓማፅያን ፡ ኅቡረ ፡ ወየኀጥኡ፡ዘያጠፍእ፡ሎሙ፡እሳቶሙ።

## ማክሰኞ፡መዓልት፡በ፩፡ሰዓት/ነግህ።

እውነት ፡ የሚነገርባት ፡ የጽዮን ፡ ከተማ፡ እንዴት፡አመንዝራ፡ሆነች?ዛሬ፡ግን፡ወንበ ዴዎችና፡ነፍሰ፡ገዳዮች፡መሉባት።

፳፪፤ ብርሽና፡ወርቅሽም፡ግብዞች፡ናቸው፡መሸተ ኞችሽም፡በወይኑ፡ውኃን፡ይጨምራሉ።

፳፫፤ ቀማኞች ፡ የሚሆኑ ፡ አለቆችሽም ፡ ከሌቦች፡ ጋራ፡ ይተባበራሉ ፤ ወደ ፡ መስረቅ ፡ ወደ፡ መቀማትም፡የሚነዳዱ፡ናቸው፤መማለጃንም፡ የሚወዱ፡ናቸው፤ፍርድንም፡ይለውጡ፡ዘንድ፡ ይወዳሉ፤ባል፡የሌላት፡ሴትን፡አያደምጡም፡ እናት፡አባት፡ለሌለው፡ልጅም፡አይፈርዱም፡

፳፬፤ ስለዚህ ፡ ነገር ፡ **አሸናፊ ፡ እግዚአብሔር፡** እንዲህ ፡ አለ ፤ ለእስራኤል ፡ መኳንንቶች፡ ወዮላቸው! ቁጣዬ፡ከጠላቶቼ፡አይበርድም፤ ጠላቶቼንም፡እበቀላቸዋለሁ።

፳፭፤ እደ፡መዐቴንም፡በአንቺ፡ላይ፡አመጣለሁ፤ አግልሻለሁ ፤ ዝገትሽንም ፡ በማጣሪያ፡ አጠራለሁ ፤ ቅልቅልሽንም ፡ ሁሉ ፡ አስወግ ዳለሁ፤እኔን፡የካዱኝንም፡አቃጥላቸዋለሁ፤ ዓመፀኞችንም፡ሁሉ፡ካንቺ፡አርቃቸዋለሁ፡

፳፮፤ መኳንንቶችሽን፡አማካሪዎችሽንም፡እንደ፡ ቀድሞው ፡ እሾምልሻለሁ ፤ ከዚህ ፡ በኋላ፡ የታመንሽ ፡ የጽዮን ፡ አገሮች ፡ ከተማ፡ እውነት፡የመላባት፡አገር፡ትባያለሽ።

፳፯፤ ምርኮኞችሽ ፡ በእውነትና ፡ በምጽዋት፡ ይድናሉ።

፳፰፤ ዓመፀኞችና ፡ ኃጢአተኞች ፡ በአንድነት፡ ይጠፋሉ ። **እግዚአብሔርን ፡** በአምልኮ፡ የተዉት፡ሰዎች፡ሁሉ፡ይጠፋሉ።።

፳፱፤ እነሱ ፡ መክረው ፡ በሠሩአቸው ፡ በጣኦቶ ቻቸው፡ያፍራሉ፤በወደዱአቸው፡በጣዖቶቻ ቸውም፡ያፍራሉ።

፴፤ ቅጠሏ፡እንደረገፈ፡ቡጥ፡እንደምትባል፡ እንጨት ፡ ውኃም ፡ እንደሌለባት ፡ እንደ፡ ተክል፡ቦታ፡ይሆናሉ።

፴፩፤ ሠራዊታቸውም ፡ እንደ ፡ መቃ ፡ መስበሪ፡ ይሆናል፤ሥራቸውም፡እንደ፡እሳት፡ፍም፡ ይሆናል ፤ በደለኞችና ፡ ኃጢአተኞች፡ ሰዎችም፡በአንድነት፡ይቃጠላሉ፤እሳታቸ ውንም፡የሚአጠፋላቸው፡ያጣሉ።

Scanned by CamScanner

በ፩፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሠሉስ/ነግህ።

ዘሆሴዕ ፡ ነቢይ ፡ በረከቱ ፡ ትኩን ፡ ምስሌነ ፡ ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

ምዕ፤፬፤፩-፰።

፩፤ ስምዑ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ደቂቀ ፡
እሥራኤል ፡ እስመ ፡ ይትዋቀሶሙ ፡ እግዚአ
ብሔር፡ለእለ፡ይነብሩ፡ውስተ፡ምድር።
፪፤ እስመ ፡ አልቦ ፡ ጽድቅ ፡ ወአልቦ ፡ ምሕረት ፡
ወአልቦ ፡ አእምሮ ፡ እግዚአብሔር ፡ ውስተ ፡
ምድር፡ዘእንበለ፡ሐሰት፡ወቀትል፡ወስርቅ፡
ወዝሙት፡መልአ፡ምድረ፡ወይደምሩ፡ደመ፡
ምስለ፡ደም።
፫፤ በእንተ፡ዝንቱ፡ትላሁ፡ምድር፡ወትውህድ፡
ምስለ ፡ ኵሎሙ ፡ እለ ፡ ይነብሩ ፡ ውስቴታ ፡
ወምስለ፡አራዊተ፡ገዳም፡ወምስለ፡አዕዋፈ፡
ሰማይ፡ወአራዊተ፡ምድር፡ወየኀልቁ፡ዓሣተ፡
ባሕር።
፬፤ ወአልቦ፡እንከ፡መኑሂ፡ዘይትዋቀስ፡ወአልቦ፡
ዘይዛለፍ፡ወኢመኑሂ፡ወሕዝብየሰ፡ካህናት፡
እለ፡ይትዋሥኡ፡ኮኑ፡ከመ፡ዘኢይትዋሥኡ።
፭፤ ወይደክሙ ፡ በፍኖት ፡ ካህን ፡ ወነቢይ ፡
ወሕዝብ ፡ ኅቡረ ፡ ወትመስል ፡ እምክሙ ፡
ሌሊተ።
፮፤ ወይመስሉ ፡ ሕዝብየ ፡ ከመ ፡ ዘአልቦ ፡ ልብ ፡
እስመ ፡ ለከሂ ፡ ኅደገከ ፡ ልብከ ፡ ወአነሂ ፡
ኅደጉከ፡ኢትሡዕ፡ሊተ፡እስመ፡ረሳዕከ፡ሕገ፡
አምላክከ፡ወአነሂ፡እረስዖሙ፡ለደቂቅከ።
፯፤ በከመ ፡ ብዝኆሙ ፡ ከማሁ ፡ አበሱ ፡ ሊተ ፡
ወእሬስዮ፡ኃሣረ፡ለክብሮሙ።
፰፤ ወትበልዖሙ፡ኃጢአቶሙ፡ለሕዝብየ፡ወይነ
ሥእዋ፡ለነፍሶሙ፡በጌጋዮሙ።

ክፍል፡፪።
ሃይማኖተ፡አበው።

ምዕ፤፹፪፤፩-፲።

፩፤ ይቤ፡ቴዎዶስዮስ፡ተአማኒ፡በጽድቅ፡ውስተ፡
ጠማረ ፡ መልእክቱ ፡ እንተ ፡ ጸሐፋ ፡ ሶበ ፡
ተሰይመ፡ሊቀ፡ጳጳሳት፡ዲበ፡መንበረ፡እስክ
ንድርያ ፡ ወፈነዋ ፡ ኀበ ፡ ንጹሕ ፡ ሳዊሮስ ፡

ማክሰኞ፡መዓልት፡በ፩፡ሰዓት/ነግህ።

የነቢዩ ፡ የሆሴዕ ፡ ትንቢት ፡ በረከቱ ፡ ከእኛ ፡ ጋራ፡ለዘላለሙ፡ትኑር፡አሜን።

ምዕ፤፬፤፩-፰።

፩፤ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ የሚኖ
ሩትን ፡ ሰዎች ፡ እግዚአብሔር ፡ ይወቅሳቸ
ዋልና፡የእግዚአብሔርን፡ቃል፡ስሙ።
፪፤ በዚህ፡ዓለም፡እውነት፡ነገር፡ርኅራኄ፡እግዚአ
ብሔርንም፡ማወቅ፡የለምና፡ሐሰት፡ከመናገር፡
ነፍስ፡ከመግደል፡የሰው፡ገንዘብም፡ከመስረቅ፡
በቀር ፡ ዝሙታቸው ፡ ምድርን ፡ መላ፤ ዘርንም ፡
ከዘር፡ጋር፡ይደባልቃሉ።
፫፤ ስለዚህ ፡ ምድር ፡ ታለቅሳለች ፤ በሰማይ ፡
ከሚበሩ፡ አዕዋፍና ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ ካሉ ፡
አራዊት፡ጋራ፡(ከውሻና፡ከድመት፡ጋራ)፡በሷ፡
ከሚኖሩ ፡ ከነዚሁ ፡ ሁሉ ፡ ጋራ ፡ ትጠፋለች ፤
በባሕር፡የሚኖሩ፡ዓሣዎችም፡ያልቃሉ።
፬፤ እንግዲህ፡ወዲያም፡የሚከራከር፡የሚመክር፡የሚ
አስተምር፡ ማንም ፡ ማን ፡ የለም ፤ ቀድሞ ፡ የሚ
መክሩ ፡ የሚአስተምሩ ፡ ወገኖቼ ፡ ካህናት ፡ ግን ፡
ዛሬ፡እንደማይመክሩ፡እንደማያስተምሩ፡ሆኑ።
፭፤ አንድነትም ፡ ተማርከው ፡ ሲሔዱ ፡ ነቢዩና ፡
ካህኑ ፡ ሕዝቡም ፡ በጕዳና ፡ ይደክማሉ ፤ እናታ
ችሁም፡ሌሊት፡ትመስላለች።(ትጠቁራለች)
፮፤ ወገኖቼ፡አእምሮ፡እንደሌላቸው፡ይመስላሉ፤
አንተን ፡ አእምሮህ ፡ ተለይቶሃልና ፡ እኔም ፡
በረድኤት ፡ ተለይቼሃለሁና ፡ አትሠዋልኝ ፤
አንተ፡የፈጣሪህን፡ሕግ፡ዘንግተሃልና፡እኔም፡
ልጆችህን፡እዘነጋቸዋለሁ።
፯፤ እንደ ፡ ብዛታቸው ፡ መጠን ፡ እኔን ፡ በደሉኝ ፡
ክብራቸውንም፡ጕስቍልና፡አደርገዋለሁ።
፰፤ ወገኖቼንም፡ኃጢአታቸው፡ታጠፋቸዋለች፤
በበደሉትም ፡ በደል ፡ (አሕዛብ) ፡ ሰውነታ
ቸውን፡ማርከው፡ይወስዷታል።

ክፍል፡፪።
የአባቶች፡ሃይማኖት።

ምዕ፤፹፪፤፩-፲።

፩፤ በእውነተኛ ፡ ሃይማኖት ፡ የሚያምን ፡ ቅዱስ ፡
ቴዎዶስዮስ ፡ በእስክንድርያ ፡ መንበር ፡
የጳጳሳት ፡ አለቃ ፡ ሆኖ ፡ በተሾመበት ፡ ጊዜ ፡
ንጹሕ ፡ ወደሚሆን ፡ ወደ ፡ አንጾኪያ ፡ ሊቀ ፡

Scanned by CamScanner

## በ፩፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሠሉስ/ነግሀ።

ሊቀ፡ጳጳሳት፡ዘአንጾኪያ።

፩፤ አአምን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ከመ ፡ ውእቱ፡ ዕሩይ ፡ በመለኮት ፡ ምስለ ፡ እግዚአ ብሔር ፡ አቡሁ ፡ ዘሀሎ ፡ ምስሌሁ ፡ በኵሉ ፡ መዋዕል፡ብርሃን፡ዘእምብርሃን፡ጻድቅ፡ዘእም ጻድቅ ፡ አርአያሁ ፡ ለአብ ፡ ሕያው ፡ ዘቦቱ ፡ አካል ፡ ውእቱ ፡ ተሠገወ ፡ ወኮነ ፡ ሰብአ ፡ ንከሥት ፡ ምሥጢረ ፡ ለዘይሰምዕ ፡ ጥበበ ፡ በፍቅር፡ዐቢይ።

፪፤ ንሕነሰ ፡ ተምህርነ ፡ ከመ ፡ ቃል ፡ ዘውእቱ ፡ አምላክ ፡ በህላዌሁ ፡ ወውእቱ ፡ ኮነ ፡ ሰብአ ፡ ዘበአማን ፡ እንዘ ፡ አምላክ ፡ ውእቱ ፡ ለሊሁ ፡ አንደየ ፡ ርእሶ ፡ በፈቃዱ ፡ ወበሥምረቱ ፡ ወኢኅደገ ፡ ምንተኒ ፡ እምነ ፡ ትስብእቱ ፡ ወዳእሙ፡ኮነ፡አሐደ፡ምስለ፡ሥጋ።

፫፤ ወኢተወለጠ፡አካለ፡ሥጋ፡ዘውእቱ፡ዕሩይ፡ ምስለ፡ህላዌ፡ዚአነ፡በተወክፎ፡ሕማማት፡ ወቦቱ፡ነፍስ፡ነባቢት፡ወለባዊት፡ነሥአ፡ አርአያነ፡በኵሉ፡ግብር፡ዘእንበለ፡ኃጢአት፡ ባሕቲታ፡እስመ፡መጻሕፍት፡ይቤላ፡ከመ፡ ውእቱ ፡ ኢአበሰ ፡ ወኢተረክበ ፡ ሐሰት ፡ ውስተ፡አፉሁ።

፬፤ እስመ፡ሶበ፡ተመውዐ፡ህላዌ፡ዚአነ፡በአዳም፡ ቀዳሚ፡ብእሲ፡ዓዲመ፡ለሊሁ፡ለብሰ፡ጌራ፡ መዊዕ፡ማሰነ፡ሞት፡በእግዚእነ፡ኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ዳግማይ፡አዳም።

ወበእንተዝ፡ብፁዕ፡ጳውሎስ፡ፈቀደ፡ከመ፡ ይምህረነ ፡ ምክንያተ ፡ ዘበእንቲአሁ ፡ ኮነ ፡ መድኃኒነ ፡ ሰብአ ፡ ወይቤ ፡ እስመ ፡ ደቂቅ ፡ ተሳተፍዎ ፡ በሥጋ ፡ ወደም ፡ ወውእቱ ፡ ኮነ ፡ ከማሆሙ ፡ ከመ ፡ በሞቱ ፡ ያብጥሎ ፡ ለዘቦቱ ፡ ዕዘዘ፡ሞት፡ዘውእቱ፡ሰይጣን፡ወያድኅኖሙ፡ ለእለ ፡ እሙንቱ ፡ ውስተ ፡ ፍርሀተ ፡ ሞት ፡ አምጣነ ፡ ኵሉ ፡ መዋዕለ ፡ ሕይወቶሙ ፡ ሙቁሓን፡በሞት።

፭፤ እመሰ፡ለነ፡በህላዌነ፡ዘሞዐነ፡ሰይጣን፡ወእግ ዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ኢነሥአ ፡ ካልአ ፡ ህላዌ ፡ ዘእንበለ፡ህላዌ፡ዚአነ፡ወረሰዮ፡አሐደ፡አካለ፡

## ማክሰኞ፡መዓልት፡በ፩፡ሰዓት/ነግሀ።

ጳጳሳት ፡ ወደሳዊሮስ ፡ ጽፎ ፡ በላከው ፡ መልእክት፡እንዲህ፡አለ።

፩፤ በዘመኑ ፡ ሁሉ ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ ካለ ፡ ከአባቱ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ጋር ፡ በባሕርይ ፡ አንድ፡ እንደሆነ፡በእግዚአብሔር፡ቃል፡እምናለሁ፡ ከብርሃን ፡ የተገኘ ፡ ብርሃን ፡ ከባሕርይ ፡ አምላክ፡የተገኘ፡የባሕርይ፡አምላክ፡ሕያው፡ አብን፡የሚመስለው፡አካላዊ፡ቃል፡ነፍስን፡ ሥጋን ፡ ነሥቶ ፡ ሰው ፡ እንደሆነ ፡ በፍጹም፡ ፍቅር ፡ ሃይማኖትን ፡ ለሚማር ፡ ለሚረዳ፡ ምሥጢርን፡እንገልጻለን።

፪፤ እኛስ ፡ በባሕርዩ ፡ አምላክ ፡ የሚሆን፡ እውነተኛ፡ሰው፡የሆነ፡እሱ፡አካላዊ፡ቃል፡ አምላክ ፡ ሲሆን ፡ እርሱ ፡ በፍጹም ፡ ፈቃዱ፡ ሰው፡እንደሆነ፡ተምረናል ። ከነፍስ፡ከሥጋ፡ ማናቸውንም ፡ አልተወም ። ከሥጋ ፡ ጋር፡ አንድ፡አካል፡አንድ፡ባሕርይ፡ሆነ፡እንጂ፡

፫፤ መከራ ፡ በመቀበል ፡ ከእኛ ፡ ባሕርይ ፡ ጋራ፡ አንድ ፡ የሚሆን ፡ የሥጋ ፡ አካልም ፡ አልተለ ወጠም ። የምትናገር ፡ የምታውቅ ፡ ነፍስም፡ አለችው ። ከኃጢአት፡ብቻ፡በቀር፡በሥራው፡ ሁሉ ፡ እኛን ፡ መምሰልን ፡ ገንዘብ ፡ አደረገ፡ እርሱ ፡ እንዳልበደለ ፡ በአንደበቱም ፡ ሐሰት፡ እንዳልተገኘበት፡መጻሕፍት፡ተናግረዋልና፡

፬፤ በቀደመ ፡ ሰው ፡ አዳም ፡ ባሕርያችን ፡ ድል፡ ከተነሣ ፡ በኋላ ፡ እንደገና ፡ ድል ፡ መንሳትን፡ ገንዘብ ፡ አድርጓልና ፡ በዳግማዊ ፡ አዳም፡ በጌታችን፡በኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ሞት፡ጠፋ፡ ስለዚህም ፡ የተመሰገነ ፡ ጳውሎስ ፡ መድኃኒ ታችን፡ሰው፡የሆነበትን፡ምክንያት፡ሊአስተ ምረን ፡ ወደደ ። ምእመናን ፡በነፍስ ፡ በሥጋ፡ እንደመሰሉት ፡ እርሱም ፡ እንደነርሱ ፡ እንደሆነ፡ተናገረ።የሞት፡ሥልጣን፡ያለው፡ ሰይጣንን፡በሞቱ፡ያጠፋው፡ዘንድ፡በሞት፡ ቍራኛነት፡ተይዘው፡ባለ፡ዘመናቸው፡ሁሉ፡ ሞትን፡በመፍራት፡የነበሩትን፡ያድናቸው፡ ዘንድ።

፭፤ ሰይጣን፡እኛን፡ድል፡የነሣን፡በባሕርያችን፡ ከሆነ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቃልም ፡ የእኛን፡ ባሕርይ፡እንጂ፡ሌላ፡ባሕርይ፡ካልተዋሐደ፡

Scanned by CamScanner

በ፮፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሠሉስ/ነግህ።

ምስሌሁ ፡ ወረሰዮ ፡ ኢሐማሚ ፡ ወኢመዋቴ፡እምአመ፡ተዋሐደ፡በከመ፡ተሀበሉ፡ ሰብእ ፡ ዐላውያን ፡ ይበሉ ፡ ዘንተ ፡ እመሰ ፡ ከመዝ ፡ ውእቱ ፡ ከንቱኬ ፡ ሃይማኖትነ።

፯፤ ወአኮ ፡ ውእቱ ፡ ግብር ፡ ዐቢይ ፡ ከመ ፡ ይማዖ ፡ እግዚእ ፡ ለሰይጣን ፡ ሶበ ፡ አኮ ፡ እግዚእነ ፡ ክርስቶስ ፡ ለብሰ ፡ ዘተመውዐ ፡ ቅድመ ፡ ወቦቱ ፡ ተወክፈ ፡ ሕማማተ ፡ ዘአልቦቱ ፡ ጌጋይ ፡ በሥጋ፡ ዘይትዔረይ ፡ ምስሌነ፡በህላዌ፡እምኢተነክረ፡ተወክፎቱ፡ ሕማማተ ፡ ወሶበ ፡ አኮ ፡ አማሰኖ ፡ ለሞት ፡ በሥጋሁ ፡ እምኢማስነ ፡ ቀኖቱ ፡ ለሞት ፡ ዘውእቱ ፡ ኃጢአት ፡ ወዓዲ እምኢበጠለ ፡ ሥልጣኑ፡ለሞት።

፰፤ እመሰ፡ወፅአ፡እምዘርዐ፡ዳዊት፡ወነሥአ፡ አርአያነ፡በኵሉ፡ግብር፡ዘእንበለ፡ኃጢአት፡ ባሕቲታ፡ንሕነሰ፡እንከ፡አኃዊሁ፡በጽድቅ፡ በከመ፡ይቤ፡ጳውሎስ፡ጠቢብ።

፱፤ ወለሞት ፡ ተወክፎ ፡ በፈቃዱ ፡ በሥጋሁ ፡ ዘውእቱ፡ሐማሚ፡በህላዌነ፡ወበተወክፎቱ፡ ሕማማተ፡ዚአነ፡እንዘ፡አልቦቱ፡ጌጋይ፡ሞዖ፡ በጽድቅ፡ለዘቦቱ፡ሥልጣነ፡ሞት።

፲፤ ወበህላዌ ፡ መለኮቱሰ ፡ ኢሐማሚ ፡ ውእቱ ፡ ጥዩቀ ፡ እፎኑ ፡ ኢንትሜካሕ ፡ በዝንቱ ፡ ሙዓት፡ ወናሁ ፡ ንሕነ ፡ ወፃእነ ፡ እምቅንየተ ፡ ግብርናት ፡ ወመኑ ፡ ውእቱ ፡ ዘኢያነክር ፡ እምሥጢረ ፡ መጻሕፍት ፡ ወኢይሰድዶ ፡ ለአውጣኪ ፡ ወኢያርኀቆ ፡ ሎቱ ፡ ወለኵሉ ፡ ዘይኄሊ፡ዕበደ፡ዚአሁ።

በረከቱ፡ለዝንቱ፡መምህር፡ተሃሉ፡ምስሌነ፡ ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

ተግሣጽ ፡ ዘአቡነ ፡ አባ ፡ ሲኖዳ ፡ በረከቱ ፡ ትኩን፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

፩፤ አነ፡አጤይቀክሙ፡በክልኤቱ፡ግብር፡እስመ፡ እለ ፡ ይትፌሣሕ ፡ በሙ ፡ እግዚአብሔር ፡

ማክሰኞ፡መዓልት፡በ፩፡ሰዓት/ነግህ።

ከእርሱ ፡ ጋርም ፡ አንድ ፡ ካደረገው ፡ መናፍቃን፡አልታመመም፡አልሞተም፡ይሉ፡ ዘንድ፡ደፍረው፡እንደተናገሩም፡ከተዋሐደ፡ ጀምሮ ፡ ሕማም ፡ ሞት ፡ የማይስማማው ፡ ካደረገው ፡ እንዲህ ፡ ከሆነ ፡ ታመመ ፡ ሞተ ፡ ብለን፡ማመናችን፡ከንቱ፡ነዋ።

፯፤ ጌታ ፡ ሰይጣንን ፡ ድል ፡ ቢነሣው ፡ የሚደንቅ ፡ ሥራ ፡ አይደለም ። ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ቀድሞ ፡ ድል ፡ ተነሥቶ ፡ የነበረ ፡ ሥጋን፡የተዋሐደ፡ባይሆን፡በባሕርይ፡ከእኛ፡ ጋር፡አንድ፡በሚሆን፡ሥጋ፡ዕዳ፡በደል፡ያል ተገኘበት፡እርሱ፡በሥጋ፡መከራን፡የተቀበለ፡ ባይሆን ፡ ኖሮስ ፡ መከራ ፡ መቀበሉ ፡ ባልተደነቀም፡ነበር።ሞትንም፡በሥጋው፡ያጠፋው፡ ባይሆን ፡ ኖሮ ፡ ሞትን ፡ የሚአሠለጥን ፡ ኃጢአት ፡ ባልጠፋም ፡ ነበር ። የሞት ፡ ሥልጣንም፡ባልተሻረም፡ነበር።

፰፤ ከዳዊት ፡ ወገን ፡ ከተወለደና ፡ ከኃጢአት ፡ ብቻ፡ በቀር ፡ እኛን ፡ መምሰልን ፡ ገንዘብ ፡ ካደረገ፡እንኪያስ፡ዐዋቂው፡ጳውሎስ፡እንደ ተናገረ፡እኛ፡በእውነት፡ወንድሞቹ፡እንባ ላለን።

፱፤ በእኛ፡ባሕርይ፡የታመመ፡እርሱ፡በፈቃዱ፡ በሥጋው፡ሞትን፡ተቀበለው።በደል፡ሳይኖርበት፡የእኛን፡መከራ፡በመቀበሉም፡የሞት፡ ሥልጣን፡ያለው፡ዲያብሎስን፡በእውነት፡ ድል፡ነሣው።

፲፤ በባሕርየ ፡ መለኮቱ ፡ ግን ፡ ሕማም ፡ ሞት ፡ የሌለበት ፡ ነው ። በዚህ ፡ ድል ፡ መንሣት ፡ እንደምን ፡ አንመካም? እነሆ ፡ እኛ ፡ ለኃጢአት፣ ለሞት ፡ ከመገዛት ፡ ድነናል ። የመጻሕፍትን ፡ ምሥጢር ፡ የማያደንቅ ፡ አውጣኪንስ፡የእርሱን፡ክህደት፡የያዘውንም፡ሁሉ፡ አውግዞ፡የማይለይ፡ማነው?

የዚህ ፡ መምህር ፡ በረከቱ ፡ ከእኛ ፡ ጋራ ፡ ለዘላለሙ፡ትኑር፡አሜን።

የአባታችን፡የአባ፡ሲኖዳ፡ምክር፡እዝናት፡ ይህ፡ነው፤በረከቱ፡ከእኛ፡ጋራ፡ለዘላለሙ፡ ትሁን፡አሜን።

፩፤ እኔ፡ቦሁለት፡ነገር፡አስረዳችኋለሁ፤በምድር፡ ንስሓ ፡ ስለ ፡ ገቡ ፡ ሰዎች ፡ እግዚአብሔር ፡

Scanned by CamScanner

## በ፩፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሠሉስ/ነግህ።

በውስተ፡ሰማይ፡በእንተ፡ንስሓሆሙ፡በዲበ፡
ምድር፤እስመ፡እሙንቱ፡ኢይሬእዩ፡ሐዘነ፡
ወኢሕማመ፡በውስተ፡መካን፡ደኃሪ።

፲፱፡ እለሰ ፡ ኢይትፌሣሕ ፡ ልቦሙ ፡ በውስተ ፡
ሰማይ ፡ በእንተ ፡ ኢተመይጦቶሙ ፡ ወኢነስ
ሐቶሙ ፡ በዲበ ፡ ምድር፤እስመ ፡ ኢይሬእዩ ፡
ፍሥሓ ፡ ወኢ ፡ ዕረፍተ ፡ በህየ ፡ በውስተ ፡
መካን፡ ደኃሪ ፡ እስመ ፡ እለ ፡ ይትፌሥሑ ፡
በውስተ፡ዝ፡ዓለም፡ኢይሬእዩ፡ፍሥሓ፡ወኢ
ዕረፍተ፡በህየ።

፳፡ ኢሰማዕክሙኑ ፡ ዘይቤ ፡ ብፁዓን ፡ እለ ፡
ይላሕዉ ፡ ይእዜ ፡ እስመ ፡ እሙንቱ ፡
ይትፌሥሑ።

፳፩፡ ወከመ ፡ እለ ፡ ይትፌሥሑ ፡ በዲበ ፡ ምድር ፡
ኢይረክቡ ፡ ፍሥሓ ፡ በሰማያት ፡ ኢሰማዕ
ክሙኑ፡ዘይቤ፡አሌ፡ለክሙ፡እለ፡ትሥሕቁ፡
ይእዜ ፡ እስመ ፡ አንትሙ ፡ ትበክዩ ፡
ወተሐዝኑ።

፳፪፡ ዝንቱ ፡ ውእቱ ፡ ዘመን ፡ ዘይጸንዑ ፡ ቦቱ ፡
ቅዱሳን፡ወድኩማን፡ይብሉ፡ንሕነ፡ጽኑዓን፡
በከመ፡ውእቱ፡ጽሑፍ፡ወአልቦሙ፡በከመ፡
ይቤ ፡ ነቢይ ፡ ብዙኃን ፡ እለ ፡ አድከሙ ፡
ሥጋሆሙ፡በዝሙት።

፳፫፡ ወካዕበ ፡ ያደክሙ ፡ ርእሶሙ ፡ በከመ ፡ ይቤ ፡
መጽሐፍ ፡ በእንቲአሆሙ ፡ እስመ ፡ ኀጥእ ፡
ይሰበር፡በርስሐተ፡ርእሱ።

፳፬፡ ወለእለሰ ፡ ይትቃተሉ ፡ በጥብዓት ፡ ይብል ፡
መጽሐፍ ፡ በእንቲአሆሙ ፡ አስተፋጥን ፡
ከመ ፡ ትረሲ ፡ ርእሰከ ፡ ኅሩየ ፡ ለኀበ ፡ እግዚአ
ብሔር ፡ ከመ ፡ ገባራዊ ፡ ዘኢይትኀፈር ፡
ዘርቱዐ፡ ይመትር ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡
በጽድቅ።

ምንተኑ፡አአሥየኪ፡በል።

ተአምሪሃ፡ለእግዝእትነ፡ቅድስት፡ድንግል፡
በ፪ኤ፡ማርያም፡ወላዲተ፡አምላክ፡ጸሎታ፡
ወበረከታ፡የሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡
አሜን።

፳፭፡ ወሀሎ ፡ አሐዱ ፡ ብእሲ ፡ ወእንዘ ፡ የኀዕብ ፡
አልባሲሁ፡መጽአ፡ካልእ፡ብእሲ፡ወሚጠ፡

## ማክሰኞ፡መዓልት፡በ፩፡ሰዓት/ነግህ።

በሰማይ ፡ ደስ ፡ ይሰኙባቸዋል ፤ እነርሱ ፡
በኋለኛው ፡ ዓለም ፡ ሐዘንን ፡ ሥቃይንም ፡
አያዩምና።

፲፱፡ በሰማይ፡ደስ፡የማይሰኙባቸው፡ግን፡በምድር፡
ሳሉ፡ከክፉ፡ሥራቸው፡ተመልሰው፡ንስሐ፡
ባልገቡ፡ሰዎች፡ነው፤በዚያ፡በወዲያኛው፡
ዓለም፡ዕረፍትን፡ተድላ፡ደስታን፡አያዩምና፡
በዚህ፡ዓለም፡ደስ፡ብሏቸው፡የኖሩ፡ሁሉ፡
በዚያ፡በወዲያኛው፡ቦታ፡ተድላ፡ደስታን፡
ዕረፍትንም፡አያገኙምና።

፳፡ ዛሬ፡የሚያዝኑ፡ብፁዓን፡ናቸው፤ደስ፡ይላቸ
ዋልና፡ያለውን፡አልሰማችሁምን?

፳፩፡ በምድር ፡ ደስ ፡ ብሏቸው ፡ ኑረው ፡ በሰማይ፡
ተድላ ፡ ደስታ ፡ ስለማያገኙት ፡ ሰዎች ፡ ዛሬ፡
በዚህ፡ዓለም፡ሳላችሁ፡የምትሥቁ፡ወዮላችሁ!
በወዲያኛው፡ዓለም፡ታለቅሳላችሁና፡ታዝናላ
ችሁና፡ያለውን፡አልሰማችሁምን?

፳፪፡ በገድል ፡ የደከሙ ፡ ቅዱሳን ፡ የሚጸኑበት፡
ዘመን፡ይህ፡ነው፤እኛ፡ጽኑዓን፡ነን፡የሚሉ፡
ጽናት፡የሌላቸው፡ናቸው፤ነቢይ፡ብዙዎች፡
ሥጋቸውን ፡ በዝሙት ፡ አደከሙ ፤ እንዳለ፡
ድካመ፡ነፍስ፡አለባቸው።

፳፫፡ ስለ ፡ እርሳቸው ፡ ኃጥእ ፡ ሰው ፡ በራሱ፡
ኃጢአት፡ ይጠፋል ፡ ብሎ ፡ መጽሐፍ፡እንደተ
ናገረ ፡ ዳግመኛ ፡ ጽንዓ ፡ ነፍስ ፡ አጥተው፡
ራሳቸውን፡ያደክማሉ።

፳፬፡ ጨክነው፡ትሩፋት፡በመሥራት፡የሚጋደሉትን
ግን፡ስለእሳቸው፡መጽሐፍ፡እንዲህ፡ይላል፤በእ
ግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ራስህን ፡ የተመረጠ፡
ታደርግ፡ዘንድ፡ለማስተማር፡ቸኩል፤በእውነት፡
የእግዚአብሔርን፡ቃል፡በቅን፡የሚአስተምር፡
ሰው፡እንደማያፍር፡ገበሬ፡ነው።

ምንተኑ፡አአሥየኪ፡በል።

ልመናዋ ፡ በረከቷ ፡ ከእኛ ፡ ጋራ ፡ ለዘላለሙ፡
ይኑርና ፡ በሁለት ፡ ወገን ፡ ድንግል ፡ የሆነች፡
አምላክን፡የወለደች፡ክብርት፡እመቤታችን፡
ማርያም፡ያደረገችው፡ተአምር፡ይህ፡ነው።

፳፭፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ነበረ ፡ ልብሶቹንም ፡ ሲያጥብ፡
ሌላ፡ሰው፡መጥቶ፡ያንን፡ውኃ፡ሌላ፡መንገድ፡

Scanned by CamScanner

በ፭፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሠሉስ/ነግህ።

ውእተ፡ማየ፡ኀበ፡ካልእ፡ፍኖት።
፪፤ ወይቤሎ ፡ ውእቱ ፡ ኀጸቢ ፡ አመኃጽነከ ፡
በጸሎታ ፡ ለእግዝእትነ ፡ ማርያም ፡ ወላዲተ ፡
አምላክ፡ኀድግ፡ዘንተ፡ማየ።
፫፤ ወሖሮ ፡ ዝንቱ ፡ ብእሲ ፡ ወአውገዞ ፡ ካዕበ ፡
ወሦልሰ፡አበዮ፡ውእቱ፡ብእሲ።

፬፤ ወውእተ ፡ ጊዜ ፡ ተመይጠ ፡ ማይ ፡ መንገለ ፡
ዐቀብ ። ወተጋብኡ ፡ ኵሉ ፡ ሰብእ ፡ ወሕዝብ ፡
ብዙኃን ፡ ወአንከሩ ፡ ዘኮነ ፡ ወነበረ ፡ ጕንዱየ ፡
ሰዓተ።

፭፤ ወእምዝ ፡ ተመይጠ ፡ ማይ ፡ ኀበ ፡ ማኅደሩ ፡
በፈቃደ፡እግዚአብሔር፡ወበስእለታ፡ለእግዝ
እትነ፡ቅድስት፡ድንግል፡በክልኤ፡ማርያም፡
ወላዲተ፡አምላክ።
ጸሎታ፡ወበረከታ፡የሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡
ዓለም፡አሜን።

ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ጥዑመ፡ስም፡በል።

ተአምር፡ወመንክር፡ዘገብረ፡እግዚእነ፡ወአ
ምላክነ ፡ ወመድኃኒነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡
ዘከመ ፡ አለበዎሙ ፡ ለአርዳኢሁ ፡ ከመ ፡
የሐውር፡ኢየሩሳሌም፡ይፈጽም፡ትንቢተ፡
ነቢያት ፡ ወዘከመ ፡ ሦጠት ፡ ብእሲት ፡
ዘማዊት፡ ዕፍረተ ፡ ላዕለ ፡ ርእሱ ፡ ወዘከመ ፡
ይቤሎሙ፡ተኃሥሡኒ፡ወኢትረክቡኒ።
ሣህሉ፡ወምሕረቱ፡የሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡
ዓለም፡አሜን።
፮፤ ወሶበ ፡ ፈጸመ ፡ እግዚእ ፡ ኢየሱስ ፡ ዘንተ ፡
ትእዛዘ፡ይቤሎሙ፡ለአርዳኢሁ፡ንሑር፡ኢየ
ሩሳሌም፡ከመ፡ይትፈጸም፡ትንቢተ፡ነቢያት፡
ዘተነበዩ፡በእንቲአየ፡እምቅድመ፡ያግብእኒ፡
ዘያገብእ ፡ ኀበ ፡ አይሁድ ፡ በከመ ፡ ተጽሕፈ ፡
በካልእ፡አንቀጸ፡ዝንቱ፡መጽሐፍ።

፯፤ ዘይቤ ፡ ወሶበ ፡ ሰምዐ ፡ ሰይጣን ፡ ቃሎ ፡ ለእግ
ዚእነ ፡ ወርእየ ፡ ኀይሎ ፡ ዲበ ፡ መቃብረ ፡
አልዓዛር፡ሐዘነ፡ጥቀ፡ወይቤሎሙ፡ለሐራሁ፡
ለእመ፡ነበረ፡ዝንቱ፡ብእሲ፡እንዘ፡ይገብር፡
ዘንተ፡ኀይለ፡ዘርኢኩ፡ኢንረክብ፡ዕረፍተ።
፰፤ ባሕቱ ፡ አሐውር ፡ ኀበ ፡ ሰብአ ፡ ዓለም ፡ ወእሬ

ማክሰኞ፡መዓልት፡በ፭፡ሰዓት/ነግህ።

መለሰው።
፪፤ ያም ፡ ልብስ ፡ አጣቢ ፡ አምላክን ፡ በወለደች ፡
በእመቤታችን ፡ ማርያም ፡ ጸሎት ፡ አማጽኜ
ሃለሁ፡ይህን፡ውኃ፡ተው፡አለው።
፫፤ ያም ፡ ሰው ፡ እምቢ ፡ ብሎ ፡ ወሰደበት፤ይህም ፡
አጣቢ ፡ ሁለት ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ መላልሶ ፡
አማጸነው።
፬፤ ያን፡ጊዜ፡ውኃው፡ሽቅብ፡ተመለሰ፤ሰዎችም፡
ሁሉ ፡ ብዙ ፡ ሕዝቦችም ፡ ተሰበሰቡ ፤ የሆነ
ውንም ፡ ተአምር ፡ አደነቁ ። ውኃውም ፡ ወደ ፡
ዐቀበቱ፡እንደተመለሰ፡ብዙ፡ሰዓቶች፡ቆየ።

፭፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፈቃድ ፡
በሁለት ፡ ወገን ፡ ድንግል ፡ በሆነች ፡ ቅድስት ፡
እመቤታችን ፡ ማርያም ፡ ልመና ፡ ውኃው ፡
ወደቦታው፡ተመለሰ።
ልመናዋ ፡ በረከቷ ፡ ከእኛ ፡ ጋራ ፡ ለዘላለሙ ፡
ይኑር፡አሜን።

ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ጥዑመ፡ስም፡በል።

ይቅርታውና፡ቸርነቱ፡ለዘለዓለሙ፡ይደርብንና፡
በነቢያት ፡ ስለእርሱ ፡ የተነገረውን ፡ ትንቢት ፡
ይፈጽም ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ እንደ
ሚሄድ፡ለደቀ፡መዛሙርቱ፡እንዳስገነዘባቸው፡
አመንዝራ፡የነበረች፡ሴትም፡በራሱ፡ላይ፡ሽቱ፡
እንደ ፡ ጨመረችና ፡ ትፈልጉኛላችሁ፡ አታገ
ኙኝም፡እንዳላቸው፡የሚገልጽ፡ጌታችን፡ፈጣሪ
ያችንና ፡ መድኃኒታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡
ያደረገው፡ድንቅ፡ተአምር፡ይህ፡ነው።
፮፤ ጌታ፡ኢየሱስ፡ይህን፡ትእዛዝ፡በፈጸመ፡ጊዜ፡
ደቀ፡መዛሙርቱን፡ይህ፡መጽሐፍ፡የሚለው፡
በሌላ፡አንቀጽ፡እንደተጻፈ፡ወደ፡አይሁድ፡
አሳልፎ፡የሚሰጠኝ፡አሳልፎ፡ከመስጠቱ፡
አስቀድሞ ፡ ነቢያት ፡ ስለእኔ ፡ የተናገሩት ፡
ትንቢት፡ይፈጸም፡ዘንድ፡ወደ፡ኢየሩሳሌም፡
እንሂድ፡አላቸው።
፯፤ ሰይጣን፡የጌታን፡ቃሉን፡በሰማ፡ጊዜ፡በአል
ዓዛር፡መቃብር፡ላይ፡ያደረገውንም፡ኃይሉን፡
በአየ፡ጊዜ፡እጅግ፡አዘነ።ለጭፍሮቹም፡ይህ፡
ሰው ፡ ይህን ፡ ያየሁትን ፡ ኃይል ፡ እያደረገ ፡
ከኖረ፡ዕረፍትን፡አናገኝም፡አላቸው።
፰፤ ነገር ፡ ግን ፡ በዓለም ፡ ወደአሉ ፡ ሰዎች ፡ ሂጄ ፡

Scanned by CamScanner

## በ፩፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሠሉስ፡/ነግሀ።

ስዮሙ፡ይስቅልዎ፡ዲበ፡ዕፅ፡ወይመጥውዎ፡ ለሞት።

፬፤ ባሕቱ ፡ አሌ ፡ ሎቱ ፡ ለውእቱ ፡ ብእሲ ፡ ዘያመጽኦ፡ለእኪት፡በእዴሁ፡እምኀየሶ፡ሶበ፡ ኢተወልደ።

፭፤ ዓዲ ፡ እምኀየሶ ፡ ከመ ፡ ይእስሩ ፡ በክሣዱ ፡ ማሕረጸ ፡ አድግ ፡ ወያሥጥምዎ ፡ ውስተ ፡ ልጐተ፡ባሕር።

፮፤ ወእምዝ ፡ ሖረ ፡ እግዚእ ፡ ኢየሱስ ፡ ወቦአ ፡ ቤተ፡ ስምዖን ፡ ወሀለወት ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ብእሲት ፡ ዘማዊት ፡ ዘትሁብ ፡ ርእሳ ፡ ለኵሉ ፡ ዘየኃሥሣ ፤ ወእምነገደ ፡ ይሁዳ ፡ ይእቲ ፡ ወስማ፡ ማርያም።

፯፤ ወሶበ፡ሰምዐት፡ከመ፡ሀሎ፡እግዚእ፡ኢየሱስ፡ ምስለ፡አርዳኢሁ፡ውስተ፡ቤተ፡ስምዖን፡ ነሥአት፡ሠለስተ፡ምእተ፡ዲናረ፡ወርቅ፡ ወሖረት ፡ ኀበ ፡ ርእሰ ፡ ነጋድያን ፡ እለ ፡ ይሠይጡ ፡ አፈወ ፡ ወስሙ ፡ ለውእቱ ፡ ሐድኖክ፡እምነገደ፡ሮቤል፡ወትቤሎ፡ይትረ ክብኑ ፡ በኀቤከ ፡ ቅብዕ ፡ አፈው ፡ ዘይደሉ ፡ ለነገሥት።

፰፤ ወሀሎ፡ውስተ፡ቤቱ፡ለውእቱ፡ነጋዲ፡ቀርነ፡ ወርቅ ፡ ዘኮነ ፡ ውስተ ፡ ታቦት ፡ ቀዲሙ ፡ በደብተራ ፡ ስምዕ ፡ ወምሉእ ፡ ውስቴቱ ፡ ዘወሀቦ፡እግዚአብሔር፡ለሙሴ፡ገብሩ፡ከመ፡ ይቅባዕ ፡ ቦቱ ፡ ነገሥተ ፡ ወነቢያተ ፡ ወካህናተ።

፱፤ እስመ ፡ ሙሴ ፡ ነቢይ ፡ ወኵሎሙ ፡ ነቢያት ፡ እለ፡ መጽኡ ፡ እምድኅሬሁ ፡ ለእመ ፡ ፈቀዱ ፡ ይቅብዑ ፡ በዝንቱ ፡ ቅብዕ ፡ ነቢየ ፡ አው ፡ ንጉሠ፡ አው ፡ ካህነ ፡ ያነብርዎ ፡ ለቀርን ፡ ዲበ ፡ ርእሱ።

፲፤ ወቅብዕሂ ፡ ይፈልፍል ፡ እምኔሁ ፡ ወይ ወርድ ፡ ውስተ ፡ ጸሕለ ፡ ወርቅ ፡ ዘልዱቅ ምስለ፡ቀርን።

፲፩፤ ወሐድኖክሰ ፡ ነጋዲ ፡ ኢየአምር ፡ ግብሮ ፡ ለዝንቱ፡ቅብዕ፡ወኢ፡ሤጠ፡ወኮነት፡እሙ፡ ለሐድኖክ፡ተአምር፡ግብሮ፡ለቅብዕ፡ወኢነ ገረቶ፡ለወልዳ።

ወጼናሁ፡ለዝንቱ፡ቅብዕ፡ይጼኑ፡እምኵሉ፡ አፈው፡ዘሀሎ፡ኀበ፡ነጋድያን።

፲፪፤ ወሐድኖክ ፡ ነጋዲ ፡ ኢይፈቅድ ፡ ይሢጦ ፡ በእንተ፡ ፍቅረ ፡ ጼናሁ ። ወሶበ ፡ መጽአት ፡

## ማክሰኞ፡መዓልት፡በ፩፡ሰዓት/ነግሀ።

በእንጨት ፡ ላይ ፡ ሰቅለው ፡ ለሞትም ፡ አሳልፈው፡እንዲሰጡት፡አደርጋለሁ።

፬፤ ነገር ፡ ግን ፡ ክፋትን ፡ በእጁ ፡ ለሚያመጣት፡ ለዚያ፡ሰው፡ወዮለት፤ባይወለድ፡በተሻለው፡ ነበር።

፭፤ ዳግመኛም፡አህያ፡የሚአሽከረክረውን፡የወፍጮ፡ ደንጊያ ፡ በአንገቱ ፡ አስረው ፡ ከጥልቅ ፡ አዘቅት፡ ባሕር፡ቢአሠጥሙት፡በተሻለው፡ነበር።

፮፤ ከዚህ ፡ በኋላም ፡ ጌታ ፡ ኢየሱስ ፡ ሄዶ ፡ ወደ፡ ስምዖን፡ቤትም ፡ ገባ። በኢየሩሳሌምም፡ለሚ ፈልጋት ፡ ሁሉ ፡ ራስዋን ፡ ለዝሙት ፡ የምትሰጥ፡አመንዝራ፡ሴት፡ነበረች፤እሷም፡ ከይሁዳ ፡ ወገን፡ ናት ፡ ስሟም ፡ ማርያም፡ (እንተ፡እፍረት)፡ይባል፡ነበር።

፯፤ ጌታ ፡ ኢየሱስም ፡ ከደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ጋራ ፡ በስምዖን ፡ ቤት ፡ እንዳለ ፡ በሰማች፡ ጊዜ ፡ ሽቱ ፡ ለሚሸጡ ፡ ሁሉ ፡ ነጋዴዎች፡ አለቃ ፡ ወደሚሆን ፡ ስሙ ፡ ሐድኖክ ፡ ወደ፡ ሚባል ፡ ሰው ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ብር ፡ ይዛ፡ ሂዳ ፡ ለነገሥታት ፡ የሚገባ ፡ የሽቱ ፡ ቅባት ፡ በአንተ ፡ ዘንድ ፡ ይገኛልን ፡ አለችው።

፰፤ ነገሥታትን ፡ ነቢያትን ፡ ካህናትን ፡ ይቀባ፡ ዘንድ ፡ ለባለሟሉ ፡ ለሙሴ ፡ እግዚአብሔር፡ የሰጠው ፡ የሽቱ ፡ ቅባትን ፡ የተመላ ፡ በምስክሩ፡ ድንኳን ፡ ተቀምጦ ፡ የነበረ ፡ የወርቅ ፡ ብልቃጥ ፡ በዚያ ፡ ነጋዴ ፡ ቤት፡ ተቀምጦ፡ነበር።

፱፤ ነቢዩ ፡ ሙሴና ፡ ከሙሴም ፡ በኋላ ፡ የተነሡ፡ ነቢያት ፡ ሁሉ ፡ ንጉሥንም ፡ ሆነ ፡ ወይም፡ ነቢይን ፡ ወይም ፡ ካህንን ፡ ይህን ፡ ቅባት፡ ለመቀባት ፡ የፈለጉ ፡ እንደሆነ ፡ ብልቃጡን፡ በራሱ፡ላይ፡ያኖሩታል።

፲፤ ቅባቱም ፡ ከወስጡ ፡ ገንፍሎ ፡ ከብልቃጡ፡ ጋራ፡ አንድ ፡ ሁኖ ፡ ከተሠራው ፡ ወደ፡ወርቁ፡ ጻሕል፡(ፍንጃል)፡ይወርድ፡ነበር።

፲፩፤ ነጋዴው፡ሐድኖክም፡የሽቱውን፡ምሥጢር፡ አያውቅም ። ዋጋውንም ፡ አያውቅም፡ ነበር፡ እናቱ፡ግን፡ታውቅ፡ነበር። ለልጇም አልነገረ ችውም።

የዚያም ፡ ሽቱ ፡ መዓዛ ፡ ከነጋዴዎች ፡ ዘንድ፡ ከሚገኝ፡ሽቱ፡ሁሉ፡ይበልጣል።

፲፪፤ ሐድኖክም፡መዓዛውን፡ከመውደዱ፡የተነሣ፡ ሊሸጠው ፡ አይወድም ፡ ነበር ። ለነገ

Scanned by CamScanner

**በ፩፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሠሉስ፡/ነግህ።**

ማርያም፡ወሰአለቶ፡በእንተ፡ቅብዕ፡ዘይደሉ፡ ለነገሥት፡አውሥአ፡ወይቤላ፡ሀሎ፡ዐቢይ፡ ቅብዕ፡መንከረ፡ጼና፡ወውእቱ፡ይደሉ፡ለዘት ፈቅዲ።

፲፫፡ ወወሀበቶ፡ሠለስተ፡ምእተ፡ዲናረ፡ወርቅ፡ ዘሀሎ፡ምስሌሃ፡ወመጠዋ፡ሐድኖከ፡ውእተ፡ ቀርነ፡ቅብዕ።

፲፬፡ ወይእቲሰ ፡ ሖረት ፡ ቤተ ፡ ስምዖን ፡ ወጐድጐደት፡ አንቀጸ ፡ ወወፅአ ፡ ኀቤሃ ፡ ስምዖን፡ወሶበ፡አጼነወ፡ጼና፡ዘኢያጼነወ፡ ዘከማሁ፡ቀዲሙ፡እስመ፡ጼናሁ፡ለውእቱ፡ ቅብዕ ፡ ፍትው ፡ ጥቀ ፡ ይቤላ ፡ ለዘማዊት ፡ እሬእየኪ ፡ ከመ ፡ ተቀባዕኪ ፡ አፈወ ፡ ወመጻእኪ፡ኀቤነ።

፲፭፡ ሑሪ፡እምኔነ፡በሰላም፡ወተዐቀቢ፡ከመ፡ ኢተዐዪ፡በላህበ፡እሳቱ፡ለውእቱ፡ብእሲ፡ ዘሀሎ፡ኀቤነ።
እስመ ፡ ውእቱ ፡ ጻድቅ ፡ ወይጸልአሙ ፡ ለኃጥአን፡ወለመናፍቃን።

፲፮፡ ወኀደጋ፡እንዘ፡ትቀውም፡በአፍአ፡ወዐጸወ፡ ኆኅተ፡በገጻ፡ወቦአ፡ቤቶ።

፲፯፡ ወይቤሎ፡እግዚእ፡ኢየሱስ፡መኑ፡ጐድጐደ፡ አንቀጸ፡ቤትከ፡አ፡ስምዖን፡ወዘጐድጐደ፡ በአይ፡ግብር፡ዘኢያባእኮ።

፲፰፡ ወይቤሎ፡ስምዖን፡አ፡እግዚእየ፡ጐድጐደ፡ ኆኅተ፡ብእሲ፡ዘኢይደሉ፡ይባእ፡ዘከማሁ፡ ኀቤከ።

፲፱፡ እስመ ፡ ይእቲ ፡ ብእሲት ፡ እምነገደ ፡ ይሁዳ ፡ ዕውቅት ፡ በዝሙት ፡ ወሙስንት ፡ እምአዋልደ፡ ህጉላን ፡ እለ ፡ ሀለዋ ፡ በኢ የሩሳሌም።

፳፡ ወይቤሎ ፡ እግዚእ ፡ ኢየሱስ ፡ አ ፡ ስም ዖን፡ኢመጽአ፡ወልደ፡ዕጓለ፡እመሕያው፡ ውስተ፡ምድር፡ከመ፡ያሕዩ፡ጻድቃነ፡አላ፡ ኃጥአነ፡እለ፡አልቦሙ፡ጻሕቅ፡ለንስሓ፡ፃእ፡ አንተሰ ፡ ወአርኅዋ ፡ ለዛቲ ፡ ብእሲት ፡ ወአብእ፡ ኃቤየ ፡ እስመ ፡ ሀሎ ፡ ምስሌሃ ፡ ብዙኅ፡ንዋይ።

፳፩፡ ወወፅአ፡ስምዖን፡እንዘ፡ይበኪ፡ወይቴክዝ፡ በእንተ፡በአታ፡ለብእሲት፡ውስተ፡ቤቱ፡ ወአርኀወ፡ላቲ።

፳፪፡ ወሶበ፡ቦአት፡ቆመት፡ቅድመ፡እግዚእ፡ ኢየሱስ፡ወሰገደት፡ሎቱ፡ወአውዕአት፡ቀርነ

**ማክሰኞ፡መዓልት፡በ፩፡ሰዓት/ነግህ።**

ታት ፡ ስለሚገባ ፡ የሽቱ ፡ ቅባት ፡ ማርያም ፡ መጥታ፡በለመነችው፡ጊዜ፡መዓዛው፡ድንቅ፡ የሆነ፡ታላቅ፡የሽቱ፡ቅባት፡አለ፡አንቺ፡ለምት ፈልጊው፡እርሱ፡ይገባል፡ብሎ፡መለሰላት።

፲፫፡ የያዘችውን ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ብር ፡ ሰጠችው ፤ ሐድኖከም ፡ ያንን ፡ የሽቱ ፡ ቅባት ፡ የተመላ ፡ ብልቃጥ፡ሰጣት።

፲፬፡ እርስዋም፡ወደ፡ስምዖን፡ቤት፡ሂዳ፡በሩን፡ አንኳኳች ፡ ስምዖንም ፡ ወደርሷ ፡ ወጣ ። እንደርሱ ፡ ያለ ፡ አስቀድሞ ፡ ያላሸተተው ፡ የሽቱ፡መዐዛ፡በሸተተው፡ጊዜ፡የዚያ፡ሽቱ፡ መዐዛ፡እጅግ፡የተወደደ፡ነበረና፡አመንዝራ ይቱን ፡ ሽቱ ተቀብተሽ ፡ ወደ ፡ እኛ ፡ እንደ ፡ መጣሽ፡አይሻለሁ።

፲፭፡ አሁንም፡ከእኛ፡ዘንድ፡በሰላም፡ተመለሽ፤ ከእኛ፡ዘንድ፡ባለው፡ሰው፡በእሳቱ፡ሙቀት፡ እንዳትቃጠዪ፡ተጠበቂ፤እርሱ፡ጻድቅ፡ነው፤ ኀጢአተኞችንና ፡ ከሐዲዎችን ፡ ይጠላቸ ዋልና፡አላት።

፲፮፡ በውጭ ፡ እንደቆመች ፡ ተዋት ፡ በፊትዋም ፡ ላይ፡በሩን፡ዘግቶ፡ወደቤቱ፡ገባ።

፲፯፡ ጌታ ፡ ኢየሱስም ፡ ስምዖን ፡ ሆይ ፡ የቤትህን ፡ መግቢያ ፡ በር ፡ ያንኳኳ ፡ ማነው ? ያላስገባ ኸውስ፡በምን፡ሥራ፡ነው፡አለው።

፲፰፡ ስምዖንም ፡ ጌታዬ ፡ ሆይ ፡ እንደርሱ ፡ ያለ ፡ ወደ ፡ አንተ ፡ መግባት ፡ የማይገባው ፡ ሰው ፡ ነው።

፲፱፡ እርሷም፡ከይሁዳ፡ወገን፡የሆነች፡በአመንዝ ራነቷ ፡ የታወቀች ፡ በኢየሩሳሌምም ፡ ከሚኖሩ፡በዝሙት፡ከረከሱ፡ሴቶች፡ልጆች፡ ሁሉ፡የረከሰች፡ናት፡አለው።

፳፡ ጌታ ፡ ኢየሱስም ፡ ስምዖን ፡ ሆይ ፡ ለንስሓ ፡ ትጋት ፡ የሌላቸውን ፡ ኃጢአተኞችን ፡ ለማዳን፡ እንጂ ፡ ጻድቃንን ፡ ያድን ፡ ዘንድ ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ወደ ፡ ዓለም ፡ አልመጣም ፤ አንተም፡ወጥተህ፡ለዚያች፡ሴት፡በሩን፡ክፈ ትላትና፡ወደ፡እኔ፡አስገባት፤ከእርሷ፡ጋራ፡ ብዙ፡ገንዘብ፡አለና፡አለው።

፳፩፡ ስምዖንም ፡ ስለ ፡ ሴቲቱ ፡ ወደቤቱ ፡ መግባት ፡ ፈጽሞ ፡ እያዘነ ፡ ወጥቶ ፡ ከፈተ ላት።

፳፪፡ በገባችም ፡ ጊዜ ፡ በጌታ ፡ ኢየሱስ ፡ ፊት ፡ ቆመች፡ ሰገደችለትም ፡ የያዘችውንም ፡ የሽቱ

Scanned by CamScanner

| በ፩፡ሰዓተ፡መዓልትዘሠሉስ፡/ነግህ። | ማክሰኞ፡መዓለት፡በ፩፡ሰዓት። |
|---|---|
| ቅብዕ ፡ ዘሀሎ ፡ ምስሌሃ ፡ ወሶጠቶ ፡ ለቅብዕ ፡ ላዕለ፡ርእሱ፡ወእገሪሁ፡እስመ፡ዝንቱ፡ቅብዕ፡ ይደልዎ ፡ እስመ ፡ ቅብዐ ፡ መንግሥት ፡ ወትንቢት፡ወክህነት፡ሎቱ፡ውእቱ። | ብልቃጥ ፡ አውጥታ ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ ሽቶውን፡ አፈሰሰችው፡እግሮቹንም፡አሸች፤ይህ፡ቅባት፡ ስለሚገባው ፡ የመንግሥት ፡ የትንቢት ፡ የክህነት፡ቅባት፡ለርሱ፡ገንዘቡ፡ነውና። |
| ፳፫፤ ወእምዝ ፡ ዓዲ ፡ ይቤሎሙ ፡ ዕቀቡ ፡ ኵሎ ፡ ትእዛዝየ ፡ ወኢትክሥቱ ፡ ለመኑሂ ፡ እስከ ፡ እርገትየ፡ውስተ፡ሰማያት። | ፳፫፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ዳግመኛ ፡ እንዲህ ፡ አላቸው፡ ትእዛዜን፡ጠብቁ፤ወደ፡ሰማይ፡እስከምወጣ፡ ድረስ፡ለማንም፡አትግለጡ። |
| ፳፬፤ ወይእዜሰ ፡ ጸሐፍዋ ፡ ውስተ ፡ ሠሌዳ ፡ ልብክሙ፡ወኅብእዋ፡በውሳጥያቲክሙ። | ፳፬፤ አሁንም፡በልቡናችሁ፡ሠሌዳነት፡ጻፉትሁ፡ በአእምሮአችሁ፡ውስጥ፡ሠውሯት። |
| ፳፭፤ ዕቀቡ ፡ ምሥጢራትየ ፡ ዘወሀብኩክሙ ፡ ኢታብጥሉ፡አሐደ፡እምኔሆሙ። | ፳፭፤ የገለጽኩላችሁንም፡ምሥጢሮቼን፡ጠብቁ፤ከ ርሳቸውም፡አንዱን፡እንኳን፡አታጉድሉ። |
| ፳፮፤ አእምሩ ፡ ኢየኀድገክሙ ፡ ተሀልዉ ፡ ትኩዛ ኒክሙ፡ወትረ። | ፳፮፤ ሁልጊዜ ፡ አዝናችሁ ፡ ተክዛችሁ ፡ ትኖሩ፡ ዘንድ፡እንደማልተዋችሁ፡ዕወቁ። |
| ፳፯፤ አእምሩ ፡ እስመ ፡ ኀዳጠ ፡ መዋዕለ ፡ ተኀሥሡኒ፡ ወኢትረክቡኒ ፡ ወኀበሂ ፡ አሐውር፡ኢትክሉ፡መጺአ፡አንትሙ። | ፳፯፤ ጥቂት፡ቀን፡ትሹኝአላችሁ።አታገኙኝምና፡ ዕወቁ ፤ እኔ ፡ ወደምሄድበትም ፡ እናንተ፡ መምጣት፡አትችሉም። |
| ፳፰፤ ወሶቤሃ ፡ ተከዙ ፡ አርዳእ ፡ በእንተዝ ፡ ነገር ፡ ወይቤሉ ፡ በበይናቲሆሙ ፡ አይቴኑ ፡ መካን ፡ የሐውር ፡ ዘኢንክል ፡ ንርአዮ ፡ ወበእንተዝ ፡ ነገር፡ተዐቅፉ፡አርዳኢሁ፡ጥቀ። | ፳፰፤ ስለዚህም፡ነገር፡ያንጊዜ፡ደቀ፡መዛሙርቱ፡ አዘኑ፤እርስ፡በርሳቸውም፡እኛ፡ልናገኘው፡ የማንችል፡ወዴት፡ቦታ፡ይሄዳል፡ተባባሉ፤ ስለዚህም፡ነገር፡እጅግ፡ታወኩ። |
| ፳፱፤ ወአእመረ ፡ እግዚእ ፡ ኢየሱስ ፡ ዘተበሀሉ ፡ አርዳኢሁ ፡ በበይናቲሆሙ ፡ ወይቤሎሙ ፡ አኀውየ ፡ ኢትትዐቀፉ ፡ በዝ ፡ ነገር ፡ ዘእቤ ለክሙ ። እስመ ፡ አነ ፡ ከሠትኩ ፡ ለክሙ ፡ አእሚርየ፡ዘይክል፡ልቡናክሙ፡ጸዊሮቶ። | ፳፱፤ ጌታ ፡ ኢየሱስም ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ርስ፡ በርሳቸው ፡ የተባባሉትን ፡ አውቆ ፡ ወንድሞቼ፡ በዚህ ፡ በነገርኋችሁ ፡ ነገር፡ አትታወኩ፤በልቡናችሁ፡ልትወስኑት፡የም ትችሉትን፡ገልጨላችኋለሁና፡አላቸው። |
| ፴፤ አእምሩ፡ከመ፡መንፈስ፡ይፈቅድ፡ወሥጋ፡ ይደክም፡በእንተ፡ሕማም። | ፴፤ መንፈስ፡እንደሚሻ፡ሥጋ፡ግን፡ስለመከራ፡ እንደሚደክም፡ዕወቁ። |
| ፴፩፤ ወብየ ፡ ብዙኅ ፡ ነገር ፡ እምዘነገርኩክሙ ፡ ይእዜ፡ወባሕቱ፡ኢትክሉ፡ጸዊሮቶ። | ፴፩፤ ዛሬ፡ከነገርኋችሁ፡ሌላ፡ብዙ፡ነገር፡ነበረኝ፤ ነገር፡ግን፡ልትወስኑት፡አትችሉም። |
| ፴፪፤ ወበእንተዝ፡ኀደጉ፡ነገሮተክሙ፡ወዕቀቡ፡ ዘወሀብኩክሙ።ሣህሉ፡ወምሕረቱ፡የሀሉ፡ ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን። | ፴፪፤ ስለዚህ ፡ መናገሩን ፡ ተውኩ ፤ የሰጠኋችሁን፡ ትዕዛዝ ፡ ጠብቁ ፡ አላቸው ። ይቅርታው፡ ቸርነቱ፡ከእኛ፡ጋር፡ለዘላለሙ፡ይኑር፡አሜን። |

| ክፍል፡፫። | ክፍል፡፫። |
|---|---|
| ይ፡ዲ፡ቅድመ፡ወንጌል። | ዲያቆኑ፡ከወንጌል፡በፊት። |
| መዝ፤፴፬፡፬። | መዝ፤፴፬፡፬። |
| ለይትኀፈሩ ፡ ወይኀሰሩ ፡ እለ ፡ የኀሥሥዋ ፡ ለነፍስየ። ለይግብኡ ፡ ድኅሬሆሙ ፡ ወይትኀፈሩ ፡ እለ ፡ መከሩ፡እኩየ፡ላዕሌየ። ለይኩኑ፡ከመ፡ጸበል፡ዘቅድመ፡ገጸ፡ነፋስ። | ሰውነቴን ፡ ለማጥፋት ፡ የሚሿት ፡ ሁሉ ፡ ይፈሩ፤ ይጐስቍሉም ፤ በእኔ ፡ ክፉ ፡ ሊአመ ጡብኝ ፡ የመከሩብኝ ፡ ሁሉ ፡ ወደኋላቸው ፡ ይመለሱ፤ይፈሩ። በነፋስ፡ፊት፡እንዳለ፡ትቢያ፡ይሁኑ፡ይበሉ። |

በ፩፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሠሉስ/ነግሀ።

## ወንጌል፡ዘማቴዎስ።

ምዕ፡፳፮፡፩-፲፬።

፩፡ ወሶበ ፡ ፈጸመ ፡ እግዚእ ፡ ኢየሱስ ፡
ዘንተ ፡ ኵሎ ፡ ነገረ ፡ ይቤሎሙ ፡ ለአ
ርዳኢሁ።
፪፡ ተአምሩሁ ፡ ከመ ፡ እምድኅረ ፡ ክልኤ ፡
መዋዕል፡ ይከውን ፡ ፋሲካ ፡ ወይእኅዝዎ ፡
ለወልደ፡ዕጓለ፡እመሕያው፡ወይሰቅልዎ።
፫፡ ወእምዝ ፡ ተጋብኡ ፡ ሊቃነ ፡ ካህናት ፡
ወጸሐፍት ፡ ወሊቃናተ ፡ ሕዝብ ፡ ውስተ ፡
ዐጸደ፡ሊቀ፡ካህናት፡ዘስሙ፡ቀያፋ።
፬፡ ወተማከሩ ፡ ከመ ፡ በሕብል ፡ የአኀዝዎ ፡
ለእግዚእ፡ኢየሱስ፡ወይቅትልዎ።
፭፡ ወይቤሉ ፡ ባሕቱ ፡ አኮኬ ፡ በበዐል ፡ ከመ ፡
ኢይኩን፡ሀከክ፡በውስተ፡ሕዝብ።
፮፡ ወበጺሖ ፡ እግዚእ ፡ ኢየሱስ ፡ ቢታንያ ፡ ቦአ ፡
ቤተ፡ስምዖን፡ዘለምጽ።
፯፡ ወመጽአት ፡ ኀቤሁ ፡ ብእሲት ፡ እንተ ፡ ባቲ ፡
ቢረሌ ፡ ዘምሉእ ፡ ዕፍረተ ፡ ዘአልባስጥሮስ ፡
ዘብዙኅ ፡ ሤጡ ፡ ወሶጠት ፡ ዲበ ፡ ርእሱ ፡
ለእግዚእ፡ኢየሱስ፡እንዘ፡ይረፍቅ።
፰፡ ወርእዮሙ፡ዘንተ፡አርዳኢሁ፡ተምዑ፡ወአን
ጐርጐሩ ፡ ወይቤሉ ፡ ለምንት ፡ ዘመጠነዝ ፡
ዕፍረተ፡አኅጐለት፡ዛቲ፡ብእሲት።
፱፡ እምኢተሠይጠኑ ፡ ለብዙኅ ፡ ንዋይ ፡
ወየሀብዎ፡ምጽዋተ፡ለነዳያን።
፲፡ ወአእመሮሙ ፡ እግዚእ ፡ ኢየሱስ ፡
ወይቤሎሙ፡ ለምንት ፡ ታሠርሕዋ ፡ ለዛቲ ፡
ብእሲት፡ሠናየ፡ግብረ፡ገብረት፡ላዕሌየ።
፲፩፡ ወለነዳያንሰ ፡ ዘልፈ ፡ ትረክብዎሙ ፡ ወጊዜ ፡
ፈቀድክሙ፡ታሤንዩ፡ሎሙ፡ወኪያየሰ፡አኮ፡
ዘልፈ፡ዘትረክቡኒ።
፲፪፡ ወዘንተሰ ፡ ዕፍረተ ፡ ዘሶጠት ፡ ዲበ ፡ ርእስየ ፡
ለቀበርየ፡ገብረት።
፲፫፡ አማን ፡ እብለክሙ ፡ በኀበ ፡ ሰበክዋ ፡
ለዛቲ ፡ ወንጌል ፡ በውስተ ፡ ኵሉ ፡ ዓለም ፡
ያንብቡ ፡ ላቲ፡ ዘገብረት ፡ ዛቲ ፡ ብእሲት ፡
ወይዝክርዋ።
፲፬፡ ወእምዝ ፡ ሖረ ፡ አሐዱ ፡ እምዐሠርቱ ፡
ወክልኤቱ፡አርዳኢሁ፡ዘስሙ፡ይሁዳ፡አስቆ
ሮታዊ፡ኀበ፡ሊቃነ፡ካህናት።

ማክሰኞ፡መዓልት፡በ፩፡ሰዓት/ነግሀ።

## የማቴዎስ፡ወንጌል።

ምዕ፡፳፮፡፩-፲፬።

፩፡ ጌታ፡ኢየሱስ፡ይህን፡ሁሉ፡ነገር፡ተናግሮ፡
ከጨረሰ፡በኋላ፡ደቀ፡መዛሙርቱን፡እንዲህ፡
አላቸው።
፪፡ ከሁለት ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ ፋሲኺ ፡ እንደሚሆን ፡
ታውቃላችሁን ፡ የሰው ፡ ልጅንም ፡
ይይዙታል፤ይሰቅሉታል።
፫፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ የካህናት ፡ አለቆች ፡ ጸፎችና
የሕዝብ ፡ ሹማምንት ፡ ቀያፋ ፡ በሚባለው ፡
በሊቀ፡ካህናቱ፡ግቢ፡ተሰበሰቡ።
፬፡ ጌታ ፡ ኢየሱስንም ፡ በሐሰት ፡ ይዘው ፡
ይገድሉት፡ዘንድ፡ተማከሩ።
፭፡ ነገር፡ግን፡በሕዝቡ፡መካከል፡ሁከት፡እንዳ
ይሆን፡በበዓል፡አይሁን፡አሉ።
፮፡ ጌታ ፡ ኢየሱስም ፡ ቢታንያ ፡ ደርሶ ፡ ወደ ፡
ለምጻሙ፡ስምዖን፡ቤት፡ገባ።
፯፡ ዋጋው፡ብዙ፡የሆነ፡አልባስጥሮስ፡የሚባል፡
ሽቱ፡የተመላ፡ብርሌን፡የያዘች፡ሴት፡ወደሱ፡
መጣች፤ ጌታ ፡ ኢየሱስም ፡ ለምሳ፡ተቀምጦ፡
ሳለ፡በራሱ፡ላይ፡አፈሰሰችው።
፰፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱም ፡ ይህን ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡
ተቆጥተው፡ይህች፡ሴት፡ይህን፡ያህል፡ሽቱ፡
ለምን፡አባከነች?
፱፡ ለድኆች ፡ ምጽዋት ፡ ይሰጥ ፡ ዘንድ ፡ በብዙ ፡
ገንዘብ፡ባለተሸጠም፡ነበር፡አሉ።
፲፡ ጌታ ፡ ኢየሱስም ፡ አወቀባቸውና ፡ ይህቺን ፡
ሴት ፡ ለምን ፡ ታዳክሚታላችሁ ? ለእኔ ፡
መልካም፡ሥራ፡ሠርታልኛለች።
፲፩፡ ድኆችንማ፡ዘወትር፡ታገኟቸዋላችሁ፤በወደ
ዳችሁትም፡ጊዜ፡በጎ፡ታደርጉላቸዋላችሁ፤
እኔን፡ግን፡ዘወትር፡የምታገኙኝ፡አይደለም።
፲፪፡ ይህንንስ፡በራሴ፡ያፈሰሰችውን፡ሽቱ፡ለምቀ
በርበት፡ቀን፡አስጠበቀች።
፲፫፡ እውነት ፡ እላችኋለሁ ፤ በዓለሙ ፡ ሁሉ ፡
ይህችን፡ ወንጌል ፡ በሚሰብኩበት ፡ ቦታ ፡
ይህች፡ ሴት ፡ ያደረገችውን ፡ ይንገሩላት ፤
ያስቧትም።
፲፬፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ከዐሥራ ፡ ሁለቱ ፡ ደቀ ፡
መዛሙርቱ፡አንዱ፡ይሁዳ፡የሚባለው፡የአስ
ቆሮቱ፡ሰው፡ወደ፡ካህናት፡አለቆች፡ሄደ።

Scanned by CamScanner

## በ፩፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሠሉስ/ነግህ።

፲፭፤ ወይቤሎሙ ፡ ሚ ፡ መጠነ ፡ ትሁቡኒ ፡ እመ ፡ አገብእ ፡ ለክሙ ፡ ወተናገሩ ፡ ምስሌሁ ፡ ወተሰነዐዉ፡የሀብዎ፡ሠላሳ፡ብሩረ።
፲፮፤ ወእምይእቲ ፡ ዕለት ፡ ኮነ ፡ የኃሥሥ ፡ ሣሕተ ፡ ከመ፡ያግብአ፡ሎሙ።

### ዓዲ፡ቅድመ፡ወንጌል።

መዝ፤፻፲፱፡፪።

እግዚኦ ፡ አድኅና ፡ ለነፍስየ ፡ እምከናፍረ ፡ ዐመፃ ። ወእምልሳነ ፡ ጽልሑት ። ብዙኀ ፡ ተዐገሠት ፡ ነፍስየ ፡ ምስለ ፡ እለ ፡ ይጸልኡ ፡ ሰላመ ። እንዘ ፡ ሰላማዊ ፡ አነ ፡ ሶበ ፡ እትናገሮሙ፡ይጸብኡኒ፡በከንቱ።

### ወንጌል፡ዘዮሐንስ።

ምዕ፤፰፡፳፩–፳፱።

፳፩፤ ወካዕበ፡ይቤሎሙ፡እግዚእ፡ኢየሱስ፡አንሰ፡ አሐውር ፡ ተኀሥሡኒ ፡ ወኢትረክቡኒ ፡ ወትመውቱ ፡ በኃጢአትክሙ ፡ ወኀበ ፡ አነ ፡ አሐውር፡አንትሙ፡ኢትክሉ፡መጺአ።
፳፪፤ ወይቤሉ፡አይሁድ፡ይቀትልኑ፡እንጋ፡ርእሶ፡ ለሊሁ ፡ ዘይብለነ ፡ ኀበ ፡ አነ ፡ አሐውር ፡ አንትሙ፡ኢትክሉ፡መጺአ።
፳፫፤ ወይቤሎሙ ፡ አንትሙሰ ፡ እምታሕቱ ፡ አንትሙ ፡ ወአንሰ ፡ እምላዕሉ ፡ አነ ፡ አንትሙሰ ፡ እምዝንቱ ፡ ዓለም ፡ አንትሙ ፡ ወአንሰ፡ኢኮንኩ፡እምዝንቱ፡ዓለም።
፳፬፤ ወናሁ፡እቤለክሙ፡ከመ፡ትመውቱ፡በኃጢአትክሙ ፡ ለእመ ፡ ኢአመንክሙ ፡ ከመ ፡ አነ ፡ ውእቱ፡ትመውቱ፡በኃጢአትክሙ።
፳፭፤ ወይቤልዎ ፡ አንተ ፡ መኑ ፡ አንተ ፡ ወይቤሎሙ፡እግዚእ፡ኢየሱስ፡ቀዳሚኒ፡ነገርኩክሙ።
፳፮፤ ወብዙኀ ፡ ብየ ፡ ዘእብል ፡ በእንቲአክሙ ፡ ወእኴንን፡ቦቱ፡ወባሕቱ፡ዘፈነወኒ፡ጻድቅ፡ ውእቱ፡ወአንሰ፡ዘሰማዕኩ፡በኀቤሁ፡እነግር፡ ለዓለም።
፳፯፤ ወኢያእመሩ፡ከመ፡በእንተ፡አብ፡ይቤሎሙ።
፳፰፤ ወይቤሎሙ ፡ እግዚእ ፡ ኢየሱስ ፡ አመ ፡ ተለዓለ፡ወልደ፡ዕጓለ፡እመሕያው፡ይእተ፡ አሚረ፡ተአምሩ፡ከመ፡አነ፡ውእቱ፡ወአኮ፡ ዘእምኀቤየ፡ዘእነግር፡አላ፡በከመ፡መሀረኒ፡ አቡየ፡ከማሁ፡እነግር።
፳፱፤ ወዘፈነወኒ ፡ ሀሎ ፡ ምስሌየ ፡ ወኢየኀድገኒ ፡ አብ ፡ ባሕቲትየ ፡ እስመ ፡ አነ ፡ ሥምረቶ ፡ እገብር፡ዘልፈ።

## ማክሰኞ፡መዓልት፡በ፩፡ሰዓት/ነግህ።

፲፭፤ ባስይዛችሁ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ገንዘብ ፡ ትሰጡኛላችሁ ፤ አላቸው ። ከእርሱ ፡ ጋራም ፡ ተነጋግረው፡ሠላሳ፡ብር፡ሊሰጡት፡ተስማሙ።
፲፮፤ ከዚያችም ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ ለእነሱ ፡ አሳልፎ፡ ይሰጠው፡ዘንድ፡ምቹ፡ጊዜ፡ይሻ፡ጀመር።

### ዳግመኛ፡ከወንጌል፡በፊት።

መዝ፤፻፲፱፡፪።

አቤቱ ፡ ከአመፀኛ ፡ ከንፈር ፡ ሰውነቴን ፡ አድናት ። ከሸንጋይም ፡ አንደበት ፡ ሰውነቴ፡ ብዙ፡ታገሠች። ሰላምን፡ከሚጠሉ፡ጋር። እና፡ ሰላማዊ ፡ ስሆን ፡ በተናገርኋቸው ፡ በከንቱ፡ ይጠሉኛል።

### የዮሐንስ፡ወንጌል።

ምዕ፤፰፡፳፩–፳፱።

፳፩፤ ዳግመኛም፡ጌታ፡ኢየሱስ፡እኔ፡እሄዳለሁ፤ትሹኛላችሁ፡አታገኙኝም፤በኃጢአታችሁ፡ትሞታላችሁ ፤ እኔ ፡ ወደምሄድበትም ፡ እናንተ፡ መምጣት፡አይቻላችሁም፡አላቸው።
፳፪፤ አይሁድም ፡ እኔ ፡ ወደምሄድበት ፡ እናንተ፡ መምጣት፡አትችሉም፡የሚለን፡እርሱ፡ራሱ፡ ራሱን፡ይገድል፡ይሆን፡አሉ።
፳፫፤ እናንተስ ፡ ከምድራዊ ፡ ወገን ፡ ናችሁ ፤ እኔ፡ ግን ፡ ከላይ ፡ ነኝ ፤ እናንተ ፡ ከዚህ ፡ ዓለም፡ ናችሁ ፤ እኔ ፡ ግን ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ አይደለሁም።
፳፬፤ እነሆ፡በኃጢአታችሁ፡ትሞታላችሁ፡እንዳልኋችሁ፡እኔ፡እንደሆንኩ፡ካላመናችሁ፡በኃጢአታችሁ፡እንዳላችሁ፡ትሞታላችሁ።
፳፭፤ እነርሱም ፡ አንተ ፡ ማነህ ፡ አሉት ፤ ጌታ፡ ኢየሱስም ፡ አስቀድሜ ፡ ነግሬአችኋለሁ፡ አላቸው።
፳፮፤ ስለእናንተ ፡ የምለውና ፡ የምፈርደው ፡ ብዙ፡ አለኝ ፤ የላከኝም ፡ እውነተኛ ፡ ነው ። እኔም፡ በእርሱ ፡ ዘንድ ፡ የሰማሁትን ፡ ለዓለም ፡ እናገራለሁ።
፳፯፤ ስለ፡አብ፡እንደ፡ነገራቸው፡አላወቁም።
፳፰፤ ጌታ፡ኢየሱስም፡እንዲህ፡አላቸው፤የሰው፡ልጅ፡ከፍ፡ከፍ፡ባለ፡ጊዜ፡ያንጊዜ፡እኔ፡እንደ፡ሆንኩ፡ታውቃላችሁ፤የምናገረውም፡ከእኔ፡አይደለም። አባቴ፡እንደነገረኝ፡እንዲሁ፡እናገራለሁ፡እንጂ።
፳፱፤ የላከኝም፡ከእኔ፡ጋር፡አለ፤አብ፡ብቻየን፡አልተወኝም፤እኔ፡ዘወትር፡ፈቃዱን፡አደርጋለሁና።

## በ፩፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሠሉስ/ነግህ።

### ድኅረ፡ወንጌል።

**በዕለተ፡ሠሉስ፡ጊዜ፡ነግህ፡ዘይትነበብ**

**ዘየኀብር፡ምስለ፡ትንቢት።**

፩፤ ወመጽኡ፡እስራኤል፡ኀበ፡ደብረ፡ራፌድ፡
እምድኅረ፡ሠለስቱ፡አውራኅ፡ወኀደሩ፡
ውስተ፡ገዳም።
፪፤ ወመጽኡ፡ደቂቀ፡እስራኤል፡እምግብጽ፡
ኀበ፡ደብረ፡ሲና፡እስከ፡በጽሑ፡ኀበ፡ውእቱ፡
መካን።
፫፤ ወመጽአ፡ሙሴ፡ኀበ፡እግዚአብሔር፡
ወጸውዖ፡ወተናገረ፡ምስሌሁ፡ወይቤሎ፡
ንግሮሙ፡ለቤተ፡ያዕቆብ፡ዛተ፡ቃለ፡
ወዜንዎሙ፡ለደቂቀ፡እስራኤል።
፬፤ እስመ፡ናሁ፡ርኢክሙ፡አንትሙ፡ምግባርየ፡
ብዙኀተ፡እንተ፡ገበርክዋ፡በሰብአ፡ግብጽ።
፭፤ ወጾርኩክሙ፡አነ፡በኃይልየ፡ጽንዕት፡ከመ፡
ዘአንትሙ፡ላዕለ፡ክንፈ፡አንስርት።
፮፤ ወዐቀቡ፡ሕግየ፡ወትእዛዝየ፡ወስምዑ፡
ቃልየ፡ ወግበሩ፡ፈቃድየ፡እስመ፡ኀረይ
ኩክሙ፡እምኵሉ፡አሕዛብ፡እስመ፡ዚአየ፡
ምድር፡በምልዓ።
፯፤ ወባሕቱ፡ኀቡረ፡ትከውኑ፡ሊተ፡መንግሥተ፡
ወሕዝበ፡ኅሩየ፡ወንጹሐ።
፰፤ ወመጽአ፡ሙሴ፡ወነገሮሙ፡ለሕዝብ፡ዘንተ፡
ቃለ፡ዘይቤሎ፡እግዚአብሔር።
፱፤ ወጸርሑ፡ሕዝብ፡በአሐዱ፡ቃል፡ወይቤልዎ፡
እስመ፡ለዘሠርዖሙ፡እግዚአብሔር፡
ነዐቅቦሙ።
፲፤ ወተንሥአ፡ሙሴ፡ወዜነዎ፡ለሊቅ፡
እስመ፡ሰምዐ፡ሕዝብ፡ትእዛ
ዛቲሁ።
፲፩፤ ወገብአ፡እስራኤል፡ወያዕቆብ፡ኀደረ፡
ወደቂቅ፡ተግሕሡ፤እስመ፡ኮና፡ትእዛዛቲሁ፡
ከመ፡ወኢምንት፡ ወሕገጋቲሁ፡ኮና፡ጽሩ
ዐተ፡ ወበእንተዝ፡ረሰዮሙ፡ጽሩራነ፡
ወጽሉዓነ፡ወተቀንዩ፡ለአዝማድ፡
ነኪር።

## ማክሰኞ፡መዓልት፡በ፩ሰዓት/ነግህ።

**ማክሰኞ፡በነግህ፡ከወንጌል፡በኋላ፡የሚነበብ፡**

**ከትንቢቱ፡ቃል፡ጋራ**

**የሚስማማ፡ይህ፡ነው።**

፩፤ እስራኤል፡ከግብጽ፡በወጡ፡በሦስተኛው፡
ወር፡ከራፌድ፡አልፈው፡በበረኃ፡ውስጥ፡
አደሩ።
፪፤ ከዚያ፡ቦታ፡እስከ፡ደረሱ፡ድረስ፡እስራኤል፡
ከግብጽ፡መጥተው፡በደብረ፡ሲና፡በኩል፡
ይጓዙ፡ነበር።
፫፤ ሙሴም፡ወደ፡እግዚአብሔር፡መጣ፤እግዚአብ
ሔርም፡ጠርቶት፡ከእርሱ፡ጋራ፡እንዲህ፡ብሎ፡
ተነጋገረ፤ይችን፡ቃል፡ለያዕቆብ፡ወገን፡
ንገራቸው፤ለእስራኤል፡ልጆችም፡አስረዳቸው።
፬፤ እነሆ፡ብዙ፡የሆነውን፡በግብጻውያን፡ላይ፡ያደ
ረግሁትን፡ሥራዬን፡እናንተ፡አይታችኋልና።
፭፤ እናንተ፡በንስር፡ክንፍ፡ላይ፡እንደሆናችሁ፡
አድርጌ፡በጸናችው፡ሥልጣኔ፡ተሸከምኋችሁ።
፮፤ ሕጌን፡ትእዛዜን፡ጠብቁ፤ቃሌንም፡
ሰምታችሁ፡ፈቃዴን፡ፈጽሙ፤ከአሕዛብ፡
ሁሉ፡መርጬአችኋለሁና፡መላዋ፡ምድር፡
ፈጽማ፡የእኔ፡ናትና።
፯፤ እናንተም፡ለመንግሥት፡የተመረጠ፡ንጹሕ፡
ወገን፡ትሆኑኛላችሁ፡ብለህ፡ንገራቸው፡አለው።
፰፤ ሙሴም፡መጥቶ፡እግዚአብሔር፡ያለውን፡
ይህን፡ለሕዝቡ፡ነገራቸው።
፱፤ ሕዝቡም፡በአንድ፡ቃል፡እግዚአብሔር፡የሠ
ራቸውን፡ሥርዓቶች፡እንጠብቃቸዋለን፡
ብለው፡አሰምተው፡ተናገሩ።
፲፤ ሕዝቡም፡ትእዛዙን፡ሰምቷልና፡ሙሴም፡
ለፈጣሪው፡ለእግዚአብሔር፡ተመልሶ፡
መልሱን፡ነገረው።
፲፩፤ የያዕቆብ፡ወገን፡እስራኤልም፡ወደቦታው፡
ተመልሶ፡አደረ፤የእስራኤል፡ልጆችም፡
ከሕጉ፡ከሥርዐቱ፡ፈቀቅ፡አሉ፤ትእዛዞቹንም፡
እንደ፡ኢምንት፡አደረጉ፤ሕጎችንም፡መጠበ
ቃቸው፡ቀረ፤ስለዚህም፡የተጠሉ፡ጠላቶች፡
ሆኑ፤በባዕድ፡እጅም፡የሚገዙ፡ሆኑ።

## በ፩፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሠሉስ/ነግህ።

፲፱፤ አጽንኑ ፡ አርእስቲሆሙ ፡ ቅድመ ፡ አሕዛብ ፡
ወኮኑ፡ውስተ፡ኀፍረት፡ወኍፋሬ፡ለዓለም ።
ክርስቶስ፡መድኃኒነ፡መጽአ፡ወሐመ፡ወበሕ
ማማቲሁ፡አድኃነነ።

ዓዲ፡በሠሉስ፡ነግህ፡ዘይትነበብ።

፩፤ ነዋ ፡ ሰማዕነ ፡ ይእዜ ፡ እግዚእነ ፡ ዘሎቱ ፡
ስብሐት፡ዘከረ፡ለደቂቀ፡እስራኤል፡ዘገብረ፡
በግብጻውያን ፡ ኪያሆሙ ፡ በእንቲአሆሙ ፡
ወዘከመ፡ከሠተ፡ተአምራተ፡በቅድሜሆሙ፡
ለአድኅኖቶሙ።

፪፤ ወይቤ፡እምድኅረ፡ዝንቱ፡አንትሙ፡ለእመ፡
ሰማዕክሙ፡ቃልየ፡ወኪያክሙ፡አፍቀርኩ፡
እምኵሎሙ ፡ ሕዝብ ፡ ወአሕዛብ ፡ ከመ ፡
ትኩኑኒ ፡ ሊተ ፡ ለመንግሥት ፡ ንጹሕ ፡
ወሕዝበ፡ቅዱሰ።

፫፤ ወሶበ ፡ ኢተመጠዉ ፡ ዘንተ ፡ ግብረ ፡
በእከዮሙ፡ወዐጸዉ፡እምሰሚዕ፡እዘኒሆሙ፡
ወተእኅዙ ፡ በአሕባለ ፡ ፍትወተ ፡ ዓለም ፡
ወተከልኡ፡እምነ፡ለብዎ፡ነገራተ፡ጽድቅ፡
ወሥርዓት፡ወወድቁ፡ውስተ፡ባሕረ፡እከይ።

፬፤ ወውእቱ፡ዘተሠገወ፡ለመድኃኒቶሙ፡ወጾረ፡
ሕማማተ ፡ በሥጋሁ ፡ ከመ ፡ ይፈውሶሙ ፡
ወመሀሮሙ፡በነገር፡ጥዑም፡ወበምግባራት፡
ትሩፋት፡ወበክብር፡ወበሞገስ፡ፍጹም።

፭፤ ወአርኀወ ፡ ሎሙ ፡ አናቅጸ ፡ መንግሥት ፡
ወመዐዶሙ፡በንብረት፡ውስተ፡ገዳም፡ለእለ፡
ኢሰምዑ፡ትእዛዞ፡በከመ፡ይደሉ፡ወኢገብሩ፡
ባቲ፡በከመ፡ይረትዕ።

፮፤ በአይ፡ልሳን፡ይትረገሙ፡ወአይ፡ኵነኔ፡ዘይደ
ልዎሙ፡ይረክቦሙ።

፯፤ ወሰማዕክሙ ፡ ለአይሁድ ፡ ዘይቤ ፡ ወተሣ
ሀሎቶ ፡ ላዕሌሆሙ ፡ ለእመ ፡ ይመይጠሙ ፡
ሎሙ፡ጊዜ፡በምዒድ፡ወጊዜ፡በተግሣጽ።

## ማክሰኞ፡መዓልት፡በ፩፡ሰዓት/ነግህ።

፲፱፤ በአሕዛብ፡ፊትም፡ራሳቸውን፡አዋረዱ፤ለዘላ
ለሙም፡በኀፍረትና፡በጕስቁልና፡ውስጥ፡ኖሩ።
መድኃኒታችን፡ክርስቶስ፡ሰው፡ሁኖ፡መጥቶ፡
መከራ፡ተቀበለ፤በመከራውም፡አዳነን።

ማክሰኞ፡በጧት፡የሚነበብ።

፩፤ እነሆ ፡ የክብር ፡ ባለቤት ፡ ጌታችን ፡ የእስ
ራኤል፡ ልጆች ፡ እነርሱን ፡ ለማዳን ፡ ስለ፡
እነርሱ ፡ በግብጻውያን ፡ ላይ ፡ ያደረገውን፡
በፊታቸው ፡ ተአምራቱን ፡ እንደ ፡ ገለጸ፡ማስ
ታወሱን፡ሰማን።

፪፤ ከዚህ፡በኋላ፡እንዲህ፡አለ ። እናንተ፡ቃሌን፡
ብትሰሙ ፡ የተለየ ፡ ወገን ፡ ትሆኑኝ፡ዘንድ፡
ከሕዝብና፡ከአሕዛብ፡ሁሉ፡ለይቼ፡እናንተን፡
ወደድሁ ፤ ንጹሕ ፡ መንግሥትና ፡ የተለየ፡
ወገንን፡ትሆኑኝ፡ዘንድ።

፫፤ ከክፋታቸውም፡የተነሣ፡ይህን፡ሥራ፡ባልተ
ቀበሉ፡ጊዜ፡ጆሮአቸውን፡ከመስማት፡ደፈኑ፤
በዓለማዊ ፡ ፍትወት ፡ ገመድም ፡ ተያዙ፤
እውነትና፡የሥርዓት፡ነገርን፡ከማስተዋል፡
ተከልክለው፡በክፋት፡ባሕር፡ወደቁ።

፬፤ እርሱም፡ጌታ፡ሊአድናቸው፡ሰው፡የሆነ፡ደዌ
ሳቸው ፡ ዘንድ ፡ በሥጋው ፡ መከራን ፡ ተቀበለ፤
ጣዕም፡ባለው፡አነጋገር፡ትሩፋትን፡በመሥራት፡
ፍጹም፡በሆነ፡ግርማና፡ክብር፡አስተማራቸው።

፭፤ የመንግሥትንም ፡ በር ፡ ከፈተላቸው ፡
በበረኻም፡ በመቀመጥ ፡ እንደሚገባ ፡
ትእዛዙን ፡ ላልሰሙት ፡ ለእነርሱ ፡
መከራቸው፡እንደሚገባም፡አልሠሩም።

፮፤ በምን ፡ አንደበት ፡ ይረገሙ ፡ ይሆን ፡ የሚአገ
ኛቸው፡የሚገባቸው፡ምን፡ፍርድ፡ይሆን?

፯፤ ከልቡናቸው ፡ ድንዳኔ ፡ ይመለሱ ፡ ዘንድ ፡
አንድ ፡ ጊዜ ፡ በምክር ፡ አንድ ፡ ጊዜም ፡
በመገሠጽ ፡ አንድ ፡ ጊዜም ፡ ተአምራት ፡

Scanned by CamScanner

| በ፩፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሠሉስ/ነግህ። | ማክሰኞ፡መዓልት፡በ፩፡ሰዓት/ነግህ። |
|---|---|
| ወጊዜ፡በአርእዮ፡ተአምራት፡ወጊዜ፡በምግባራተ፡ፍርሀት፡ከመ፡ይትመየጡ፡እምግዘፈተ፡ክሣዶሙ። | በማድረግ፡አንድ፡ጊዜም፡አስፈሪ፡የሆነ፡ግርማን፡በማሳየት፡ምን፡አልባት፡ቢመለሱ፡ለአይሁድ፡የተናገረውንና፡በእነርሱ፡ላይ፡ያደረገውን፡ርኅራኄውን፡ሰምታችኋል። |
| ፰፤ ወይግብኡ፡ኀቤሁ፡ከመ፡ያሡኒ፡ሎሙ። ወበዝየ፡ይቤ፡ምዕዳነ፡ሎሙ፡ወተግሣጸ፡ለሐኬቶሙ። | ፰፤ በጎ፡ያደርግላቸው፡ዘንድ፡ወደ፡እርሱ፡እንዲመለሱ። በተንኰላቸው፡እነሱን፡በመምከርና፡በመገሠጽ፡በዚህ፡እንዲህ፡አለ። |
| ፱፤ እስመ፡አነ፡ሶበ፡ሖርኩ፡እምኔክሙ፡ወኢአመንክሙ፡ትመውቱ፡በኃጢአትክሙ። | ፱፤ እኔ፡ከእናንተ፡ተለይቼ፡በሄድኩ፡ጊዜ፡አላመናችሁብኝምና፡በኃጢአታችሁ፡እንዳላችሁ፡ትሞታላችሁ። |
| ፲፤ ወሶበ፡ተለዓለ፡ወልደ፡ዕጓለ፡እመሕያው፡ተአምሩ፡ከመ፡አነ፡ውእቱ። | ፲፤ የሰው፡ልጅም፡ከፍ፡ከፍ፡ባለ፡ጊዜ፡እኔ፡እንደሆንኩ፡ያን፡ጊዜ፡ታውቃላችሁ። |
| ፲፩፤ ወሶበ፡አበዩ፡እሉ፡ጽልሕዋን፡ተመይጦ፡እምእከዮሙ፡ወተኈለቁ፡ምስለ፡ጊጉያን፡ወህጉላን። | ፲፩፤ ሽንገላን፡የተመሉ፡እነርሱ፡ከክፋታቸው፡መመለስን፡እምቢ፡ባሉ፡ጊዜ፡ከጥፋተኞችና፡ከበደለኞች፡ጋራ፡ተቈጠሩ። |
| ፲፪፤ እፎኬ፡ኢንነቅሕ፡ንህነ፡እምንዋምነ፡ወንለቡ፡ነገራተ፡**እግዚእ**፡ወንትጋደል፡ለዐቂበ፡ትምህርት፡ዘይትነበብ፡ላዕሌነ፡ወንፍረይ፡ፍሬ፡ክቡረ፡ዘይደሉ፡ለትክለትነ፡ወንትመሰል፡በምግባራተ፡ጻድቃን፡እለ፡ተባልሑ። | ፲፪፤ እንግዲህ፡እኛ፡ከእንቅልፋችን፡የማንነቃ፡እንዴት፡ነው? **የጌታችንንም**፡ነገር፡ልብ፡እናድርግ፤በእኛ፡ላይ፡የሚነበበውን፡ትምህርቱን፡ለመጠበቅ፡እንጋደል፤፡ለመተከላችንም፡የሚገባውን፡የከበረ፡የሠመረ፡ፍሬ፡እናፍራ፤ከኃጢአት፡በዳኑ፡በጻድቃን፡ሥራዎች፡እርሳቸውን፡መስለን፡እንጽና። |
| ፲፫፤ አ፡መንክር፡ለሐዊር፡እለ፡ይፈቅዱ፡ኀበ፡ኵብኲብ፡ዘዝ፡ዓለም፡ኀላፊ። | ፲፫፤ በዚህ፡በኀላፊው፡ዓለም፡ወደሚደረገው፡ሠርግ፡መሄድን፡ለሚፈልጉ፡ምን፡ይደንቅ? |
| ፲፬፤ ትሬእይዎሙ፡በአስተንትኖ፡በአንጽሖ፡ሥጋሆሙ፡ወያጸርዩ፡ወይትቀብዑ፡ዕፍረተ፡ወይሠረገዉ፡በአልባስ፡ወያሤንዩ፡በአስተሣንዮ፡ሎሙ፡በአባሎሙ፡ወያጸምዑ፡ቃለ፡እለ፡ይነቡ፡በማሕሌት። | ፲፬፤ አካላቸውን፡በማንጻትና፡በማጥራት፡ሽቱ፡በመቀባት፡በልብሶች፡በመሸለም፡በማጌጥ፡ሁለንተናቸውን፡በማሳመር፡ሁነው፡ሲዘጋጁ፡ታዩአቸዋላችሁ፤እንዲህም፡ሁነው፡የዘፈኑን፡ዜማ፡ያዳምጣሉ። |
| ፲፭፤ ወእለ፡ይትናገሩ፡በተውኔት፡ወይትመየጡ፡ለነጽሮ፡ተውኔት፡ወይሁቡ፡ንዋዮሙ፡በተጠናቅቆ፡ወይትኤመሩ፡ለዐቂበ፡መሐድምቶሙ፡ወይትጋደሉ፡ለአፍልሶ፡ንባቦሙ፡ወይገብሩ፡ለፈጽሞ፡ሥምረተ፡አስተናጽሖቶሙ፡በከመ፡ይደሉ። | ፲፭፤ በዘፈን፡ጊዜ፡የሚጨዋወቱትን፡ዘፈን፡ወደማየት፡ይመለሳሉ፤ገንዘባቸውንም፡ለዘፋኞች፡በመስጠት፡ይመለከታሉ፤በእንቆቅልሽና፡በተረት፡ለማሸነፍ፡ይታገላሉ፤ፍላጎታቸውንም፡ጠብቆ፡ለመፈጸምና፡ለማጣራት፡ሲሉ፡እንደሚገባ፡አድርገው፡ይታገላሉ። |
| ፲፮፤ ወኢይገብሩ፡ከመዝ፡ለሐዊር፡ኀበ፡ቤተ፡ክርስቲያን፡ለሰሚዐ፡**ቃለ፡እግዚአብሔር**፡ከመዝ፡ዳእሙ፡ንሬእዮሙ፡ይሰረገዉ፤በአልባስ፡በኑኃሠ፡ስባሔ፡ከንቱ። | ፲፮፤ **የእግዚአብሔርን፡ቃል**፡ለመስማት፡ወደ፡ቤተ፡ክርስቲያን፡ለመሄድ፡እንዲህ፡አላደረጉም፤ነገር፡ግን፡ውዳሴ፡ከንቱ፡በመሻት፡ተሸልመው፡ሲሄዱ፡እንደዚህ፡እናያቸዋለን፡እንጂ። |
| ፲፯፤ ወለእመኒ፡አእመሩ፡ኢይገብሩ፡ወሶበ፡ | ፲፯፤ ምንም፡ቢያውቁ፡አያደርጉትም፤መለኮት፡ |

## በ፮፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሠሉስ/ነግህ።

ይትነበቡ ፡ ነገራተ ፡ መለኮት ፡ ላዕ ሌሆሙ ፡ ይትሂየዩ ፡ ለሰሚያቶሙ ፡ ወይት ሀከዩ።

፲፰፤ ወበእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ይወድቁ ፡ ውስተ ፡ መርበብተ፡ጸላኢ፡ወየሐውሩ፡ውስተ፡አብያ ቲሆሙ፡ዘሙስና።

፲፱፤ ወለእመኒ ፡ ኮነ ፡ እግዚእነ ፡ ሎቱ ፡ ስብሐት ፡ ገሠጸ ፡ ለሐዊር ፡ ውስተ ፡ ብርሃን፡ወለተዐቅቦ፡እምተራክቦ፡ጽልመት፡ ግብተ፡ እፎኬ ፡ ዘኢነሐውር ፡ በፍኖተ ፡ ሕይወትነ።

፳፤ ወናብርህ፡ማኅቶተ፡ሥርዓትነ፡እምቅድመ፡ ይዕፅዉ፡ብነ፡አንቀጸ፡ርሒበ፡ወይሰፍሑ፡ ብነ፡መንገሌነ፡እእዳወ፡ውሉጣተ፡ወኢይት ዐቀፍ፡ውስተ፡ጽልመት፡ሕይወትነ፡ከመ፡ ኢንተክዝ፡ላዕለ፡ዘኀለፈ፡ምግባሪነ፡አመ፡ ንቀውም ፡ ቅድመ ፡ እግዚእነ ፡ ጽምሑያነ ፡ በብካይ ፡ ውብሩሀነ ፡ ወጽኑሐነ ፡ ለጐንድዮ ፡ ውስተ፡ገሀነም፡ልህዋነ፡በአስሕቶ፡መዋዕለ፡ ሕይወትነ ፡ በተደልዎ ፡ መብልዕ ፡ ኀላፊ ፡ ወፍትወት ፡ እኩይ ፡ ወኵሉ ፡ ዘኢይደሉ ፡ ለኄራን።

፳፩፤ ይደልወነኬ ፡ ከመ ፡ ንዕቀብ ፡ ትእዛዞ ፡ ወንንቃህ፡እምንዋምነ፡ወንትገሠጽ፡እምጽ ርዓትነ ፡ ወንጐድጕድ ፡ አንቀጸ ፡ ምሕረቱ ፡ ለአምላክነ፡ዘሎቱ፡ስብሐት፡እስከ፡ለዓለመ፡ ዓለም፡አሜን።

በእንተ፡ጽንዐ፡ዛቲ፡በል ። ወፈጽም፡ኵሎ፡ በከመ፡ሥርዓቱ፡በከመ፡ተጽሕፈ፡በዕለተ፡ ሰኑይ፡በነግህ።

### ምዕራፍ፡፳፩።

ትእዛዝ ፡ ወእምዝ ፡ ይትጋብኡ ፡ ካህናት ፡ ውስተ፡ቤተ፡ክርስቲያን፡ቅድስት፡በጊዜ፡ ሠለስቱ፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘዕለተ፡ሠሉስ።

ወይጸልዩ፡ጸሎተ፡በከመ፡ተጽሕፈ፡በዕለተ፡ ሰኑይ ፡ ጊዜ ፡ ሠለስቱ ፡ ሰዓት ፡ ወኵሎ ፡ ሥርዓቱ፡ከማሁ።

## ማክሰኞ፡መዓልት፡በ፮፡ሰዓት/ነግህ።

የተናገራቸውም ፡ ቃሎች ፡ በላያቸው ፡ በተነበቡ፡ጊዜ፡መስማትን፡ቸል፡በማለት፡ ይሰንፋሉ።

፲፰፤ ስለዚህ ፡ በጠላት ፡ ዲያብሎስ ፡ አሽክላ ፡ ተይዘው ፡ ይወድቃሉ ፤ ወደሚጠፉበት ፡ ቤታቸው፡ወደ፡ገሀነም፡ይሄዳሉ።

፲፱፤ የክብር ፡ ባለቤት ፡ ጌታችን ፡ ወደ ፡ ብርሃን፡ መሄድን ፡ በድንገት ፡ ከጨለማ ፡ ከመግባት፡ መጠበቅን፡የመከረና፡ያስተማረ፡ከሆነ፡ሕይ ወትነት ፡ ባለው ፡ መንገድ ፡ የማንሄድ ፡ እንዴት፡ነው?

፳፤ ሰፊውንም ፡ በር ፡ ሳይዘጉብን ፡ ወደ ፡ እኛም፡የተለዩ፡እጆችን፡ሳይዘረጉብን፡ሕይ ወታችንም ፡ በጨለማ ፡ ሳይሰናከል ፡ በገሀነም ፡ ለመቆየት ፡ የተጠበቅን ፡ ሁነን፡ በመፍራትና ፡ በማልቀስ ፡ ጠውልገን ፡ በጌታችን፡ፊት፡በምንቆም፡ጊዜ፡በአለፈው፡ ሥራችን፡እንዳናዝን፡እንዳንጸጸት፡ለደጋጎች፡ በማይገባ ፡ ለኀላፊው ፡ መብልና ፡ ለክፉ፡ ሥራ ፡ አሳብ ፡ ሁሉ ፡ በመሳሳት ፡ በመዘ ጋጀት ፡ ርቀን ፡ የሥርዐታችንን ፡ መብራት፡ እናብራ።

፳፩፤ ትእዛዙን፡እንጠብቅ፡ዘንድ፡ይገባናል፤ከእን ቅልፋችንም፡ነቅተን፡ከሥራ፡ፈትነታችን፡ እንገሠጽ፤እንመክር፤የፈጣሪያችንም፡የምሕ ረቱን፡በር፡እናንኳኳ፤እስከ፡ዘላለሙ፡ድረስ፡ ለእርሱ፡ክብር፡ምስጋና፡ይሁን፤አሜን።

በእንተ፡ጽንዐ፡ዛቲ፡ብለህ፡እንደ፡ሥርዓቱ፡ ፈጽም ፤ ሰኞ ፡ በጧት ፡ ተጽፎ ፡ እንዳለ ፡ ተመልከት።

### ምዕራፍ፡፳፩።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ካህናቱ ፡ በከበረች ፡ ቅድስት ፡ ቤተ፡ክርስቲያን፡ማክሰኞ፡ከቀኑ፡በ፫፡ሰዓት ፡ይሰብሰቡ።

ሰኞ ፡ በሦስት ፡ ሰዓት ፡ እንደተጻፈውም ፡ ሥርዓቱ ፡ ሁሉ ፡ እንዲሁ ፡ ነውና ፡ ከዚያ ፡ በተጻፈው፡አይነት፡ይጸልዩ።

Scanned by CamScanner

## በ፫፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሠሉስ።

### ክፍል፡፩።
### ምንባብ።
### ኦሪት፡ዘዳግም።
### ምዕ፡፰፡፲–፲፰።

፲፡ ዑቅ ፡ ርእሰከ ፡ ወኢትርሥዖ ፡ ለእግዚአብሔር ፡
አምላክከ ፡ ከመ ፡ ትዕቀብ ፡ ትእዛዞ ፡ ወኵነኔሁ ፡
ወፍትሖ፡ወኵሎ፡ዘእኤዝዘከ፡አነ፡ዮም።
፲፩፡ ዮጊ ፡ ሶበ ፡ በላዕከ ፡ ወፀገብከ ፡ ወነደቀ ፡ አብያተ፡
ሠናያነ፡ወነበርከ፡ውስቴቶሙ።
፲፪፡ ወበዝኃ፡ለከ፡አባግዒከ፡ወአልሕምቲከ፡ወሶበ፡በዝኀ፡
ለከ፡ወርቅ፡ውብሩር፡ወበዝኀ፡ለከ፡ኵሉ፡ንዋይከ።
፲፫፡ ዮጊ፡ታዓቢ፡ልበከ፡ወትረሥዖ፡ለእግዚአብሔር፡
አምላክከ ፡ ዘአውጽአከ ፡ እምድረ ፡ ግብጽ ፡
እምቤተ፡ቅንየት።
፲፬፡ ወወሰደከ ፡ ውስተ ፡ ገዳም ፡ ዐቢይ ፡ ወግሩም ፡
ዘውስቴቱ ፡ አራዊተ ፡ ምድር ፡ ዘይነስኩ ፡ ወአቃ
ርብት ፡ ወጽምዕ ፡ ዘአልቦ ፡ ማይ ፡ ለሰትይ ፡
ዘአውጽአ ፡ ለከ ፡ እምውስተ ፡ እብነ ፡ ኰኵሕ ፡
ነቅዓ፡ማይ፡ጥዑም።
፲፭፡ ወሴሰየከ ፡ መና ፡ በገዳም ፡ ዘኢየአምሩ ፡ አበዊከ፡
ከመ፡ያሕምምከ፡ወያመክርከ፡ወያሠኒ፡ላዕሌከ፡
በደኃሪት፡መዋዕሊከ።
፲፮፡ ወኢትበል፡በልብከ፡በኃይልየ፡ወበጽንዐ፡እዴየ፡
ገበርኩ፡ሊተ፡ዘንተ፡ኵሎ፡ኃይለ፡ዐቢየ።
፲፯፡ ወተዘከሮ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አምላክከ ፡ እስመ፡
ውእቱ ፡ ይሁበከ ፡ ኃይለ ፡ ከመ ፡ ያቅም ፡ ኪዳኖ ፡
ዘመሐለ፡ለአበዊከ፡በከመ፡ዮም።
፲፰፡ ወለእመ ፡ ረሢዐ ፡ ረሣዕካሁ ፡ ለእግዚአብሔር ፡
አምላክከ ፡ ወሖርከ ፡ ድኅረ ፡ ባዕዳን ፡ አማልክት ፡
ወአምለካሆሙ ፡ ወሰገድከ ፡ ሎሙ፡ አሰምዕ ፡
ላዕሌከ፡ ዮም ፡ ሰማየ ፡ ወምድረ ፡ ከመ ፡ ጠፊዐ ፡
ትጠፍዕ ። ወበከመ ፡ አሕዛብ ፡ ኵሎሙ ፡ እለ ፡
ደምሰሶሙ ፡ እግዚአብሔር ፡ እምቅድመ ፡ ገጽከ ፡
ለእመ፡ኢሰማዕከ፡ቃለ፡እግዘአብሔር፡አምላክከ።

## ማክሰኞ፡መዓልት፡በ፫፡ሰዓት።

### ክፍል፡፩።
### ምንባብ።
### ኦሪት፡ዘዳግም።
### ምዕ፡፰፡፲–፲፰።

፲፡ ለራስህ ፡ ዕወቅ ፤ ትእዛዙን ፡ ፍርድ ፡ ፍርዱን ፡
ቅጣቱን፡እኔ፡ዛሬ፡የማዝዝህን፡ሁሉ፡ትጠብቅ፡
ዘንድ፡ፈጣሪህ፡እግዚአብሔርን፡አትዘንጋው።
፲፩፡ ወይም ፡ እኮ ፡ በልተህ ፡ በጠገብክ ፡ ጊዜ ፡ ያማሩ ፡
ቤቶችንም፡ሠርተህ፡በውስጣቸው፡በተቀመጥክ፡ጊዜ።
፲፪፡ ላሞችህ፡በጎችህ፡በበዙልህ፡ጊዜ፡ወርቁም፡ብሩም፡
በበዛልህ፡ጊዜ፡ገንዘብህ፡ሁሉ፡በበዛልህ፡ጊዜ።
፲፫፡ ወይም፡እኮ፡ልብህን፡ታኮራው፡ይሆናል፡አገዛዝ፡
ካለበት፡ቤት፡ከምድረ፡ግብጽ፡ያወጣህ፡ፈጣሪ፡እግ
ዚአብሔርን፡ትረሳው፡ይሆናል።
፲፬፡ ጽኑ ፡ የሚአስፈራ ፡ በረሃ ፡ በውስጡ ፡ የሚናከሱ ፡
አውሬዎች ፡ ጊንጦችም ፡ ወዳሉበት ፡ ለመጠጣት ፡
ውኃ፡ወደሌለበት፡ውኃ፡ጥም፡ወደጸናበት፡ምድረ፡
በዳ፡የወሰደህ፡የጠራ፡የውኃ፡ምንጭ፡ከድንጋያው፡
ላንተ፡ያወጣልህ።
፲፭፡ ያሳዝንህ ፡ ይፈትንህ ፡ በፍጻሜ ፡ ዘመንህ ፡ በጎ ፡ ያደር
ግልህ፡ዘንድ፡በምድረ፡በዳ፡አባቶችህ፡ያላወቁትን፡
መና፡የመገበህ፡ፈጣሪህ እግዚአብሔርን፡ትረሣው፡
ይሆናል።
፲፮፡ በልቡናህም፡በኃይሌ፡በሥልጣኔ፡ጽናት፡ይህን፡
ሁሉ፡ደገኛ፡ኃይልን፡አደረግኹ፡አትበል።
፲፯፡ እንደዛሬ ፡ ላባቶችህ ፡ የማለውን ፡ መሐላውን ፡
ያጸናልህ፡ ዘንድ ፡ እርሱ ፡ ኃይልን ፡ ይሰጥሃልና ፡
ፈጣሪህ፡እግዚአብሔርን፡አስበው።
፲፰፡ ፈጣሪህ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ፈጽመህ ፡ ብትዘ
ነጋው፡ ልዩ ፡ የሆኑ ፡ ጣዖታትን ፡ ተከትለህ ፡ ብት
ሄድ ፡ ብታመልካቸው ፡ ብትሰግድላቸውም ፡
ፈጽመህ፡ እንዳትጠፋ፡ ሰማይና ፡ ምድርን ፡ አዳኝ
ብሃለሁ ፤ የፈጣሪህ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡
ካልሰማህ ፡ ከፊትህ ፡ እንዳጠፋቸው ፡ አሕዛብ ፡
ሁሉ፡እንደዚሁ፡ትጠፋለህ።

ወእምከመ ነሰከ አርዌ ምድር
ለሰብእ ኵሉ ዘተነሰከ ለይርአዮ
ወይሕየው ።



የምድር እባብ ሰውን በነደፈው ጊዜ
የተነደፈው ሰው ሁሉ አይቶት ይዳን
አለው ።

ዘኍ፡፳፩፡፱።

በ፫፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሠሉስ።

ጥበበ ፡ ሲራክ ፡ በረከቱ ፡ ትኩን ፡ ምስሌነ ፡ ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

ምዕ፤፪፤፩-፲።

፩፤ ወልድየ ለእመ፡ሖርከ፡ትትቀነይ፡ለእግዚአብሔር፡አስተዳሉ፡ነፍስከ፡ለሕማም።

፪፤ ወአርትዕ ፡ ልበከ ፡ ወተዓገሥ ፡ ወኢትትወላወል፡ወለእመ፡ተመንደብከ፡ወኢትናፍቅ።

፫፤ ዳእሙ ፡ ትልዎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ወኢትኅድጎ ፡ ከመ ፡ ትብዛኅ ፡ ሕይወትከ ፡ በደኀሪትከ።

፬፤ ወተወከፍ ፡ ኵሎ ፡ እንተ ፡ በጽሐተከ ፡ ወተዓገሥ፡በመዋዕለ፡ተጽናስከ።

፭፤ እስመ፡በእሳት፡ያሜክርዎ፡ለወርቅ፡ወለብእሲኒ፡ጻድቅ፡በሕማመ፡ተፅናስ፡ያሜክርዎ።

፮፤ ተአመኖ ፡ ዳእሙ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ወይረድእከ፡ወአርትዕ፡ፍናዊከ፡ወተወከል፡ቦቱ።

፯፤ እለ፡ትፈርህዎ፡ለእግዚአብሔር፡ጽንሕዎ፡ለምሕረቱ፡ወኢትትገኀሡ፡እምኔሁ፡ከመ፡ኢትደቁ።

፰፤ እለ፡ትፈርህዎ፡ለእግዚአብሔር፡ተአመንዎ፡ወኢትህጐሉ፡ዕሤተክሙ።

፱፤ እለ፡ትፈርህዎ፡ለእግዚአብሔር፡ተሰፈውዋ፡ለሠናይቱ ፡ ወትፍሥሕተ ፡ ምሕረቱ ፡ ዘለዓለም።

ክፍል፡፪።
አንቀጽ፡ዕሥራ፡ወተሥዓቱ።

እመጽሐፈ፡ዲድስቅልያ፡ዘአበዊነ፡ቅዱሳን፡ሐዋርያት።
በረከቶሙ፡የሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

፩፤ ወበሠሉስ ፡ ዕለት ፡ ወሰኩ ፡ ወአፈድፈዱ ፡ ምክረ፡በእኩይ፡ምግባሮሙ፡እንተ፡አልባቲ፡ተፍጻሜት።

፪፤ ወበእንተዝ፡ይቤ፡እግዚአ፡መኑ፡የአምነነ፡ስምዐነ፡ወቃለነ፡ወለመኑ፡ተከሥተ፡መዝራዕትከ።

ማክሰኞ፡መዓልት፡በ፫፡ሰዓት።

የሲራክ፡የጥበብ፡ነገር፡ይህ፡ነው። በረከቱ፡ከእኛ፡ጋራ፡ለዘላለሙ፡ትኑር፡አሜን።

ምዕ፤፪፤፩-፲።

፩፤ ልጄ፡ለእግዚአብሔር፡ትገዛ፡ዘንድ፡ከሰው፡ተለይተህ፡ብትሄድ፡ሰውነትህን፡ለመከራ፡አዘጋጅ።

፪፤ ልብህንም ፡ አቅንተህ ፡ ሳትወላውል ፡ መከራውን፡ታገሥ፤ምንም፡ብትቸገር፡አትጠራጠር።

፫፤ እግዚአብሔርን ፡ ተከተለው ፡ እንጂ ፡ ክብርህም ፡ በመጨረሻ ፡ ትበዛልህ ፡ ዘንድ ፡ አትተወው።

፬፤ የመጣብህንም፡መከራ፡በምስጋና፡ተቀበል፤ ከክብርም፡በተቸገርክበት፡ወራት፡ታገሥ።

፭፤ ወርቁን፡በእሳት፡እንዲፈትኑት፡ጻድቁንም፡ሰው፡ሥላሴ፡በመከራ፡ይፈትኑታልና።

፮፤ እግዚአብሔርን፡ብቻ፡እንዲረዳህ፡እመነው፤ በሱም፡እምነህ፡ሥራህን፡አቅና።

፯፤ እግዚአብሔርን ፡ የምትፈሩት ፡ ሰዎች ፡ ቸርነቱን ፡ ጠብቋት ፤ በመከራም ፡ እንዳትወድቁ፡እሱን፡ደጅ፡ከመጥናት፡አትራቁ።

፰፤ እግዚአብሔርን ፡ የምትፈሩት ፡ ሰዎች ፡ ዋጋችሁን፡እንዳታጡ፡እመኑት።

፱፤ እግዚአብሔርን ፡ የምትፈሩት ፡ ሰዎች ፡ ቸርነቱን ፡ ተስፋ ፡ አድርጓት ፤ ለዘላለም ፡ በሚሆን ፡ ቸርነቱም ፡ የሚገኘውን ፡ ደስታ ፡ አለኝታ፡አድርጉ።

ክፍል፡፪።
ሃያ፡ዘጠነኛ፡አንቀጽ።

ከዲድስቅልያ፡የተገኘ፡የአባቶቻችን፡የቅዱሳን፡ሐዋርያት፡መጽሐፍ፡ይህ፡ነው።
በረከታቸው፡ከእኛ፡ጋራ፡ለዘላለሙ፡ይኑር፡አሜን።

፩፤ በሦስተኛውም ፡ ቀን ፡ ፍጻሜ ፡ በሌላት ፡ ክፉ ፡ ሥራቸው ፡ ጨምረውና ፡ አብዝተው ፡ መከሩ።

፪፤ ስለዚህም ፡ አቤቱ ፡ ምስክርነታችንን ፡ ማን ፡ ያምነናል? ክንድህስ ፡ (የእግዚአብሔር ክንድ)፡ለማን፡ተገለጠ፡አለ።

Scanned by CamScanner

## በ፫፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሠሉስ።

፫፤ ወካዕበ ፡ ይቤ ፡ ሰሚዐ ፡ ትሰምዑ ፡ ወኢት
ሌብዉ ፡ ወራእየ ፡ ትሬእዩ ፡ ወኢተአምሩ ።
እስመ፡ጽሉል፡ልቦሙ፡ለዝንቱ፡ሕዝብ።

፬፤ ወበእንተዝ፡ተሠረወት፡እምኔሆሙ፡ጥበብ፡
እስመ ፡ ርእዮሙ ፡ ኢየአምሩ ፡ ወሰሚዖሙ ፡
ኢይሌብዉ።
፭፤ ወአንትሙሰ ፡ ሕዝብ ፡ ወለክሙ ፡ ተውህበ ፡
መንግሥት።
፮፤ እንዘ ፡ ቀዲሙ ፡ ኢተአምርዎ ፡ ለእግዚአ
ብሔር፡ ወይእዜሰ፡አእመርክምዎ፡በርትዕት፡
ሃይማኖት ፡ ወበስብከተ ፡ ወንጌለ ፡ ኢየሱስ ፡
ክርስቶስ ፡ መድኃኒነ ፡ ወሀቤ ፡ ሕይወት ፡
ለኵሎሙ፡እለ፡ይሴፈዉ፡ኪያሁ።
፯፤ ናሁ፡አንትሙ፡ኅደግሙ፡አምልኮ፡ጣዖታት፡
እለ ፡ አልቦሙ ፡ ነፍስ ፡ ወመነንክሙ ፡
መሥዋዕተ፡ርኩሰ፡ወክሕድክምዎሙ፡ለመ
ላእክተ፡ጽልመት።
፰፤ ወበእንተዝ ፡ ቦእክሙ ፡ ውስተ ፡ ብርሃን ፡
ዘበአማን ፡ እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡
ወቦቱ፡አእመርክምዎ፡ለአሐዱ፡ጻድቅ፡እግ
ዚአብሔር ፡ አብ ፡ ወኮንክሙ ፡ ወራስያነ ፡
መንግሥቱ፡እሰመ፡ተጠመቅሙ፡በሞቱ፡
ወበትንሣኤሁ።

፱፤ መፍትው፡ትኩኑ፡ከመ፡ሕፃናት፡እለ፡ይእዜ፡
ተወልዱ ፡ እለ ፡ አልቦሙ ፡ እከይ ፡ ውስተ ፡
ልቦሙ።
፲፤ ወአእትቱ ፡ እምኔክሙ ፡ ኃጢአተ ፡ እስመ ፡
ቤዘወክሙ ፡ በደሙ ፡ ክቡር ፡ ከመ ፡
ታምልክዎ፡ለእግዚአብሔር፡ሕያው።
፲፩፤ ይቤ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሕያው ፡ በውእቱ ፡
መዋዕል ፡ በእንተ ፡ እስራኤል ፡ ዘኀበ ፡ እለ ፡
ኢየአምኑ፡ትትሀየድ፡መንግሥተ፡ሰማያት፡
ወትትወሀብ፡ለሕዝብ፡እለ፡ይገብሩ፡ጽድቀ።

፲፪፤ ወአንትሙሰ፡ቅንኡ፡ለገቢረ፡ፍሬ፡ጥበብ፡
ጥዑም፡እስመ፡ኪያክሙ፡ፈነወ፡ትካት፡ኀበ፡
ዐጸደ ፡ ወይን ፡ ወእሙንቱሰ ፡ ኢሰምዕዎ ፡
ወአግዘፉ፡ልቦሙ።
፲፫፤ ወተንሥኡ፡ላዕለ፡ዐቀብተ፡ወይኑ፡ለእግዚአ
ብሔር፡ ወአኅዝዎሙ ፡ ቦ ፡ ዘቀተሉ ፡ በመጥ

## ማክሰኞ፡መዓልት፡በ፫፡ሰዓት።

፫፤ ሁለተኛም ፡ መስማትን ፡ ትሰማላችሁ ፤ ልብ ፡
አታደርጉም ፡ እንጂ ፤ ማየትን ፡ ታያላችሁ ፡
አታውቁም፡እንጂ፤የዚህ፡ሕዝብ፡ልቡናው፡
ደንድኗልና፡አለ።
፬፤ ስለዚህም ፡ ዕውቀት ፡ ከእርሳቸው ፡ ጠፋች ፤
አይተው፡አያውቁምና፡ሰምተውም፡አያስተ
ውሉምና፡ዕውቀት፡ከእርሳቸው፡ጠፋች።
፭፤ እናንተ ፡ ወገኖች ፡ ግን ፡ መንግሥት ፡
(ልጅነት)፡ለእናንተ፡ተሰጥቶአል።
፮፤ ቀድሞ ፡ እግዚአብሔርን ፡ የማታውቁት ፡
ስትሆኑ ፡ ዛሬ ፡ ግን ፡ ተስፋ ፡ ለሚአደርጉት ፡
ሁሉ፡ሕይወትን፡የሚሰጥ፡የመድኃኒታችን፡
ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ወንጌል ፡ በመሰበኩ ፡
በቀናች፡ሃይማኖት፡አወቃችሁት።
፯፤ እነሆ ፡ ነፍስ ፡ የሌላቸው ፡ ጣዖታትን ፡
ማምለክ፡ የረከሰ ፡ መሥዋዕታቸውንም ፡
ትታችኋል፤የጨለማ፡አበጋዞች፡የሆኑ፡አጋን
ንትንም፡ክዳችኋቸዋል።
፰፤ ስለዚህም ፡ እውነተኛ ፡ ብርሃን ፡ ወደሆነው ፡
ወደ፡ጌታችን፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ገባችሁ፤
ተዋሐዳችሁ ፤ በእርሱም ፡ አንድ ፡ የሆነ ፡
የባሕርይ ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ አብን ፡
አወቃችሁት ፤ ሞቱን ፡ መነሣቱን ፡
አምናችሁ፡ስለተጠመቃችሁ፡የመንግሥቱ፡
ወራሾች፡ሆናችሁ።
፱፤ በልባቸው፡ክፋት፡እንደሌለባቸው፡ዛሬ፡እን
ደተወለዱ ፡ ሕፃናት ፡ ትሆኑ ፡ ዘንድ ፡ ይገባ
ችኋል።
፲፤ ሕያው ፡ እግዚአብሔርንም ፡ ታመልኩት ፡
ዘንድ ፡ በከበረ ፡ ደሙ ፡ዋጅቷችኋልና ፡
ከእናንተ፡ኃጢአትን፡አርቁ።
፲፩፤ በዚያም ፡ ወራት ፡ በማያምኑት ፡ ዘንድ ፡ ስለ ፡
እሥራኤል ፤ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ከእነርሱ ፡
እንደምትወሰድና ፡ ፈቃዱን ፡ ለሚሠሩት ፡
ወገኖች ፡ እንደምትሰጥ ፡ ሕያው ፡ እግዚአ
ብሔር፡ ተናገረ።
፲፪፤ እናንተ ፡ ግን ፡ ጣፋጭ ፡ የሆነ ፡ የዕውቀትን ፡
ፍሬ፡ ለማፍራት ፡ ቅኑ ፤ አስቀድሞ ፡ እናንተን ፡
ወደ ፡ ወይኑ ፡ ቦታ ፡ ልኮአችኋልና ፡ እነዚያ ፡
ግን፡ልባቸውን፡አደንድነው፡አልሰሙትም።
፲፫፤ በእግዚአብሔር ፡ የወይን ፡ ቦታ ፡ ባሉ ፡
ሠራተኞች ፡ ላይም ፡ ተነሡባቸው ፤ ይዘውም ፡

Scanned by CamScanner

በ፫፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሠሉስ።

፫፡ ወከዕበ ፡ ይቤ ፡ ሰሚዐ ፡ ትሰምዑ ፡ ወኢትሌብዉ ፡ ወራእየ ፡ ትሬእዩ ፡ ወኢተአምሩ ። እስመ፡ጽሉል፡ልቦሙ፡ለዝንቱ፡ሕዝብ።

፬፡ ወበእንተዝ፡ተሠረወት፡እምኔሆሙ፡ጥበብ፡ እስመ ፡ ርእዮሙ ፡ ኢየአምሩ ፡ ወሰሚዖሙ ፡ ኢይሌብዉ።

፭፡ ወአንትሙሰ ፡ ሕዝብ ፡ ወለክሙ ፡ ተውህበ ፡ መንግሥት።

፮፡ እንዘ ፡ ቀዲሙ ፡ ኢተአምርዎ ፡ ለእግዚአብሔር፡ ወይእዜሰ፡አእመርክምዎ፡በርትዕት፡ ሃይማኖት ፡ ወበስብከተ ፡ ወንጌለ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ መድኃኒነ ፡ ወሀቤ ፡ ሕይወት ፡ ለኵሎሙ፡እለ፡ይሴፈዉ፡ኪያሁ።

፯፡ ናሁ፡አንትሙ፡ኀደግሙ፡አምልኮ፡ጣዖታት፡ እለ ፡ አልቦሙ ፡ ነፍስ ፡ ወመነንክሙ ፡ መሥዋዕተ፡ርኩሰ፡ወክሕድክምዎሙ፡ለመላእክተ፡ጽልመት።

፰፡ ወበእንተዝ ፡ ቦእክሙ ፡ ውስተ ፡ ብርሃን ፡ ዘበአማን ፡ እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ወቦቱ፡አእመርክምዎ፡ለአሐዱ፡ጻድቅ፡እግዚአብሔር ፡ አብ ፡ ወኮንክሙ ፡ ወራስያነ ፡ መንግሥቱ ፡ እሰመ ፡ ተጠመቅሙ ፡ በሞቱ ፡ ወበትንሣኤሁ።

፱፡ መፍትው፡ትኩኑ፡ከመ፡ሕፃናት፡እለ፡ይእዜ፡ ተወልዱ ፡ እለ ፡ አልቦሙ ፡ እከይ ፡ ውስተ ፡ ልቦሙ።

፲፡ ወአእትቱ ፡ እምኔክሙ ፡ ኃጢአተ ፡ እስመ ፡ ቤዘወክሙ ፡ በደሙ ፡ ክቡር ፡ ከመ ፡ ታምልክዎ፡ለእግዚአብሔር፡ሕያው።

፲፩፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሕያው ፡ በውእቱ ፡ መዋዕል ፡ በእንተ ፡ እስራኤል ፡ ዘኀበ ፡ እለ ፡ ኢየአምኑ፡ትትሀየድ፡መንግሥተ፡ሰማያት፡ ወትትወሀብ፡ለሕዝብ፡እለ፡ይገብሩ፡ጽድቀ።

፲፪፡ ወአንትሙሰ፡ቅንኡ፡ለገቢረ፡ፍሬ፡ጥበብ፡ ጥዑም፡እስመ፡ኪያክሙ፡ፈነወ፡ትካት፡ኀበ፡ ዐጻደ ፡ ወይን ፡ ወእሙንቱሰ ፡ ኢሰምዕዎ ፡ ወአግዘፉ፡ልቦሙ።

፲፫፡ ወተንሥኡ፡ላዕለ፡ዐቀብተ፡ወይኑ፡ለእግዚአብሔር ፡ ወአኀዝዎሙ ፡ ቦ ፡ ዘቀተሉ ፡ በመጥ

ማክሰኞ፡መዓልት፡በ፫፡ሰዓት።

፫፡ ሁለተኛም፡መስማትን፡ትሰማላችሁ፤ልብ፡ አታደርጉም ፡ እንጂ ፤ ማየትን ፡ ታያላችሁ ፡ አታውቁም፡እንጂ፤የዚህ፡ሕዝብ፡ልቡናው፡ ደንድኗልና፡አለ።

፬፡ ስለዚህም ፡ ዕውቀት ፡ ከእርሳቸው ፡ ጠፋች ፤ አይተው፡አያውቁምና፤ሰምተውም፡አያስተውሉምና፤ዕውቀት፡ከእርሳቸው፡ጠፋች።

፭፡ እናንተ ፡ ወገኖች ፡ ግን ፡ መንግሥት ፡ (ልጅነት)፡ለእናንተ፡ተሰጥቶአል።

፮፡ ቀድሞ ፡ እግዚአብሔርን ፡ የማታውቁት ፡ ስትሆኑ፤ዛሬ፡ግን፡ተስፋ፡ለሚአደርጉት፡ ሁሉ፡ሕይወትን፡የሚሰጥ፡የመድኃኒታችን፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ወንጌል ፡ በመሰበኩ ፡ በቀናች፡ሃይማኖት፡አወቃችሁት።

፯፡ እነሆ ፡ ነፍስ ፡ የሌላቸው ፡ ጣዖታትን ፡ ማምለክ፡ የረከሰ ፡ መሥዋዕታቸውንም ፡ ትታችኋል፤የጨለማ፡አበጋዞች፡የሆኑ፡አጋንንትንም፡ክዳችኋቸዋል።

፰፡ ስለዚህም፡እውነተኛ፡ብርሃን፡ወደሆነው፡ ወደ፡ጌታችን፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ገባችሁ፤ ተዋሓዳችሁ ፤ በእርሱም ፡ አንድ ፡ የሆነ ፡ የባሕርይ፡አምላክ፡እግዚአብሔር፡አብን፡ አወቃችሁት ፤ ሞቱን ፤ መነሣቱን ፡ አምናችሁ፡ስለተጠመቃችሁ፡የመንግሥቱ፡ ወራሾች፡ሆናችሁ።

፱፡ በልባቸው፡ክፋት፡እንደሌለባቸው፡ዛሬ፡እንደተወለዱ ፡ ሕፃናት ፡ ትሆኑ ፡ ዘንድ ፡ ይገባችኋል።

፲፡ ሕያው ፡ እግዚአብሔርንም ፡ ታመልኩት ፡ ዘንድ ፡ በከበረ ፡ ደሙ ፡ ዋጅቷችኋልና ፡ ከእናንተ፡ኃጢአትን፡አርቁ።

፲፩፡ በዚያም፡ወራት፡በማያምኑት፡ዘንድ፡ስለ፡ እሥራኤል፡መንግሥተ፡ሰማያት፡ከእነርሱ፡ እንደምትወሰድና ፡ ፈቃዱን ፡ ለሚሠሩት ፡ ወገኖች ፡ እንደምትሰጥ ፡ ሕያው ፡ እግዚአብሔር፡ ተናገረ።

፲፪፡ እናንተ፡ግን፡ጣፋጭ፡የሆነ፡የዕውቀትን፡ ፍሬ፡ለማፍራት፡ቅኑ፤አስቀድሞ፡እናንተን፡ ወደ፡ወይኑ፡ቦታ፡ልኮአችኋልና፡እነዚያ፡ ግን፡ልባቸውን፡አደንድነው፡አልሰሙትም።

፲፫፡ በእግዚአብሔር ፡ የወይን ፡ ቦታ ፡ ባሉ ፡ ሠራተኞች፡ላይም፡ተነሡባቸው፤ይዘውም፣

Scanned by CamScanner

## በ፫፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሠሉስ።

ባህት ፡ ወቦ ፡ ዘወሠሩ ፡ በሞሠርት ፡ ወቦ ፡ ዘቀተሉ፡ውስተ፡ቤተ፡መቅደስ።

፲፬፡ ወዓዲ ፡ ቀተልዎ ፡ ለወራሲ ፡ ወመነንዎ ፡ ወወገርዎ፡ከመ፡እብን፡እንተ፡መነንዎ፡ነደቅት።

፲፭፡ ወበእንቲአከሙ ፡ ይቤ ፡ ሕዝብ ፡ ዘኢየአምር ፡ ተቀንየ ፡ ሊተ ፡ ወውስተ ፡ ምስማዐ ፡ እዝን ፡ ተሰጥዉኒ።

በረከቶሙ ፡ ለሐዋርያት ፡ የሀሉ ፡ ምስሌነ ፡ ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

### ሃይማኖተ፡አበው።

፩፡ ሃይማኖት ፡ ቅድስት ፡ እንተ ፡ ጸሐፋ ፡ ቅዱስ ፡ ሳዊሮስ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ዘሀገረ ፡ እግዚአብሔር፡ዐባይ፡አንጾኪያ።

ምዕ፡፹፩፡፫–፲፩።

፫፡ ይቤ ፡ ይደልወነ ፡ ንእመን ፡ ከመዝ ፡ በእግዚአብሔር፡ቃል፡ከመ፡ቦቱ፡ክልኤቱ፡ልደታት፡ አሐዱ ፡ እምአብ ፡ እምቀዲሙ ፡ እንበለ ፡ ሱታፌ ፡ ምስካበ ፡ አንስት ፤ ልደት ፡ ዘኢይትረከብ ። ወካልእ ፡ በደኃሪ ፡ መዋዕል ፡ እምቅድስት ፡ ድንግል ፡ ማርያም ፡ እንበለ ፡ ሩካቤ ፡ ተባዕት ፤ ልደት ፡ ዘኢይትነገር ፡ ወኢይትረከብ ። ወዘንተ፡ባሕቲ፡ነአምር፡ከመ፡ቃል፡ሥጋ፡ኮነ፡ወኅደረ፡ላዕሌነ፡ወርኢናሁ፡በአዕይንቲነ፡ወገሠሥናሁ፡በእደዊነ።

፬፡ ወኢፈጠሮ፡አብ፡ከመ፡አሐዱ፡እመላእክት፡ ወኢ ፡ ከመ ፡ አሐዱ ፡ እምሱራፌል ፡ ወኪሩቤል፡ አላ ፡ ውእቱ ፡ ተወልደ ፡ እምህላዌሁ ፡ ለአብ ፡ ወውእቱ ፡ ይትሌዓል ፡ እምኵሉ፡ ሥልጣናት ፡ ወአጋዕዝት ፡ ወኵሉ ፡ ስም ፡ ዘይሰመይ ፡ በዝ ፡ ዓለም ፡ ወበዘይመጽእ፡ ወዕሩይ ፡ ውእቱ ፡ ምስለ ፡ አቡሁ ፡ ወመንፈስ፡ ቅዱስ ፡ ወውእቱ ፡ ህልው ፡ ለዓለም ፡ በመለኮቱ፡ባሕቲቱ።

፭፡ ወበእንተ፡ዝ፡ይቤ፡በእንተ፡መንፈስ፡ቅዱስ፡ ውእቱ ፡ ይነሥእ ፡ እምዚአየ ፡ ወይሁበከሙ ፡

## ማክሰኞ፡መዓልት፡በ፫፡ሰዓት።

በሰይፍ ፡ የገደሉአቸው ፡ አሉ ፤ በመጋዝም፡ የሠነጠቁአቸው ፡ አሉ ፤ በቤተ ፡ መቅደስም፡ ውስጥ፡የገደሉአቸው፡አሉ።

፲፬፡ ዳግመኛም፡ወራሹን፡ገደሉት፤አቃለሉትም፡ አናጢዎች፡እንደ፡ናቋት፡ደንጊያም፡ጣሉት።

፲፭፡ ስለ፡እናንተም፡መገዛት፡የማያውቅ፡ሕዝብ፡ ተገዛልኝ፤በአደባባይ፡በአዋጅ፡ተቀበሉኝ፡ አለ።

የሐዋርያት ፡ በረከታቸው ፡ ከእኛ ፡ ጋራ፡ ለዘላለሙ፡ይኑር፡አሜን።

### የአባቶች፡ሃይማኖት።

፩፡ የእግዚአብሔር ፡ ሀገር ፡ የምትሆን ፡ የታላቋ፡ የአንጾኪያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ቅዱስ ፡ ሳዊሮስ፡ የጻፋት፡የከበረች፡ሃይማኖት፡ይህች፡ናት። (ቁጥሩ፡እያለፈ፡እያለፈ፡ነው።)

ምዕ፡፹፩፡፫–፲፩።

፫፡ ሁለት ፡ ልደት ፡ እንዳለው ፡ በእግዚአብሔር፡ ቃል ፡ እንዲሁ ፡ ልናምን ፡ ይገባናል ፤ አንዱ፡ ቅድመ ፡ ዓለም ፡ ከአብ ፡ ያለ ፡ እናት ፡ የተወለደው ፡ የማይመረመር ፡ ልደት ፡ ነው ። ሁለተኛውም ፡ በኋላ ፡ ዘመን ፡ ከንጽሕት ፡ ድንግል፡ ማርያም ፡ ያለአባት ፡ የተወለደው ፡ የማይመረመር ፡ የማይነገር ፡ ልደት ፡ ነው ። ነገር፡ግን፡ ቃል ፡ ሥጋ ፡ እንደሆነ ፡ ባሕርያችንንም፡ ባሕርይ፡እንዳደረገ፡በዓይናችን፡እንዳየነው፡ በእጃችንም ፡ እንደዳሠሥነው ፡ ይህን ፡ ብቻ፡ እናውቃለን፡አለ።

፬፡ አብ፡ከመላእክት፡እንዳንዱ፡ከኪሩቤል፡ከሱራፌልም፡እንዳንዱ፡አልፈጠረውም፤እርሱ፡ አካል ፡ ዘእምአካል ፡ ባሕርይ ፡ ዘእምባሕርይ፡ ከአብ ፡ ተወለደ ፡ እንጂ ፡ ከሥልጣናት ፡ ሁሉ፡ ከአጋዕዝትም ፡ ሁሉ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ በሚመጣውም ፡ ዓለም ፡ ከሚጠራው ፡ ስም ፡ ሁሉ፡ እርሱ ፡ ይበልጣል ፤ ከባሕርይ ፡ አባቱ ፡ ከአብ፡ ከባሕርይ ፡ ሕይወቱ ፡ ከመንፈስ ፡ ቅዱስም፡ ጋር ፡ አንድ ፡ ነው ፤ በመለኮቱም ፡ ለዘላለሙ፡ ጸንቶ፡ይኖራል።

፭፡ ስለዚህም ፡ የመንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ነገር ፡ ሲያስተምር፡ቃልነትን፡ከእኔ፡ገንዘብ፡አድርጎ፡

በ፫፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሠሉስ።

ዝንቱ ፡ ዘተርእየ ፡ በዮርዳኖስ ፡ በአምሳለ ፡
ርግብ፡ወወረደ፡ዲበ፡ወልድ። ወሶበ፡ርእየ፡
ቃል ፡ ከመ ፡ ኃጢአት ፡ በዝኀ ፡ ወረደ ፡
እምሰማይ፡ወኀደረ፡ውስተ፡ከርሠ፡ድንግል፡
ማርያም፡ቅድስት፡ ወሐነጸ፡ሎቱ፡እምኔሃ፡
ሥጋ፡በምሥጢር፡ዘኢይትረከብ፡ወዘኢይት
ነገር ፡ ወነበረ ፡ ውስተ ፡ ከርሣ ፡ ተሰዓተ ፡
አውራኀ፡ወውእቱ፡ዘፈጠረ፡ሎቱ፡ሥጋ፡
እምኔሃ፡።
፲፩፤ ወአኮ፡አብ፡ዘኀደረ፡ውስተ፡ከርሠ፡ድንግል፡
ለተሰብኦ፡ከመ፡ኢይበል፡መኑሂ፡ይትፋለስ፡
አብ፡ለከዊነ፡ወልድ፡ አላ፡ውእቱ፡ወልድ፡
ዘኀደረ፡ውስተ፡ከርሠ፡ድንግል፡በፈቃደ፡
አቡሁ፡ ወበሥምረተ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡
እስመ፡ እሐቲ፡ይእቲ፡ሥምረት፡ዘሥሉስ፡
ቅዱስ፡ኢይትበሀል፡እስመ፡ካልኡ፡ፈጠሮ፡
ሎቱ ፡ ከመ ፡ ይረስዮ ፡ ነኪረ ፡ እመለኮት ፡
አላ ፡ ውእቱ ፡ ባሕቲቱ ፡ ተሠገወ ፡ ወተ
ዐገሠ ፡ ሕማማተ ፡ ሥጋ ፡ እንተ፡ አልባቲ ፡
ኃጢአት።

ጸሎቱ፡ወበረከቱ፡ተሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡
ዓለም፡አሜን።

ምንተኑ፡አአስየኪ፡በል።

ተአምሪሃ፡ለእግዝእትነ፡ቅድስት፡ድንግል፡
በክልኤ፡ማርያም፡ወላዲተ፡አምላክ፡ጸሎታ፡
ወበረከታ፡የሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡
አሜን።

፩፤ ተብህለ ፡ ከመ ፡ ሀሎ ፡ አሐዱ ፡ መነኮስ ፡
ወአልቦቱ ፡ አልባስ ፡ ወአራዝ ፡ ወሲሳይ ፡
ወማኅደር ። ወይትአመና ፡ ለእግዝእትነ ፡
ቅድስት ፡ ድንግል ፡ በክልኤ ፡ ማርያም ፡
ወላዲተ፡አምላክ፡ ወይቤላ፡አዝዚ፡ሊተ፡
ዘእበልዕ፡ወዘእለብስ፡ወኢይኩን፡ንፉቀ፡
እምኔኪ፡ወዘንተ፡ብሂሎ፡ኖመ።

፪፤ ወመጽአት፡ኀቤሁ፡እግዝእትነ፡ቅድስት፡
ድንግል ፡ በክልኤ ፡ ማርያም ፡ ወላዲተ ፡
አምላክ፡ዘበዕብራይስጢ፡ማሪሃም፡ ወከዊኖ፡
መንፈቀ፡ሌሊት፡አስተርአየቶ፡እግዝእትነ፡

ማክሰኞ፡መዓልት፡በ፫፡ሰዓት።

ተምራችኋል ፡ አለ ፤ በዮርዳኖስ ፡ በርግብ ፡
አምሳል፡የታየ፡በወልድ፡ላይ፡የተቀመጠ፡
ይህ፡መንፈስ፡ቅዱስ፡ነው፤ቃል፡ኃጢአት፡
እንደበዛ ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ ከሰማይ ፡ ወርዶ ፡
በንጽሕት፡ድንግል፡ማርያም፡ማኅፀን፡አደረ፤
በማይመረመር ፡ በማይነገር ፡ ምሥጢር፡
ሥጋን፡ ከእርሷ ፡ ተዋሐደ ፤ ዘጠኝ ፡ ወር ፡
ከአምስት፡ቀን፡በማኅፀኗ፡ኖረ፤ሊዋሐደው፡
ሥጋን፡ከእርሷ፡የፈጠረ፡እርሱ፡ነው።
፲፩፤ አብ ፡ ሰው ፡ ለመሆን ፡ በድንግል ፡ ማኅፀን ፡
ያደረ ፡ አይደለም ፤ ማንም ፡ ማን ፡ አብ ፡
ወልድን፡ ወደመሆን፡ይለወጣል፡እንዳይል፡
የሥላሴ ፡ ፈቃድ ፡ አንዲት ፡ እንደመሆኗ ፡
መጠን፡በአባቱ፡ፈቃድ፡በመንፈስ፡ቅዱስ፡
ፈቃድ፡በድንግል፡ማኅፀን፡ያደረ፡ወልድ፡
ነው፡እንጂ፡ከፈጣሪነት፡ይለየው፡ዘንድ፡
አብ፡ እርሱን፡ፈጠረው፡አይባልም፤እርሱ፡
ራሱ፡ወልድ፡ሰው፡ሆነ፡እንጂ፡የኃጢአት፡
ምክንያት ፡ ያልተገኘባትን ፡ የሥጋን ፡
መከራም፡ተቀበለ፡እንጂ።

ጸሎቱና፡በረከቱ፡ከእኛ፡ጋራ፡ለዘላለሙ፡
ትኑር፡አሜን።

ምንተኑ፡አአስየኪ፡በል።

ልመናዋ፡በረከቷ፡ከእኛ፡ጋራ፡ለዘላለሙ፡
ይደርብንና ፡ በሁለት ፡ ወገን ፡ ድንግል ፡
የሆነች፡ አምላክን ፡ የወለደች ፡ ቅድስት ፡
ድንግል ፡ እመቤታችን ፡ ማርያም ፡ ያደረ
ገችው፡ተአምር፡ይህ፡ነው።
፩፤ ስለ ፡ አንድ ፡ መነኩስ ፡ ተነገረ ፤ እርሱም ፡
ልብስ፡ የዕለትም ፡ ምግብና ፡ ማደሪያ ፡
የሌለው፡ነው፤በድንጋሌ፡ሥጋ፡በድንጋሌ፡
ነፍስ ፡ የጸናች ፡ ክብርት ፡ እመቤታችን ፡
ማርያምን ፡ ይተማመናት ፡ ነበር ፤ እንዲህ ፡
ብሎ ፡ ጸለየ ፤ አንቺን ፡ የምጠራጠር ፡ እንዳ
ልሆን ፡ የምበላውንና ፡ የምለብሰውን ፡
እዘዝልኝ፡አላት፤ይህንም፡ብሎ፡ተኛ።
፪፤ በሁለት፡ወገን፡ድንግል፡የሆነች፡አምላክን፡
የወለደች፡ክብርት፡እመቤታችን፡ማርያም፡
በዕብራይስጥ፡ማሪሃም፡ የምትባል፡እኩለ፡
ሌሊት፡በሆነ፡ጊዜ፡ወደ፡እርሱ፡መጣች፤

Scanned by CamScanner

### በ፫፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሠሉስ።

በሕልም፡ወበራእይ፡ወትቤሎ፡ኦ፡መነኮስ፡ምንተ፡ትብል፡ወንሣእ፡ዘንተ፡ልብሰ፡ከመ፡ይኩንከ።
፫፤ ወነቅሀ ፡ እምንዋሙ ፡ ወረከበ ፡ ልብሰ ፡ ወተፈሥሐ፡ዐቢየ፡ፍሥሐ።
፬፤ ወአንከሩ፡ኵሎሙ፡ሕዝብ፡እለ፡ርእዩ፡ዘንተ፡ተአምረ ፡ መንክረ ፡ ዘገብረት ፡ እግዝእትነ ፡ ቅድስት ፡ ድንግል ፡ በክልኤ ፡ ማርያም ፡ ወላዲተ፡አምላክ። ወወሀቡ፡ስብሐተ፡ለፍሬ፡ከርሣ።

ጸሎታ፡ወበረከታ፡የሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ ጥዑመ፡ስም፡በል።

ተአምር፡ወመንክር፡ዘገብረ፡እግዚእነ፡ወአምላክነ ፡ ወመድኃኒነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ዘከመ ፡ ነገሮሙ ፡ ምዝባሬሃ ፡ ለኢየሩሳሌም ፡ በእንተ ፡ እከየ ፡ አይሁድ ፡ ወይትበቀሎሙ ፡ ሐዲሳን፡ሕዝብ፡በሥጋሁ፡ወበደሙ።

ሣህሉ፡ወምሕረቱ፡የሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።
፭፤ ወተመይጠ፡እግዚእ፡ኢየሱስ፡ውስተ፡ኢየሩሳሌም ፡ ወይቤ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ኢየሩሳሌም ፡ እንተ ፡ ትቀትሊዮሙ ፡ ለነቢያት ፡ አእምሪ ፡ እስመ፡ሀለወኪ፡ትትመዘበሪ፡ወኢይተርፍ፡እምኔኪ፡እብን፡ዲበ፡እብን።
፮፤ ወእምድኅረዝ ፡ እሬስየኪ ፡ ማኅደረ ፡ አድግ ፡ ገዳም ፡ ዘዘከርኩ ፡ ግብረ ፡ ፀአቱ ፡ እምውስተ ፡ ገዳም፡እስመ፡የኀድር፡ውስቴትኪ፡ሠለስተ፡ምእተ፡ወዕለታተ፡ንኡሳነ።
፯፤ ወለእመ ፡ ኢጸንኡ ፡ ሕዝብየ ፡ በሃይማኖት ፡ ርትዕት ፡ ወተዓደዉ ፡ ትእዛዝየ ፡ ውእተ ፡ አሚረ፡እሬስየኪ፡ኢየሩሳሌም፡እምድኅረ፡ኀደሩ፡ውስቴትኪ፡አእዱግ፡ገዳም፡ዘከመ፡ወጠንኩ ፡ ለኪ ፡ ወእሬሲ ፡ ይኀድር ፡ ውስቴትኪ ፡ ጕጓ ፡ ወእሬሲ ፡ ይሴባሕ ፡ ውስቴትኪ፡ካልእ፡ስም፡ዘኢኮነ፡ስምየ።
፰፤ ብፁዕ ፡ ብእሲ ፡ ዘነበረ ፡ በሃይማኖትየ ፡ በውእቱ፡መዋዕል።

### ማክሰኞ፡መዓልት፡በ፫፡ሰዓት።

በሕልሙም ፡ በመገለጥ ፡ ታየችው ፤ አንተ፡ መነኵሴ ፡ ምን ፡ ትላለህ? ልብስ ፡ ይሆንህ፡ ዘንድ፡ይህን፡ውሰድ፡አለችው።
፫፤ ከእንቅልፉም ፡ ነቅቶ ፡ ያንን ፡ ልብስ፡አገኘ፤ በፍጹም፡ደስታም፡ደስ፡አለው።
፬፤ በድንጋሌ ፡ ሥጋ ፡ በድንጋሌ ፡ ነፍስ፡የጸናች፡ አምላክን፡የወለደች፡ክብርት፡እመቤታችን፡ ማርያም ፡ ያደረገችውን ፡ ድንቅ ፡ ተአምር፡ ያዩ፤ ሕዝቡ ፡ ሁሉ ፡ አደነቁ ፤ ለማኅፀንዋም፡ ፍሬ፡ለጌታ፡ምስጋና፡አቀረቡ።

ልመናዋ ፡ በረከቷ ፡ ከእኛ ፡ ጋራ ፡ ለዘላለሙ፡ ይኑር፡አሜን።

ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ ጥዑመ፡ስም፡በል።

ጌታችን ፡ ፈጣሪያችን ፡ መድኃኒታችን፡ ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ ስለ፡አይሁድ፡ክፉ፡ሥራ፡ የኢየሩሳሌምን ፡ መፍረስና ፡ ስለ ፡ ሐዲሳን፡ አማንያን ፡ በሥጋውና ፡ በደሙ ፡ መጠቀም፡ እንደ፡ነገራቸው፡የሚናገር፡ድንቅ፡ተአምር፡ ይህ፡ነው።

ይቅርታውና ፡ ቸርነቱ ፡ ለዘለዓለሙ ፡ ከእኛ፡ ጋራ፡ይሁን፡አሜን።
፭፤ ጌታ ፡ ኢየሱስም ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም፡ ተመልሶ፡ ነቢያትን ፡ የምትገድሊያቸው፡ኢየ ሩሳሌም፡ኢየሩሳሌም፡ሆይ፤ ከአንቺ፡ዘንድ፡ ድንጊያ ፡ በድንጊያ ፡ ላይ ፡ ሁኖ ፡ ሳይቀር፡ ትፈርሺ፡ዘንድ፡እንዳለሽ፡እወቂ፡አለ።
፮፤ ከዚህ፡በኋላም፡ከበረኻ፡ውስጥ፡አወጣሁን፡ የተናገርኩት፡የበረኻ፡አህያ፡ለርሱ፡ማደሪያ፡ አደርግሻለሁ ፤ በውስጥሽም ፡ ሦስት ፡ መቶ፡ ቀኖችና ፡ ታናናሽ ፡ ቀኖች ፡ ያህል ፡ ይኖራል፡ አለ።
፯፤ ወገኖቼ ፡ እስራኤልም ፡ በቀናች ፡ ሃይማኖት፡ ካልጸኑ ፡ ትእዛዜንም ፡ ከተላለፉ ፡ ያን ፡ ጊዜ፡ የበረኻ ፡ አህዮች ፡ ማደሪያ ፡ ሁነሽ ፡ ከኖርሽ፡ በኋላ፡ኢየሩሳሌም፡ሆይ፡እንደ፡ጀመርኩብሽ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ጉጉት ፡ ያድርብሽ ፡ ዘንድ ፡ አደር ጋለሁ ፤ የእኔ ፡ ስም ፡ ያልሆነም ፡ ሌላ ፡ ስም፡ በውስጥሽ፡እንዲመሰገን፡አደርጋለሁ።
፰፤ በዚያን፡ወራት፡በሃይማኖቴ፡ጸንቶ፡የሚኖር፡ የተመሰገነ፡ነው።

Scanned by CamScanner

በ፫፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሠሉስ።

፭፤ አሌ ፡ ለኪ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ እምዘይሄሉ ፡ ምስሌኪ ፡ ነገሩ ፡ ለሐሳዊ ፡ ዘአቅደምኩ ፡ ዘክሮቶ ። እስመ ፡ ይሄሉ ፡ ውስቴትኪ ፡ ኀይልየ፡ወበውስቴትኪ፡አርኢ፡ስብሓትየ፡ ለጸላእትየ ፡ ለለ ፡ ኵሉ ፡ ዓመት ፡ በዕለተ ፡ ትንሣኤየ።

፮፤ አሌ ፡ ለኪ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ እምዘይሄሉ ፡ ላዕሌኪ፡ በተፍጻሜተ ፡ ዘመን ፡ እስመ ፡ መሥዋዕት፡ንጽሕት፡ትበጥል፡እምኔኪ፡ወይ ትዌደስ፡ውስቴትኪ፡ካልእ፡ስም፡ከንቱ፡ ዘኢኮነ፡ስምየ።

፯፤ ኢየሩሳሌም፡ሰቃሊተ፡አምላክ፡እስፍንቱ፡ ተአምራት፡ተገብሩ፡በውስቴትኪ፡ወኢአ መንኪ።

፰፤ ወእምዝ፡ይቤሎሙ፡እግዚእ፡ኢየሱስ፡ለአር ዳኢሁ፡ብክዩ፡አ፡አኀውየ፡በእንተ፡ኢየሩ ሳሌም፡ወበዘይረክባ፡በደኅሪ፡መዋዕል።

፱፤ እስመ፡እንስሳ፡በድው፡ወአእዱግ፡ገዳም፡ ይመልኡ ፡ ውስቲታ ። አራዊተ ፡ ምድር ፡ አቃርብት፡ወአፍዖት።

፲፤ ብክዩ ፡ አኀውየ ፡ በእንተ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ በከመ፡አስቈቀወ፡ኤርምያስ፡ነቢይ፡ላዕሌሃ።

፲፩፤ ብክዩ፡ላዕሌሃ፡በእንተ፡ዘሀሎ፡ይርከባ፡ እነሥእ፡እምሰብአ፡መንግሥተ፡ወክህነተ፡ ወትንቢተ ፡ ወእሜጥዎ ፡ ለጸላእቶሙ ፡ ወአወርሶ፡ለሕዝብ፡ሐዲስ፡ዘይትወለድ፡ ሊተ፡በስብከትክሙ፡እምነ፡ጥምቀት።

፲፪፤ እስመ፡ይከውኑ፡ውስተ፡እዴየ፡እሉ፡ሕዝብ፡ ዘተነበየ፡በእንቲአሆሙ፡ዳዊት፡ነቢይ።

፲፫፤ ይቤ፡በእንተ፡እሉ፡ሕዝብ፡ዘይትፈጠር፡ ይሴብሖ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በእንቲአየ ፡ ወቡሩክ፡ዘይከውን፡ዝንቱ፡ሕዝብ።

፲፬፤ ዝ፡ንጹሕ፡ወቡሩክ፡ዘኀረይኩ፡እምቅድመ፡ መዋዕል፡ወአዝማን።

፲፭፤ ወአበጥል ፡ መሥዋዕተ ፡ አልሕምት ፡ ወአጣሊ፡ወአባግዕ፡ወንዝኀተ፡ደም፡ወኵሎ፡ ግብሮ፡ለአሮን፡አበጥል፡እምኢየሩሳሌም።

ማክሰኞ፡መዓልት፡በ፫፡ሰዓት።

፭፤ ኢየሩሳሌም፡ሆይ፡አስቀድሜ፡የተናገርኩት፡ የሐሳዊ ፡ መሲሕ ፡ ትምህርቱ ፡ በውስጥሽ ፡ ከመኖሩ፡የተነሣ፡ወዮልሽ፡በተነሣሁባት፡ ቀን፡በየዓመቱ፡ጌትነቴን፡ለጠላቶቼ፡እገል ጣለሁና፡ሥልጣኔ፡በአንቺ፡ላይ፡ይጸናል።

፮፤ ኢየሩሳሌም ፡ ሆይ ፡ በመጨረሻው ፡ ዘመን ፡ በውስጥሽ ፡ ከሚኖረው ፡ ዐመፅ ፡ የተነሣ ፡ ንጹሕ፡መሥዋዕት፡ካንቺ፡ይጠፋልና፡የእኔ፡ ያልሆነም፡የከንቱ፡ሐሳዊ፡መሲሕ፡ስም፡ በውስጥሽ፡ይመሰገናልና፡ወዮልሽ።

፯፤ አምላክ፡ፈጣሪን፡ሰቅለሽ፡የገደልሽ፡ኢየሩ ሳሌም፡ሆይ፡በውስጥሽ፡የተደረጉ፡ተአም ራቶች፡ስንት፡ነበሩ? አንቺ፡ግን፡አላመንሽም።

፰፤ ከዚህ፡በኋላም፡ጌታ፡ኢየሱስ፡ለደቀመዛ ሙርቱ፡በኋለኛው፡ዘመን፡ስለሚአገኛት፡ መከራ፡ስለ፡ኢየሩሳሌም፡እዘኑ፤አልቅሱ፡ አላቸው።

፱፤ የዱር፡እንስሳና፡የበረኻ፡አህዮች፡የምድር፡ አራዊት፡እፉኝቶችና፡ጊንጦች፡ይመሉባ ታልና።

፲፤ ወንድሞቼ፡ሆይ፡ኤርምያስ፡በእርሷ፡ላይ፡ እንዳለቀሰ፡ስለ፡ኢየሩሳሌም፡አልቅሱ።

፲፩፤ ስለሚያገኛት ፡ መከራም ፡ መንግሥትን ፡ ክህነትን ፡ ትንቢትን ፡ ከእርሷ ፡ ወስጄ ፡ ጠላቶቿ፡ለነበሩት፡እሰጣለሁ፤በትምህርታ ችሁም፡በጥምቀት፡ለሚወለድልኝ፡አዲስ፡ ሕዝብ፡አወርሰዋለሁ።

፲፪፤ እነዚህም፡ስለ፡እርሳቸው፡ዳዊት፡ትንቢት፡ የተናገረላቸው፡ናቸው፡በእምልኮቴ፡ውስጥ፡ ይሆናሉና።

፲፫፤ ስለ፡እርሳቸውም፡ሁለተኛ፡የሚነሣ፡ሕዝብ፡ ከጊዜው፡ደርሶ፡እግዚአብሔርን፡ያመሰግ ነዋል፡ያለው፡ስለ፡እኔ፡የሚከብረው፡ይህ፡ ሕዝብ፡ነው።

፲፬፤ ይህ፡ንጹሕ፡ቡሩክ፡የሆነ፡ሕዝብ፡ከዕለታት፡ ከአዝማናት፡አስቀድሞ፡የመረጥኩት፡ነው።

፲፭፤ የላሙን፡የፍየሉን፡የበጉንም፡መሥዋዕት፡እሽ ራለሁ፤የደም፡መርጨቱንም፡አሮን፡ሲሠራው፡ የነበረውን፡ሁሉ፡ከኢየሩሳሌም፡አጠፋለሁ።

Scanned by CamScanner

## በ፫፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሠሉስ።

፲፮፤ ወአኀብር ፡ ውስቴታ ፡ ህየንተ ፡ አይሁድ ፡ ሕዝበ፡ እለ ፡ የአምኑ ፡ ብየ ፡ ወእለ ፡ የዐቅቡ ፡ ሕግየ፡ወይጠመቁ፡በስምየ፡ወይሰመዩ፡ክርስቲያነ፡በጽድቅ።

፲፯፤ ወትከውን ፡ መሥዋዕቶሙ ፡ ህየንተ ፡ አልሕምት፡ወአጣሊ፡ወአባግዐ፡መሥዋዕት፡ አምላካዊት ፡ ኅብስተ ፡ ሥርናይ ፡ ንጹሕ ፡ ይከውን ፡ ሥጋየ ፡ ወይትፌተት ፡ በእንተ ፡ ስርየተ፡ኃጢአት።

፲፰፤ እስመ፡እሰሪ፡ኀጢአተ፡ዅሉ፡ዘይበልዕ፡በሃይማኖት፡ርትዕት።

፲፱፤ ወህየንተ፡ደመ፡እንስሳ፡ዘይጸይእ፡እሬሲ፡ዐጺረ፡ወይን፡ንጹሕ፡ይኩን፡አምሳለ፡ደምየ፡ክቡር።

፳፤ እስመ ፡ በጊዜ ፡ ይትቀዳሕ ፡ ውስተ ፡ ጽዋዕ ፡ በርደተ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ላዕሌሁ ፡ ይትመየጥ ፡ እምከዊነ ፡ ወይን ፡ ኀበ ፡ ከዊነ ፡ ደምየ፡ዘይትከዐው፡ለስርየተ፡ኃጢአት።

፳፩፤ ወእሬሲ፡ህየንተ፡ጼና፡ሥብሕ፡ጽዩእ፡ዕጣነ፡ እምዅሉ ፡ አፈው ፡ ጽስጥቂስ ፡ ወአምዕዝ ፡ ጼናሁ ፡ ለዘየዓጥን ፡ በቅድሜየ ፡ ወትረ ፡ ወእኅድግ፡ሎቱ፡ኃጢአቶ።

፳፪፤ ወእሬሲ፡መዐዛ፡ዕጣኑ፡ለሥርየተ፡ጌጋይ።

ሣህሉ፡ወምሕረቱ፡የሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ ዓለም፡አሜን።

### ክፍል፡፫።

ይ፡ዲ፡ቅድመ፡ወንጌል።

መዝ፤፻፲፰፡፻፶፬።
ፍታሕ፡ፍትሕየ፡ወባልሐኒ።
ወበእንተ ፡ ቃልከ ፡ አሕይወኒ ። ርኁቅ ፡ ሕይወትየ፡እምኃጥአን።

### ወንጌል፡ዘማቴዎስ።

ምዕ፤፳፫፡፴፯–፴፱።

፴፯፤ ኢየሩሳሌም ፡ ኢየሩሳሌም ፡ እንተ ፡ ትቀትሊዮሙ ፡ ለነቢያት ፡ ወትዌግሪዮሙ ፡ ለሐዋርያት ፡ እለ ፡ ተፈነዉ ፡ ኀቤኪ ፡ ሚ ፡ መጠነ ፡ ፈቀድኩ፡አስተጋብኦሙ፡ለውሉድኪ፡ከመ፡ እንተ፡ታስተጋብእ፡ዶሮሆ፡ዕጐሊሃ፡ታሕተ፡

## ማክሰኞ፡መዓልት፡በ፫፡ሰዓት።

፲፮፤ በውስጥዋም፡የሚአምኑብኝንና፡ሕጌን፡የሚጠብቁትን ፡ በእኔ ፡ ስም ፡ ተጠምቀው፡ በእውነት ፡ ክርስቲያን ፡ የተባሉትን ፡ በአይሁድ፡ፈንታ፡አኖራለሁ።

፲፯፤ መሥዋዕታቸውም ፡ በላም ፡ በፍየል ፡ በበግ፡ መሥዋዕት ፡ ፈንታ ፡ ከሥንዴ ፡ በሚሆን፡ ኅብስት ፡ አምላካዊ ፡ አካል ፡ ንጹሕ ፡ ሥጋዬ፡ ሁኖ ፡ ስለ ፡ ኃጢአት ፡ ማስተስረያ ፡ ይፈተታል።

፲፰፤ በቀናች ፡ ሃይማኖት ፡ ሁኖ ፡ የሚቀበለውን፡ ሁሉ፡ኃጢአቱን፡አስተሰርይለታለሁና።

፲፱፤ ስለሚሸት ፡ የእንስሳ ፡ ደም ፡ ፈንታ ፡ የከበረ፡ ደሜ ፡ አምሳል ፡ የንጹሕ ፡ ወይን ፡ ጭማቂ፡ ይሆን፡ዘንድ፡አደርጋለሁ።

፳፤ ወደ ፡ ጽዋው ፡ በሚቀዳ ፡ ጊዜ ፡ በመንፈስ፡ ቅዱስ ፡ መውረድ ፡ ከወይንነቱ ፡ ተለውጦ፡ የኃጢአት ፡ ማስተስረያ ፡ የሚፈሰውን፡ ደሜን፡ይሆናልና።

፳፩፤ ስለሚሸት ፡ የሥብ ፡ መዐዛም ፡ ጽስጥቂስ፡ከሚባል፡ሽቱ፡ሁሉ፡ዕጣንን፡አደርጋለሁ፤በፊቴም፡ ዘወትር ፡ ለሚአጥነው ፡ መዐዛውን ፡ አጣፍጥለታለሁ፤ኃጢአቱንም፡አስተሰርይለታለሁ።

፳፪፤ የዕጣኑ ፡ መዓዛንም ፡ ለበደል ፡ ሁሉ ፡ ማስተስረያ፡አደርጋለሁ።

ቸርነቱ፡ይቅርታው፡ከእኛ፡ጋራ፡ለዘላለሙ፡ ትኑር፡አሜን።

### ክፍል፡፫።

ዲያቆኑ፡ከወንጌል፡በፊት።

መዝ፤፻፲፰፡፻፶፬።
ፈርደህ፡ከመከራ፡አድነኝ።
ሕግህንም ፡ ስለጠበቅሁ ፡ አድነኝ ። ሕይወት፡ (እግዚአብሔር)፡ከኃጥአን፡የራቀ፡ነው፡ይበል፡

### የማቴዎስ፡ወንጌል።

ምዕ፤፳፫፡፴፯–፴፱።

፴፯፤ ነቢያትን ፡ የምትገድሊያቸው ፡ ወደ ፡ አንቺ፡ የተላኩትን ፡ ሐዋርያትንም ፡ የምትደበድቢ ያቸው ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ዶሮ፡ ጫጩቶቿን ፡ በክንፏ ፡ ውስጥ ፡ እንደምትሰ በስብ፡ልጆችሽን፡ልሰበስባቸው፡ምን፡ያህል፡

Scanned by CamScanner

| በ፫፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘሠሉስ። | ማክሰኞ፡መዓልት፡በ፫፡ሰዓት። |
| --- | --- |

ክነፊሃ፡ወአበይክሙ።

፴፰፤ ናሁ፡ይትኀደግ፡ለክሙ፡ቤትክሙ፡በድው።

፴፱፤ አማን፡እብለክሙ፡እምይእዜሰ፡ኢትሬእዩኒ፡ እስከ ፡ ሶበ ፡ ትብሉ ፡ ቡሩክ ፡ ዘይመጽእ ፡ በስመ፡እግዚአብሔር።

ምዕ፤፳፬፤፩–፪።

፩፤ ወወፂአ ፡ እግዚእ ፡ ኢየሱስ ፡ እምቤተ ፡ መቅደስ ፡ እንዘ ፡ የሐውር ፡ ቀርቡ ፡ ኀቤሁ ፡ አርዳኢሁ ፡ ወአርአይዎ ፡ ንድቀ ፡ ሕንጻሁ ፡ ለቤተ፡መቅደስ።

፪፤ ወአውሥአ፡እግዚእ፡ኢየሱስ፡ወይቤሎሙ፡ ትሬእዩኑ፡ዘንተ፡ኵሎ፡አማን፡እብለክሙ፡ ኢይትኀደግ፡ዝየ፡እብን፡ዲበ፡እብን፡ዘኢይ ትነሠት።

ድኅረ፡ወንጌል።

በሠለስቱ፡ሰዓት፡መዐልት፡ዘሠሉስ።

፩፤ እስመ፡ብዙኀ፡ጊዜ፡ይቤ፡ፈቀድኩ፡አስተጋ ብእሙ ፡ ለውሉድኪ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ከመ ፡ ዶሮሆ ፡ ዘታስተጋብእ ፡ ዕጕሊሃ ፡ ታሕተ ፡ ክነፊሃ።

፪፤ አነ ፡ አኀድግ ፡ ለክሙ ፡ ቤተክሙ ፡ በድወ ይኩን፡ መዝበረ ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር ፡ እምዮም።

፫፤ ወይትቀተሉ ፡ እምአይሁድ ፡ ምእት ፡ ወዕሥራ፡እልፍ፡በአፈ፡ሰይፍ።

፬፤ ወወረደ ፡ እምኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ መዐት ፡ ዐቢይ ፡ ወመርገም ፡ ከደነት ፡ ገጸቲሆሙ ። ክርስቶስ፡መድኃኒነ፡መጽአ፡ወሐመ፡ወበሕ ማማቲሁ፡አድኃነነ።

ጸልዩ ፡ በእንተ ፡ ጽንዐ ፡ ዛቲ ፡ በል ፤ ወኵሎ ፡ በከመ፡ሥርዓቱ፡ፈጽም።

## ምዕራፍ፡፳፪።

ትእዛዝ፤ወእምዝ፡ይትጋብኡ፡ካህናት፡ውስተ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ቅድስት ፡ በጊዜ ፡ ስድስቱ ፡

---

ወደድኩ፡እናንተ፡ግን፡እምቢ፡አላችሁ።

፴፰፤ እነሆ ፡ ቤታችሁ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ሁኖ ፡ ይቀርላ ችኋል።

፴፱፤ እውነት፡ እላችኋለሁ፤ በእግዚአብሔር፡ ስም፡ የሚመጣ፡ቡሩክ፡ነው፡እስከምትሉበት፡ጊዜ፡ ድረስ፡ከዛሬ፡ጀምሮ፡አታዩኝም፡እላችኋለሁ።

ምዕ፤፳፬፤፩–፪።

፩፤ ጌታ ፡ ኢየሱስ ፡ ከቤተ ፡ መቅደስ ፡ ወጥቶ ፡ ሲሄድ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ቀረብ ፡ ብለው ፡ የቤተ ፡ መቅደስን ፡ የሕንጻውን ፡ አሠራር ፡ አሳዩት።

፪፤ ጌታ፡ኢየሱስም፡ መልሶ፡ይህን፡ሁሉ፡ታያላ ችሁን ፡ እውነት ፡ እላችኋለሁ ፤ ደንጊያ ፡ በደንጊያ ፡ ላይ ፡ ሳይፈርስ ፡ አይቀርም ፡ አላቸው።

ማክሰኞ፡ከቀኑ፡በሦስት፡ሰዓት፡

ከወንጌል፡በኋላ፡የሚነበብ፡ይህ፡ነው።

፩፤ ኢየሩሳሌም ፡ ዶሮ ፡ ጫጩቶቿን ፡ ከክንፏ ፡ በታች፡እንደምትሰበስብ፡ልጆችሽን፡እሰበስ ባቸው፡ዘንድ፡ብዙ፡ጊዜ፡ወድጄ፡ነበር፡አለ።

፪፤ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከዛሬ ፡ ጀምሮ ፡ ቤታችሁን፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ አድርጌ ፡ እተወ ዋለሁ፤የፈረሰ፡ይሆን፡ዘንድ።

፫፤ ከአይሁድም፡አንድ፡ሚሊዮን፡ሁለት፡መቶ፡ ሺህ፡በሰይፍ፡ስለት፡ይገደላሉ፡አለ።

፬፤ ከእግዚአብሔር፡ዘንድም፡ታላቅ፡ቁጣ፡ወረደ፤ የርግማን፡ኀፍረትም፡ፊታቸውን፡ሸፈነቻቸው፤ መድኃኒታችን፡ክርስቶስ፡ ሰው፡ሁኖ፡መጥቶ፡ መከራ፡ተቀበለ፤በመከራውም፡አዳነን።

ጸልዩ፡በእንተ፡ጽንዐ፡ዛቲ፡በል፤ሁሉንም፡ እንደ፡ሥርዓቱ፡ፈጽም።

## ምዕራፍ፡፳፪።

ከቀኑ፡በስድስት፡ሰዓት፡ካህናቱ፡በቅድስት፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ይሰብሰቡ ፤ አስቀድሞ ፡

## በ፫፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሠሉስ።

ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሠሉስ፡ወይጸልዩ፡በከመ፡ቀዳሚ።
ወይበል፡መራሂ፡(በ፩)፡ስብሐት፡ለአብ።

ወእምዝ፡ይበሉ፡ለከ፡ኃይል።

ክፍል፡፩።
ምንባብ።

ዘሕዝቅኤል ፡ ነቢይ ፡ በረከቱ ፡ ትኩን ፡ ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

ምዕ፤፳፩፤፫–፲፯።

፫፤ ወተነበይ ፡ ለምድረ ፡ እስራኤል ፡ ወበል ፡
ከመዝ፡ይቤ፡አዶናይ፡እግዚአብሔር፡ናሁ፡
አነሥእ፡እዴየ፡ላዕሌኪ፡ወአወፅአ፡ለመጥባ
ሕትየ ፡ እምነ ፡ ቀቀባ ፡ ወእሤሩ ፡ እምኔኪ ፡
ጻድቀ፡ወኃጥአ።
፬፤ ወእሤርዎሙ ፡ ለኃጥአን ፡ ወለዓማፅያን ፡
እስመ ፡ አጥፋእኩ ፡ እምውስቴትኪ ፡ ኃጥአ ፡
ወዐማፄ ፡ ወከማሁ ፡ አነሥእ ፡ እዴየ ፡
ወአወፅእ፡መጥባሕትየ፡ላዕለ፡ኵሉ፡ዘነፍስ፡
እምጽባሕ፡እስከ፡ደቡብ።

፭፤ ወየአምሩ፡ኵሉ፡ዘነፍስ፡ከመ፡አነ፡እግዚአ
ብሔር፡ወአንሣእኩ፡እዴየ፡ወኢይመይጦ፡
እንከ።

፮፤ ወአንተ፡ወልደ፡ዕጓለ፡እመሕያው፡ብኪ፡በእ
ንተ፡ቅጥቃጤ፡ሐቌከ፡ወገዐር፡በሕማም፡እስከ፡
የሐብጥ፡ጐርዔከ፡በቅድመ፡አዕይንቲሆሙ።
፯፤ ወለእመ፡ይብሉከ፡ምንት፡ያበክየከ፡በሎሙ፡
በእንተ ፡ ዜና ፡ ዘይመጽእ ፡ ወይትቀጠቀጥ ፡
ልቡ ፡ ወይደክም ፡ ኵሉ ፡ እድ ፡ ወይትቀፃዕ ፡
ኵሉ፡ነፍስ፡ወኵሉ፡መንፈስ፡ውስተ፡ኵሉ፡
መሌሊቱ ፡ ይበኈብኍ ፡ ወይመግል ፡ ናሁ ፡
ይበጽሕ፡ወይከውንሂ፡ይቤ፡አዶናይ፡እግዚአ
ብሔር፡እግዚእ።
፰፤ ወነበበኒ፡እግዚአብሔር፡ወይቤለኒ።
፱፤ ወልደ ፡ ዕጓለ ፡ እመሕያው ፡ ተነበይ ፡ ወበል ፡
ከመዝ፡ይቤ፡አዶናይ፡እግዚአብሔር፡ወበል፡
ኲናት፡ብልሒ፡ወተምዕዒ፡ከመ፡ትርግዚ፡
ወትቅትሊ።

## ማክሰኞ፡መዓልት፡በ፫፡ሰዓት።

እንደተጻፈው፡እንደ፡ሥርዓቱ፡ይጸልዩ።

መሪው ፡ በአንድ ፡ ሃሌታ ፡ ስብሐት ፡ ለአብ፡ ይበል።

ለከ፡ኃይል፡ይበሉ።

ክፍል፡፩።
ምንባብ።

የነቢዩ ፡ የሕዝቅኤል ፡ በረከት ፡ ከእኛ፡ ጋራ፡ ለዘላለሙ፡ትኑር፡አሜን።

ምዕ፤፳፩፤፫–፲፯።

፫፤ ገኸር ፡ ፈጣሪ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ አለ፡
ብለህ ፡ በእስራኤል ፡ አገር ፡ ትንቢት፡ ተናገር፤
እነሆ ፡ በአንቺ ፡ እደ ፡ መዐቴን ፡ አነሣለሁ፤
ሾተሌንም፡ከሰገባዋ፡እመዛታለሁ፤ከአንቺም፡
ኃጢአተኛውንና፡ጻድቁን፡አጠፋለሁ።
፬፤ ዓመፀኞችንና ፡ ኃጢአተኞችን ፡ አጠፋለ
ዋለሁ ፤ ከአንቺ ፡ ዓመፀኛንና ፡ ኃጢአተኛን፡
አጥፍቻለሁና ፡ እንደዚሁ ፡ እደ ፡ መዐቴን፡
አነሣለሁ፤ዕውቀት፡ባለው፡ሰው፡ሁሉ፡ላይ፡
ከምሥራቅ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ደቡብ ፡ ድረስ፡
ሾተሌን፡እመዛለሁ።
፭፤ ዕውቀት፡ያላቸው፡ሰዎች፡ሁሉ፡እኔ፡እግዚአ
ብሔር ፡ እንደሆንሁ ፡ ያውቃሉ ፤ እደ፡
መዐቴንም፡አነሣለሁ፡እንግዲህ፡ወዲህ፡አላ
መልሰውም።
፮፤ አንተ ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ወገብህን ፡ አጉብጠህ፡
አልቅስ ፤ በፊታቸውም ፡ ጉሮሮህ ፡ እስኪዘጋ፡
ድረስ፡ጨኸኸ፡አልቅስ።
፯፤ ምን ፡ ያስለቅስሃል ፡ ቢሉህ ፡ ስለሚመጣው፡
ወሬ ፡ ነው ፡ በላቸው ፤ ልቡ ፡ ይደነግጣል፡
የሰውም፡ሁሉ፡ልጅ፡ይደክማል፤ሰው፡ሁሉ፡
ይጐብጣል፤የሰው፡ሁሉ፡ሰውነቱ፡ይሸታል፡
ይመግላል ፤ ፈጣሪ ፡ ገኸር ፡ እግዚአብሔር፡
እነሆ፡ይኸው፡ፈጥኖ፡ይደርሳል፤ይደረጋል፡
አለ።
፰፤ እግዚአብሔር፡እንዲህ፡ብሎ፡ነገረኝ።
፱፤ የሰው፡ልጅ፡ትንቢት፡ተናገር፤ፈጣሪ፡እግዚ
አብሔር ፡ እንዲህ ፡ በል ፡ አለኝ ፤ ጦር፡
ሆይ ፡ ተሳዪ ፤ ወግተሽ ፡ ትገድሊ ፡ ዘንድ፡
ተቆጭ።

## በ፯፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሠሉስ።

፲፡ ወብልሒ፡ከመ፡ትብርቂ፡ወአጥብዒ፡ከመ፡
ትቅትሊ፡ወከመ፡ታውድቂ፡ኵሎ፡ዕፀ።
፲፩፡ ወወሀባ፡ለጽኑዕ፡ከመ፡የአኅዛ፡በእዴሁ፡
ወበልሐት፡ኵናት፡ወአስተዳለውዋ፡ከመ፡
ይመጥውዋ፡ውስተ፡እደ፡ዘይረግዝ፡ባቲ።
፲፪፡ ወውዕ፡ወአውዩ፡ወልደ፡ዕጓለ፡እመሕያው፡
እስመ፡ከመዝ፡ይከውን፡ላዕለ፡ሕዝብየ፡
ወላዕለ፡ኵሉ፡መኳንንተ፡እስራኤል፡ወያፈል
ስዎሙ፡በኲናት፡ለሕዝብየ፡ወበእንተ፡
ዝንቱ፡ጥፋሕ፡በእደዊከ።
፲፫፡ እስመ፡በጽሐት፡መንሱት፡ወምንተ፡ኮኑ፡
ሕዝብ፡ዘርኅቁ፡ወኢሀለዉ።
፲፬፡ ይቤ፡አዶናይ፡እግዚአብሔር፡አንተ፡ወልደ፡
ዕጓለ፡እመሕያው፡ተነበይ፡ወጥፋሕ፡እዴከ፡
በዲበ፡እዴከ፡ወአመክዕባ፡ለኲናት፡
ወሠልሳ፡ ለኲናት፡ወአብድንት፡ብዙኅ፡
ወበኲናት፡ዘየዐቢ፡ቀትል።

፲፭፡ ወታደነግፆሙ፡ከመ፡ይጥፋእ፡ልቦሙ፡
ወይበዝኁ፡ድውያን፡በኀበ፡ኵሉ፡አናቅ
ጺሆሙ፡ወይትወሀቡ፡ለቀትል፡በኲናት፡
ወትበርቅ፡ቀትል።
፲፮፡ ወይመልሳ፡በመንገለ፡የማን፡ወጸጋም፡
በሕቁ፡በኀበ፡ተመይጠ፡ገጽከ።
፲፯፡ ወአነሂ፡እጠፍሕ፡እዴየ፡በዲበ፡እዴየ፡
ወእፌኑ፡መዐትየ፡አነ፡እግዚአብሔር፡
ዘነበብኩ።

ጥበበ፡ሲራክ፡በረከተ፡አምላኩ፡ተሀሉ፡
ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

ምዕ፤፬፡፳—፴፩።

፳፡ ተዐቀብ፡ጊዜሁ፡ወዑቅ፡ለእመሂ፡እኩይ፡
ወኢታድሉ፡በሐሰት፡በእንተ፡ነፍስከ።
፳፩፡ እስመ፡ቦ፡ዘበኀፍረት፡ይገብር፡ኃጢአተ፡
ወቦ፡ዘበኀፍረት፡ይገብር፡ጽድቀ፡ወይረክብ፡
ሞገሰ።

፳፪፡ ኢታድሉ፡ለገጽ፡እንዘ፡ላዕለ፡ነፍስከ፡
ይበጽሐከ፡ወኢትኀፈር፡ከመ፡ታውድቅ፡
ነፍስከ።
፳፫፡ ወኢትክልአ፡ነቢበ፡ቃሉ፡ለዘይትናገር።

## ማክሰኞ፡መዓልት፡በ፯፡ሰዓት።

፲፡ ብልጭ፡ትዪ፡ዘንድ፡ተሳዪ። ዕንጨቱንም፡
ሁሉ፡እንድትጥዪ፡ጨክኚ።
፲፩፡ በእጁ፡ይይዛት፡ዘንድ፡ለአርበኛው፡ሰው፡
ሰጣት፤ጦርም፡ተሳለች፤በሚወጋባት፡
ሰውም፡እጅ፡ይሰጧት፡ዘንድ፡አዘጋጇት።
፲፪፡ የሰው፡ልጅ፡ጩኽ፡ደንፋ፡በወገኖቼ፡ላይ፡
በእስራኤልም፡መኳንንት፡ሁሉ፡ላይ፡
እንዲህ፡ ይደረጋልና፤ወገኖችንም፡በጦር፡
ማርከው፡ይወስዱአቸዋልና፡ስለዚህ፡
በእጅህ፡አጨብጭብ።
፲፫፡ ጥፋት፡ደርሳለችና፡ከእኔ፡የራቁ፡ከእኔም፡
ጋራ፡የሌሉ፡ወገኖች፡ምን፡ሆኑ።
፲፬፡ ፈጣሪ፡እግዚአብሔር፡አንተ፡የሰው፡ልጅ፡
ትንቢት፡ተናገር፤እጅህን፡በእጅህ፡ላይ፡
አጨብጭብ፤ጦርን፡መልሰሽ፡መላልሰሽ፤
ውጊ፡በላት፤ጦርን፡ሦስት፡ጊዜ፡ውጊ፡በላት፤
ሬሳውም፡ብዙ፡ይሁን፤በጦርም፡ብዙ፡
ሰልፍ፡ተደረገ።
፲፭፡ ልባቸው፡ይጠፋ፡ዘንድ፡ታስደነግጣቸዋለች፤
ሕመምተኞችም፡በአደባባያቸው፡ይበዛሉ፤
በጦርም፡ለሰልፍ፡ይሰጣሉ፤ጦርም፡ቦግ፡ቦግ፡
ትላለች፤ሰልፉም፡እያነሰ፡ይሄዳል።
፲፮፡ ፊትህ፡በተመለሰበት፡ቦታ፡ጦሪቱንም፡ወደ፡
ግራና፡ወደቀኝ፡ፈጽሞ፡ይመልሳታል።
፲፯፡ እኔም፡እጄን፡በእጄ፡ላይ፡አጨበጭባለሁ፤
እኔ፡እግዚአብሔር፡የተናገርሁትን፡መዐቴን፡
አመጣለሁ።

በረከቱ፡ከእኛ፡ጋራ፡ለዘላለሙ፡ትኑርና፡
ጥበበኛው፡ሲራክ፡የተናገረው፡ይህ፡ነው፡
አሜን።

ምዕ፤፬፡፳—፴፩።

፳፡ ጊዜውን፡ጠብቅ፤ከክፉ፡ነገርም፡ተጠንቀቅ፤
ስለ፡ነፍስህ፡በሐሰት፡አታድላ።
፳፩፡ ሰውን፡አፍሮ፡ኃጢአትን፡የሚሠራ፡አለና፡
በማፈርም፡ጽድቅን፡የሚሠራና፡እውነትን
በመፍረድ፡በእግዚአብሔርና፡በሰው፡ዘንድ፡
ባለሟልነትን፡የሚያገኝ፡አለና።
፳፪፡ ጉዳት፡በራስህ፡ስለሚደርስብህ፡የሰው፡ፊት፡
አይተህ፡አታድላ፤ሰውነትህንም፡ታጠፋ፡
ዘንድ፡ሰውን፡አትፈር።
፳፫፡ የሚናገርን፡ሰው፡መናገሩን፡አትከልክለው።

Scanned by CamScanner

## በ፲፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘሠሉስ።

፳፬፤ እስመ፡እምቃሉ፡ይትዓወቅ፡ጥበቢሁ፡ወት ምህርቱ፡እምቃለ፡ልሳኑ።
፳፭፤ ወኢትትከሀድ፡በእንተ፡ጽድቅ፡ወተጋነይ፡ በእንተ፡ዘስሕትከ።
፳፮፤ ወኢትኀፈር፡ነጊረ፡ጌጋይከ፡ወኢትትኀየል፡ ውኂዘ፡ፈለግ።
፳፯፤ ወኢታትሕት፡ርእሰከ፡ለብእሲ፡አብድ፡ ወኢታድሉ፡ለገጸ፡ዐቢይ።
፳፰፤ እስከ፡ትበጽሕ፡ለሞት፡ተበዓስ፡በእንተ፡ ጽድቅ፡እስመ፡እግዚአብሔር፡አምላክከ፡ ይትበዓስ፡በእንቲአከ።
፳፱፤ ወኢትኩን፡ዝሉፈ፡በአፉከ፡ወኢትጸመም፡ ተግባረከ።
፴፤ ወኢትትአርወይ ፡ ከመ ፡ አንበሳ ፡ በውስተ ፡ ቤትከ ፡ ወኢታደንግፅ ፡ ነባ ሪከ።
፴፩፤ ወኢትስፋሕ፡እዴከ፡ለተለቅሖ፡ወሰበ፡ ለፈድዮ፡ኢትግባእ፡ትኅባዕ፡የማነከ።

ምዕ፤፭፡፩-፫።

፩፤ ወኢትክዓው፡ንዋየከ፡በከንቱ፡ወኢትበል፡ ኮንየ፡አከለኒ።
፪፤ ወኢትትሉ፡ግዕዘ፡ኃይለ፡ነፍስከ።
፫፤ ወኢትበል፡ኃያል፡አነ፡ወመኑ፡ይክለኒ፡ እስመ፡እግዚአብሔር፡በቀለ፡ይትቤቀል።

### ክፍል፡፪።
### ሃይማኖተ፡አበው።

ምዕ፤፹፱፤፩-፲፪።

፩፤ ይቤ፡ቅዱስ፡አባ፡ብንያሚ፡ሊቀ፡ጳጳሳት፡ ዘእለ፡እስክንድርያ፡በጦማረ፡መልእክቱ፡ ዘዐሠርቱ፡ ወስድስቱ፡እንዘ፡ያስተኀፍር፡ ዕልወተ ፡ አርዮሳውያን ፡ ወአቡሊናርዮሳ ውያን፡እለ፡ይብሉ፡ከመ፡መለኮተ እግዚአ ብሔር፡ቃል፡ሐማሚ፡ወመዋቲ።
፪፤ ንኩን፤ድልዋነ፡ይእዜ፡አ፡አኀውየ፡ወፍቁ ራንየ፡ለጾም፡ወለመልእክተ እግዚአብሔር፡ ወለኵሉ፡ምግባረ፡ሠናይ፡ዘምሉዕ፡ትሩፋት፡ ወፈድፋደሰ፡ለሃይማኖት፡እንተ፡ኢትጸንን፡

## ማክሰኞ፡መዓልት፡በ፲፡ሰዓት።

፳፬፤ ጥበቡ፡(ዕውቀቱ)፡ከቃሉ፡የተነሣ፡ትምህርቱም፡ ከአንደበቱ፡ንግግር፡የተነሣ፡ይታወቃልና።
፳፭፤ ጽድቅን ፡ አትቃወም ፤ ስለበደልከው፡ በደልም፡ንስሐ፡ገብተህ፡ተለማመጥ።
፳፮፤ ኃጢአትህንም፡መናገርን፡አትፈር፤የውኃ፡ ሙላትንም፡ተጋፍቼ፡እሻገራለሁ፡አትበል።
፳፯፤ ለሰነፍ፡ሰው፡ራስህን፡አታዋርድ፤የባለጸጋ ውንም፡ፊት፡አይተህ፡ፍርድ፡አታድላ።
፳፰፤ ስለ፡እውነት፡ለሞት፡እስክትደርስ፡ሁነህ፡ ተከራከር፤ፈጣሪህ፡እግዚአብሔር፡ስለአንተ ይከራከርልሃልና።
፳፱፤ በገዛ፡አፍህ፡አትነቀፍ፤ሥራህንም፡ቸል፡ አትበል።
፴፤ በቤትህም ፡ ውስጥ ፡ እንደ ፡ አንበሳ፡ አታስፈራ፤ የሚአስፈራ ፡ ነገርንም፡ ተናግረህ፡ቤተሰብህን፡አታስደንግጥ።
፴፩፤ ለመበደር፡እጅህን፡አትዘርጋ፤በመክፈልም፡ ጊዜ፡እጅህን፡አትመልስ።

ምዕ፤፭፡፩-፫፤

፩፤ ገንዘብህን ፡ በከንቱ ፡ አትበትን ፤ ገንዘብ፡ የቀረው፡በቃኝ፡አትበል።
፪፤ ለሰውነትህ ፡ ለባሕርይዋ ፡ የሚስማማትን፡ ሁሉ፡ላድርግ፡አትበል።
፫፤ ኃይለኛ፡ነኝ፡ማን፡ይችለኛል፡አትበል፤ይህን፡ በማለትህ፡እግዚአብሔር፡ተበቅሎ፡ያጠፋልና።

### ክፍል፡፪።
### የአባቶች፡ሃይማኖት።

ምዕ፡፹፱፡፩-፲፪።

፩፤ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ባሕርዩ ፡ የሚ ታመም፡የሚሞት፡ነው፡የሚሉ፡የአቡሊናር ዮሳውያንንና ፡ የአርዮሳውያንን ፡ ክህደት፡ ነቅፎ ፡ ዘልፎ ፡ በጻፈበት ፡ የእስክንድርያ፡ ሊቀ፡ጳጳሳት፡ቅዱስ፡አባ፡ብንያሚ፡እንዲህ፡ አለ።
፪፤ ወንድሞቼ፡ወዳጆቼ፡አሁንም፡ለጾም፡እግዚ አብሔርን፡ለማገልገል፡ትሩፋትን፡ለተሞላ፡ ለበጎ ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ ይልቁንም ፡ ጽኑነት፡ ላሌለባት፡በአካል፡ሦስት፡በባሕርይ፡አንድ፡

## በ፮፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሠሉስ።

ዘሥሉስ፡ቅዱስ።

፫፤ ወንበል ፡ ነአምን ፡ በአብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ሥሉስ ፡ ዕሩይ ፡ ስቡሕ ፡ ወቅዱስ ፡ ሠለስቱ ፡ አካላት ፡ ዕሩያን ፡ በኵሉ ፡ ግብር ፡ በምግባር ፡ ወበንባብ ፡ ሠለስቱ ፡ ገጻት ፡ ወአሐዱ ፡ መለኮት ፡ ወአሐዱ ፡ አምሳል ፡ ወአሐቲ፡ሥምረት።

፬፤ ወይደሉ ፡ ንትናገር ፡ በእንተ ፡ አሐዱ ፡ ዘእምቅድስት ፡ ሥላሴ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ዘኮነ ፡ ሥጋ ፡ በአካሉ ፡ ባሕቲቱ ፡ እንበለ ፡ ፍልጠት ፡ ወኢቱስሕት ፡ እምሥጋሃ ፡ ወደማ ፡ ለወላዲተ ፡ አምላክ ፡ ቅድስት ፡ ማርያም ፡ እንተ ፡ ይእቲ ፡ ድንግል ፡ በኵሉ ፡ መዋዕል ፡ ወዝንቱ ፡ ሥጋ ፡ ዘይትዔረየነ፡ሐማሚ፡ዘከማነ፡ወቦቱ፡ነፍስ፡ ነባቢት፡ወለባዊት።

፭፤ ወአብዳን ፡ ሰብእ ፡ እለ ፡ ኢይሌብዉ ፡ ይትዐቀፉ ፡ ፈድፋደ ፡ በእንተ ፡ ዘጸሐፍነ ፡ በዘኀለፈ ፡ ዓም ፡ በጦማረ ፡ መልእክት ፡ ዘዐሥርቱ ፡ ወኀምስቱ ፡ ክፍል ፡ እምነገረ ፡ ቅዱስ፡ጎርጎርዮስ፡ነባቤ፡መለኮት፡ዘይብል፡ እስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ሐማሚ ፡ በሥጋሁ፡እንዘ፡ኢየሐምም፡በመለኮቱ።

፮፤ ወከመዝ፡በካልእ፡ክፍል፡እምነገረ፡ቅዱስ፡ ቄርሎስ ፡ ዘይብል ፡ እግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ሐመ፡ በሥጋ ፡ ወአኮ ፡ በህላዌ ፡ መለኮት ፡ ዘከመ፡ ሐፂን ፡ አው ፡ ዘከመ ፡ ካልእ ፡ አመ ፡ ይሳተፍ ፡ ምስለ ፡ ኃይለ ፡ እሳት ፡ ይትዌከፍ ፡ እሳተ ፡ ወይመልእ ፡ እምነ ፡ ላህቡ ፡ ወካዕበ ፡ አመ ፡ ይዘበጥ ፡ ሐፂን ፡ በሴፌልያ ፡ አው ፡ በካልእ ፡ በዲበ ፡ ሐፂን ፡ ይወድቅ ፡ ዝብጠት ፡ ወህላዌ ፡ እሳትሰ ፡ ኢይትረከብ ፡ ግሙራ ፡ ለዘቢጥ ፡ ከመዝ ፡ ነአምን ፡ ወንብል ፡ ከመ ፡ ወልደ፡እግዚአብሔር፡ሐመ፡በሥጋ፡ወአኮ፡ በህላዌ፡መለኮት።

፯፤ ወሶበ ፡ ሰምዑ ፡ እልክቱ ፡ አብዳን ፡ ዘንተ ፡ ተቃረኑነ ፡ ወይብሉ ፡ እስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ሐመ ፡ ወሞተ ፡ በመለኮት ፡ ምስለ ፡ ሥጋ ፡ ወእሙንቱኒ ፡ ህጉላን ፡ ይኄልዩ ፡ ንባበ ፡ አርዮሳ

## ማክሰኞ፡መዓልት፡በ፮፡ሰዓት።

ብለን ፡ ለምናምንባት ፡ ሃይማኖት ፡ የተዘጋጀን፡እንሁን።

፫፤ በአካል ፡ ሦስት ፡ በባሕርይ ፡ አንድ ፡ በሚሆኑ ፡ ፈጽመው ፡ በተመሰገኑ ፡ በአብ ፡ በወልድ ፡ በመንፈስ፡ቅዱስ፡እናምናለን፡እንበል፡ሦስት፡ አካላት፡በሥራው፡ሁሉ፡በማድረግ፡በመናገር፡ አንድ ፡ ናቸው ፤ በገጽ ፡ ሦስት ፡ ናቸው ፤ በመለኮት፤በሥራ፡በፈቃድ፡አንድ፡ናቸው።

፬፤ በዘመኑ ፡ ሁሉ ፡ ድንግል ፡ ከምትሆን ፡ አምላክን ፡ ከወለደች ፡ ከቅድስት ፡ ማርያም ፡ ነፍስን ፡ ሥጋን ፡ ነሥቶ ፡ ያለ ፡ መቀላቀል ፡ ያለመለየት ፡ በተለየ ፡ አካሉ ፡ ሥጋን ፡ የተዋሐደውን ፡ ከሦስቱ ፡ አካላት፡ የአንዱን ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃልን ፡ ነገር፡ ልንናገር ፡ ይገባል ፤ ይኸውም ፡ እኛን ፡ የሚመስል ፡ እንደ ፡ እኛ ፡ የሚታመም ፡ የምታውቅ ፡ የምትናገር ፡ ነፍስ ፡ ያለችው፡ሥጋ፡ነው።

፭፤ የማያስተውሉ፡አላዋቆች፡ሰዎች፡አንድነትን፡ ሦስትነትን ፡ የተናገረ ፡ ጎርጎርዮስ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ በመለኮቱ ፡ ሕማም ፡ የሌለበት ፡ ሲሆን፤በሥጋ፡የሚታመም፡ነው፡ሲል፡ከተናገረው ፡ አምጥተን ፡ በዐሥራ ፡ አምስተኛው ፡ ክፍል ፡ መልእክት ፡ በአለፈው ፡ ዘመን ፡ ስለ ፡ ጻፍነው፡ነገር፡ፈጽመው፡ይጠራጠራሉ።

፮፤ እንዲሁም ፡ በሌላ ፡ ክፍል ፡ ብረት ፡ ወይም ፡ መዳብ ፡ ከእሳት ፡ ባሕርይ ፡ በተዋሐደ ፡ ጊዜ ፡ እሳትን ፡ እንዲመስል ፤ ሙቀቱን ፡ ብርሃኑን ፡ ግለቱን ፡ ገንዘብ ፡ እንዲአደርግ ፡ ዳግመኛም ፡ ብረት ፡ በመዶሻ ፡ ወይም ፡ በሌላ ፡ ነገር ፡ በተመታ፡ጊዜ፡የመዶሻ፡ኃይል፡በብረት፡ላይ፡ እንዲወድቅ ፡ የእሳት ፡ ባሕርይ ፡ ግን ፡ እንዳይመታ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ በመለኮት ፡ ያይደለ ፡ በሥጋ ፡ ታመመ ፡ ብሎ ፡ ከተናገረው ፡ ከቅዱስ፡ቄርሎስ፡ቃል፡እንዲህ፡ተቀብለን፡እናምናለን፤የእግዚአብሔር፡ልጅም፡በመለኮት፡ ያይደለ፡በሥጋ፡እንደታመመ፡እንናገራለን።

፯፤ እነዚያ፡አላዋቆችም፡ይህን፡በሰሙ፡ጊዜ፡እግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ከሥጋ ፡ ጋር ፡ በመለኮት፡ ታመመ ፡ ሞተ ፡ ብለው ፡ ተከራከሩን ፤ አእምሮን፡ያጡ፡እነዚያም፡የአርዮስ፡የአቡሊ

በ፮፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሠሉስ።

ውያን ፡ ወአቡሊናርዮሳውያን ፡ ወገናዳቢሳ
ውያን።
፰፤ ወኢሰምዕዎ ፡ ለቅዱስ ፡ ሐዋርያ ፡ ወኢለአ
በዊነ ፡ ለባስያነ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወባሕቱ ፡
ነአምሮሙ፡ከመ፡እሙንቱ፡ስሕቱ፡እምነ፡
ጽድቅ ፡ ፈድፋደ ፡ ወኢፈተዉ ፡ ያንሶስዉ ፡
በፍኖተ፡መንግሥት፡አላ፡በፍኖተ፡በድው፡
ዘምሉዕ፡አሥዋከ፡ይቤ፡ጴጥሮስ፡ሊቀሙ፡
ለሐዋርያት፡እስመ፡ክርስቶስ፡ ሐመ ፡ በእን
ቲአነ ፡ በሥጋ ፡ እንዘ ፡ ሕያው ፡ ውእቱ ፡
በመንፈስ።
፱፤ ወአትናቴዎስ ፡ ሐዋርያዊ ፡ ይቤ ፡ በራ
ብዕ ፡ ድርሳኑ ፡ እንዘ ፡ ይትዋሥአሙ ፡
ለአርዮሳውያን ፡ በዝንቱ ፡ ኢይቤ ፡ ሐዋ
ርያ ፡ ከመ ፡ ክርስቶስ ፡ ሐመ ፡ መለኮቱ ፡
አላ ፡ ይቤ ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ ሐመ ፡ በእ
ንቲአነ ፡ በሥጋ ፡ ከመ ፡ ናእምር ፡ እስመ ፡
ሕማም ፡ ዘሥጋ ፡ እሙን ፡ ወአኮ ፡ ውእቱ ፡
ዘቃል፡በህላዌሁ።
፲፤ ወካዕበ ፡ አብ ፡ ኤጲፋንዮስ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡
ዘቆጵሮስ፡ጸሐፈ፡ኀበ፡ዕልወተ፡አቡሊናርዮ
ሳውያን ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ እመሰ ፡ ክርስቶስ ፡
ሞተ ፡ በእንቲአነ ፡ አኮ ፡ በመለኮቱ ፡ ዘሞተ ፡
አላ፡ ሞተ ፡ በሥጋ ፡ በከመ ፡ ጽሑፍ ፡ ከመ ፡
ውእቱ፡ሞተ፡በሥጋ፡እንዘ፡ሕያው፡ውእቱ፡
በመንፈስ ፡ ወንትአመን ፡ ቦቱ ፡ በመንከር ፡
ከመ ፡ ውእቱ ፡ ሐመ ፡ ዘበአማን ፡ እንዘ ፡
ኢየሐምም ፡ እሙነ ፡ ኢሐመ ፡ መለኮት ፡
በምንትኒ ፡ እስመ ፡ ውእቱ ፡ ኢሐማሚ ፡
ወኢመዋቲ ፡ ወኢይትዌለጥ ፡ ወዕሩይ ፡
ውእቱ፡ምስለ፡አብ።
፲፩፤ ወካዕበ፡ይቤ፡ጠቢብ፡ቄርሎስ፡በአውሥአቱ፡
ዘጸሐፎ ፡ በውስተ ፡ ዐሠርቱ ፡ ወክልኤቱ ፡
ክፍል ፡ እንዘ ፡ ያስተ ኀፍር ፡ ክሕደተ ፡ ታእድ
ሪጣስ፡እስመ፡ውእቱ፡ሐመ፡በዝንቱ፡ሥጋ፡
በፈቃዱ ፡ እንዘ ፡ ለሊሁ ፡ መድኃኔ ፡ ኵሉ ፡
ፍጡራን፡ወንትአመን፡ከመዝ፡ከመ፡ውእ
በጸጋ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጥዕመ ፡ ሞተ ፡ በሥጋ ፡

ማክሰኞ፡መዓልት፡በ፮፡ሰዓት።

ናርዮስ ፡ የገናዳቢስ ፡ ወገኖች ፡ የሚናገሩትን፡
ይናገራሉ።
፰፤ ቅዱሱን፡ሐዋርያ፡ጴጥሮስን፡አልሰሙትም፡እግ
ዚአብሔር፡ያደረባቸው፡አባቶቻችንንም፡አልሰ
ሟቸውም፤ ነገር ፡ ግን ፡ እነርሱ ፡ ከውነተኛው፡
ሃይማኖት ፡ ፈጽመው ፡ እንደወጡ ፡ እናውቃቸ
ዋለን፤ በንጉሥ ፡ ጥርጊያ ፡ ጐዳና ፡ ይሄዱ፡ዘንድ፡
አልወደዱም፤እሾኽን፡የተመላ፡ዱርን፡ጥሰው፡
መሄድን ፡ ወደዱ ፡ እንጂ ፡ የሐዋርያት ፡ አለቃ፡
ጴጥሮስ፡ክርስቶስ፡በመለኮት፡ ሕማም፡የሌለበት፡
ሲሆን፡ስለ፡እኛ፡በሥጋ፡እንደ፡ታመመ፡ተናገረ፡
፱፤ ሐዋርያዊው ፡ አትናቴዎስም ፡ በአራተኛው፡
ድርሳኑ ፡ ጴጥሮስ ፡ የተናገረውን ፡ ጠቅሶ፡የአር
ዮስን ፡ ወገኖች ፡ ሲከራከራቸው ፡ ክርስቶስ፡
በመለኮቱ፡እንደታመመ፡ሐዋርያ፡ጴጥሮስ፡አል
ተናገረም፤ ሕማም፡በእውነት፡የሥጋ፡ገንዘብ፡
እንደሆነ ፡ በባሕርየ ፡ መለኮቱ ፡ ለቃል ፡ ገንዘቡ፡
እንዳይደለ፡እናውቅ፡ዘንድ፡እርሱ፡ስለ፡እኛ፡
በሥጋ፡እንደ፡ታመመ፡ተናገረ፡እንጂ፡አለ።
፲፤ ዳግመኛ፡የቆጵሮስ፡ኤጲስቆጶስ፡አባት፡ኤጲ
ፋንዮስ ፡ በመለኮት ፡ ሕያው ፡ ሲሆን ፡ በሥጋ፡
ሞተ ፡ ተብሎ ፡ እንደ ፡ ተጻፈ ፡ ክርስቶስ ፡ ስለ፡
እኛ ፡ ቢሞትም ፡ በሥጋ ፡ ሞተ ፡ እንጂ፡
በመለኮት ፡ የሞተ ፡ አይደለም፤ በእውነት፡
ሕማም ፡ የሌለበት ፡ ሲሆን ፡ በእውነት ፡ እንደ፡
ታመመ ፡ በድንቅ ፡ ሥራው ፡ እናምንበታለን፤
መለኮት ፡ በምንም ፡ በምን ፡ አልታመም፤
ሕማም ፡ ሞት ፡ የሌለበት ፡ ነውና ፡ አይለወ
ጥምና ፡ ከአብ ፡ ጋራም ፡ አንድ ፡ ነውና ፡ ብሎ፡
የአቡሊናርዮስን ፡ ወገኖች፡ ክሕደት ፡ ወደ
ያዙ፡ሰዎች፡ጻፈ።
፲፩፤ ዳግመኛ ፡ ብልህ ፡ ቄርሎስ ፡ የታእድሪጣስን፡
ክሕደት፡ነቅፎ፡ዘልፎ፡በዐሥራ፡ሁለተኛው፡
ክፍል ፡ በጻፈው ፡ ምላሹ ፡ ፍጡራንን ፡ ሁሉ፡
የሚአድን ፡ ሲሆን ፡ በፈቃዱ ፡ በዚህ ፡ ሥጋ፡
ታመመ ፡ አለ፤ ሐዋርያው ፡ ጳውሎስ ፡ እንደተ
ናገረ ፡ ዳግመኛም ፡ ጴጥሮስ ፡ ክርስቶስ፡
በመለኮቱ ፡ ያይደለ ፡ ስለ ፡ እኛ ፡ በሥጋ ፡ ሞተ፡

Scanned by CamScanner

## በ፮፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘሠሉስ።

በእንተ፡ኵሉ፡በከመ፡ይቤ፡ጳውሎስ፡ቅዱስ፡ሐዋርያ፡ወዓዲ፡በከመ፡ስምዐ፡ኮነ፡ጴጥሮስ፡በጥበቡ፡ወይቤ፡እስመ፡ክርስቶስ፡ሐመ፡በእንቲአነ፡በሥጋ፡ወአኮ፡በመለኮቱ፡ወካዕበ፡ይቤ፡ዝንቱ፡ጠቢብ፡ቄርሎስ፡በካልእ፡ድርሳኑ፡እስመ፡ውእቱ፡በጸጋ፡እግዚአብሔር፡ጥዕመ፡ሞተ፡በሥጋ፡በእንተ፡ኵሉ።

፲፪ ኢይትሀበል፡መኑሂ፡ከመ፡ንሕነ፡ንወድቅ፡በኀሊና፡ርኩስ፡አው፡ንኄሊ፡ግሙራ፡አው፡ናወሥእ፡ቃለ፡በዘይብሉ፡እልክቱ፡ከመ፡ህላዌ፡መለኮት፡ምስለ፡ሥጋ፡ሐመ።

በረከቶሙ፡ለእሉ፡ቅዱሳን፡መምህራን፡የሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

### እመጽሐፈ፡ስንክሳር።

፩ በስመ፡አብ፡ወወልድ፡ወመንፈስ፡ቅዱስ፡አሐዱ፡አምላክ፡እመ፡ዕሥራ፡ወረቡዑ፡ለመጋቢት፡በዛቲ፡ዕለት፡ካዕበ፡ተጋብኡ፡ማኅበረ፡አይሁድ፡ውስተ፡ቤተ፡ቀያፋ፡ሊቀ፡ካህናት።

፪ ወተማከሩ፡ላዕለ፡እግዚእ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ሎቱ፡ስብሐት፡ከመ፡ይቅትልዎ፡ሣህሉ፡ወምሕረቱ፡የሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

### ምንተኑ፡በል።

ተአምሪሃ፡ለእግዝእትነ፡ቅድስት፡ድንግል፡በክልኤ፡ማርያም፡ወላዲተ፡አምላክ፡ጸሎታ፡ወበረከታ፡የሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

፩ ወሀለወት፡አሐቲ፡ብእሲት፡እምዐበይተ፡ሀገረ፡ቂሳርያ።

፪ ወኮነት፡ባዕልተ፡በሕቁ፡በወርቅ፡ወበብሩር፡ወበንዋየ፡ዝንቱ፡ዓለም፡ኀላፊ፡ወይእቲ፡ኮነት፡ፅንስተ።

፫ ወሶበ፡በጽሐ፡ዕለተ፡ወሊዶታ፡ተአስረ፡ማኅፀና፡ወበጽሐት፡ኀበ፡ዐቢይ፡ሡንኬ፡እስከ፡ለሞት።

፬ ወአበዊሃሰ፡ጸርዋ፡ላዕለ፡ዐራት፡ወሖሩ፡ኀበ፡ቤተ፡ክርስቲያን፡ዘእግዝእትነ፡ቅድስት፡ድንግል፡በክልኤ፡ማርያም፡

## ማክሰኞ፡መዓልት፡በ፮፡ሰዓት።

ብሎ፡በሃይማኖቱ፡እንደመሰከረ፡እርሱ፡በእግዚአብሔር፡ቸርነት፡ለሁሉ፡ቤዛ፡ሆኖ፡በሥጋ፡እንደ፡ሞተ፡እንዲህ፡እናምናለን፤ዳግመኛም፡ይህ፡ብልህ፡ቄርሎስ፡በሁለተኛ፡ድርሳኑ፡እርሱ፡በእግዚአብሔር፡ቸርነት፡ስለ፡ሁሉ፡ቤዛ፡ሆኖ፡በሥጋ፡ሞተ፡አለ።

፲፪ እኛ፡በጽኑ፡ክሕደት፡እንድንያዝ፡ወይም፡ፈጽመን፡እንድናስብ፡ወይም፡የመለኮት፡ባሕርይ፡ከሥጋ፡ጋር፡ታመመ፡ብለው፡እነዚያ፡የሚናገሩትን፡እንደምንናገር፡አድርጎ፡ይናገርብን፡ዘንድ፡ማንም፡አይድፈር።

የእነዚህ፡የከበሩ፡መምህራን፡በረከታቸው፡ለዘላለሙ፡ይደርብን፤አሜን።

### ከስንክሳር፡መጽሐፍ።

፩ አንድ፡አምላክ፡በሆነ፡በአብ፡በወልድ፡በመንፈስ፡ቅዱስ፡ስም፡መጋቢት፡ሃያ፡አራት፡በዚች፡ቀን፡በሊቀ፡ካህናቱ፡በቀያፋ፡ቤት፡የአይሁድ፡ማኅበር፡ሁለተኛ፡ተሰበሰቡ።

፪ ይገድሉት፡ዘንድ፡ምስጋና፡ይግባውና፤በጌታ፡በኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ላይም፡ተማከሩ። ይቅርታው፡ቸርነቱ፡ከእኛ፡ጋራ፡ለዘላለሙ፡ይኑር፡አሜን።

### ምንተኑ፡በል።

ልመናዋ፡በረከቷ፡ከእኛ፡ጋራ፡ለዘላለሙ፡ይኑርና፡አምላክን፡የወለደች፡በሁለት፡ወገን፡ድንግል፡የሆነች፡እመቤታችን፡ክብርት፡ማርያም፡ያደረገችው፡ተአምር፡ይህ፡ነው።

፩ ከቂሳርያ፡ሀገር፡ከታላላቆች፡ሰዎች፡ወገን፡የሆነች፡አንዲት፡ሴት፡ነበረች።

፪ እርሷም፡በዚህ፡በኀላፊው፡ዓለም፡ገንዘብ፡በወርቅ፡በብር፡እጅግ፡የበለጸገች፡ናት፡እሷም፡ጸንሳ፡ነበረች።

፫ የመውለጃዋም፡ቀን፡በደረሰ፡ጊዜ፡ማሕፀኗ፡ታሰረ፤ለሞት፡ወደሚአበቃ፡ታላቅ፡ሥቃይም፡ደረሰች።

፬ ወላጆቿ፡ግን፡በአልጋ፡ላይ፡ተሸከመው፡በድንጋሌ፡ሥጋ፡በድንጋሌ፡ነፍስ፡ወደ፡ድንግል፡ወደ፡ሆነች፡ወደ፡ጸናች፡የአምላክ፡እናት፡

## በ፲፩፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘሠሉስ።

ወላዲተ፡እምላክ።

፩፡ ወሶበ ፡ ቀርበ ፡ ጎበ ፡ ጥንተ ፡ እፍእ ፡ ተሀውከ ፡ እማዑቲሃ ፡ ወወለደት ፡ ወልደ ፡ ተባዕተ።

፪፡ ወእበዊሃኒ ፡ ተፈሥሑ ፡ ዐቢየ ፡ ፍሥሐ ፡ ወእብዝኑ ፡ ሰብሐ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ወለወላዲቱ ፡ ድንግል ፡ ሰአሊተ ፡ ምሕረት ፡ ለውሉደ፡ ዕጓለ ፡ እመሕያው ፡ እግዝእትነ ፡ ቅድስት ፡ ድንግል፡በክልኤ፡ማርያም፡ወላዲተ፡እምላክ።

፫፡ ወገብሩ ፡ ዐቢየ ፡ ምጽዋተ ፡ ለነዳያን ፡ ወለጎጡእን።

፬፡ ወወሀቡ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወርቀ ፡ ወብሩረ፡ በስማ ፡ ለእግዝእትነ ፡ ቅድስት ፡ ድንግል ፡ በክልኤ ፡ ማርያም ፡ ወላዲተ ፡ እምላክ።

ጸሎታ፡ወበረከታ፡የሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ጥዑመ፡ስም፡በል።

ተአምር፡ወመንክር፡ዘገብረ፡እግዚእነ፡ወአምላክነ፡ወመድኃኒነ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ነገረ፡ፍትሕ፡ዘገብረ፡በብእሲት፡ዘማዊት፡ሣህሉ፡ወምሕረቱ፡የሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

፭፡ ወእንዘ፡ሀሎ፡እግዚእነ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ኢየሩሳሌም ፡ በእሐቲ ፡ ዕለት ፡ ተጋብኡ ፡ ጎቤሁ፡ሊቃውንተ፡አይሁድ፡ወጸሐፍቶሙ፡ወሐራሆሙ።

፮፡ ወይቤልዎ፡ንሕነ፡ነአምር፡ከመ፡እምኀበ፡እግዚአብሔር፡መጻእከ፡ወኵሉ፡ዘትገብር፡ግብረ፡እግዚአብሔር፡ውእቱ።

፯፡ ወአቀሙ፡ቅድሜሁ፡ብእሲተ፡ወይቤልዎ፡እስመ ፡ ዛቲ ፡ ብእሲት ፡ ዘማዊት ፡ ወእሉ ፡ ሰብእ፡ ይከውኑ ፡ ስምዓ ፡ ላዕሌሃ ፡ ወአንተ ፡ ፍታሕ፡በከመ፡ሕግ፡ዘይደሉ፡ላዕሌሃ፡እስመ፡አንተ፡ኰናኒሆሙ፡ለእስራኤል።

፰፡ ወሶበ ፡ ሰምዐ ፡ እግዚእ ፡ ኢየሱስ ፡ ዘንተ ፡ እምኔሆሙ ፡ ነጸራ ፡ ለብእሲት ፡ እንተ ፡ አብጽሕዋ ፡ ጎቤሁ ፡ ወእእመረ ፡ ለእመ ፡ ኢፈትሐ ፡ ላዕሌሃ ፡ በከመ ፡ ሕጉ ፡ ለሙሴ ፡

## ማክሰኞ፡መዓልት፡በ፲፩፡ሰዓት።

ቅድስት ፡ እመቤታችን ፡ ማርያም ፡ ቤተክርስቲያን፡ወሰደች።

፩፡ ወደ፡ውጭው፡በር፡በቀረቡ፡ጊዜ፡እንጀቷ፡ተናውጾ ፡ ወንድ ፡ ልጅን ፡ ወለደች ፡ ወላጆቿም፡እጅግ፡ደስ፡አላቸው።

፪፡ እግዚአብሔርንም ፡ አብዝተው ፡ አመሰገኑ፡ ለሰው፡ልጅ፡ሁሉ፡ምሕረትን፡የምትለምን፡በድንጋሌ፡ሥጋ፡በድንጋሌ፡ነፍስ፡የጸናች፡የአምላክ ፡ እናት ፡ ክብርት ፡ እመቤታችን፡እናቱ፡ድንግል፡ማርያምንም፡አመሰገኑአት፡

፫፡ ለድኆችና ፡ ለጦም ፡ አዳሪዎች ፡ ታላቅ፡ምጽዋትን፡አደረጉ።

፬፡ በሁለት፡ወገን፡ድንግል፡በሆነች፡አምላክን፡በወለደች ፡ በክብርት ፡ እመቤታችን ፡ ማርያም፡ስም፡ለቤተ፡ክርስቲያን፡ወርቅንና፡ብርንም፡ሰጡ።

ልመናዋ ፡ በረከቷ ፡ ከእኛ ፡ ጋራ ፡ ለዘላለሙ፡ይኑር።

ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ጥዑመ፡ስም፡በል።

ይቅርታውና፡ቸርነቱ፡ከኛ፡ጋራ፡ለዘላለሙ፡ይኑርና ። በአንዲት ፡ አመንዝራ ፡ ሴት ፡ ላይ፡ስለተደረገው፡የፍርድ፡ነገር፡ጌታችን፡ፈጣሪያችንና፡መድኃኒታችን፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ያደረገው፡ድንቅ፡ተአምር፡ይህ፡ነው።

፭፡ ጌታ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስም ፡ በኢየሩሳሌም፡ሳለ ፡ የአይሁድ ፡ ሊቃውንት ፡ ጸሐፍቶቻቸውና ፡ ጭፍሮቻቸውም ፡ ወደ ፡ እርሱ፡በአንዲት፡ቀን፡ተሰበሰቡ።

፮፡ የምትሠራው፡ሁሉ፡የእግዚአብሔር፡ሥራ፡ነውና፡አንተ፡ከእግዚአብሔር፡ዘንድ፡እንደ፡መጣህ፡እኛ፡እናውቃለን፡አሉት።

፯፡ በፊቱም፡ሴቲቱን፡አቁመው፡ይህቺ፡ሴት፡ስትሰስን፡ተገኝታለችና፡እነዚህም፡ሰዎች፡በእርሷ፡ላይ፡ምስክሮች፡ናቸውና፡አንተም፡እንደሕጉ፡በእርሷ፡ላይ፡ፍረድ፤አንተ፡የእስራኤል፡ፈራጅ፡ነህና።

፰፡ ጌታ፡ኢየሱስም፡ከእነርሱ፡ይህን፡በሰማ፡ጊዜ፡ወደእርሱ፡ያመጡአትን፡ሴት፡ተመለከታት፡እንደ፡ሙሴ፡ሕግ፡በእርሷ፡ላይ፡ባይፈርድ፡እን ደሚነቅፉት ፡ ትምህርቱንም ፡ ሐሰት ፡ ነው፡

Scanned by CamScanner

በ፱፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘሠሉስ።

ወያስተሐቅርዎ፡ወያሔስዉ፡ቃሎ።

፭ ውእቱሰ፡አድነነ፡ርእሶ፡ውስተ፡ምድር፡
ወአኀዘ፡ይጽሐፍ፡በአጽባዕቱ፡ዲበ፡ምድር፡
ኃጢአተ፡ኵሎሙ።

፮ ወእምዝ ፡ አልዓለ ፡ ርእሶ ፡ ኀቤ
ሆሙ ፡ ወይቤሎሙ ፡ ድልወት ፡ ይእቲ ፡
ከመ ፡ ትትወገር ፡ በእብን ፡ ዘበሕግ ፡
እስከ፡ትመውት፡ ሰድዋ፡ ይእዜሰ፡ መካነ፡
ኵነኔ፡ ወዓዲ፡ አምጽእዋ፡ ኀቤየ፡ ውስተ፡
ዛቲ ፡ መካን፡ ከመ ፡ ትገርዋ ፡ በቅ
ድሜየ።

፯ ወወሰድዋ፡ለይእቲ፡ብእሲት፡መካነ፡ኵነኔ፡
ወአስተጋብኡ ፡ ላቲ ፡ አእባነ ፡ ወእምዝ ፡
ተመይጡ፡ኀበ፡እግዚእ፡ኢየሱስ።

፰ ወካዕበ፡ደነነ፡ውስተ፡ምድር፡ወጸሐፈ፡በአ
ጽባዕቱ፡እንዘ፡ይብል፡ኃጢአቱ፡ለዕገሌ፡
ከመዝ፡ወከመዝ፡ለዕገሌ፡ኃጢአቱ።

፱ ወሶበ፡ርእዩ፡ዘንተ፡ዘለፋ፡ወፅኡ፡ኵሎሙ፡
ወአንሥአ ፡ እግዚእ ፡ ኢየሱስ ፡ ርእሶ ፡
ወርእዮሙ፡ወኢረከበ፡መነሂ፡እምሰብአ፡
አይሁድ ፡ ዘእንበለ ፡ ብእሲት ፡ ባሕቲታ ፡
ዘአቀምዋ፡ውስተ፡መካነ፡ኵነኔ።

፲ ወይቤላ ፡ እግዚእ ፡ ኢየሱስ ፡ አ ፡ ብእሲቶ ፡
አይቴ ፡ ሀለዉ ፡ እለ ፡ ይኴንኑኪ ፡ ወትቤሎ ፡
እግዚእየ ፡ ጐዩ ፡ እምኵነኔከ ፡ ንጹሕ ፡
ተኀፈሮሙ።

፲፩ ወይቤላ፡እግዚእ፡ኢየሱስ፡እምይእዜሰ፡ዐቂ፡
ርእሰኪ፡ኢትአብሲ፡ዳግመ፡ከመ፡ኢይርከብኪ፡ኵነኔ፡ዘአልቦቱ፡መልክእ።ወአንሰ፡
ኀደጉ፡ለኪ፡ኃጢአተኪ።

፲፪ ወወፅአት፡ይእቲ፡ብእሲት፡ወቦአት፡ሀገረ፡
ወነገረት ፡ ለሰብእ ፡ ዜናሁ ፡ ወበእንቲአሁ ፡
አምኑ ፡ ብዙኃን ፡ በእግዚእ ፡ ኢየሱስ ፡
ወሰብሕዎ፡ለእግዚአብሔር።

ሣህሉ፡ወምሕረቱ፡የሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡
ዓለም፡አሜን።

አመ፡ትመጽእ፡ለኰንኖ፡በል።

ማክሰኞ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

እንዲሉ፡ያውቃልና።

፭ እርሱ፡ራሱን፡ወደ፡ምድር፡ዘንበል፡አድርጎ፡
የሁሉንም፡ኃጢአት፡በምድር፡ላይ፡ይጽፍ፡
ዘንድ፡ጀመረ።

፮ ከዚህም፡በኋላ፡ራሱን፡ወደ፡እነርሱ፡ቀና፡
አድርጎ፡እስከ፡ምትሞት፡ድረስ፡እንደ፡ሕጉ፡
በድንጋይ ፡ ትደበደብ ፡ ዘንድ ፡ ይገባታል ፤
አሁንም ፡ ወደፍርድ ፡ ቦታ ፡ ውሰዱአት ፤
ዳግመኛም፡ወደምትደበደብበት፡ወደዚህ፡
ቦታ፡በፊቱ፡ትደበድቧት፡ዘንድ፡ወደእኔ፡
አምጧት፡አላቸው።

፯ ያችንም፡ሴት፡ወደ፡ቅጣቱ፡ቦታ፡ወሰደው፡
ደንጊያ፡ሰበሰቡ፤ከዚህም፡በኋላ፡ወደ፡ጌታ፡
ኢየሱስ፡ተመለሱ።

፰ ሁለተኛም፡ወደ፡ምድር፡ዘንበል፡ብሎ፡
የዕገሌ፡ኃጢአት፡እንዲህ፡ነው፤የዕገሌም፡
ኃጢአት፡ይህ፡ነው፡እያለ፡በጣቱ፡ጻፈ።

፱ ይህንንም ፡ ተግሣፅ ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡ ሁሉም ፡
ወጥተው፡ሄዱ፤ጌታ፡ኢየሱስም፡ራሱን፡ቀና፡
አድርጎ ፡ ቢመለከት ፡ በፍርድ ፡ ቦታ ፡
ካቆሙዋት፡ ከዚያች ፡ ሴት ፡ ብቻ ፡ በቀር ፡
ከአይሁድ፡ሰዎች፡ማንንም፡ማንን፡አላገኘም።

፲ ጌታ ፡ ኢየሱስም ፡ የሚከሱሽ ፡ ሰዎች ፡
ወዴት ፡ አሉ ፡ አላት ፤ እርሷም ፡ ንጹሕ ፡
ከሆነው፡ፍርድህ፡የተነሣ፡አፍረው፡ሸሹ፡
አለችው።

፲፩ ጌታ ፡ ኢየሱስ ፡ ለራስሽ ፡ ዕወቂ ፤ መልክ ፡
የሌለው ፡ ፍርድ ፡ እንዳያገኝሽ ፡ ሁለተኛ ፡
አትበድዪ ፡ አላት ፤ እኔም ፡ ኃጢአትሽን ፡
ይቅር፡ብየሻለሁ፡አላት።

፲፪ ያቺም፡ሴት፡ወጥታ፡ሄደች፤ወደከተማውም፡
ገብታ፡የእርሱን፡ነገር፡ለሰው፡ሁሉ፡አወራች፤
ስለ፡እርስዋም፡ብዙዎች፡በጌታችን፡ኢየሱስ፡
አምነው፡እግዚአብሔርን፡አመሰገኑት።

ይቅርታው፡ቸርነቱ፡ከእኛ፡ጋራ፡ለዘላለሙ፡
ይኑር፤አሜን።

አመ፡ትመጽእ፡ለኰንኖ፡በል።

በ፮፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሠሉስ።

## ክፍል፡፫።

ይ፡ዲ፡ቅድመ፡ወንጌል።

መዝ፣፷፫፣፪።

አድኅነኒ ፡ እግዚኦ ፡ እምፀርየ ። ወእምጸላእትየ፡እስመ፡ይኄይሉኒ።ዘይባልሐኒ፡እምጸላእትየ ፡ ምንስዋን ፡ ወዘያሌዕለኒ ፡ እምእለቆሙ፡ላዕሌየ።

### ወንጌል፡ዘዮሐንስ።

ምዕ፣፰፣፲፪–፳።

፲፪፤ ወካዕበ፡ነበቦሙ፡እግዚእ፡ኢየሱስ፡ወይቤ፡አነ ፡ ውእቱ ፡ ብርሃኑ ፡ ለዓለም ፡ ዘተለወኒ ፡ ኢየሐውር፡ውስተ፡ጽልመት፡አላ፡ይረክብ፡ብርሃነ፡ሕይወት።

፲፫፤ ወይቤልዎ ፡ ፈሪሳውያን ፡ ለሊከኑ ፡ ትንዕድ ፡ ርእሰከ፡ኢኮነ፡ጽድቀ፡ስምዕከ።

፲፬፤ ወአውሥአ ፡ እግዚእ ፡ ኢየሱስ ፡ ወይቤሎሙ ፡ እመኒ፡ ለልየ ፡ ስምዐ ፡ ኮንኩ ፡ ለርእስየ ፡ ጽድቅ ፡ ውእቱ ፡ ስምዕየ ፡ እስመ ፡ አነ ፡ አአምር ፡ እምኀበ ፡ መጻእኩ ፡ ወኀበ፡ አሐውር ፡ ወአንትሙሰ ፡ ኢተአምሩ፡እምኀበ፡መጻእኩ፡ወኀበ፡አሐውር።

፲፭፤ አንትሙሰ፡ሕገ፡ዘሥጋ፡ትኬንኑ፡ወአንሰ፡ኢይኬንን፡ወኢመነሂ።

፲፮፤ ወእመሂ ፡ ኰነንኩ ፡ አነ ፡ ጽድቀ ፡ እኴንን ፡ እስመ ፡ ኢኮንኩ ፡ አነ ፡ ባሕቲትየ ፡ አላ ፡ አነ ፡ ወአብ፡ዘፈነወኒ።

፲፯፤ አኮኑ ፡ ጽሑፍ ፡ ውስተ ፡ ኦሪትክሙ ፡ ከመ ፡ ስምዐ፡ክልኤቱ፡ሰብእ፡እሙን፡ውእቱ።

፲፰፤ ወአነሂ፡ሰማዕት፡ለርእስየ፡ወአብ፡ዘፈነወኒ፡ሰማዕትየ።

፲፱፤ ወይቤልዎ ፡ አይቴ ፡ ውእቱ ፡ አቡከ ፡ ወአውሥአ፡እግዚእ፡ኢየሱስ፡ወይቤሎሙ፡ኢ፡ኪያየ፡ተአምሩ፡ወኢ፡አቡየ፡ሶበሰ፡ኪያየ፡አእመርክሙ፡እምአእመርክምዎ፡ለአቡየኒ።

፳፤ ወዘንተ፡ነገረ፡ተናገሮሙ፡እግዚእ፡ኢየሱስ፡በኀበ፡ሙዳየ፡ምጽዋት፡እንዘ፡ይሜህሮሙ፡በምኵራብ ፡ ወኢአኀዝዎ ፡ እስመ ፡ ዓዲ ፡ ኢበጽሐ፡ጊዜሁ።

ማክሰኞ፡መዓልት፡በ፮፡ሰዓት።

## ክፍል፡፫።

ዲያቆኑ፡ከወንጌል፡አስቀድሞ።

መዝ፣፷፫፣፪።

አቤቱ ፡ ከጠላቶቼ ፡ አድነኝ፤ከሚበረቱብኝ፡ጠላቶቼ ፡ አድነኝ ፤ ጥፋተኞች ፡ ከሆኑ፡ጠላቶቼም፡የሚያድነኝ፡እሱ፡ነው፤በጠላትነት፡ከተነሡብኝም፡ጠላቶቼ፡በላይ፡ከፍ፡ከፍ፡የሚያ ደርገኝ፡እርሱ፡ነው፡ይበል።

### የዮሐንስ፡ወንጌል።

ምዕ፣፰፣፲፪–፳።

፲፪፤ ዳግመኛ፡ጌታ፡ኢየሱስ፡የዓለም፡ብርሃን፡እኔ ነኝ፤የተከተለኝ፡ወደጨለማ፡አይሄድም፤የሕ ይወትን፡ብርሃን፡ያገኛል፡እንጂ፡ብሎ፡አስተ ማራቸው።

፲፫፤ ፈሪሳውያንም፡ራስህን፡በራስህ፡ታመሰግናለህ፡ምስክርነትህ፡እውነት፡አይደለም፡አሉት።

፲፬፤ ጌታ፡ኢየሱስም፡መልሶ፡እንዲህ፡አላቸው፤እኔ ፡ ለራሴ ፡ ብመሰክርም ፡ ምስክርነቴ፡እውነት፡ነው፤እኔ፡የመጣሁበትንና፡የምሄ ድበትን፡አውቃለሁና፤እናንተ፡ግን፡የመጣሁበ ትንና፡የምሔድበትን፡አታውቁም።

፲፭፤ እናንተ፡ሥጋዊ፡ፍርድን፡ትፈርዳላችሁ፤እኔ ግን፡በማንም፡በማን፡አልፈርድም።

፲፮፤ እኔ፡ብፈርድም፡እውነት፡እፈርዳለሁ፤እኔ ብቻዬን፡ አይደለሁምና ፡ እኔና ፡ የላከኝ፡አብም፡እንጂ፤

፲፯፤ በሕጋችሁ ፡ የሁለት ፡ ሰው ፡ ምስክርነት፡የታመነ፡እንደሆነ፡ተጽፎ፡የለምን።

፲፰፤ እኔ፡ለራሴም፡ምስክር፡ነኝ፤የላከኝ፡አብም፡ምስክሬ፡ነው።

፲፱፤ አባትህ፡የት፡ነው?አሉት፤ጌታ፡ኢየሱስም፡እኔን ፡ አታውቁ ፤ አባቴንም ፡ አታውቁ፤እኔንስ፡ ብታውቁ ፡ አባቴን ፡ ባወቃችሁት፡ነበር፡ብሎ፡መለሰላቸው።

፳፤ ጌታ ፡ ኢየሱስም ፡ በምኩራብ ፡ ሲያስተም ራቸው፡በሙዳየ፡ምጽዋት፡አጠገብ፡ይህን፡ተናገራቸው፤ግን፡አልያዙትም፤ጊዜው፡ገና፡አልደረሰምና።

Scanned by CamScanner

በ፮፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሠሉስ።

ድኅረ፡ወንጌል፡በስድስቱ፡ሰዓት፡እምዕለተ፡ሠሉስ።

፩፤ **አምላክ** ፡ ዘበአማን ፡ ዘመጽአ ፡ ኀበ ፡ ዓለም ፡ በአፉሁ፡ዘኢይሔሱ፡ይነብብ፡በጽድቅ፡አነ፡ውእቱ ፡ ብርሃኑ ፡ ለዓለም ፡ ዘተለወኒ ፡ ኢየሐውር፡ውስተ፡ጽልመት፡አላ፡ይረክብ፡ብርሃነ ፡ ሕይወት ፡ ዘይመርሕ ፡ ኀበ ፡ ፍኖተ ፡ ጽድቅ።

፪፤ እስመ ፡ አንተ ፡ ውእቱ ፡ በአማን ፡ ብርሃኑ ፡ ለዓለም ፡ ወአርአያ ፡ ዘወፅአ ፡ እምባሕርይ ፡ ዘስብሐቶ፡አሥረቀ፡በብርሃን፡ዐቢይ፡ላዕለ፡ዓለም ፡ እስከ ፡ ተፍጻሜቱ ፡ ወሰሐበነ ፡ ለነ ፡ ለአሕዛብ ፡ ነኪራን ፡ ኀበ ፡ አእምሮ ፡ ጽድቅ ፡ በእንተ፡ስሙ።

ወአብርሀ ፡ ላዕሌነ ፡ ብርሃነ ፡ ጽድቁ ፡ ለእለ ፡ ንነብር፡ውስተ፡ጽልመት፡ወጽላሎተ፡ሞት።

፫፤ ወለአይሁድ ፡ ዐላውያን ፡ እለ ፡ እሙንቱ ፡ እሊአሁ ፡ አግብአሙ ፡ ውስተ ፡ ጽልመት ፡ ዘውስተ፡ሲኦል፡እስከ፡ለዓለም።

፬፤ እስመ ፡ እሙንቱ ፡ ገደፉ ፡ ቃላቲሁ ፡ ወኢተወክፍዎ ፡ ወፈትሑ ፡ ላዕሌሁ ፡ ፍትሐ ፡ ሞት።

፭፤ ወንሕነ፡ለናልዕል፡ስሞ፡ቅዱሰ፡ወንሰብሖ፡ዘእንበለ፡ዕርዐት።

**ክርስቶስ፡መድኃኒነ፡**መጽአ፡ወሐመ፡ወበሕማማቲሁ፡አድኃነነ፤ወቤዘወነ።

ጸልዩ፡በእንተ፡ጽንዐ፡ዛቲ፡በል።

ወኵሉ ፡ ሥርዓቱ ፡ ከመ ፡ ቀዳሚ ፡ ዘዕለተ ፡ ሰኑይ፡ዘስድስቱ፡ሰዓት፡በል።

## ምዕራፍ፡፳፫።

ምንባብ፡ዘተሰዓቱ፡ሰዓተ፡መዐልት፡ዘሠሉስ።

ክፍል፡፩።

አሪት፡ዘልደት።

ምዕ፡፮፡፳–፳፱።

፳፩፤ ወሶበ ፡ ርእየ ፡ **እግዚአብሔር** ፡ ከመ ፡ በዝኀ ፡ ዕከዮሙ ፡ ለዕጓለ ፡ እመሕያው ፡ ላዕለ ፡ ምድር ፡ ወበኵሉ ፡ ጊዜ ፡ ውስተ ፡ እኪት ፡ ወኵሉ ፡

ማክሰኞ፡መዓልት፡በ፮፡ሰዓት።

ማክሰኞ፡ከቀኑ፡በስድስት፡ሰዓት፡ከወንጌል፡በኋላ፡የሚነበብ።

፩፤ ወደ ፡ ዓለም ፡ የመጣ ፡ እውነተኛ ፡ የባሕርይ ፡ **አምላክ** ፡ ሐሰት ፡ በሌለበት ፡ አንደበቱ ፡ የዓለም፡ብርሃን፡እኔ፡ነኝ፤የተከተለኝ፡ወደ፡ጨለማ ፡ አይገባም ፤ ወደ ፡ እውነተኛ ፡ መንገድ፡የሚአደርስ፡የሕይወት፡ብርሃንን፡ያገኛል፡እንጂ፡ብሎ፡በእውነት፡ተናገረ።

፪፤ በዓለም ፡ ላይ ፡ እስከ ፡ መጨረሻ ፡ ድረስ ፡ በታላቅ፡ብርሃን፡ጌትነቱን፡የገለጠ፡እኛንም፡ልዩ ፡ ወገኖች ፡ ስንሆን ፡ ስለ ፡ ስሙ ፡ እርሱን ፡ ወደ ፡ ማወቅ ፡ የሳበን ፡ ከባሕርይ ፡ **አምላክ** ፡ የተገኘ ፡ አርአያ ፡ በእውነት አንተ ፡ የዓለም ፡ ብርሃን፡ነህ፤በጨለማና፡በሞት፡ጥላ፡ውስጥ፡ለምንኖር ፡ ለእኛ ፡ የእውነቱን ፡ ብርሃን፡አበራልን።

፫፤ ወገኖቹ፡የነበሩ፡ከሀድያን፡አይሁድን፡ግን፡በሲኦል ፡ ወደአለ ፡ ጨለማ ፡ እስከ ፡ ዘላለሙ ፡ መለሳቸው።

፬፤ እነርሱም፡ሕጉን፡ጣሉ፤ትምህርቱንም፡አል ተቀበሉትምና ፡ የሞት ፡ ፍርድንም ፡ ፈረዱበት።

፭፤ እኛ ፡ ግን ፡ የከበረ ፡ ስሙን ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ እናድርግ፤ያለ፡ማቋረጥም፡እናመስግነው።

**መድኃኒታችን ፡ ክርስቶስ** ፡ መጥቶ ፡ ሰው ፡ ሁኖ ፡ መከራ፡ተቀበለ፤በመከራውም፡ፈጽሞ፡አዳነን።

ጸልዩ፡በእንተ፡ጽንዐ፡ዛቲ፡በል።

ሥርዓቱ ፡ ሁሉ ፡ ሰኞ ፡ በስድስት ፡ ሰዓት ፡ አስቀድሞ፡እንደተጻፈው፡ነው።

## ምዕራፍ፡፳፫።

ማክሰኞ፡ቀን፡በዘጠኝ፡ሰዓት፡የሚነበብ።

ክፍል፡፩።

አሪት፡ዘፍጥረት።

ምዕ፡፮፡፳–፳፱።

፳፩፤ **እግዚአብሔርም** ፡ የሰው ፡ ልጆች ፡ ኃጢአት ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ እንደበዛ ፡ ሁልጊዜም ፡ ወደ ፡ ኃጢአት ፡ እንደሄዱ ፡ ከሕፃንነታቸው ፡ ጀምሮ፡ በለ ፡ ዘመናቸውም ፡ ሁሉ ፡ አሳባቸው ፡ ወደ ፡

Scanned by CamScanner

## በ፱፡ሰዓተ፡መዓልትዘሠሉስ።

ንእሰሙ፡በኵሉ፡መዋዕሊሆሙ።

፮፡ ወነስሐ ፡ **እግዚአብሔር** ፡ እስመ ፡ ገብሮ ፡ ለዕጓለ፡እመሕያው፡ላዕለ፡ምድር።

፯፡ ወኀለየ ፡ ወይቤ ፡ **እግዚአብሔር** ፡ እደ መስሶ ፡ ለዕጓለ ፡ እመሕያው ፡ ዘገበርክዎ ፡ እምላዕለ ፡ ምድር ፡ እምሰብእ ፡ ወእስከ ፡ እን ስሳ ፡ ወአራዊት ፡ ወአዕዋፈ ፡ ሰማይ ፡ ወዘ ይትሐወስ፡ እስመ ፡ ነሳሕኩ ፡ በእንተ ፡ ዘገበ ርክዎ።

፰፡ ወኖኅሰ ፡ ረከበ ፡ ሞገሰ ፡ በቅድመ ፡ **እግዚአ ብሔር**።

፱፡ ወከመዝ ፡ ውእቱ ፡ ፍጥረቱ ፡ ለኖኅ ፡ ወብእሲ ፡ ጻድቅ ፡ ውእቱ ፡ ወፍጹም ፡ ወእምልደቱ ፡ አሥመሮ ፡ **ለእግዚ አብሔር**።

፲፡ ወወለደ ፡ ኖኅ ፡ ሠለስተ ፡ ደቂቀ ፡ እሉ ፡ እሙንቱ፡ሴም፡ወካም፡ወያፌት።

፲፩፡ ወማሰነት፡ምድር፡በቅድመ፡**እግዚአብሔር**፡ ወመልዓት፡ዐመፃ።

፲፪፡ ወርእያ ፡ **እግዚአብሔር** ፡ ለምድር ፡ ከመ ፡ ማሰነት ፡ ወከመ ፡ አማሰኑ ፡ ፍኖቶሙ ፡ በዲበ ፡ ምድር፡ኵሉ፡ዘሥጋ።

፲፫፡ ወይቤሎ ፡ **እግዚአብሔር ፡ አምላኩ** ፡ ለኖኅ ፡ ጊዜሁ፡ለዕጓለ፡እመሕያው፡በጽሐ፡ቅድሜየ፡ እስመ ፡ መልዐ ፡ ዓመፃ ፡ ዲበ ፡ ምድር ፡ እምኔሆሙ ፡ ወናሁ ፡ አነ ፡ እደመስሶሙ ፡ እምድር።

፲፬፡ ወግበር ፡ ለከ ፡ ታቦተ ፡ እንተ ፡ ዕፅ ፡ ርብዕተ ፡ ወትቀብዓ፡እንተ፡ውስጣ፡ወእንተ፡አፍአሃኒ፡ በፒሳ።

፲፭፡ ወከመዝ፡ትገብራ፡ሠለስተ፡ምዕተ፡በእመት፡ ኑኃ ፡ ወኀምሳ ፡ በእመት ፡ ራኅባ ፡ ወሠላሳ ፡ በእመት፡ሥራዕ።

፲፮፡ ወመስኮተ ፡ ግበር ፡ ለይእቲ ፡ ታቦት ፡ ወሶበ ፡ በጽሐት ፡ ለተፈጽሞ ፡ አሐቲ ፡ እመት ፡ እንዘ ፡ ትተርፍ ፡ ግበር ፡ ሀየ ፡ ኖኀታ ፡ ውስተ ፡ ገቦሃ ፡ ወግበር ፡ ላቲ ፡ መዓርጋተ ፡ ተጽራሐ ፡ ወተሥላሰ፡ግበር።

፲፯፡ ወናሁ ፡ አነ ፡ አመጽእ ፡ ማየ ፡ አይኅ ፡ በዲበ ፡

## ማክሰኞ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

ክፋት፡እንደሆነ፡ባየ፡ጊዜ።

፮፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ሰውን ፡ ስለፈጠረው ፡ **እግዚአ ብሔር**፡ አዘነ ፤ (ተጸጸተ)።

፯፡ **እግዚአብሔርም** ፡ ስለ ፡ ፈጠርኩት ፡ አዝኛ ለሁና፡(ተጸጽቻለሁና)፡የፈጠርኩት፡ሰውን፡ ከሰው ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ እንስሳ ፡ እስከ ፡ አውሬ ዎችም ፡ እስከ ፡ ሰማይ ፡ ወፎችና ፡ የሚንቀሳቀ ሱትንም ፡ እንቅስቃሴ ፡ ከምድር ፡ ላይ ፡ አጠፋ ቸዋለሁ፡ብሎ፡አሰበ።

፰፡ ኖኅ ፡ ግን ፡ **በእግዚአብሔር** ፡ ፊት ፡ ባለሟል ነትን፡አገኘ።

፱፡ የኖኅም ፡ ትውልዱ ፡ እንዲህ ፡ ነው ፤ እርሱም፡ እውነተኛ ፡ ሰው ፡ ነበር ፤ በምግባር ፡ በሃይማኖቱ ፍጹም፡ነበር፤ከተወለደም፡ጀምሮ፡**እግዚአብሔርን** በሥራው፡ደስ፡አሰኝቶታል፡አገልግሎታል።

፲፡ ኖኅም ፡ ሦስት ፡ ልጆችን ፡ ወለደ ፤ እነዚህም፡ ሴም፡ካም፡ያፌት፡ናቸው።

፲፩፡ ምድርም ፡ **በእግዚአብሔር** ፡ ፊት ፡ ተበላሸች፤ ኃጢአትንም፡መላች።

፲፪፡ **እግዚአብሔርም** ፡ ምድርን ፡ እንደተበላሸች፡ አያት ፤ ሥጋዊ ፡ ደማዊም ፡ ሁሉ ፡ ሥራቸውን፡ በዚህ፡ዓለም፡እንዳበላሹ፡አየ።

፲፫፡ ከእሳቸው ፡ የተነሣ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ኃጢአት፡ በዝቷልና ፡ **ፈጣሪው ፡ እግዚአብሔር**፡ ኖኅን፡ ሰው ፡ በትእዛዜ ፡ የሚጠፋበት ፡ ጊዜ፡ ደረሰ ፡ አለው ። እነሆ ፡ እኔም ፡ ሰዎችን፡ ከምድር፡አጠፋቸዋለሁ።

፲፬፡ አራት ፡ ማዕዘን ፡ አድርገህ ፡ ላንተ ፡ የእንጨት፡ መርከብን ፡ ሥራ ፤ እዳሪዋንና ፡ ውስጧንም፡ የአደሮ፡ማር፡ሙጫ፡ቀባት፡አለው።

፲፭፡ አቈልቋይዋን ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ወርዷንም፡ አምሳ፡ቁመቷንም፡ሠላሳ፡ክንድ፡አድርገህ፡ ሥራት፡አለው።

፲፮፡ ለዚያችም ፡ መርከብ ፡ መስኮት ፡ አውጣለት፡ አለው፤ለመጨረስም፡በደረሰች፡ጊዜ፡አንዲት፡ ክንድ ፡ ስትቀር ፡ በዚያ ፡ የጐድኗ ፡ ደጃፍ፡ አውጣላት ፤ የአዳራሽነቷን ፡ እርከን ፡ ሥራለት፡ ሦስት፡ክፍልም፡አድርገህ፡ሥራት፡አለው።

፲፯፡ እነሆ ፡ እኔ ፡ የጥፋት ፡ ውኃን ፡ በዚህ ፡ ዓለም፡

## በ፱፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሠሉስ።

ምድር ፡ ወእደመስስ ፡ ኵሎ ፡ ዘሥጋ ፡ ዘቦ ፡ መንፈስ ፡ ሕይወት ፡ ዘሀሎ ፡ ላዕለ ፡ ምድር ፡ ወመትሕተ ፡ ሰማይ ፡ ወይመውት ፡ ኵሉ ፡ ዘሥጋ፡ዘቦ፡መንፈሰ፡ሕይወት፡ዘሀሎ፡ላዕለ፡ ምድር፡ወመትሕተ፡ሰማይ።

፲፰፤ ወአቀውም ፡ ኪዳንየ ፡ ምስሌከ ፡ ወት በውዕ ፡ አንተ ፡ ውስተ ፡ ታቦት ፡ ወብ እሲትከ ፡ ወደቂቅከ ፡ ወአንስትያ ፡ ደቂቅከ ፡ ምስሌከ።

፲፱፤ ወእምኵሉ ፡ እንስሳ ፡ ወአዕዋፍ ፡ ወዘይት ሐወስ ፡ ወአራዊት ፡ ወእምኵሉ ፡ ዘሥጋ ፡ ታበውዕ፡ምስሌከ፡ተባዕተ፡ወአንስተ።

፳፤ ወንሣእ ፡ ለከ ፡ እምኵሉ ፡ መባልዕት ፡ ዘይሴሰዩ።

፳፩፤ ወአስተጋብዕ ፡ ኀቤከ ፡ ወይከውነከ ፡ መብልዐ፡ ለከ ፡ ወለኵሎሙ ፡ አራዊት ፡ ወእንስሳ።

፳፪፤ ወገብረ፡ኖኅ፡በከመ፡አዘዞ፡**እግዚአብሔር፡ አምላክ**።

### ምዕ፤፯፣፩-፳፬።

፩፤ ወይቤሎ፡**እግዚአብሔር**፡ለኖኅ፡ባእ፡አንተ፡ ወኵሉ፡ቤትከ፡ውስተ፡ታቦት፡እስመ፡ኪያከ ረከብኩ ፡ ጻድቀ ፡ በቅድሜየ ፡ በዛቲ ፡ ትውልድ።

፪፤ ወእምእንስሳ፡ዘንጹሕ፡አብእ፡ምስሌከ፡፯ተ፡ ፯ተ ፡ ተባዕተ ፡ ወአንስተ ፡ ወእምእንስሳ ፡ ዘኢኮነ፡ ንጹሐ ፡ ፪ተ ፡ ፪ተ ፡ ተባዕተ ፡ ወአንስተ።

፫፤ ወእምኵሉ፡አዕዋፈ፡ሰማይ፡ዘንጹሕ፡፯ተ፡ ፯ተ ፡ ተባዕተ ፡ ወአንስተ ፡ ወእምአዕዋፈ ፡ ሰማይ፡ዘኢኮነ፡ንጹሐ፡፪ተ፡፪ተ፡ተባዕተ፡ ወአንስተ ፡ ዘትሴሰይ ፡ ወዘይከውን ፡ ዘርዐ ፡ በዲበ፡ምድር።

፬፤ እስመ ፡ እስከ ፡ ሰብዑ ፡ መዋዕል ፡ አመጽእ ፡ ዝናመ፡ዲበ፡ምድር፡፵፡መዐልተ፡ወ፵፡ ሌሊተ ፡ ወእደመስስ ፡ ኵሎ ፡ ዘይትሐወስ ፡ ዲበ፡ምድር።

፭፤ ወገብረ፡ኖኅ፡ኵሎ፡ዘአዘዞ፡**እግዚአብሔር፡ አምላክ**።

፮፤ ወአሚሁ ፡ ኮኖ ፡ ለኖኅ ፡ ስድስተ ፡ ምዕተ ፡

## ማክሰኞ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

አመጣለሁ፤በደመ፡ነፍስ፡ሕያው፡የሆነውን፡ ሥጋዊውን፡ደማዊውንም፡ሁሉ፡አጠፋለሁ፤ በዚህ፡ዓለም፡ያለው፡ከሰማይ፡በታች፡ያለው፡ በደመ፡ነፍስ፡ሕያው፡የሆነ፡ሥጋዊ፡ደማዊ፡ ሁሉ፡ይሞታል።

፲፰፤ ቃል፡ኪዳኔንም፡(መሐላዬን)፡ካንተ፡ጋራ፡ አጸናለሁ፤አንተም፡ወደመርከብ፡ትገባለህ፤ ሚስትህም ፡ ልጆችህም ፡ የልጆችህም ፡ ሚስቶች፡ካንተ፡ጋራ፡ይገባሉ።

፲፱፤ ከእንስሳ፡ከወፎችም፡እንቅስቃሴ፡ካላቸው፡ ካውሬዎችም ፡ ከሥጋዊ ፡ ከደማዊ ፡ ሁሉ ፡ ወንዶችና፡ሴቶችን፡ካንተ፡ጋራ፡ታገባለህ።

፳፤ ከሚበሉት ፡ መብሎች ፡ ሁሉ ፡ ላንተ ፡ ውሰድ።

፳፩፤ በአንተ ፡ ዘንድ ፡ ሰብስበህ ፡ አኑር ። ላንተ ፡ ምግብ ፡ ይሆናል ። ለአውሬዎችም ፡ ለከብ ቶችም፡ሁሉ።

፳፪፤ ኖኅም ፡ ገዥ ፡ **ፈጣሪ ፡ እግዚአብሔር** ፡ እንዳ ዘዘው፡አደረገ።

### ምዕ፤፯፣፩-፳፬።

፩፤ **እግዚአብሔርም** ፡ ኖኅን ፡ በዚች ፡ ትውልድ ፡ በፊቴ ፡ አንተን ፡ ደግ ፡ ሰው ፡ ሁነህ ፡ አግኝቻ ለሁና፡አንተ፡ከወገኖችህ፡ሁሉ፡ጋራ፡ወደ፡ መርከብ፡ግባ፡አለው።

፪፤ ከሚበሉ፡እንስሳት፡እንስትና፡ተባት፡ሰባት፡ ሰባት፡ካንተ፡ጋራ፡አስገባ፤ከማይበሉ፡እንስ ሳትም ፡ እንስትና ፡ ተባት ፡ ሁለት ፡ ሁለት ፡ ካንተ፡ጋራ፡አስገባ።

፫፤ ከሚበሉት ፡ ከሰማይ ፡ ወፎችም ፡ እንስትና ፡ ተባት ፡ ሰባት ፡ ሰባት ፡ ከማይበሉ ፡ ከሰማይ ፡ ወፎችም፡እንስትና፡ተባት፡ሁለት፡ሁለት፡ አንተ ፡ የምትመገበውን ፡ በዚህ ፡ ዓለምም ፡ ዘር፡የሚሆነውን፡ወደ፡መርከብ፡አስገባ።

፬፤ እስከ፡ሰባት፡ቀን፡ድረስ፡አርባ፡ቀን፡አርባ፡ ሌሊት፡በዚህ፡ዓለም፡የጥፋት፡ውኃን፡አመ ጣለሁና፡በዚህ፡ዓለም፡የሚንቀሳቀሰውን፡ ሁሉ፡አጠፋለሁና፡አስገባ፡አለው።

፭፤ ኖኅም፡**እግዚአብሔር፡አምላክ**፡ያዘዘውን፡ ሁሉ፡አደረገ።

፮፤ የዚያን፡ጊዜ፡ለኖኅ፡ስድስት፡መቶ፡ዓመት፡

Scanned by CamScanner

## በ፱፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሠሉስ።

ዓመተ ፡ ወመጽአ ፡ ማየ ፡ አይኅ ፡ ላዕለ ፡ ኵሉ ፡
ምድር።
፯፤ ወቦአ ፡ ኖኅ ፡ ወብእሲቱ ፡ ወደቂቁ ፡ ወአን
ስትያ፡ ደቂቁ ፡ ምስሌሁ ፡ ውስተ ፡ ታቦት ፡
በእንተ፡ማየ፡አይኅ።
፰፤ ወእምአዕዋፍ፡ዘንጹሕ፡ወዘኢኮነ፡ንጹሐ፡
ወእምእንስሳ ፡ ንጹሕ ፡ ወዘኢኮነ ፡ ንጹሐ ፡
ወእምኵሉ፡ዘይትሐወስ።
፱፤ ወቦኡ፡ኅበ፡ኖኅ፡ውስተ፡ታቦት፡ተባዕት፡
ወአንስት ፡ በከመ ፡ አዘዞ ፡ እግዚአብሔር ፡
ለኖኅ።
፲፤ ወኮነ፡እምድኅረ፡ሰቡዕ፡መዋዕል፡መጽአ፡
ማየ፡አይኅ፡ላዕለ፡ኵሉ፡ምድር።
፲፩፤ አመ፡ኮነ፡ስድስተ፡ምዕተ፡ዓመተ፡ሕይወቱ፡
ለኖኅ፤በካልእ፡ወርኅ፡አመ፡፲ወ፪፡አመ፡
አሥሩ፡ወሰብዑ፡ለጽልመት ። ወበይእቲ ፡
ዕለት ፡ ተሠጥቁ ፡ ኵሉ፡ ቀላያት ፡ ወተርኅወ ፡
አስራበ፡ሰማይ።
፲፪፤ ወኮነ፡ዝናም፡ላዕለ፡ምድር፡፵፡መዐልተ፡
ወ፵፡ሌሊተ።
፲፫፤ ወበይእቲ፡ዕለት፡ቦኡ፡ኖኅ፡ወሴም፡ካም፡
ወያፌት ፡ ደቂቁ ፡ ወብእሲቱ ፡ ወአንስትያ ፡
ደቂቁ፡ውስተ፡ታቦት።
፲፬፤ ወአራዊትኒ፡በበዘመዶሙ፡ወኵሉ፡እንስሳ፡
በበዘመዶሙ፡ወዘይትሐወስ፡ወአዕዋፍ፡በበ
ዘመዶሙ።
፲፭፤ ወእምነ ፡ ኵሉ ፡ ዘሥጋ ፡ ዘቦ ፡ መንፈሰ ፡
ሕይወት።
፲፮፤ ቦኡ፡ውስተ፡ታቦት፡ኅበ፡ኖኅ፡በከመ፡አዘዞ፡
እግዚእ፡እግዚአብሔር፡ለኖኅ፡ወአፀዋ፡እግዚ
አብሔር፡ለታቦት፡እምአፍኣሃ።
፲፯፤ ወኮነ፡አይኅ፡ላዕለ፡ምድር፡፵፡መዐልተ፡
ወ፵፡ሌሊተ፡ወመልአ፡ማይ፡ወአልዓላ፡
ለታቦት፡ወተለዓለት፡እምድር።
፲፰፤ ወጸንዐ፡ማይ፡ጥቀ፡ላዕለ፡ምድር፡ወበዝኀ፡
ወጸለለት፡ይእቲ፡ታቦት፡ላዕለ፡ማይ።
፲፱፤ ወፈድፋደ፡በዝኀ፡ጥቀ፡ማይ፡ዲበ፡ምድር፡
ወከደነ፡ኵሎ፡አድባረ፡ነዋኅተ፡ዘመትሕተ፡
ሰማይ።

## ማክሰኞ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

ሆኖት፡ነበር፤የጥፋት፡ውኃም፡በዚህ፡ዓለም፡
ሁሉ፡መጣ።
፯፤ የጥፋት፡ውኃ፡የሚመጣ፡ስለሆነ፡ለመዳን፡
ኖኅ፡ወደ፡መርከብ፡ገባ፤ሚስቱም፡ልጆቹም፡
የልጆቹ፡ሚስቶችም፡ከእርሱ፡ጋራ፡ገቡ።
፰፤ ከማይበሉና፡ከሚበሉ፡ወፎች፡ከማይበሉና፡
ከሚበሉ፡እንስሳ፡ከሚንቀሳቀሰውም፡ሁሉ፡
፱፤ እግዚአብሔርም ፡ ኖኅን ፡ እንዳዘዘው ፡
እንስትና ፡ ተባትም ፡ ከኖኅ ፡ ዘንድ ፡ ወደ፡
መርከብ፡ገቡ።
፲፤ ከሰባት፡ቀንም፡በኋላ፡እንዲህ፡ሆነ፤በምድር፡
ላይ፡ሁሉ፡የጥፋት፡ውኃ፡መጣ።
፲፩፤ ኖኅ ፡ በሕይወት ፡ የኖረበት ፡ ዘመን ፡ ስድስት፡
መቶ ፡ ዓመት ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ በሁለተኛው፡ወር፡
በግንቦት ፡ ጨረቃ ፡ ሠርቅ ፡ ባደረገች ፡
ጨለማዋን፡ ባጣች ፡ ባሥራ ፡ ሁለተኛው ፡ ቀን፡
ወይም፡በ፲፯ኛው፡ቀን፤በዓለሙ፡ሁሉ፡የጥፋት፡
ውኃ፡ መጣ ፤ በዚያች ፡ ቀን ፡ ወንዞች ፡ ሁሉ፡
ተከፈቱ፤የሰማይ፡መስኮቶችም፡ተከፈቱ።
፲፪፤ አርባ፡ቀን፡አርባ፡ሌሊት፡በዚህ፡ዓለም፡የጥፋት፡
ዝናም፡ዘነመ።
፲፫፤ በዚያች፡ቀን፡ኖኅ፡ልጆቹ፡ሴም፡ካም፡ያፌትም፡
ሚስቱም፡የልጆቹ፡ሚስቶችም፡ወደ፡መርከብ፡
ገቡ።
፲፬፤ አውሬዎችም፤በየወገናቸው፡እንስሶችም፡በየወ
ገናቸው ፡ የሚንቀሳቀሱትና ፡ ወፎችም ፡ በየወ
ገናቸው።
፲፭፤ የደመ ፡ ነፍስ ፡ ሕይወት ፡ ያላቸው ፡ ከሥጋዊ፡
ከደማዊም፡ሁሉ።
፲፮፤ ፈጣሪ፡እግዚአብሔር፡ኖኅን፡እንዳዘዘው፡ከኖኅ፡
ዘንድ ፡ ወደ ፡ መርከብ ፡ ገቡ ፤ እግዚአብሔርም፡
መርከቢቱን፡በስተኋላዋ፡ዘጋት።
፲፯፤ በዚህም ፡ ዓለም ፡ አርባ ፡ ቀን ፡ አርባ ፡ ሌሊት፡
ጥፋት፡ተደረገ፤የጥፋት፡ውኃም፡መልቶ፡መርከ
ቢቱን ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አደረጋት ፡ ከምድርም፡ከፍ፡
ከፍ፡አለች።
፲፰፤ የጥፋት ፡ ውኃም ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ አጥለቀለቀ፡
ያቺም፡መርከብ፡በውኃ፡ላይ፡ተንሳፈፈች።
፲፱፤ በዚህ ፡ ዓለም ፡ የጥፋት ፡ ውኃው ፡ ፈጽሞ ፡ በዛ፡
ከሰማይ ፡ በታች ፡ ያሉ ፡ ረጃጅም ፡ ተራሮችንም፡
ሁሉ፡ሸፈነ።

Scanned by CamScanner

በ፱፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሠሉስ።

፳፤ ዐሠርተ፡ወኀምስተ፡እመተ፡ተለዓለ፡መልዕልቶሙ፡ማይ።
፳፩፤ ወሞተ፡ኵሉ፡ዘሥጋ፡ወዘይትሐወስ፡ዲበ፡ምድር፡ወኵሉ፡ዕጓለ፡እመሕያው።
፳፪፤ ወኵሉ፡ዘመንፈስ፡ወኵሉ፡ዘሀሎ፡ላዕለ፡የብስ፡ሞተ።
፳፫፤ ወተደምሰሰ፡ኵሉ፡ዘይትሐወስ፡ዲበ፡ገጸ፡ለምድር፡እምዕጓለ፡እመሕያው፡እስከ፡እንስሳ፡ወአዕዋፈ፡ሰማይ፡ወተርፈ፡ኖኅ፡ባሕቲቱ፡ወእለ፡ቦኡ፡ምስሌሁ፡ውስተ፡ታቦት።
፳፬፤ ወተለዓለ፡ማይ፡መልዕልተ፡ምድር፡ምዕተ፡ወሃምሳ፡ዕለተ።

ምዕ፤፰፡፩–፳፪።

፩፤ ወተዘከሮ፡እግዚአብሔር፡ለኖኅ፡ወለኵሉ፡አራዊት፡ወለኵሉ፡እንስሳ፡ወለኵሉ፡ዘሀሎ፡ምስሌሁ፡ውስተ፡ታቦት፡ወአምጽአ፡እግዚአብሔር፡ነፋሰ፡ላዕለ፡ምድር፡ወነትገ፡ማይ።
፪፤ ወተከሥቱ፡አንቅዕተ፡ቀላይ፡ወአስራበ፡ሰማይኒ፡ተዓፅወ፡ወቆመ፡ዝናም፡እምሰማይ።
፫፤ ወአኅዘ፡ይኅልቅ፡ማይ፡ወይሑር፡እምነ፡ምድር፡ወእምድኅረ፡፻ወ፶፡ዕለት፡ሐፀ፡ማይ።
፬፤ ወነበረት፡ይእቲ፡ታቦት፡በሳብዕ፡ወርኅ፡አመ፡ዐሡሩ፡ወሰኑዩ፡ለጽልመት፡ላዕለ፡ደብረ፡አራራት።
፭፤ ወማይሰ፡የሐፅፅ፡ወይነትግ፡እስከ፡ዐሠርቱ፡ወርኅ፡ወአመ፡ኮነ፡ዐሠርተ፡ወአሐዱ፡አውራኅ፡አመ፡ርእሰ፡ሠርቀ፡ወርኅ፡አስተርአዩ፡እርእስቲሆሙ፡ለአድባር።
፮፤ ወኮነ፡እምድኅረ፡አርብዓ፡ዕለት፡አርኀወ፡ኖኅ፡መስኮታ፡ለታቦት፡እንተ፡ገብረ፡ወፈነዎ፡ለቋዕ፡ከመ፡ይርአይ፡እመ፡ነትገ፡ማይ፡እምገጸ፡ምድር።
፯፤ ወሖረ፡ወኢገብአ፡እስከ፡አመ፡ሐልቀ፡ማይ፡እምድር።
፰፤ ወፈነዋ፡ለርግብ፡እምድኅሬሁ፡ከመ፡ትርአይ፡እመ፡ነትገ፡ማይ፡እምገጸ፡ምድር።
፱፤ ወኢረከበት፡ኅበ፡ታእርፍ፡እገሪሃ፡ወገብአት፡

ማክሰኞ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

፳፤ ውኃውም፡በላያቸው፡አሥራ፡አምስት፡ክንድ፡ከፍ፡ከፍ፡አለ።
፳፩፤ ሥጋዊ፡ደማዊ፡ሁሉም፡ሞተ፤በዚህ፡ዓለም፡የሚኖረውም፡ተንቀሳቃሽ፡ሰውም፡ሁሉ።
፳፪፤ በደመ፡ነፍስ፡ሕያው፡የሆነም፡ሁሉ፡በምድር፡ላይ፡ያለው፡ሁሉ፡ሞተ።
፳፫፤ ከሰው፡ጀምሮ፡እስከ፡እንስሳ፡እስከ፡ሰማይ፡ወፎችም፡ድረስ፡በዚህ፡ዓለም፡የሚኖረው፡ሁሉ፡ጠፍቶ፡ኖኅም፡አብረውት፡በመርከብ፡ከነበሩት፡ጋራ፡ብቻውን፡ቀረ።
፳፬፤ ውኃውም፡መቶ፡ሃምሳ፡ቀን፡በምድር፡ላይ፡ከፍ፡ከፍ፡አለ።

ምዕ፤፰፡፩–፳፪።

፩፤ እግዚአብሔርም፡ኖኅን፡አሰበው፤አውሬዎችንም፡ሁሉ፡እንስሳንም፡ሁሉ፡ከእርሱ፡ጋራ፡በመርከብ፡ያለውንም፡ሁሉ፡አሰበው፤እግዚአብሔርም፡ነፋስን፡በምድር፡ላይ፡አመጣ፤ውኃውም፡ጎደለ።
፪፤ የውኃ፡ምንጮችም፡ተከፈቱ፤የሰማይም፡ፉፉቴ፡ተዘጋ፤ዝናምም፡ከሰማይ፡ተገታ።
፫፤ ውኃውም፡ከምድር፡እየጐደለ፡ይሄድ፡ጀመረ፡ውኃውም፡ከመቶ፡ሃምሳ፡ቀን፡በኋላ፡ጎደለ።
፬፤ ጨረቃ፡ሠርቅ፡ባደረገ፡ጨለማውንም፡ባጣ፡ባሥራ፡ሁለተኛው፡ቀን፡በሰባተኛው፡ወር፡በጥቅምት፡ይቺ፡መርከብ፡አራራት፡በሚባል፡ተራራ፡ላይ፡ተቀመጠች።
፭፤ ውኃው፡ግን፡እስከ፡ዐሥረኛው፡ወር፡ድረስ፡ይጎድል፡ነበር፤አሥራ፡አንድ፡ወር፡በሆነ፡ጊዜ፡በሚያዝያ፡መባቻ፡የተራሮች፡ራሶች፡ታዩ።
፮፤ ከአርባ፡ቀንም፡በኋላ፡እንዲህ፡ሆነ፤ኖኅ፡የሠራውን፡የመርከቧን፡መስኮት፡ከፈተ፤ከምድር፡ላይ፡ውኃው፡ጎድሎ፡እንደሆነ፡ያይ፡ዘንድ፡ቁራን፡ላከው።
፯፤ ከምድር፡ላይ፡ውኃው፡እስኪጎድል፡ድረስ፡ሂዶ፡አልተመለሰም።
፰፤ ከምድር፡ላይ፡ውኃ፡ጎድሎ፡እንደሆነ፡ታይ፡ዘንድ፡ከእርሱ፡በኋላ፡ርግብን፡ላካት።
፱፤ እግርዋንም፡የምታሳርፍበት፡አላገኘችም፤

| በ፱፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሠሉስ። | ማክሰኞ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት። |
|---|---|
| ኅቤሁ፡ውስተ፡ታቦት፡እስመ፡ማይ፡ሀሎ፡ውስተ፡ኵሉ፡ገጸ፡ምድር፡ወሰፍሐ፡እዴሁ፡ወነሥአ፡ውስተ፡ታቦት፡ኀቤሁ። | በምድር፡ሁሉ፡ውኃ፡አለና፡ከእርሱ፡ዘንድ፡ወደ፡መርከብ፡ተመለሰች፤እጁንም፡ዘርግቶ፡ከእርሱ፡ዘንድ፡ወደ፡መርከብ፡አገባት። |
| ፲፡ ወተዓጊሦ፡ሰቡዐ፡መዋዕለ፡ካዕበ፡ፈነዋ፡ለርግብ፡ውስተ፡ምድር፡ከመ፡ትርአይ። | ፲፡ ሰባት፡ቀንም፡ቆይቶ፡ታይ፡ዘንድ፡ዳግመኛ፡ርግብን፡ወደ፡ምድር፡ላካት። |
| ፲፩፡ ወገብአት፡ኀቤሁ፡ርግብ፡ፍና፡ሠርክ፡ወባቲ፡ውስተ፡አፉሃ፡ቈጽለ፡ዘይት፡ወአእመረ፡ኖኅ፡ከመ፡ነትገ፡ማይ፡እምድር። | ፲፩፡ ርግብም፡ማታ፡ጊዜ፡ወደ፡እርሱ፡ተመለሰች፤በአፉዋም፡የዘይት፡ቅጠል፡ነበረ፤ኖኅም፡ውኃው፡ከምድር፡እንደጎደለ፡አወቀ። |
| ፲፪፡ ወተዓጊሦ፡ካዕበ፡ሰቡዐ፡መዋዕለ፡ፈነዋ፡ለርግብ፡ወኢደገመት፡ገቢአ፡ኀቤሁ። | ፲፪፡ ሰባት፡ቀን፡ቆይቶ፡ዳግመኛ፡ርግብን፡ላካት፤እንደገናም፡ወደ፡እርሱ፡አልተመለሰችም። |
| ፲፫፡ ወአመ፡ኮነ፡ስድስተ፡ምዕተ፡ወአሐደ፡ዓመተ፡ሕይወቱ፡ለኖኅ፡አመ፡ርእሰ፡ሠርቀ፡ቀዳማይ፡ወርኅ፡ሐልቀ፡ማይ፡እምድር፡ወከሠተ፡ኖኅ፡ጠፈራ፡ለታቦት፡እንተ፡ገብረ፡ወርእየ፡ከመ፡ሐልቀ፡ማይ፡እምገጸ፡ምድር። | ፲፫፡ ኖኅ፡በሕይወት፡የኖረበት፡ዘመን፡ስድስት፡መቶ፡አንድ፡ዓመት፡በሆነ፡ጊዜ፡በመጀመሪያው፡ወር፡ከወሩም፡በመጀመሪያው፡ቀን፡ውኃው፡ከምድር፡ፈጽሞ፡ጎደለ፤ኖኅም፡የሠራውን፡የመርከቡን፡ድፍንት፡(ጣሪያ)፡ገለጠ፤ውኃውም፡ከምድር፡ላይ፡እንደጎደለ፡አየ። |
| ፲፬፡ ወበካልዕ፡ወርኅ፡አመ፡ዐሡሩ፡ወሰኑዩ፡ለጽልመት፡የብሰት፡ምድር። | ፲፬፡ ጨረቃ፡ሠርቅ፡ባደረገ፡ጨለማውን፡ባጣ፡በአሥራ፡ሁለተኛው፡ቀን፡በሁለተኛው፡ወር፡በግንቦት፡ምድር፡ደረቀች። |
| ፲፭፡ ወይቤሎ፡እግዚአብሔር፡ለኖኅ፡ፃእ፡እምነ፡ታቦት። | ፲፭፡ እግዚአብሔርም፡ኖኅን፡ከመርከብ፡ውጣ፡አለው። |
| ፲፮፡ አንተ፡ወብእሲትከ፡ወደቂቅከ፡ወአንስትያ፡ደቂቅከ፡ወኵሉ፡ዘሀሎ፡ምስሌከ። | ፲፮፡ አንተ፡ሚስትህም፡ልጆችህም፡የልጆችህ፡ሚስቶችም፡ካንተ፡ጋራ፡ያለውም፡ሁሉ። |
| ፲፯፡ ወኵሉ፡ዘሥጋ፡እምአዕዋፍ፡እስከ፡እንስሳ፡ወዘይትሐወስ፡ዲበ፡ምድር፡አውፅእ፡ምስሌከ፡ብዝኁ፡ወተባዝኁ፡ወምልዕዋ፡ለምድር። | ፲፯፡ ሥጋዊ፡ደማዊም፡ሁሉ፤ከወፎች፡ጀምሮ፡እስከ፡እንስሳ፡ድረስ፡በዚህ፡ዓለም፡የሚኖረውንም፡ተንቀሳቃሽ፡ሁሉ፡ካንተ፡ጋራ፡አውጣ፡አለው፤ብዙ፡የብዙ፡ብዙም፡ሁኑ፡ምድርንም፡ምሉዋት፡አላቸው። |
| ፲፰፡ ወወጽአ፡ኖኅ፡ወብእሲቱ፡ወደቂቁ፡ወአንስትያ፡ደቂቁ፡ምስሌሁ። | ፲፰፡ ኖኅም፡ወጣ፤ሚስቱም፡ልጆቹም፡የልጆቹም፡ሚስቶች፡ከእርሱ፡ጋራ፡ወጡ። |
| ፲፱፡ ወኵሉ፡አራዊት፡ወእንስሳ፡ወአዕዋፍ፡ወዘይትሐወስ፡ዲበ፡ምድር፡በበዘመዶሙ፡ወጽኡ፡እምታቦት። | ፲፱፡ አውሬዎችም፡ሁሉ፡እንስሳትም፡ወፎችም፡በዚህ፡ዓለም፡የሚንቀሳቀሰውም፡በየወገናቸው፡ከመርከብ፡ወጡ። |
| ፳፡ ወነደቀ፡ኖኅ፡ምሥዋዐ፡ለእግዚአብሔር፡ወነሥአ፡እምእንስሳ፡ወእምኵሉ፡ዘንጹሕ፡ወአዕረገ፡ቍርባነ፡ዲበ፡ምሥዋዑ። | ፳፡ ኖኅም፡ለእግዚአብሔር፡መሠዊያ፡የሚሠዋበትን፡ቦታ፡አዘጋጀ፤ከእንስሳት፡ንጹሕም፡ከሆነ፡ሁሉ፡አምጥቶ፡ለእግዚአብሔር፡መሥዋዕት፡በሚአቀርብበት፡ቦታ፡መሥዋዕት፡አቀረበ። |
| ፳፩፡ ወአጼነወ፡እግዚአብሔር፡መዐዛ፡ሠናየ፡ወይቤ፡እግዚአብሔር፡ኅለይኩ፡ከመ፡ | ፳፩፡ እግዚአብሔርም፡ያማረ፡የተወደደ፡መሥዋዕት፡አድርጎ፡ተቀበለው፤ከሕፃን |

በ፱፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘሠሉስ።

ኢይድግም ፡ ረጊሞታ ፡ ለምድር ፡ በእንተ ፡
ምግባሩ፡ለዕጓለ፡እመሕያው፡እስመ፡ሥዑም፡
ውስተ፡ልቦሙ፡ለዕጓለ፡እመሕያው፡እከይ፡
በኵሉ ፡ ጊዜ ፡ እምንዕሶሙ ፡ ወኢይደግም ፡
እንከ፡አማስኖቶ፡ለኵሉ፡ዘሥጋ፡ዘሕያው።

፳፪፤ በከመ፡ገበርኩ፡ኵሎ፡መዋዕሊሃ፡ለምድር፡
ዘርዕ ፡ ወማእረር ፡ ቍር ፡ ወሀፍ ፡ ሐጋይ ፡
ወክረምት ፡ መዐልት ፡ ወሌሊት ፡ ኢይት
ኀደግ።

ምዕ፱፡፩–፯።

፩፤ ወባረኮሙ፡እግዚአብሔር፡ለኖኅ፡ወለደቂቁ፡
ወይቤሎሙ፡ብዝኁ፡ወተባዝኁ፡ወምልዕዋ፡
ለምድር፡ወኰንንዋ።
፪፤ ወይፍርሁክሙ ፡ ወይርዓዱ ፡ እምኔክሙ ፡
ኵሉ፡ አራዊተ ፡ ገዳም ፡ ወአዕዋፈ ፡ ሰማይ ፡
ወእንስሳ ፡ ወዘይትሐወስ ፡ ዲበ ፡ ምድር ፡
ወዓሣተ ፡ ባሕር ፤ ወሀብኩክሙ ፡ ውስተ ፡
እዴክሙ።

፫፤ ወይኩንክሙ ፡ ለክሙ ፡ ኵሉ ፡ ዘይትሐወስ ፡
ዘሕያው ፡ ለክሙ ፡ ይኩንክሙ ፡ መብልዐ ፡
ከመ፡ ሐመልማለ ፡ ሣዕር ፡ ወሀብኩክሙ ፡
ኵሎ።
፬፤ ወባሕቱ፡ኵሎ፡ሥጋ፡ዘቦ፡ደም፡ኢትብልዑ፡
እስመ፡ደመ፡ነፍስክሙ፡ውእቱ።
፭፤ ወእትኃሠሥ ፡ እምእደ ፡ ኵሉ ፡ አራዊት ፡
ወእምኵሉ፡እደ፡ሰብእ፡ወእምእደ፡ብእሲ፡
ዘእኁሁ ፡ እትኃሠሥ ፡ ነፍሰ ፡ ኵሉ ፡ ዕጓለ ፡
እመሕያው።
፮፤ ዘከዐወ፡ደመ፡ሰብእ፡ህየንተ፡ደመ፡ዝንቱ፡
ይትከዐው፡ደሙ፡እስመ፡በአምሳለ፡እግዚአ
ብሔር፡ገበርክዎ፡ለሰብእ።

፯፤ ወአንትሙሰ ፡ ብዝኁ ፡ ወተባዝኁ ፡
ወምልዕዋ፡ለምድር።

ምሳሌያተ ፡ ሰሎሞን ፡ በረከተ ፡ አምላኩ ፡
ትኩን፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

ምዕ፲፡፩–፲፩።

፩፤ ጥበብ ፡ ሐነፀት ፡ ላቲ ፡ ቤተ ፡ ወአቀመት ፡
ሰብዓተ፡አዕማደ።

፪፤ ዘብሐት፡ዘዚአሃ፡ጥብሐ፡ወቶስሐት፡ውስተ፡

ማክሰኞ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

ታቸው፡ጀምረው፡ሁልጊዜ፡በሰዎች፡ልቡና፡
ምንም ፡ ኃጢአት ፡ ቢኖር ፡ ስለ ፡ ሰው ፡
ኃጢአት፡እግዚአብሔር፡ዳግመኛ፡ምድርን፡
እንዳላጠፋት ፡ አሰብኩ ፡ አለ ፤ እንግዲህ ፡
በደመ ፡ ነፍስ ፡ ሕያው ፡ የሆነውን ፡ ሥጋዊ ፡
ደማዊ፡ሁሉ፡ማጥፋት፡አልደግምም፡አለ።
፳፪፤ ሁሉን ፡ እንዳደረግሁ ፡ ምድር ፡ ጸንታ ፡
በኖረችው፡ዘመን፡መከርና፡ዘርእ፡ሙቀትና፡
ውርጭ፡ክረምትና፡በጋ፡ሌሊትና፡ቀን፡አያቋ
ርጥም፡አለ።

ምዕ፱፡፩–፯።

፩፤ እግዚአብሔርም ፡ ኖኅንና ፡ ልጆቹንም ፡
መረቃቸው ፤ ብዙ ፡ ተባዙ ፡ ምድርንም ፡
ምሏት፤ግዟትም፡አላቸው።
፪፤ ከእናንተ ፡ የተነሣ ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ ያሉ ፡
አውሬዎች፡ሁሉ፡ይፍሩአችሁ፤ይንቀጥቀጡ
ላችሁ፤እንስሳትንና፡በሰማይ፡ያሉ፡ወፎችን፡
በባሕር ፡ ያሉ ፡ ዓሣዎችንና ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡
የሚኖሩ ፡ ተንቀሳቃሾችን ፡ ሁሉ ፡ በእጃችሁ ፡
ሰጠኋችሁ፡አለ።
፫፤ በደመ ፡ ነፍስ ፡ ሕያው ፡ የሆነውን ፡ ተንቀሳ
ቃሹን ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ እህል ፡ ፍሬ ፡ ምግብ ፡
ይሆናችሁ፡ዘንድ፡ሁሉን፡ሰጠኋችሁ፡አለ።

፬፤ ነገር፡ግን፡ደም፡ሕይወታችሁ፡ነውና፡ደም፡
ያለውን፡ሥጋ፡ሁሉ፡አትብሉ፡አላቸው።
፭፤ ከአውሬዎችም፡ሁሉ፡እጅ፡ከሰውም፡እጅ፡
ሁሉ ፡ ወንድሙ ፡ ከሚሆን ፡ ሰው ፡ እጅ ፡
የሰውን፡ሁሉ፡ሰውነት፡እሻለሁ፡አላቸው።

፮፤ ሰውን ፡ በእኔ ፡ አምሳል ፡ ፈጥሬዋለሁና ፡
የሰውን ፡ ደም ፡ ያፈሰሰ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ስለ ፡
አፈሰሰው፡ስለዚያ፡ሰው፡ደም፡ፈንታ፡ደሙ፡
ይፈስሳል፡አላቸው።
፯፤ እናንተ ፡ ግን ፡ ብዙ ፡ የብዙ ፡ ብዙም ፡ ሁኑ ፤
ምድርንም፡ምሉአት፡አላቸው።

የሰሎሞን፡የምሳሌ፡ነገር፡የፈጣሪው፡በረከት፡
ከሁላችን፡ጋራ፡ትሁን፡ለዘላለሙ፡አሜን።

ምዕ፲፡፩–፲፩።

፩፤ ጥበብ ፡ ወልድ ፡ ለእሷ ፡ ቤትን ፡ ሠራች ፡
(ፈጠረች) ፤ ሰባት ፡ ምሰሶቿንም ፡ ሰባቱን ፡
ዕለታት፡አቆመች።
፪፤ የሷን ፡ እርድ ፡ አረደች ፤ የሚበላውንም ፡

Scanned by CamScanner

| በ፱፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘሠሉስ። | ማክሰኞ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት። |
|---|---|
| ስያሓ ፡ ዘዚአሃ ፡ ወይነ ፡ ወአስተዳለወት ፡ ዘዚአሃ፡ማዕደ። | (ፈጠረች) ፤ ወይኗን ፡ በማድጋዋ ፡ ጨመረች፤ የሚጠጣውን ፡ ፈጠረች ፡ ማዕዷንም ፡ አዘጋጀች። |
| ፫፡ ወፈነወት ፡ ዘዚአሃ ፡ አግብርተ ፡ እንዘ ፡ ትጼውዕ፡በነዋኅ፡ሰብከት። | ፫፡ ብዙ ፡ ትምህርትን ፡ ለማስተማር ፡ ሰውን፤ ለመጥራት፡ባሮቿን፡ፀሐይ፡ጨረቃን፡ላከች። |
| ፬፡ እንዘ፡ትብል፡ዘአብድ፡ውእቱ፡ይትገኃሥ፡ ኀቤየ፡ወለእለሂ፡የሐፆሙ፡አእምሮ። | ፬፡ አላዋቂ ፡ የሆነ ፡ ከእኔ ፡ ዘንድ ፡ ይወገድ፤ ዕውቀት፡ያነሳቸውም። |
| ፭፡ ትቤ ፡ ንዑ ፡ ብልዑ ፡ ኅብስትየ ፡ ወስትዩ ፡ ወይንየ፡ዘቀዳሕኩ፡ለክሙ። | ፭፡ እንጀራዬን ፡ መጥታችሁ ፡ ብሉ ፤ የቀዳሁላችሁንም ፡ ወይኔን ፡ ጠጡ ፡ ስትል ፡ ፀሐይ፡ ጨረቃን፡ላከች። |
| ፮፡ ወኅድግዋ ፡ ለእበድ ፡ ወኅሡ ፡ አእምሮ ፡ ከመ ፡ ትሕየዉ። | ፮፡ ስንፍናን ፡ ተዋት ፤ በሕይወትም ፡ ትኖሩ፡ ዘንድ፡ዕውቀትን፡ፈልጉ። |
| ፯፡ አርትዑ፡አእምሮ፡በጠይቆ፡ወዘይሚህሮሙ፡ ለዕኩያን፡ይነሥእ፡ሎቱ፡ኀሣረ። | ፯፡ በመረዳት፡ዕውቀትን፡አቅንታችሁ፡ተማሩ፤ ክፉዎች ፡ ሰዎችን ፡ የሚአስተምር ፡ ሰው፡ ውርደትን፡ይቀበላል። |
| ፰፡ ወዘይጌሥፆ፡ለረሲዕ፡የሐይስ፡ርኵሶ። | ፰፡ እግዚአብሔርን ፡ የዘነጋውን ፡ ሰው ፡ የሚአስ ተምር፡ራሱን፡ያስነቅፋል። |
| ፱፡ ኢትዝልፎሙ ፡ ለአብዳን ፡ ከመ ፡ ኢይጽ ልኡከ። | ፱፡ እንዳይጠሉህ ፡ ሰነፎች ፡ ሰዎችን ፡ አታስተም ራቸው፤አትዝለፋቸው። |
| ፲፡ ዝልፎ ፡ ለጠቢብ ፡ ወያፈቅረከ ፡ አብድሰ ፡ ይጸልአከ ፡ ሀቦ ፡ ለጠቢብ ፡ ምክንያተ ፡ ወያፈ ደፍድ፡ጥበበ፡አእምሮ፡ለጠቢብ፡ወይዌስክ፡ ተወክፎ። | ፲፡ ብልህን ፡ ሰው ፡ አስተምረው ፤ ይወድሃል፤ አላዋቂ ፡ ግን ፡ ብትመክረው ፡ ይጠላሃል፤ ለብልህ ፡ ሰው ፡ ምክንያትን ፡ ስጠው ፡ ዕውቀ ትንና፡ጥበብን፡ያበዛል፤ለብልህ፡ሰው፡አመል ክተው፡በጥበብ፡ላይ፡ጥበብን፡ይጨምራል። |
| ፲፩፡ ቀዳሚሃ ፡ ለጥበብ ፡ ፈሪሃ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወምክረ ፡ ቅዱሳን ፡ አእምሮ ፡ ወአእምሮ ፡ ሕግሰ፡ለልብ፡ኄር፡ውእቱ። | ፲፩፡ የጥበብ ፡ መጀመሪያ ፡ እግዚአብሔርን ፡ መፍ ራት፡ነው፤የቅዱሳንም፡ምክር፡ዕውቀት፡ነው፤ ሕግን፡ማወቅ፡ግን፡ለበጎ፡ልቡና፡ስምም፡ነው። |
| ፲፪፡ በዝ፡ሥርዓት፡ብዙኀ፡መዋዕለ፡ተሐዩ፡ወይ ትዌሰካከ፡ዓመታተ፡ሕይወትከ። | ፲፪፡ በዚህ ፡ ሥርዓት ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ ትኖራለህ፤ በሕይወት ፡ የምትኖርባቸው ፡ ዘመኖችም ፡ ይጨመሩልኻል። |
| ትርጓሜ፡ምሳሌያተ፡ሰሎሞን። | የሰሎሞን፡ምሳሌ፡የምሥጢር፡ትርጓሜ። |
| ፩፡ ይቤ፡መተርጕም፡ጥበብ፡ሐነፀት፡ላቲ፡ቤተ፡ ይብል። | ፩፡ ጥበብ፡ለራስዋ፡ቤትን፡ሠራች፡አለ። |
| ፪፡ በእንተ ፡ ጥበብ ፡ ለኀበ ፡ ወልድ ፡ እግዚእነ ፡ ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ ወሕንጻ፡ቤትኒ፡ውእቱ፡ ቤተ፡ክርስቲያን፡ቅድስት፡ዘረሰያ፡መርሶ፡ መድኃኒቶሙ፡ለመሀይምናን፡ቦቱ። | ፪፡ ጥበብ ፡ ያለው ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ፤ የእግዚአብሔር፡ልጅ፡ የቤቱም፡ሕንፃ፡ለምእ መናን ፡ የድኅነታቸው ፡ ወደብ ፡ ያደረጋት፤ የከበረች ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መሆንዋን፤ ያስረዳል፡በማለት፡ተርጓሚው፡ተናገረ። |
| ፫፡ ይቤ ፡ ወአቀመት ፡ ላቲ ፡ ሰብዓተ ፡ አዕማደ ፡ ይብል ፡ በእንተ ፡ ሰብዓቱ ፡ አዕማድ ፡ እንበይነ ፡ ሰብአቱ ፡ ሠራዊታት ፡ እንተ ፡ | ፫፡ ሰባት፡ምሰሶዎችን፡አቆመች፡አለ፤ሰባትም፤ ምሰሶዎች ፡ ያለውን ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን፤ ውስጥ፡ስለተሠሩት፡ስለ፡ሰባቱ፡ሠራዊቶች፤ |

Scanned by CamScanner

## በ፱፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘሠሉስ።

ውስተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እሉ ፡ እሙንቱ ፡ መዓርጋተ፡ክህነት።

፩፤ ይቤ፡ዘብሔት፡ዝብሐታተ፡ወአስተዳለወት፡ማእደ ፡ ይብል ፡ በእንተ ፡ ውእቱ ፡ ሥጋሁ ፡ ወደሙ ፡ ለክርስቶስ ፡ ዘረሰዮ ፡ መድኃኒተ ፡ ለሕዝብ፡በውስተ፡ቤተ፡ክርስቲያን፡ህየንተ፡ጥብሐት፡ዘለደቂቀ፡እስራኤል።

፪፤ ይቤ፡ወፈነወት፡አግብርቲሃ፡ከመ፡ይጸውዑ፤ በልዑል ፡ ስብከት ፡ ይብል ፡ ዘንተ ፡ ከመ ፡ ለእመ ፡ ቦ ፡ እምኔክሙ ፡ አብድ ፡ ለይምጻእ ፡ ኀቤየ ፡ ይብል ፡ በእንተ ፡ አግብርት ፡ ለኀበ ፡ ካህናተ ፡ እግዚእ ፡ ዘረሰዮሙ ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወአዘዞሙ ፡ ከመ ፡ ኢያፅርዑ ፡ በኵሉ፡ጊዜ፡እምትምህርተ፡አሕዛብ፡ከመ፡ይሑር፡እምኔሆሙ፡እበድ፡በአዝልፎ፡ትምህርታት።

፫፤ ወይደሉ ፡ ለካህናት ፡ ካዕበ ፡ ከመ ፡ ይዋሕዩ ፡ ግብራተ ፡ መርዔቶሙ ፡ ወለእመ ፡ ኮነ ፡ ለዝሉፉ፡ ውስተ ፡ ኃጣይአ ፡ ወእበድ ፡ እምውስተ ፡ መድኃኒተ ፡ ነፍሱ ፡ ወይኒጥዎ ፡ ከመ ፡ ይትወለጥ ፡ እምእልኩ ፡ ግብራት ፡ ወይጹር፡አርዑቶ፡ለክርስቶስ፡ቀሊለ፡ወመዐርዒረ።

፬፤ ይቤ ፡ ወእብሎሙ ፡ ንዑ ፡ ብልዑ ፡ እምኅብስትየ ፡ ወስትዩ ፡ እምወይንየ ፡ ዘቱሱሕ ፡ ይብል፡እምከመ፡መዐድዎሙ፡ካህናት፡ለመርዔቶሙ ፡ ወአግኀሥዎሙ ፡ እምኀጣይአ ፡ ሶቤሃ ፡ ይመጥውዎሙ ፡ እምሥጋሁ ፡ ለእግዚእነ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ወደሙ፡ክቡር።

፭፤ ይቤ ፡ ወኅድግዋ ፡ እምኔክሙ ፡ ለእበድ ፡ ከመ ፡ ትሕየዉ ፡ ይብል ፡ ዘይትሜጦ ፡ እምሥጋሁ፡ወደሙ፡ለእግዚእነ፡ኢይግባእ፡ኀበ ፡ እበድ ፡ ዘኃጢአት ፡ ዳእሙ ፡ ይኩን ፡ ለዝሉፉ ፡ ኃሣሤ ፡ ፈቃዱ ፡ ለክርስቶስ ፡ እስመ ፡ ኢይመውት ፡ እንከሰ ፡ ውእቱ ፡ በሞተ ፡ ኃጢአት ፡ በከመ ፡ ይቤ ፡ እግዚእነ ፡

## ማክሰኞ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

ይናገራል ። እነዚህም ፡ ሰባቱ ፡ ማዕርጋተ ፡ ክህነት ፡ ናቸው ፤ ከሊቀ ፡ ጳጳስ ፡ እስከ ፡ ዓፃዊ ፡ ኖኅት።

፩፤ እርዷን፡አረደች፤ማእድንም፡አዘጋጀች፡አለ፤ ስለዚህም ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ያርዱት ፡ በነበረው፡ፈንታ፡በቤተ፡ክርስቲያን፡ውስጥ፡የሚሠዋው ፡ ለሕዝቡም ፡ መድኃኒት ፡ ያደረገው ፡ ስለ ፡ ክርስቶስ ፡ ሥጋውና ፡ ደም ፡ ይናገራል።

፪፤ በከፍተኛ ፡ ትምህርት ፡ ይጠሩ ፡ ዘንድ ፡ ባሮቿን፡ ላከች ፡ አለ ፤ ይህንም ፡ ከእናንተ ፡ ውስጥ፡ሰነፍ፡አላዋቂ፡ካለ፡ወደእኔ፡ይምጣ፡ ይላል ፤ ባሮች ፡ ስለሚለው ፡ ሁልጊዜ ፡ ሕዝቡን፡ከማስተማር፡እንዳያቋርጡ፡ትምህርትን ፡ በማዘውተር ፡ ድንቁርና ፡ ከሕዝቡ ፡ ይርቅ ፡ ዘንድ ፡ ያዘዛቸውና ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን፡ የሾማቸው ፡ የጌታ ፡ ካህናት ፡ እንደ ፡ ሆኑ፡ይናገራል።

፫፤ የመንጋዎቻቸውን፡ተግባራት፡መጕበኘት፡ ለካህናት ፡ ይገባል ፤ ምእመኑም ፡ ወደኃጢአትና ፡ ወደስንፍና ፡ የሚአዘወትር ፡ ከሆነና ፡ ከነፍሱ፡ድኅነት፡ቢርቅ፡ከእነዚህ፡ሥራዎቹ፡ ተለውጦ፡እንደ፡አምባር፡ጌጥ፡የሚሆን፡የክርስቶስን ፡ ቀላል ፡ ቀንበር ፡ ይሸከም ፡ ዘንድ ፡ ቅንነት፡የዋህነት፡ባለው፡በለሰለሰ፡ቃል፡ያስተምሩት።

፬፤ ኑ ፡ ከእንጀራዬ ፡ ብሉ ፤ ከተጨመረውም ፡ ወይኔ፡ጠጡ፡እላቸዋለሁ፡አለ፤ካህናቱ፡ምእመናኑን ፡ አስተምረው ፡ ከኃጢአት ፡ ከለዩአቸው ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ከጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ፡ከቅዱስ፡ሥጋውና፡ከክቡር፡ደሙ፡ይስጡአቸው፡ማለቱ፡እንደ፡ሆነ፡ይናገራል።

፭፤ በሕይወት፡ትኖሩ፡ዘንድ፡ከእናንተ፡ስንፍናን፡ ተውዋት ፡ አለ ፤ ይህም ፡ የጌታችንን፡ ሥጋውንና ፡ ደሙን ፡ የተቀበለ ፡ የኀጢአት ፡ ወደሆነ ፡ ድንቁርና ፡ እንዳይመለስ፡ ክርስቶስ ፡ ፈቅዶ፡የሠራውን፡ሕገ፡ወንጌልን፡ለዘወትር፡ የሚሻ ፡ ይሁን ፡ እንጂ ፡ ጌታችን ፡ ክርስቶስ ፡ ሥጋዬን፡የበላ፡እኔ፡ሕያው፡እንደሆንኩ፡ስለ፡ እኔ ፡ ሕያው ፡ ሁኖ ፡ ለዘላለሙ ፡ ይኖራል ፡

## በ፱፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘሠሉስ።

ክርስቶስ፡እመቦ፡ዘበልዐ፡ሥጋየ፡ውእቱ፡
የሐዩ፡በእንቲአየ።
፱፡ ወዓዲ፡ያጠሪ፡አእምሮታተ፡መንፈሳውያተ፡
ወይትጋደል ፡ ምስለ ፡ ዝኩ ፡ አእምሮ ፡
ለኀሢሥ፡ትሩፋተ።
፲፡ ወበእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ይርኅቅ ፡ ውእቱ ፡ እምጽ
ልመተ፡እበድ፡ወየሐዩ፡በብርሃን፡ጽድቅ።

፲፩፡ ይቤ ፡ ኅሡ ፡ ጥበበ ፡ ከመ ፡ ተሀልዉ ፡ ይብል ፡
እስመ ፡ እምከመ ፡ ኅሠሠ ፡ ብእሲ ፡ አእምሮ ፡
ወተጋደለ ፡ በእንተ ፡ አጥርዮቱ ፡ እስመ ፡
ኢይወድቅ ፡ ውእቱ ፡ እስከ ፡ ለዓለም ፡ በከመ ፡
ይቤ ፡ በወንጌል ፡ ቅዱስ ፡ በእንተ ፡ ዘሐነጸ ፡
ቤቶ፡ዲበ፡ኰኵሕ።
፲፪፡ ይቤ፡ዘይሜህሮሙ፡ለእኩያን፡ያኀስር፡ርእሶ፡
ይብል፡ዘንተኒ፡ዘይከሥት፡ምሥጢረ፡አምላ
ካዊተ ፡ ለእለ ፡ ኢኮኑ ፡ ምእመናነ ፡ እስመ ፡
እሙንቱ፡ይትሄየዩ፡ኪያሃ።

፲፫፡ ወበእንተ፡ውእቱኬ፡ይብል፡ወንጌል፡ቅዱስ፡
ኢተሀቡ፡ቅድሳተ፡ለከለባት፡ወኢትደዩ፡ባሕ
ርየክሙ፡ቅድመ፡አኅርው።
፲፬፡ ወበተፍጻሜቱ ፡ ለዝ ፡ ይቤ ፡ ሀቦ ፡ ለጠቢብ ፡
ምክንያተ ፡ ከመ ፡ ይወስክ ፡ ጥበበ ፡ ይብል ፡
ለለኵሉ ፡ ዘከሠትከ ፡ ጥበበ ፡ ለምእመናን ፡
ዘበሕገ ፡ ክርስቶስ ፡ አእምሮታተ ፡ መንፈሳ
ውያተ ፡ እስመ ፡ እሙንቱ ፡ ይዌስኩ ፡ ጥበበ ፡
ላዕለ፡ጥበቢሆሙ።
፲፭፡ ወበእንተ ፡ ውእቱ ፡ ይቤ ፡ ወንጌል ፡ ቅዱስ ፡
እስመ፡ለዘቦ፡ይሁብዎ፡ወይዌስክዎ።
፲፮፡ ይቤ ፡ ቀዳሚሃ ፡ ለጥበብ ፡ ፈሪሀ ፡ እግዚአ
ብሔር፡ ይብል ፡ ከመ ፡ ኢይግበር ፡ ብእሲ ፡
ትሩፋተ ፡ ለኀሢሠ ፡ዘኮነ ፡ እምግባራተ ፡
ዓለም፡ ዳእሙ ፡ ይኩን ፡ በኵሉ ፡ ግብራቲሁ ፡
ፈራሄ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወኀሣሤ ፡ ፈቃዱ ፡
ወበእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ይከውኑ ፡ ሎቱ ፡ ኵሎሙ ፡
ፈቃዳቲሁ።
፲፯፡ ይቤ ፡ ምክረ ፡ ቅዱሳን ፡ ይዌስክ ፡ አእምሮ ፡
ይብል ፡ በእንተ ፡ ውእቱ ፡ እስመ ፡ ለብእሲ ፡
ኢይደሉ ፡ ከመ ፡ ይትመየጥ ፡ በፈቃደ ፡ ርእሱ ፡
ዳእሙ ፡ ይትሐት ፡ ወይሕትት ፡ መምህረ ፡

## ማክሰኞ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

እንዳለ ፡ እንግዲህ ፡ በኃጢአት ፡ ሞት ፡ አይቆ
ትምና።
፱፡ ዳግመኛም ፡ ረቂቁን ፡ ዕውቀት ፡ ገንዘብ ፡
አድርጎ ፡ ትሩፋትን ፡ ለመሥራት ፡ ከዚህ ፡
ዕውቀቱ፡ጋራ፡ተጋድሎ፡ያደርጋል።
፲፡ ስለዚህም ፡ በስንፍና ፡ ከሚመጣ ፡ ድንቁርና፡
ርቆ ፡ በመንፈሳዊ ፡ ዕውቀት ፡ ሕያው ፡ ሁኖ፡
ይኖራል።
፲፩፡ ሕያው ፡ ሁናችሁ ፡ እንድትኖሩ ፡ ዕውቀትን፡
ፈልጉ ፡ አለ ፤ ሰው ፡ ዕውቀትን ፡ ከፈለገና፡
እርሷን፡ገንዘብ፡ለማድረግ፡የተጋ፡እንደሆነ፡
ለዘላለሙ ፡ እርሱ ፡ አይወድቅምና ፡ ቤቱን፡
በጭንጫ፡ላይ፡የሠራ፡ሰው፡ሕንጻው፡ጸንቶ፡
እንዲኖር፡በቅዱስ፡ወንጌል፡እንደ፡ተነገረ።
፲፪፡ ክፉዎችን፡የሚአስተምር፡ራሱን፡ያዋርዳል፡
አለ፤ይህንም፡አማኞች፡ላልሆኑ፡ከሀዲዎች፡
አምላካዊ፡መሥጢርን፡የሚገልጽ፡እነርሱ፡
ያቃልሉታልና፡ራስ፡የተባለ፡ጌታን፡ስለሚአ
ሰድብ፡ነው።
፲፫፡ ስለዚህም ፡ ቅዱስ ፡ ወንጌል ፡ የተቀደሰውን፡
(ቍርባን) ፡ ለውሾች ፡ አትስጡ ፤ ዕንቈኛ
ሁንም፡በእሪያዎች፡ፊት፡አታኑሩ፡ይላል።
፲፬፡ በዚህም ፡ ወደመጨረሻው ፡ ለብልህ ፡ ምክን
ያትን ፡ ስጠው ፤ ጥበብን ፡ ይጨምራል ፡ አለ፤
በክርስቶስ፡ሕግ፡ወንጌል፡አማኞች፡ለሆኑት፡
ዕውቀትን ፡ በምታስተምራቸው ፡ መጠን፡
ሁሉ፡እነርሱ፡መንፈሳዊ፡ዕውቀትን፡በዕውቀ
ታቸው፡ላይ፡ይጨምራሉና።
፲፭፡ ስለዚህም ፡ ቅዱስ ፡ ወንጌል ፡ ላለው ፡
ይሰጡታል፡ይጨምሩለታልም፡ይላልና።
፲፮፡ የዕውቀት ፡ መጀመሪያ ፡ እግዚአብሔርን፡
መፍራት ፡ ነው ፡ አለ ፤ ከዓለም ፡ የሆኑ ፡
ሥራዎችን ፡ ለመሥራት ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡
የሚፈልግ፡እንዳይሆን፡ይናገራል፤ነገር፡ግን፡
በሥራው፡ሁሉ፡እግዚአብሔርን፡የሚፈራና፡
ሕጉን ፡ የሚሻ ፡ ይሁን ፡ እንጂ ፡ ስለዚህም፡
የሚሻው፡ሁሉ፡ይፈጸምለታል።
፲፯፡ የቅዱሳን ፡ መምህራን ፡ ምክር ፡ ዕውቀትን፡
ይጨምራል ፡ አለ ፤ ስለዚህም ፡ ሰው ፡ ያለኝ፡
ዕውቀት ፡ በቃኝ ፡ ብሎ ፡ በራሱ ፡ ፈቃድ፡
ይመለስ፡ዘንድ፡አይገባም፤ነገር፡ግን፡ራሱን፡

Scanned by CamScanner

## በ፱፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሠሉስ።

ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በዘቦቱ ፡ ይከውን ፡ መድኀኒተ ፡ ነፍሱ ፡ እስመ ፡ ምክሮሙ ፡ ለአበው ፡ መምህራን ፡ ትሜህሮ ፡ ለብእሲ ፡ መድኃኒተ ፡ ነፍሱ ፡ ወትዌስኮ ፡ አእምሮ ፡ በእንተዝ ፡ ዘኀለፈ ፡ ወበእንተዝ ፡ ዘይመጽእ።

፲፰፤ ይቤ፡ወአእምሮ፡ሕግሰ፡ኄር፡ውእቱ፡ለልብ፡ ይብል ፡ በእንተ ፡ ሕግሰ ፡ ለኀበ ፡ ውሳንያተ ፡ እግዚእ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘወሰና ፡ እምትእዛዛት ፡ ወኀድገታት ፡ ወትኩን ፡ ኀሊናሁ ፡ ለብእሲ ፡ ምዩጠ ፡ እምኑናት ፡ ለዝሉፉ ፡ ወኀሢሥ፡ትሩፋት።

፲፱፤ ይቤ ፡ ከመ ፡ ትሕየው ፡ በዝንቱ ፡ ሥርዓት ፡ ሕይወተ ፡ ነዋኀ ፡ ወይትዌሰካከ ፡ ዓመታተ ፡ ሕይወትከ ፡ ይብል ፡ እስመ ፡ ለእመ ፡ ኮነ ፡ ብእሲ፡ የሐውር ፡ በትእዛዘ ፡ እግዚሉ ፡ ወኀሣሤ፡ ትሩፋት ፡ እስመ ፡ ሕይወት ፡ ይትወሀብ ፡ ሎቱ ፡ ወኢየሀጕል ፡ እምኔሁ ፡ ምንተኒ ፡ በአሙቶቱ ፡ ለኃጢአት ፡ ወዘሰ ፡ የሐዩ ፡ ውስተ ፡ ኃጢአት ፡ እስመ ፡ ምውት ፡ ውእቱ፡ወለእመኒ፡ኮነ፡ሕያወ፡እስመ፡ናሁ፡ ኀጽረ፡ሕይወቱ፡በኃጢአት።

፳፤ ወንስአሎ ፡ እንከ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ከመ ፡ ይርድአነ ፡ ለገቢረ ፡ ፈቃዱ ፡ ወናሥምሮ ፡ ወትረ ፡ በሃይማኖት ፡ ዘክርስቶስ ፡ ሎቱ ፡ ስብሐት ፡ ይእዜኒ ፡ ወዘልፈኒ ፡ ወለዓለመ ፡ ዓለም፡አሜን።

ዘኢሳይያስ፡ነቢይ፡በረከቱ፡ትኩን፡ምስሌነ፡ ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

ምዕ፣፵፣፱–፲፩።

፱፤ ውስተ ደብር ፡ ነዋኀ ፡ ይዕርግ ፡ ዘይዜንዋ ፡ ለጽዮን፡ክላህ፡በኀይልከ፡ወአንሥእ፡ቃለከ፡ ወዜንዋ፡ለኢየሩሳሌም።

፲፤ ክልሑ፡ወኢትፍርሁ፡ወበልዎሙ፡ለአህጉረ፡ ይሁዳ፡ነዋ፡አምላክክሙ።

## ማክሰኞ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

ዝቅ፡አድርጎ፡ለነፍሱ፡ድኅነት፡በሚሆንለት፡ ገንዘብ ፡ ከቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሊቅ ፡ ይማር ፡ እንጂ ፤ የአባቶች ፡ መምህራን ፡ ምክራቸው ፡ ለሰው ፡ የነፍሱን ፡ ድኅነት ፡ ታስተምረዋለችና፡ ላለፈውም ፡ ሆነ ፡ ለሚመጣው ፡ የነፍሱን፡ድኅነት፡የሚአገኝበትን፡ዕውቀት፡ ትጨምርለታለችና፡ይላል።

፲፰፤ ሕግን ፡ ማወቅ ፡ ግን ፡ ለበጎ ፡ ልቡና ፡ ስምም ፡ ነው ፡ አለ ፤ ስለ ፡ ሕግም ፡ ሲናገር ፡ ከሚተዉትና፡ ከማይተዉት ፡ ገዥ ፡ እግዚአብሔር ፡ የወሰናትን ፡ ውሳኔ ፡ በማመልከት ፡ የሰው ፡ ልቡናው ፡ ከተናቀ ፡ የኃጢአት ፡ ሥራ ፡ ለዘወትር፡ተመልሶ፡ትሩፋትን፡ለመሥራት፡ የሚፈልግ፡ይሆን፡ዘንድ፡ይናገራል።

፲፱፤ በዚህ ፡ ሥርዓት ፡ ረጂም ፡ ዘመን ፡ በሕይወት ፡ ትኖር ፡ ዘንድ ፡ በሕይወት ፡ የምትኖርባቸው ፡ ዘመናት፡ይጨመሩልሃል፡አለ፤ሰው፡በጌታ፡ ትእዛዝ፡ጸንቶ፡የሚኖርና፡ትሩፋትን፡የሚሻ፡ የሆነ፡እንደሆነ፡ኃጢአትን፡ድል፡በመንሳቱ፡ ሕይወት፡ይሰጠዋልና፡ምንም፡ምን፡አይጠፋ በትምና፡በኃጢአት፡ሥራ፡ውስጥ፡የሚኖር፡ ግን፡የሞተ፡ነውና፡ሕያውም፡የሆነ፡ቢኖር፡ እነሆ፡በኃጢአት፡ሕይወቱን፡አሳጥሮአልና፡ ይላል።

፳፤ እንግዲህ፡የሚወደውን፡ለመሥራትና፡ክርስቶስን ፡ በማመን ፡ ጸንተን ፡ ዘወትር ፡ እናገለግለው፡ዘንድ፡እንዲረዳን፡እግዚአብሔርን፡ እንለምነው ፤ ዛሬም ፡ ዘወትርም ፡ ለዘላለሙ ፡ ለእርሱ፡ምስጋና፡ይሁን፡አሜን።

የነቢዩ፡ኢሳይያስ፡ትንቢት፡በረከቱ፡ከእኛ፡ ጋራ፡ለዘላለሙ፡ትሁን፤አሜን።

ምዕ፣፵፣፱–፲፩።

፱፤ ለጽዮን ፡ ወሬ ፡ የሚነግራት ፡ ሰው ፡ ወደ ፡ ረጅም ፡ ተራራ ፡ ይውጣ ፤ አሰምተህ ፡ አስተምር ፤ ቃልህንም ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አድርገህ ፡ ለኢየሩሳሌም፡ንገራት።

፲፤ አስተምሩ ፤ አትፍሩም ፤ የይሁዳንም ፡ ሰዎች ፡ እነሆ ፡ ፈጣሪያችሁ ፡ በረድኤት ፡ ይመጣል ፡ በሏቸው።

| በ፱፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘሠሉስ። | ማክሰኞ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት። |
|---|---|
| ፲፩፡ ነዋ፡**እግዚአብሔር፡አምላክክሙ፡**ይመጽእ፡ ምስለ፡ኃይሉ፡ወይኴንን፡በመዝራዕቱ፡ ወነዋ፡ዕሴቱ፡ምስሌሁ፡ወምግባሩ፡ቅድመ፡ ገጹ። | ፲፩፡ እነሆ፡**ፈጣሪያችሁ፡እግዚአብሔር**፡ከመላ እክት፡ጋራ፡ይመጣል፤በሥልጣኑም፡ ይፈርዳል፤እነሆ፡ዋጋው፡ከሱ፡ጋራ፡አለ፤ ሥራውም፡በፊቱ፡ነው። |
| ፲፪፡ ከመ፡ኖላዊ፡ዘይርዒ፡አባግዒሁ፡ወያስተጋ ብአሙ፡ለአባግዕ፡በመዝራዕቱ፡ወያስተፌ ሥሖን፡ለጽኑሳት። | ፲፪፡ እረኛ፡በጎቹን፡ሰብስቦ፡እንደሚጠብቅ፤ በሥልጣኑ፡በጎቹን፡(ወገኖቹን)፡ይሰበስባል፤ የተቸገሩትንም፡ሰዎች፡ደስ፡ያሰኛቸዋል። |
| ፲፫፡ መኑ፡ዘሰፈሮ፡ለማይ፡በሕፍኑ፡ወለሰማይኒ፡ በስዝሩ፡ወዘአኀዛ፡ለኵላ፡ምድር። | ፲፫፡ ውኃን፡በእፍኙ፡የሰፈረው፡ማን፡ነው?፡ሰማይ ንስ፡በስንዝሩ፡የለካው፡ማን፡ነው?ይኸቺን፡ዓለ ምስ፡ሁሉ፡በመኻል፡እጁ፡የያዛት፡ማን፡ነው? |
| ፲፬፡ መኑ፡አቀሞሙ፡ለአድባር፡በመዳልው፡ወለአ ውግርኒ፡በመድሎት። | ፲፬፡ ኮረብቶችንና፡ተራሮችንስ፡በሚዛን፡የመዘ ናቸው፡ማን፡ነው?እኔ፡አይደለሁምን? |
| ፲፭፡ መኑ፡አእመረ፡ኅሊናሁ፡**ለእግዚአብሔር፡** ወመኑ፡መማክርቲሁ፡ዘአምከሮ። | ፲፭፡ **የእግዚአብሔርን፡**ሐሳብ፡ማን፡አወቀ?የመከ ረውስ፡መካሩ፡ማን፡ነው? |
| ፲፮፡ ወምስለ፡መኑ፡ተማከረ፡ወአምከሮ፡ወመኑ፡ አርአዮ፡ፍትሐ፡ወፍኖተ፡ጥበብኒ፡መኑ፡ አርአዮ። | ፲፮፡ ከማን፡ጋር፡ተማከረ? ማንስ፡መከረው? ፍርድንስ፡ማን፡ገለጠለት?የጥበብንስ፡ጎዳና ማን፡አሳየው? |
| ፲፯፡ ኵሎሙ፡አሕዛብ፡ከመ፡ነጥበ፡ማኅየብ፡ እሙንቱ፡ወከመ፡እንተ፡ታገብእ፡ዓይነ፡ መዳልው፡እሙንቱ፡ወከመ፡ወኢምንት፡ እሙንቱ። | ፲፯፡ አሕዛብ፡ሁሉ፡በሱ፡ዘንድ፡እንደአብሽት፡ ጠብታ፡ናቸው።የሚዛን፡ውልብልቢትን፡ እንደምትመልስ፡ናቸው።እንደ፡ኢምንትም፡ ናቸው። |
| ፲፰፡ ወኢየአክል፡ሊባኖስ፡ለአንድዶ፡ወኵሉ፡ እንስሳ፡ኢየአክል፡ለአቃርዮ። | ፲፰፡ የደጋውም፡እንጨት፡ለማንደድ፡አይበቃም፤ ከብቱም፡ሁሉ፡ለመሠዋት፡አይበቃም። |
| ፲፱፡ ወኵሎሙ፡አሕዛብ፡ከመ፡ዘኢሀለዉ፡ ወከመ፡ወኢምንት፡ይመስሉ። | ፲፱፡ አሕዛብ፡ሁሉ፡ሳሉ፡እንደሌሉ፡ናቸው፤ እንደ፡ኢምንትም፡ናቸው። |
| ፳፡ በመኑ፡ታስተማስልዎ፡**ለእግዚአብሔር፡**ወበ አምሳለ፡መኑ፡ታስተዔርይዎ። | ፳፡ እንዲህ፡ያለውን፡**ፈጣሪ፡**በማን፡ትመስሉታ ላችሁ?ማንስ፡በመሰለው፡ምስል፡ታስተካክ ሉታላችሁ። |
| ፳፩፡ በምስልኑ፡ዘገብሮ፡ጸራቢ፡ወሚመ፡ በወርቅኑ፡ዘሰበኮ፡ነሀቢ፡ወዘቀፈሎ፡ በወርቅ፡ወገብሮ፡ወመሰሎ። | ፳፩፡ ዕንጨት፡ጠራቢ፡በሠራው፡ምስል፡ትመስሉ ታላችሁን? ወይስ፡አንጥረኛ፡መትቶ፡በሠ ራው፡ወርቅ፤ወርቅንም፡በለበጠው፡መስለም፡ በሠራው፡ምስል፡ትመስሉታላችሁን? |
| ፳፪፡ እስመ፡ዕፀ፡ዘኢይነቅዝ፡የኀሊ፡ሎቱ፡ጸራቢ፡ ወበጥበቡ፡የኀሥሥ፡ዘከመ፡ያቀውም፡ ምስሎ፡ከመ፡ኢያንቀልቅል። | ፳፪፡ ዕንጨት፡ጠራቢ፡የማይነቅዝ፡ዕንጨትን፡ ይመርጥለታልና፡እንዳይነዋወጥም፡በጥበቡ ምስሉን፡ያቆመው፡ዘንድ፡ቦታ፡ይፈልግለ ታልና። |
| ፳፫፡ ኢየአምር፡ወኢይሰምዕ፡ወኢይነግረክሙ፡ ዘትካት፡ወኢየአምር፡መሠረተ፡ምድር፡ ዘያጸንዕ፡አጽናፈ፡ምድር። | ፳፫፡ እንዲህ፡አድርጎ፡የሠራው፡ጣኦት፡ አያውቅም፤አይሰማም፤የቀደመውንም፡አይ ነግራችሁም፤የምድር፡ዳርቻን፡የሚያጸና፡ የምድር፡መሠረት፡ነፋስንም፡አያውቅም። |

Scanned by CamScanner

በ፱፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሠሉስ።

፳፬፡ ወእለሂ፡ ይነብሩ፡ ውስቴታ፡ ከመ፡ አንበጣ፡ ዘሰፍሐ፡ ለሰማይ፡ ከመ፡ ቀመር፡ ወተከሎ፡ ከመ፡ደብተራ፡ማኅደር።

፳፭፡ ወይሬስዮሙ፡ለመላእክት፡ከመ፡አልቦ፡ዘይትኬነን፡ሎሙ፡ወገብራ፡ለምድር፡እምኀበ፡ወኢምንት።

፳፮፡ ወአብቈለ፡ላዕሌሃ፡እመ፡ወሣዕረ፡ወባዕደኒ፡ብዙኀ ፡ ፍጥረታተ ፡ ዘኢይትኌለቍ ፡ ወእምከመ፡ነፍሐሙ፡ነፋስ፡ይየብሱ፡ወይነሥአሙ፡ዓውሎ፡ከመ፡ኀሠር።

፳፯፡ ወይእዜኒ ፡ በመኑ ፡ ታስተማስሉኒ ፡ ወእትሜካሕ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፡ቅዱስ።

፳፰፡ ወአንሥኡ፡አዕይንቲክሙ፡ውስተ፡ሰማይ፡ወርእዩ፡መኑ፡ዘገብረ፡ዘንተ፡ኵሎ፡ዘይኌልቆሙ፡ለከዋክብት፡በምልዖሙ፡ወያመጽእሙ፡በበዕድሜሆሙ፡ወይጼውዖሙ፡ለኵሎሙ ፡ በበአስማቲሆሙ ፡ በብዝኀ ፡ ስብሐቲሁ፡ወበጽንዐ፡ኃይሉ፡አልቦ፡ዘይትረስዖ።

፳፱፡ ቦኑ ፡ ትብሎ ፡ ያዕቆብ ፡ ምንተ ፡ ነበብከኒ ፡ ተኀብአት ፡ ፍኖትየ ፡ እምእግዚአብሔር ፡ ወርኀቀ ፡ አምላኪየ ፡ እምኔየ ፡ ወኀደገ ፡ ፍትሕየ።

፴፡ ወይእዜኒ ፡ ኢያእመርክሙኑ ፡ ወኢሰማዕክሙኑ፡ከመ፡ውእቱ፡አምላክ፡ዘለዓለም፡ወከመ፡ውእቱ፡አምላክ፡ዘፈጠረ፡አጽናፈ፡ምድር ፡ ኢይርኅብ ፡ ወኢይጸምዕ ፡ ወኢይደክም፡ወአልቦ፡ዘየአምር፡ምክሮ።

፴፩፡ ወይሁቦሙ ፡ ኃይለ ፡ ለድኩማን ፡ ወኢያቴክዘሙ፡ለእለ፡የሐምሙ።

፴፪፡ ይርኅቡ ፡ መሐዛት ፡ ወይደክሙ ፡ ወራዙት ፡ ወይጸብሱ፡ጼኑዓን።

፴፫፡ ወእለሰ፡ይሴፈውዎ፡ወይትዔገሥዎ፡ለእግዚአብሔር፡ይሔድሱ፡ኃይሎሙ፡ወይበቍሉ፡ከነፈሆሙ፡ ከመ ፡ ንስር ፡ ይረውጹ ፡ ወኢይደክሙ፡የሐውሩ፡ወኢይርኅቡ።

ማክሰኞ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

፳፬፡ በእሱዋም፡ውስጥ፡የሚኖሩ፡ሰዎች፡እንደ፡አንበጣ፡ናቸው። ሰማይን፡እንደ፡ዋልታ፡የዘረጋው ፡ እንደ ፡ ማደሪያ ፡ ድንኳንም ፡ የተከለው፡እሱ፡ነው።

፳፭፡ አለቆችንም፡የሚገዛላቸው፡እንዳይኖር፡የሚያደርጋቸው ፡ እሱ ፡ ነው ። ምድርንም ፡ ካለመኖር ፡ ወደ ፡ መኖር ፡ አምጥቶ ፡ የፈጠራት፡እሱ፡ነው።

፳፮፡ በሷም፡ላይ፡ሣሩንና፡ዕንጨቱን፡ያበቀለ፡እሱ፡ነው። የማይቈጠሩ፡ሌሎች፡ብዙዎች፡ፍጥረቶችንም፡የፈጠረ፡እርሱ፡ነው። ነፋስ፡በነፈሰባቸውም፡ጊዜ፡ይደርቃሉ፤ጥቅል፡ነፋስም፡እንደ፡ገለባ፡ይበትናቸዋል።

፳፯፡ እንዲህ፡ያለሁትን፡ፈጣሪ፡በማን፡ትመስሉኛላችሁ? ንጹሕ ፡ ክቡር ፡ የሆነ ፡ እግዚአብሔር፡በአምላክነቴ፡እመካለሁ፡አለ።

፳፰፡ እስኪ ፡ ዓይናችሁን ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ አቅንታችሁ፡እዩ፤ይህን፡ሁሉ፡ያደረገ፡ማነው?፡ኮከቦችንም፡ፈጽሞ፡የሚቈጥራቸው፡እሱ፡ነው ። በየወራታቸውም ፡ የሚአመጣቸው ፡ እርሱ፡ነው። ሁሉንም፡በየስማቸው፡የሚጠራቸው ፡ እሱ ፡ ነው ። በጌትነቱ ፡ ብዛት ፡ በኃይሉ፡ጽናት፡የሚዘነጋው፡የለም።

፳፱፡ ያዕቆብ፡በውኑ፡ለምን፡ሕግ፡ሠራህልኝ፡ትለዋለህን? ሥራዬስ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ተሠወረች፤ፈጣሪዬም፡ከእኔ፡ራቀ፤በእኔ፡መፍረድንም፡ተወ፡ትለዋለህን።

፴፡ አሁንም፡በዓለም፡ጸንቶ፡የሚኖር፡ፈጣሪ፡እሱ፡እንደሆነ፡የምድር፡ዳርቻንም፡የፈጠረ፡ፈጣሪ፡እሱ፡እንደሆነ፡አላወቃችሁምን?አልሰማችሁምን?እሱም፡በባሕርዩ፡አይራብም፤አይጠማም ፤ አይደክምም ፤ ምክሩንም ፡ የሚአውቅ፡የለም።

፴፩፡ ለደካሞች፡ኃይልን፡ይሰጣቸዋል፤መከራ፡የሚቀበሉትንም፡ኢያሳዝናቸውም።

፴፪፡ ሕፃናቱ፡ይራባሉ፤ጐልማሶቹም፡ይዝላሉ፤አርበኞችም፡ይደክማሉ።

፴፫፡ እግዚአብሔርን ፡ አለኝታ ፡ ተስፋ ፡ የሚአደርጉት፡የሚታገሡት፡ሰዎች፡ግን፡ኃይላቸውን፡ያድሳሉ፤ልጆቻቸውም፡እንደ፡ንስር፡ይታደሳሉ፤ይሮጣሉ፤አይደክሙም፡ይሄዳሉ፡አይራቡም።

Scanned by CamScanner

በ፱፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሠሉስ።

ራዕይ ፡ ዘርእየ ፡ ዳንኤል ፡ ነቢይ ፡ በረከቱ ፡ ትኩን፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

ምዕ፡፯፡፩-፰።

፩፤ ወይቤ ፡ አነ ፡ ዳንኤል ፡ ሐለምኩ ፡ ሕልመ ፡ ወርኢኩ ፡ አርባዕተ ፡ ነፋሳተ ፡ ሰማይ ፡ ይነፍሑ፡ውስተ፡ባሕር፡ዐቢይ።

፪፤ ወዓርጉ፡አርባዕቱ፡አራዊት፡ዓበይት፡እምነ፡ባሕር ፡ ኅቡረ ፡ ወፍሉጣን ፡ አሐዱ ፡ እምካልኡ።

፫፤ ወቀዳማዊት ፡ ከመ ፡ አንበሳይት ፡ ወባቲ ፡ ክንፍ፡ ዖክነፊሃ፡ ከመ ፡ ንስር ፡ ወርኢክዋ ፡ እስከ ፡ ተመልሐ ፡ ክነፊሃ ፡ ወተንሥአት ፡ እምድር ፡ ወቆመት ፡ በእግረ ፡ ሰብእ ፡ ወልበ ፡ ሰብእ፡ተውህበ፡ላቲ።

፬፤ ወመጽአት ፡ ካልእት ፡ አርዌ ፡ ዘትመስል ፡ ድበ፡ ወቆመት ፡ ወአሐቲ ፡ ገጸ ፡ ወሠለስቱ ፡ ዐፅመ ፡ ገበዋት ፡ ውስተ ፡ አፉሃ ፡ ማእከለ ፡ አስናኒሃ፡ወከመ፡እቤላ፡ተንሥኢ፡ወብልዒ፡ሥጋ፡ብዙኀ።

፭፤ ወእምድኅረ ፡ ዝንቱ ፡ ርኢኩ ፡ ካልአ ፡ አርዌ ፡ ግሩመ ፡ ወመደንግፀ ፡ ከመ ፡ ነምር ፡ ወላዕሌሁ ፡ አርባዕቱ፡ክንፍ፡ከመ፡ያፍ፡ወአርባዕቱ፡አርእስቲሁ፡ለአርዌ፡ወተውህበ፡ሎቱ፡መባሕት።

፮፤ ወእምድኅሬሁ ፡ ርኢኩ ፡ ራብዐ ፡ አርዌ ፡ ግሩመ፡ወመደንግፀ፡ውኁያለ፡ጥቀ፡ወስነኒሁ፡ዘሐፂን ፡ ወጽፈሪሁ ፡ ዘብርት ፡ ዘይበልዕ ፡ ወየሐርፅ ፡ ወዘተርፈኒ ፡ ይከይድ ፡ በእግሩ ፡ ወውእቱ ፡ አርዌ ፡ የዐቢ ፡ እምኵሎሙ ፡ አራዊት ፡ ዘቅድሜሁ ፡ ወአሠርቱ ፡ አቅርንቲሁ።

፯፤ ወነጸርኩ፡አቅርንቲሁ፡ወናሁ፡ካልእ፡ቀርን፡ንኡስ፡በቈለ፡በማእከሎሙ፡ወሠለስቱ፡አቅርንቲሁ ፡ እለ ፡ እምቅድሜሁ ፡ ተመልሑ ፡ እምቅድመ ፡ ገጹ ፡ ወቦቱ ፡ አዕይንት ፡ ከመ ፡ አዕይንተ ፡ ሰብእ ፡ ወለውእቱ ፡ ቀርን ፡ ንኡስ ፡ አፉሁ፡ይነብብ፡ዐቢያተ።

ማክሰኞ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

በረከቱ ፡ ከእኛ ፡ ጋራ ፡ ለዘላለሙ ፡ ትኑርና፡ ነቢዩ ፡ ዳንኤል ፡ ያየው ፡ ራዕይ ፡ ይህ ፡ ነው፡ አሜን።

ምዕ፡፯፡፩-፰።

፩፤ እኔ ፡ ዳንኤል ፡ ሕልምን ፡ አለምኩ ፤ አራት፡ የሰማይ፡ነፋሶች፡በትልቅ፡ባሕር፡መካከል፡ሲነፍሱ፡አየሁ፡አለ።

፪፤ አራት፡ታላላቅ፡አውሬዎችም፡አንዱ፡ካንዱ፡የማይመሳሰሉ፡ከባሕር፡ሲወጡ፡አየሁ።

፫፤ መጀመሪያይቱ፡እንደ፡አንበሳይት፡ናት፤(ናቡከ ደነፆር)፡ክንፍም፡አላት፤(ሥልጣን)፡ክንፏም፡እንደ፡ንስር፡ክንፍ፡ነው።ክንፏ፡ተነቅሎ፡እስኪወድቅ፡ድረስ፡አየኋት፤(ሥልጣኑን፡እስኪነሣት)፡ተነሥታም፡በምድር፡ላይ፡እንደ፡ሰው፡እግር፡ቆመች፤የሰውም፡ልብ፡ተሰጣት።

፬፤ ተከትላ ፡ የምትመስል ፡ ሁለተኛይቱም፡ አውሬ፡ መጥታ ፡ ቆመች ፤ (ዳርዮስ)፡ፊቷም፡ አንዲት ፡ ናት ፤ (ግዛቷ ፡ አንዲት ፡ ሚዶን)፡ ሦስት ፡ የጐን ፡ አጥንቶች ፡ በአፏ ፡ ተይዘዋል፤ (ባቢሎን ፣ ሚዶን ፣ ፋርስ) ፡ እንዲህም፡ ተነስተሽ፡ብዙ፡ሥጋ፡ብዪ፡አልኋት።

፭፤ ከዚህ፡በኋላ፡በነብር፡አምሳል፡ሌላ፡አውሬ፡አየሁ፤ እንደ፡ወፍም፡አራት፡ክንፍ፡አሉት፤(ባቢሎን፣ፋርስ፡ሚዶን)፡ሥልጣንም፡ተሰጠው።

፮፤ ከሱ፡በኋላ፡ሌሊት፡በራእይ፡የሚአስፈራ፡የሚአስደነግጥ፡እጅግ፡ኃይለኛ፡የሆነ፡አራተኛ፡አውሬን ፡ አየሁ ፤ (የመንግሥተ ፡ ጽርዕ)፡ ጥርሶቹ፡ የብረት ፣ ጥፍሮቹ ፡ የናስ ፡ ናቸው። ሁሉን፡ይበላል፤ሁሉን፡ያደቃል፤የቀረውንም፡ በእግሩ፡ይረግጣል፤ያም፡አውሬ፡ከእርሱ፡አስቀድመው ፡ ከነበሩ ፡ አውሬዎች ፡ ሁሉ፡ ይበልጣል፤ዐሥርም፡ቀንዶች፡አሉት።

፯፤ ቀንዶቹን፡ባየሁ፡ጊዜ፡እነሆ፡በመካከላቸው፡ሁለተኛ ፡ ትንሽ ፡ ቀንድ ፡ በቀለ ፡ (አውሬ ፋኖስ፡አንጥያኮስ)፡ከሱ፡አስቀድሞ፡የነበሩ፡ሦስቱ፡ቀንዶችም፡ከፊቱ፡ተነቅለው፡ወደቁ፤ እንደ ፡ ሰውም ፡ ዓይኖች ፡ ያሉ ፡ ዓይኖች፡ አሉት ፤ የዚያም ፡ የትንሽ ፡ ቀንድ ፡ አፉ፡ ታላላቅ፡ነገሮችን፡ይናገራል።

Scanned by CamScanner

## በ፱፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘሠሉስ።

፱፡ ወርኢኩ፡እስከ፡አንበሩ፡መናብርተ፡ወነበረ፡ ዲቤሆሙ፡ብሉየ፡መዋዕል፡ወልብሱ፡ጸዓዳ፡ ከመ፡በረድ፡ወሥዕርተ፡ርእሱ፡ከመ፡ፀምር፡ ጸዓዳ፡ወመንበሩሂ፡እሳት፡ዘይነድድ፡ወሠረ ገላሁ፡አፍሐም፡ዘያንበለብል።

፲፡ ወፈለገ፡እሳት፡ይውኅዝ፡ቅድሜሁ፡አእላፈ፡ አእላፋት ፡ ይትለአከዎ ፡ ወትእልፌተ ፡ አእላፋት፡ ይቀውሙ ፡ ቅድሜሁ ፡ ወነበረ ፡ ዐውደ፡ወከሠተ፡መጻሕፍተ።

፲፩፡ ወርኢኩ ፡ ሶቤሃ ፡ እምቃለ ፡ ነገሩ ፡ ዐቢይ ፡ ዘይነብብ ፡ ዝኩ ፡ ቀርን ፡ እስከ ፡ ተአተተ ፡ ወእስከ፡ተቀትለ፡ውእቱ፡አርዌ፡ወጠፍአ፡ ወወሀቡ፡ሥጋሁ፡ያውዕዩ፡በእሳት።

፲፪፡ ወፈለሰ፡ሥልጣኖሙ፡ለእልክቱ፡አራዊት፡ ወተውህበ፡ሎሙ፡ነዋኅ፡ሕይወት፡እስከ፡ ዕድሜሆሙ።

፲፫፡ ወርኢኩ፡በራእየ፡ሌሊት፡ወናሁ፡መጽአ፡ ዐቢይ፡በደመና፡ሰማይ፡ከመ፡ወልደ፡ዕጓለ፡ እመሕያው፡ወበጽሐ፡ኀበ፡ብሉየ፡መዋዕል፡ ወአቅረብዎ፡ቅድሜሁ።

፲፬፡ ወተውህበ ፡ ሎቱ ፡ ምኵናን ፡ ዘለዓለም ፡ ወክብር ፡ ወመንግሥት ፡ ወሥልጣን ፡ ወኵሎሙ፡አሕዛብ፡ወሕዝብ፡ወበሐውርት፡ ወነገድ፡ወነገሥት፡ይትቀነዩ፡ሎቱ፡ወምኵ ናኑኒ፡ምኵናን፡ዘለዓለም፡ወመንግሥቱ፡ዘኢ የኀልቅ፡ወኢይማስን።

፲፭፡ ወርዕደኒ፡መንፈስየ፡አነ፡ዳንኤል፡ወደን ገፀኒ፡ልብየ፡እምራእየ፡ርእስየ።

### ትርጓሜ፡ራእየ፡ዳንኤል።

፩፡ ይቤ፡መተርጕም፡ይቤ፡አነ፡ዳንኤል፡ርኢኩ፡ በራእየ፡ሌሊት፡አንበሩ፡መናብርተ፡ይብል፡ በእንተ ፡ መናብርት ፡ ለኀበ ፡ ስብሐተ ፡ መለኮት።

፪፡ ይቤ፡ወነበረ፡ብሉየ፡መዋዕል፡ወዝንቱኒ፡ ይትሜሰል፡እስመ፡እግዚአብሔር፡ልዑል፡ አብርሀ፡ልቡናሁ፡ለነቢይ፡እስመ፡ረከቦ፡ ለአምላክ፡ዘበስብሐቲሁ።

## ማክሰኞ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

፱፡ ዙፋኖችን ፡ እስኪዘረጉለት ፡ ድረስ ፡ ደርሶ ፡ አየሁ፤ ዘመኑን፡የሚያስረጅ፡እግዚአብሔር፡ በላያቸው፡ተቀመጠ፤ልብሱም፡እንደ፡በረድ፡ ነጭ፡ነው። የራሱም፡ጠጉር፡እንደ፡ብዝት፡ ነጭ፡ነው፡ዙፋኑም፡የሚነድ፡እሳት፡ነው፡ ሠረገላውም፡የሚንቀለቀል፡ፍሕም፡ነው።

፲፡ የእሳትም፡ጐርፍ፡በፊቱ፡ይፈሳል፤የብዙ፡ ብዙ ፡ የሆኑ ፡ መላእክትም ፡ ያገለግሉታል፤ የእልፍ ፡ እልፍ ፡ መላእክትም ፡ በፊቱ ፡ ይቆማሉ፤ በአደባባይ ፡ ተቀምጦ ፡ መጻሕ ፍትን፡ገለጠ።

፲፩፡ ያን፡ጊዜም፡ይህ፡ቀንድ፡ከተናገረው፡ነገር፡ የተነሣ፡ያ፡አውሬ፡እስኪርቅና፡እስኪጠፋ፡ ድረስ፡ደርሶ፡አየሁ፤በእሳትም፡ያቃጥሉት፡ ዘንድ፡አካሉን፡አሳልፈው፡ሰጡት።

፲፪፡ የእነዚያም ፡ አውሬዎች ፡ ሥልጣናቸው ፡ ተወሰደ፤(የሮማውያን፡መንግሥት)፡ነገር፡ ግን፡እስከ፡ጊዜያቸው፡ድረስ፡ብዙ፡ዘመን፡ ተሰጣቸው።

፲፫፡ በሌሊት፡ራእይ፡አየሁ፤እነሆ፡እንደ፡ሰው፡ ልጅ፡ያለ፡ታላቅ፡በሰማይ፡ደመና፡መጣ፤ ዘመኑን ፡ ወደሚአስረጅ ፡ ወደ ፡ መለኮት ፡ ደረሰ፤ከፊቱም፡አቀረቡት።

፲፬፡ የዘለዓለም፡አገዛዝ፡ጌትነት፡መንግሥት፡የዘለ ዓለም፡ሥልጣን፡ተሰጠው፤ሕዝቡና፡አሕዛቡ፡ ሁሉ፡በአራቱ፡ማዕዘን፡የሚኖሩትና፡ነገዱም፡ ነገሥታቱም፡ሁሉ፡ይገዙለታል። አገዛዙም፡ የዘላለም፡አገዛዝ፡ነው።መንግሥቱም፡ለልጅ፡ ልጅ፡የሚያልፍ፡የማይጠፋ፡ነው።

፲፭፡ እኔ፡ዳንኤል፡ሰውነቴ፡ተንቀጠቀጠብኝ፤ራሴ፡ ካየሁት፡ራእይ፡የተነሣ፡ልቡናዬ፡ደነገጠብኝ።

### የዳንኤል፡ራእይ፡ምሥጢራዊ፡ትርጓሜ።

፩፡ እኔ፡ዳንኤል፡በሌሊት፡ራእይ፡ዙፋኖችን፡ ሲአዘጋጁ፡አየሁ፡አለ፡ብሎ፡ተርጓሚው፡ ተናገረ፤ስለ፡ዙፋኖች፡የመለኮት፡ጌትነትና፡ ክብር፡እንደሆነ፡ይናገራል።

፪፡ ዘመናትን፡የሚአስረጅ፡ተቀመጠ፡አለ፤ ይህም፡ ልዑል፡እግዚአብሔር፡የነቢዩን፡ ልቡና፡ብሩህ፡አድርጎለት፡ፈጣሪን፡በጌትነቱ፡ ሁኖ፡አይቶታልና፡ይህ፡ይመስላል።

Scanned by CamScanner

| በ፱፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሠሉስ። | ማክሰኞ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት። |
|---|---|
| ፫፤ ይቤ ፡ ወአልባሲሁኒ ፡ ጸዐዳ ፡ ከመ ፡ በረድ ፡ ይብል፡በእንተ፡ውእቱኒ፡ብርሃነ፡መለኮት። ወሥዕርተ ፡ ርእሱ ፡ ከመ ፡ ፀምር ፡ ንጹሕ ፡ ይብል፡በእንተ፡ውእቱኒ፡ለብሉየ፡መዋዕል፡ጥንቶ። | ፫፤ ልብሶቹ፡እንደ፡በረድ፡ነጭ፡ናቸው፡አለ፡ ስለዚህም ፡ የመለኮት ፡ ክብር ፡ እንደ ፡ ሆነ፡ ይናገራል ፡ ይላል ። የራሱ ፡ ፀጕርም ፡ እንደ ባዘቶ፡ ነጭ ፡ ነው ፡ አለ ፤ ይህም ፡ የመለኮትን፡ ቀዳማዊነት፡ያስረዳል። |
| ፬፤ ይቤ ፡ ወመንበሩኒ ፡ እሳት ፡ ዘይነድድ ፡ ውእቱኬ፡በከመ፡ነገርነ፡ስብሐተ፡መለኮት። | ፬፤ ዙፋኑም፡(መንበሩም)፡የሚነድ፡እሳት፡ነው፡ አለ ፤ ይህም ፡ እንደተናገርነው ፡ የጌትነቱ፡ ክብር፡ነው። |
| ፭፤ ይቤ ፡ ፈለገ ፡ እሳት ፡ ቅድሜሁ ፡ ይውኅዝ ፡ ይብል፡በእንተ፡ውእቱኒ፡ትእዛዚቲሁ፡አምላካዊት፡እንተ፡እንበለ፡ክልአት። | ፭፤ የእሳት ፡ ጐርፍ ፡ በፊቱ ፡ ይፈሳል ፡ አለ፤ ስለዚህም ፡ መከልከል ፡ የሌለባት ፡ አምላካዊት፡ትእዛዙ፡እንደሆነች፡ይናገራል። |
| ፮፤ ይቤ ፡ አእላፈ ፡ አእላፋት ፡ ወትእልፊተ ፡ አእላፋት ፡ ይቀውሙ ፡ ቅድሜሁ ፡ ይብል ፡ በእንተ ፡ ውእቱ ፡ መላእክት ፡ ወሊቃነ ፡ መላእክት፡ወኵሎሙ፡ሐራ፡መንፈሳውያን። | ፮፤ የብዙ ፡ ብዙ ፡ የሆኑ ፡ አእላፋት ፡ በፊቱ፡ ይቆማሉ፡አለ፤ይህም፡ስለ፡መላእክት፡ስለ፡ መላእክትም፡አለቆች፡ስለ፡ረቂቃን፡የመላ እክት፡ሠራዊት፡ይናገራል። |
| ፯፤ ይቤ፡በእንተ፡ቀዊም፡ቅድሜሁ፡ከመ፡ተመሰልያን ፡ ለትእዛዛቲሁ ፡ ወዐቃብያነ ፡ ግብሩ ፡ ይሴብሕዎ፡ወይቄድስዎ፡ዘእንበለ፡ዕርዐት። | ፯፤ በፊቱ፡ስለ፡መቆም፡ተናገረ፤ሕጉን፡የሚጠ ብቁና ፡ ትእዛዙን ፡ የሚፈጽሙት ፡ ያለ፡ ማቋረጥ ፡ የሚአመሰግኑትንና ፡ የሚቀድ ሱትን፡እንደሚመስል፡ያስረዳል። |
| ፰፤ ይቤ ፡ ወነበረ ፡ መኰንን ፡ ውእቱኬ ፡ በከመ ፡ ነገርነ፡ከመ፡ውእቱ፡ረከቦ፡ለአምላክ። | ፰፤ ፈራጅ፡ተቀመጠ፡አለ፤አስቀድመን፡እንደተ ናገርነው ፡ ፈጣሪን ፡ በክብሩ ፡ ሁኖ፡ ማግኘቱን፡ነው። |
| ፱፤ ይቤ ፡ ወተከሥቱ ፡ መጻሕፍት ፡ ይብል ፡ በእንተ፡ቃላቲሆሙ፡ለነቢያት፡እለ፡ተነበዩ፡ በእንተ፡ምጽአቱ፡ለክርስቶስ። | ፱፤ መጻሕፍት ፡ ተገለጹ ፡ አለ ፤ ይህም፡ስለ፡ ክርስቶስ ፡ ሰው ፡ መሆንና ፡ መምጣት፡የተና ገሩት፡የነቢያት፡ቃል፡ነው። |
| ፲፤ ይቤ፡ወርኢኩ፡ሶቤሃ፡ቃላተ፡ነገር፡ብዙኅ፡ ይብል ፡ ይባቤያተ ፡ ወስብሐተ ፡ መላእክት ፡ ቅዱሳን፡ወሊቃናት፡ወሥልጣናት። | ፲፤ ያን፡ጊዜ፡የብዙ፡ነገርን፡ቃል፡ሰማሁ፡አለ፡ ይህም፡የሊቃናት፡የሥልጣናት፡የመላእክት በዜማ፡የሚአመሰግኑት፡ቃል፡ነው። |
| ፲፩፤ ይቤ፡ይነብብዋ፡አቅርንት፡ዛቲኬ፡ስብሐተ፡ ሠራዊት፡ልዑላን፡አቅርንት፤ዘከመ፡ነገረ፡ ዮሐንስ፡ወንጌላዊ፡በውስተ፡ራእዩ፡በእንተ፡ አርባዕቱ ፡ እንስሳ ፡ ወዕሥራ ፡ ወአርባዕቱ ፡ አዕሩግ፡እሉ፡እሙንቱ፡ሠራዊት፡ልኡካን፡ ከመ ፡ እሙንቱ ፡ ይሴብሕዎ ፡ ዘእንበለ ፡ ዕርዐት፡ወይብሉ፡ቅዱስ፡ቅዱስ፡ቅዱስ። | ፲፩፤ መለከቶች ፡ ይናገሩአታል ፡ አለ ፤ ይህቺም፡ ታላላቅ ፡ መለከት ፡ የያዙ ፡ የመላእክት፡ ሠራዊት ፡ የሚአመሰግኑባት ፡ ናት ፤ ስለ፡ አርባዕቱ፡እንስሳና፡ስለ፡ሃያ፡አራቱ፡ዘሳለማ ውያን ፡ ካህናተ ፡ ሰማይ ፡ ስለ ፡ መላእክት፡ ሠራዊትም ፡ እነርሱ ፡ ያለ ፡ ማቋረጥ ፡ ቅዱስ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ እያሉ ፡ እንደሚአመሰግኑት፡ በራእዩ፡ወንጌላዊ፡ዮሐንስ፡እንደ፡ተናገረ። |
| ፲፪፤ ይቤ፡ወርኢኩ፡ዝኩ፡አርዌ፡ጠፍአ፡ሥጋሁ፡ ወተቀትለ፡ወወሀቡ፡ሥጋሁ፡ያውዕዩ፡በእሳት፡ ወተሀይደ፡ሥልጣኖሙ፡ለኵሎሙ፡አራዊት፤ ይብል ፡ አመ ፡ ከመ ፡ አስተርአየ ፡ ክርስቶስ ፡ ይትነሣእ፡ሰይጣን፡ወይለስሕ፡ኀይሉ፡ወይት | ፲፪፤ ያ ፡ አውሬ ፡ ሲገደልና ፡ ሲጠፋ ፤ ሥጋውም፡ በእሳት፡ለመቃጠል፡ሲሰጥ፡የአራዊቱ፡ሁሉ፡ ሥልጣን ፡ ሲቀማ ፡ አየሁ ፡ አለ ፤ ይህም፡ ጌታ ፡ ክርስቶስ ፡ በሥጋ ፡ በተገለጸ ፡ ጊዜ፡ በሰዎች ፡ ላይ ፡ ከአዳም ፡ እስከ ፡ ክርስቶስ |

Scanned by CamScanner

## በ፱፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሠሉስ።

ሀየድ፡ሥልጣኑ፡ዘኮነ፡ይሜብል፡ቦቱ፡ላዕለ፡
ዕጓለ ፡ እመሕያው ፡ እምአዳም ፡ እስከ ፡
ምጽአተ ፡ ክርስቶስ ፡ ወይወድይዎሙ ፡
ውስተ፡እሳተ፡ገሀነም።
፲፫ ወሶበ፡መጽአ፡እግዚእነ፡አድኀኖሙ፡እምእ
ደዊሁ፡ወአዕረጎሙ፡እምሲኦል፡ወኀደጎ፡ለዲ
ያብሎስ፡ውስተ፡እሳት፡ዘለዓለም በከመ፡
ይቤ፡ ለሊሁ ፡ በወንጌል ፡ ቅዱስ ፡ ለእለ ፡
በፀጋሙ ፡ ሑሩ ፡ ውስተ ፡ እሳት ፡ ዘለዓለም ፡
እንተ፡ድልው፡ለዲያብሎስ፡ወለሐራሁ።
፲፬ ይቤ ፡ ወርኢኩ ፡ ወናሁ ፡ መጽአ ፡ በደመና ፡
ሰማይ ፡ ከመ ፡ ወልደ ፡ ዕጓለ ፡ እመሕያው ፤
ይብል፡በእንተ፡ዝንቱ፡ከመ፡ውእቱ፡ርእየ፡
ዘይከውን፡እምትሥጉተ፡ቃለ፡አብ። ወናሁ፡
መጽአ፡በደመና፡ሰማይ፡ይብል፡በእንተ፡
ደመና፡እግዝእትነ፡ማርያም፡ንጽሕት።
፲፭ ይቤ፡ወበጽሐ፡ኀበ፡ብሉየ፡መዋዕል፡ይብል፡
በእንተ፡ውእቱ፡ዕምረተ፡ቃል፡እምላካዊ፡
ምስለ፡ብእሲ።
፲፮ ይቤ፡ወተውህበ፡ሎቱ፡ምኵናን፡ወክብር፡
ወመንግሥት ፡ ይብል ፡ በእንተ ፡ ውእቱ ፡
እምግብረ ፡ አሐዱ ፡ ክዊን ፡ ኮነ ፡ አሐደ ፡
መሲሐ፡ወአሐደ፡እግዚአ፡ወአሐደ፡ፈቃደ፡
ወአሐደ፡ቅኔ።
፲፯ ይቤ ፡ ወኵሎሙ ፡ አሕዛብ ፡ ወነገድ ፡ ወበሐ
ውርት፡ወልሳናት፡ይትቀነዩ፡ሎቱ፤ይብል፡
እስመ ፡ እምድኅረ ፡ ምጽአተ ፡ ክርስቶስ ፡
ትከውን ፡ አሐተ ፡ ዕምረተ ፡ ሕዝብ ፡ ከመ ፡
ዘደቂቀ ፡ እስራኤል ፡ ዘበበ ፡ ጊዜሆሙ ።
ወባሕቱ ፡ ኵሉ ፡ ዘአምኑ ፡ እምደቂቀ ፡ እስ
ራኤልኒ ፡ ይከውኑ ፡ በክርስቶስ ፡ ሕዝበ ፡
ኅሩየ።

፲፰ ወትርጓሜሁ ፡ ይትቀነዩ ፡ ሎቱ ፡ ዘውእቱ ፡
የአምኑ፡ቦቱ፡በስሙ፡ብሂል፡እምሥራቀ፡
ፀሐይ፡እስከነ፡ዐረብ፡ይሰግዱ፡ሎቱ።
፲፱ ይቤ፡ወመንግሥቱሂ፡ዘኢይማስን፡ዘውእቱ፡
ዘኢየኀልፍ ፡ ወመሀይምናን ፡ በክርስቶስ ፡
እስከ፡ማኅለቅተ፡ዓለም፡ወውእቱ፡ካዕበ፡
ንጉሥነ፡ወእምላክነ።

ሎቱ፡ስብሐት፡እስከ፡ለዓለመ፡ዓለም፡
አሜን።

## ማክሰኞ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

መምጣት፡ድረስ፡ሠልጥኖ፡የነበረ፡ሰይጣን፡
ኃይሉ ፡ እንደሚደክም ፡ ሥልጣኑ ፡ እንደ
ሚቀማ፡የሱ፡ሠራዊት፡የሆኑ፡አጋንንት፡ወደ፡
እሳተ፡ገሀነም፡እንደሚጨመሩ፡ይናገራል።
፲፫ ጌታችንም ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ ከእጆቹ ፡ አድኖ ፡
ከሲኦል፡አወጣቸው፤ዲያብሎስንም፡በዘለዓ
ለማዊ፡እሳት፡ውስጥ፡ተወው፤ለዲያብሎስና፡
ለሠራዊቱ፡ወደተዘጋጀ፡ወደ፡ዘላለም፡እሳት፡
ሂዱ፡ብሎ፡በግራው፡ያሉትን፡ሲአሰናብት፡
እርሱ፡ራሱ፡በቅዱስ፡ወንጌል፡እንደተናገረ።
፲፬ እነሆ ፡ እንደ ፡ ሰው ፡ ልጅ ፡ የሆነ ፡ በሰማይ ፡
ደመና ፡ ሲመጣ ፡ አየሁ ፡ አለ ፤ ስለዚህም ፡
የአብ፡አካላዊ፡ቃል፡በሥጋዌው፡ምሥጢር፡
የሆነውን፡እንዳየ፤ደመና፡ያለውም፡ንጽሕት፡
ድንግል፡እመቤታችን፡ማርያም፡እንደሆነች፡
ይናገራል።
፲፭ ዘመናትን ፡ ወደሚአስረጀው ፡ ደረሰ ፡ አለ ፤
ስለዚህ፡ሲናገር፡የመለኮትና፡የትስብእትን፡
ተዋሕዶ፡ያስረዳል።
፲፮ አገዛዝ፡ጌትነት፡መንግሥት፡ተሰጠው፡አለ፤
ስለዚህም ፡ በተዋሕዶ ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡
አንድ፡ አካል ፡ ከመሆኑ ፡ የተነሣ ፡ አንድ ፡
መንግሥት ፡ አንድ ፡ ጌታ ፡ አንድ ፡ ፈቃድ ፡
አንድ፡አገዛዝ፡መሆኑን፡ይናገራል።
፲፯ አሕዛብ ፡ ሁሉ ፡ ነገድም ፡ መንደር ፡
መንድረው፡የሚኖሩ፡በቋንቋም፡የሚለያዩ፡
ሁሉ፡ይገዙለታል፡አለ፤ይህም፡ክርስቶስ፡
ሥጋን፡ከተዋሐደና፡ሰው፡ከሆነ፡በኋላ፡የእስ
ራኤል፡ልጆች፡በየጊዜው፡በአምልኮ፡አንድ፡
ሁነው፡እንደኖሩ፡የሕዝቡ፡ተዋሕዶ፡አንድ፡
ትሆናለች ፤ ነገር ፡ ግን ፡ የአመኑት ፡ ከእስራ
ኤልም ፡ ልጆች ፡ በክርስቶስ ፡ አንድ ፡
የተመረጠ፡ወገን፡ይሆናሉ።
፲፰ ይገዙለታል ያለው ፡ ትርጓሜው ፡ ከፀሐይ ፡
መውጫ፡እስከ፡ፀሐይ፡መግቢያ፡ያሉ፡ሁሉ፡
በስሙ፡አምነው፡ይሰግዱለታል፡ማለት፡ነው።
፲፱ መንግሥቱ የማይጠፋ ፡ አለ ፤ ይኸውም ፡
የማያልፍ ፡ ነው ፤ በክርስቶስም ፡ ያመኑ ፡
ምእመናን ፡ እስከ ፡ ዓለም ፡ ፍጻሜ ፡ የማያቋ
ርጡና፡ሕያዋን፡ሁነው፡ይኖራሉ፤ዳግመኛም፡
እርሱ፡ ንጉሣችንና ፡ አምላካችን ፡ ሕያወ ፡
ባሕርይ፡እንደ፡ሆነ፡ይናገራል።
እስከ፡ዘላለሙ፡ለእርሱ፡ክብር፡ምሥጋና፡
ይሁን፡አሜን።

Scanned by CamScanner

## በ፱፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሠሉስ።

### ክፍል፡፪።
### ሃይማኖተ፡አበው።

ምዕ፤፯፡፲፰-፳፯።

ይቤ፡ቅዱስ፡ዮሐንስ፡ሊቀ፡ጳጳሳት፡ዘእስክን ድርያ፡በጦማረ፡መልእክቱ፡ኀበ፡ቅዱስ፡ኪራኮስ፡ሊቀ፡ጳጳሳት፡ዘአንጾኪያ።

፲፰፤ ወዓዲ፡ንሕነ፡ናወግዝ፡እለ፡ይብሉ፡አው፡ይኄልዩ፡ከመ፡ሥሉስ፡ቅዱስ፡ዘውእቶሙ፡አብ፡ወወልድ፡ወመንፈስ፡ቅዱስ፡ሠለስቱ፡አካላት፡ተሠገዉ፡በብሂሎቶሙ፡ከመ፡መለኮት፡ዡለንታሁ፡ዘንሬኢ፡ከመ፡ውእቱ፡በአብ፡ወወልድ፡ወመንፈስ፡ቅዱስ፡ተሠገወ፡ወአኮ፡አሐዱ፡እምአካለተ፡ሥላሴ፡ወኢይትአመኑ፡ከመ፡አሐዱ፡አካል፡ዘእግዚ አብሔር፡ቃል፡ዘቦቱ፡አካል፡ከመ፡አብ፡ወመንፈስ፡ቅዱስ፡አላ፡እሙንቱ፡ህልዋን፡በአሐዱ፡መለኮት፡ወአሐዱ፡ህላዌ፡ዘንሴብሖ፡እሙነ፡በተዋሕዶተ፡መለኮት፡ውእቱ፡ተሠገወ፡ወኮነ፡ሰብአ፡ወክልኤቱሰ፡አካላት፡እሉ፡እሙንቱ፡አብ፡ወመንፈስ፡ቅዱስ፡ኢተሠገዉ፡ወኢኮኑ፡ሰብአ።

፲፱፤ ወንሕነኒ፡ከማክሙ፡አ፡ብፁዓን፡ናአትት፡ወንፈልጥ፡ለግሙራ፡እለ፡ይብሉ፡እሰመ፡መለኮተ፡አካላት፡ዘዘዚአሁ፡ዘአብ፡ወወልድ፡ወመንፈስ፡ቅዱስ፡አኮ፡ፍሉጣን፡ዳእሙ፡ስንዕዋን፡ወኅቡራን፡በመለኮት፡ንሕነሰ፡ንትዌከፍ፡ወንትአመን፡ዡሎ፡ሥርዓተ፡አበዊነ፡እንተ፡ተጽሕፈት፡እምእግ ዚአብሔር፡በመንፈስ፡ቅዱስ።

፳፤ ወበከመ፡ንሕነ፡ስንዕዋን፡ምስሌክሙ፡በዝንቱ፡ግብር፡ዘውእቱ፡ንባብ፡በእንተ፡ቅድስት፡ሥላሴ፡ዘንሰግድ፡ሎሙ፡ወዓዲ፡ንትአመን፡ዘንተ፡ኀቤክሙ፡አ፡ንጹሐን፡ወንዜከር፡ሃይማኖተ፡አበዊነ፡ቅዱሳን፡ዘከመ፡እፎ፡ይትአመኑ፡በሥጋዌ፡እምላካዊ፡ዘውእቱ፡ትስብእተ፡አሐዱ፡አካል፡እምኔሆሙ፡እግዚአብሔር፡ቃል፡ስቡሕ፡በዅሉ፡ጊዜ፡ውስተ፡ቅድስት፡ሥላሴ፡ወያጌ

## ማክሰኞ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

### ክፍል፡፪።
### የአባቶች፡ሃይማኖት።

ምዕ፤፯፡፲፰-፳፯።

የእስክንድርያ፡ሊቀ፡ጳጳሳት፡ቅዱስ፡ዮሐንስ፡ወደ፡አንጾኪያ፡ሊቀ፡ጳጳሳት፡ወደ፡አባ፡ኪራኮስ፡በላከው፡መልእክቱ፡እንዲህ፡አለ፡

፲፰፤ ዳግመኛም፡በአብ፡በወልድ፡በመንፈስ፡ቅዱስ፡ሕልውና፡እንዳለ፡የምናውቀው፡መለኮት፡ሁለንተናው፡ሰው፡እንደሆነ፤ሰው፡የሆነው፡ከሦስቱ፡አካላት፡አንዱ፡አካል፡እን ዳይደለ፡በመናገራቸው፡ሦስቱ፡አካላት፡አብ፡ወልድ፡መንፈስ፡ቅዱስ፡ሰው፡እንደሆኑ፡የሚአስቡትን፡የሚናገሩትን፡አንድ፡መለኮት፡አንድ፡ባሕርይ፡እንደ ሚሆኑ፡እንደ፡አብ፡እንደ፡መንፈስ፡ቅዱስ፡አካል፡ያለው፡በመለኮት፡አንድነት፡ከአብ፡ከመንፈስ፡ቅዱስ፡ጋራ፡በእውነት፡የምናመ ሰግነው፡አንዱ፡የእግዚአብሐር፡ቃል፡አካል፡ነፍስን፡ሥጋን፡ነሥቶ፡ሰው፡እንደሆነ፡የማያምኑትን፡እኛ፡እናወግዛለን፤ሁለቱ፡አካላት፡አብ፡መንፈስ፡ቅዱስ፡ግን፡ፈጽሞ፡ሰው፡አልሆኑም።

፲፱፤ ብፁዓን፡ሆይ፡እኛም፡እንደ፡እናንተ፡የአካላት፡መለኮት፡የአብ፡የወልድ፡የመንፈስ፡ቅዱስ፡የየራሱን፡ነው፡የሚሉትን፡እናወግዛለን፤እንለያቸዋለን፤በመለኮት፡አንድ፡ናቸው፡እንጂ፡የተለዩ፡አይደሉምና፤እኛስ፡በመንፈስ፡ቅዱስ፡ተገለ ጸላቸው፡ከእግዚአብሔር፡አግኝተው፡የጻፉ ዋትን፡የአባቶቻችንን፡ሃይማኖት፡እናም ናለን፤እንቀበላለን።

፳፤ ስለምንሰግድላቸው፡ስለ፡ቅድስት፡ሥላሴ፡ስለ፡ምንናገረው፡በዚህ፡ምሥጢር፡ከእናንተ፡ጋር፡አንድ፡እንደሆን፡ንጹሐን፡አባቶቻችን፡ሆይ፡ይኸንን፡ደግሞ፡በእናንተ፡ዘንድ፡እንነ መናለን፤እምላክ፡በፈጸመው፡ሥጋዌ፡እንዴት፡እንደሚያምኑ፡የቅዱሳን፡አባቶቻ ችንን፡ሃይማኖት፡እንናገራለን፤ይኸውም፡ከአብ፡ከመንፈስ፡ቅዱስ፡ሁል፡ጊዜ፡የሚመ ሰገን፡ከሦስቱ፡አካላት፡አንዱ፡አካል፡እግዚ

## በ፱፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሠሉስ።

ይጥቡ ፡ ወይልሀቅ ፡ በሥጋ ፡ በበህቅ ፡ እስከ ፡ መዋዕለ ፡ ፍጻሜ ፡ መዋዕለ ፡ አካል ፡ ወተመ ሰለነ ፡ በኵሉ ፡ ግብር ፡ ወአጽንዐ ፡ ቦቱ ፡ ትስብእተ ፡ ዚአነ ፡ ዘእንበለ ፡ ኃጢአት ፡ ወነበረ፡ በዘዚአሁ ፡ ግብር ፡ እምድኅረ ፡ ትሥጉቱ።

፳፮፡ ወኢተወሰከ፡ዲበ፡ሥላሴ፡ምንትኒ፡እስመ፡ አሐዱ፡ውእቱ፡ለሊሁ፡አምላክ፡ወለሊሁ፡ ሰብእ፡ኀቡረ፡ውእቱ፡ይትዋሐድ፡ምስለ፡ አቡሁ ፡ በህላዌ ፡ መለኮት ፤ ወውእቱ ፡ ይትዔረይ ፡ ምስሌነ ፡ በህላዌ ፡ ትስብእት ፤ ውእቱ ፡ ሰማያዊ ፡ ወውእቱ ፡ ምድራዊ ፡ ውእቱ፡ ያስተርኢ ፡ ወውእቱ ፡ ኢያስተርኢ ፡ ውእቱ፡ይትገሠሥ፡ወውእቱ፡ኢይትገሠሥ፡ ውእቱ፡ይትረከብ፡ወውእቱ፡ኢይትረከብ፡ ውእቱ ፡ ሐማሚ ፡ ወውእቱ ፡ ኢየሐምም ፡ ውእቱ ፡ ሐማሚ ፡ በሥጋ ፡ ወውእቱ ፡ ኢሐማሚ፡በመለኮት።

ወስብሐት፡ለእግዚአብሔር፡እስከ፡ለዓለም፡ አሜን።

### ተግሣጽ፡ዘተሰዓቱ፡ሰዓተ፡መዐልት፡ ዘሠሉስ።

፩፡ ይደሉ፡ለነ፡ይእዜ፡ከመ፡ንጠይቅ፡ፍካሬ፡ እመጻሕፍት፡ዘመለኮት፡ሠናየ።

፪፡ ወአኮ፡ለሰሚዕ፡ባሕቲቱ፡ዘእንበለ፡ዳእሙ፡ ንብራህ ፡ በብርሃን ፡ ዘየኀቱ ፡ ውስተ ፡ አልባቢነ፡ ወይምርሐነ ፡ ኀበ ፡ መድኃኒተ ፡ ነፍሳቲነ።

፫፡ እስመ፡ነዋ፡ይእዜ፡ሶበ፡ርእዩ፡ደቂቀ፡እግዚአ ብሔር ፡ ኀበ ፡ አዋልደ ፡ ዕጓለ ፡ እመሕያው ፡ ከመ ፡ ውእቶን ፡ ሠናያተ ፡ ላሕይ ፡ ነሥኡ ፡ እምኔሆን፡አንስትያ፡ዘኀረዩ፡ነጽር፡ይእዜኬ፡ እፎ፡ይሰመዩ፡እለ፡ይቀርቡ፡ኀበ፡እግዚአ ብሔር ፡ ደቂቀ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወእለ ፡ መንገለ፡ፍትወታት፡ዘሥጋ፡ውሉደ፡ሥጋ።

፬፡ ወበእንተዝ ፡ ይቤ ፡ መጽሐፍ ፡ አምላካዊ ፡ ወሶበ ፡ ርእዩ ፡ ደቂቀ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኀበ ፡ አዋልደ፡ሰብእ፡ወውእቶን፡ሠናያተ፡ላሕይ፡ ነሥኡ፡እምኔሆን፡አንስትያ፡ዘኀረዩ።ይብል፡ ደቂቀ፡እግዚአብሔር፡በእንተ፡ደቂቀ፡ሴት፡ እስመ፡ሴት፡ኮነ፡መፍቀሬ፡እግዚአብሔር፡ ወደቂቁ፡ይመስልዎ፡በኂሩት።

## ማክሰኞ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

ሆንበት ፡ ዘመን ፡ (ሠላሳ ፡ ዘመን) ፡ ድረስ፡ ጡት፡ ጡብቶ ፡ በሥጋ ፡ በየጥቂቱ ፡ ማደግ፡ ወደደ ፤ በሥራውም ፡ ሁሉ ፡ መሰለን ፤ ያለ፡ ዘርዐ፡ ብእሲ ፡ የነሣውን ፡ የእኛን ፡ ሥጋ፡ በተዋሕዶ ፡ አጸና ፤ ሰውም ፡ ከሆነ ፡ በኋላ፡ ሳይለወጥ፡ጸንቶ፡ኖረ።

፳፮፡ በሥላሴ ፡ ምንም ፡ ምን ፡ አልተጨመረም፤ እርሱ፡አንድ፡ነውና፤እርሱ፡አምላክ፡ነው፤ በተዋሕዶ ፡ ሰው ፡ የሆነ ፡ እርሱ ፡ ነው፤ በባሕርየ ፡ መለኮት ፡ ከአባቱ ፡ ጋር ፡ አንድ፡ ነው፤እርሱ፡በሥጋ፡ባሕርይም፡ከእኛ፡ጋር፡ አንድ ፡ ነው ፤ ሰማያዊ ፡ እርሱ ፡ ነው፡ ምድራዊም ፡ እርሱ ፡ ነው ፤ እርሱ ፡ ይታያል፡ አይታይም ፤ እርሱ ፡ ይዳሰሳል ፤ አይዳሰስም፡ እርሱ ፡ ይወሰናል ፤ አይወሰንም ፤ እርሱ፡ ይታመማል ፤ አይታመምም ፤ እርሱ ፡ በሥጋ፡ ይታመማል ፤ በመለኮት ፡ አይታመምም፡

እስከ ፡ ዘላለሙ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ምሥጋና፡ ይሁን፡አሜን።

### ማክሰኞ፡ከቀኑ፡በዘጠኝ፡ሰዓት፡የሚነበብ፡ ተግሣጽ።

፩፡ አንድነትን ፡ ሦስትነትን ፡ ከሚናገሩ ፡ መጻሕ ፍት ፡ መልካሙን ፡ ምሥጢር ፡ መረዳት፡ ለእኛ፡ዛሬ፡ይገባል።

፪፡ መስማት ፡ ብቻ ፡ አይደለም ፤ ወደ ፡ ነፍሳችን፡ ድኅነት ፡ መርቶ ፡ የሚያደርሰን ፡ ብርሃንነቱ፡ በልቡናችን ፡ እንዲበራና ፡ ብሩሃን ፡ እንድ ንሆን፡ነው፡እንጂ።

፫፡ እነሆ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጆች ፡ የሰው፡ ልጆችን ፡ መልከ ፡ መልካሞች ፡ ላሕይ፡ ያላቸው ፡ እንደሆኑ ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡ ከእነርሱ፡ ለራሳቸው ፡ የመረጡትን ፡ ሚስቶች ፡ ወሰዱ፤ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ የሚቀርቡ ፡ የእግዚአ ብሔር ፡ ልጆች ፡ እንደሚባሉ ፡ ወደ ፡ ሥጋዊ፡ ፍትወት ፡ የሚሄዱ ፡ የሥጋ ፡ ልጆች ፡ እንዲባሉ፡አሁን፡ተመልከት።

፬፡ ስለዚህ ፡ አምላካዊ ፡ መጽሐፍ ፡ እንዲህ ፡ አለ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጆች ፡ የሰው ፡ ልጆች፡ ላሕይ፡ ያላቸው ፡ መልከ ፡ መልካሞች፡ እንደሆኑ፡ባዩ፡ጊዜ፡ከእነርሱ፡ለራሳቸው፡የመ ረጡትን ፡ ሚስቶች ፡ ወሰዱ ፤ የእግዚአብሔር፡ ልጆች ፡ የሚላቸው ፡ የሴት ፡ ልጆች ፡ ናቸው፡ ሴት ፡ የእግዚአብሔር ፡ ወዳጅ ፡ ነበርና

| በ፱፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘሠሉስ። | ማክሰኞ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት። |
|---|---|
| ፭፤ ወይቤ ፡ ደቂቀ ፡ ሥጋ ፡ እለ ፡ ተወልዱ ፡ እምቃየል፡ እስመ ፡ ኮኑ ፡ መፍቀርያነ ፡ ፍትወት፡ዘሥጋ። | ፭፤ ከቃየል፡የተወለዱትን፡የሥጋ፡ልጆች፡አለ፡ እነርሱ ፡ ሥጋዊ ፡ ፍትወትን ፡ ወዳጆች ፡ ነበሩና። |
| ፮፤ ነጽር ፡ ይእዜኒ ፡ አ ፡ ለዝንቱ ፡ ፍድፍድና ፤ መጽሐፍ ፡ እምላካዊ ፡ እፎ ፡ ፈከረ ፡ ለነ ፡ ርኩሰሙ ፡ ወምርዐቶሙ ፡ ከመ ፡ ውእቶሙ ፡ አኮ፡ለአውስቦ፡ወነሢአ፡አንስትያ፡ለረኪበ፡ ውሉድ ፡ ባሕቲቱ ፡ ዘኀለዩ ፡ ዳእሙ ፡ ለተመጥዎ፡ፍትወት፡ዘሥጋ። | ፮፤ ወዮ ፡ አሁንም ፡ ይህን ፡ ብልጫ ፡ እስኪ ፡ ተመልከት፤እምላካዊ፡መጽሐፍ፡እንዴት፡ እንደተረጎመልን፡እዩ፤ርኩሰታቸውና፡መዳ ራታቸው፡በጋብቻ፡አይደለም፤ሚስቶችን፡ መውሰዳቸውም፡ልጅን፡ለመውለድ፡ብለው፡ አይደለም ፤ ሥጋዊ ፡ ፍላጎታቸውን ፡ ለማርካት፡ነው፡እንጂ። |
| ፯፤ ጠይቅኬ፡እፎ፡ኮነ፡ኀልዮ፡ፍትወት፡ዘሥጋ፡ እኩይ፡እምዝሙት፡ወእምርዐት። | ፯፤ ከመዳራትና፡ከዝሙት፡የሚያደርስ፡የሥጋዊ፡ ፈቃድን፡ማሰብ፡ክፉ፡እንደሆነ፡ዕወቅ፤ተረዳ። |
| ፰፤ ወእፎ ፡ ኮነ ፡ አስተአድሞ ፡ ላሕይ ፡ ወሥን ፡ ምክንያተ ፡ ለሙስና ፡ ወሀጕል ፡ ወርሒቅ ፡ እምረድኤት፡እምላካዊ። | ፰፤ ላሕይና ፡ ደም ፡ ግባትም ፡ ለጥፋትና ፡ ለጉስ ቍልና፡ከአምላካዊ፡ረድኤትም፡ለመለየት፡ እንዴት፡ምክንያት፡እንደሆነ፡ዕወቅ፤ተረዳ። |
| ፱፤ ወበእንተዝ ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኢይከውን፡ መንፈስየ ፡ ዲበ ፡ ዝንቱ ፡ ትውልድ፡እስመ፡ሥጋ፡እሙንቱ፡ወይኩን፡ መዋዕሊሆሙ፡፻ተ፡ወ፳፡ዓመተ። | ፱፤ ስለዚህም፡እግዚአብሔር፡መንፈሴ፡በዚህ፡ ትውልድ፡ላይ፡አድሮ፡አይኖርም፤እነርሱ፡ ሥጋውያን፡ናቸውና፤ዘመናቸውም፡መቶ፡ ሃያ፡ዓመት፡ይሁን፡አለ። |
| ፲፤ ርኢኩ፡ዕበየ፡ዛቲ፡ትውልድ፡ወሕሠመ፡ ኃጥአን። | ፲፤ ለደቂቀ ፡ ሴት ፡ የነበረውን ፡ ልዕልና ፡ እንዲሁም፡የኃጢአተኞችን፡ጥፋት፡አየህን? |
| ፲፩፤ ርኢኩ ፡ እፎ ፡ ኮነ ፡ አስተአድሞ ፡ ሥጋ ፡ ምክንያተ፡ለኵሉ፡እከይ። | ፲፩፤ የሥጋ ፡ ማማርና ፡ ውበት ፡ ለክፋት ፡ ሁሉ ፡ እንዴት፡ምክንያት፡እንደሆነ፡አየህን? |
| ፲፪፤ ርኢኩ ፡ እፎ ፡ ኮነ ፡ ፍትወተ ፡ ዝሙት ፡ ምክንያተ ፡ ለኀጕል ፡ ዘይደፍን ፡ ወአሳሪተ ፡ በኵሉ፡እከይ። | ፲፪፤ የዝሙት ፡ ፍላጎት ፡ በክፋት ፡ ሁሉ ፡ የሚአ ስርና፡ በጥፋትም ፡ የሚደፍን ፡ እንዴት ፡ እንደሆነ፡አየህን? |
| ፲፫፤ ርኢኩ፡እፎ፡አርሐቀት፡፡እምሕረተ፡እግዚ አብሔር ፡ ወሠወረት ፡ ዋካ ፡ ኀብረት ፡ ወአኀ ጸረት ፡ ኑኀ ፡ መዋዕል ፡ ወአብጽሐት ፡ ኀበ ፡ ኵሉ፡እኩይ። | ፲፫፤ ከእግዚአብሔር ፡ ምሕረት ፡ እንዴት ፡ እንዳ ራቀች ፡ የአንድነት ፡ ብርሃንንም ፡ እንደሠ ወረች ፡ ረጅም ፡ ዕድሜንም ፡ እንዳሳጠረች ፡ ወደ፡ክፉ፡ጥፋትም፡እንዳደረሰች፡አየህን? |
| ፲፬፤ ርኢኩ ፡ እፎ ፡ ይሰመዩ ፡ እለ ፡ ይፈትዉ ፡ ልደታተ፡ምድራውያተ፡ዘሥጋ። | ፲፬፤ ሥጋዊ ፡ የሆነ ፡ ምድራዊ ፡ ትውልድን ፡ የሚፈልጉ ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ስም ፡ እንዲወጣ ላቸው፡አየህን? |
| ፲፭፤ ርኢኩ፡ምግባራተ፡ኃጕሎሙ፡ሚ፡መጠን፡ ድቀት፡ዘወረደ፡ዲቤሆሙ። | ፲፭፤ ምን ፡ ያህል ፡ ውድቀት ፡ በላያቸው ፡ እንደ ፡ ወረደና፡የጥፋታቸውንም፡ሥራ፡አየህን? |
| ፲፮፤ ሰማዕኩ ፡ እፎ ፡ ዘንመት ፡ አስራበ ፡ ሰማይ ፡ ወተፈትሓ ፡ አንቅዕተ ፡ ማዕምቅት ፡ ወከደነ ፡ አይኅ፡ኵሎ፡ዘሥጋ። | ፲፮፤ የሰማይ ፡ ጐርፍ ፡ እንዴት ፡ እንደ ፡ ወረደ ፡ የጥልቁም፡ምንጮች፡እንዴት፡እንደመነጩና፡ የጥፋት፡ውኃ፡ሥጋዊውን፡ሁሉ፡እንዳሰጠመ። |
| ፲፯፤ ወአማሰነ ፡ አዕዋፈ ፡ ሰማይ ፡ ወአራዊተ ፡ ወኵሎ፡ዘይትሐወስ፡ወሰራሬተ፡ወኵሎ፡ዘቦ፡ መንፈስ፡ሕይወት። | ፲፯፤ የሰማይ ፡ ወፎችን ፡ አራዊትን ፡ የሚንቀሳቀ ሰውን፡ሁሉ፡በክንፍ፡የሚበረውንም፡ሁሉ፡ በደመ ፡ ነፍስ ፡ ሕያው ፡ የሆነውን ፡ ሁሉ ፡ እንዴት፡እንዳጠፋ፡ሰማህን? |
| ፲፰፤ ርኢኩ፡ደኀሪቶሙ፡ለኃጥአን፡ምሩዓን። | ፲፰፤ ሴሰኞች፡የሆኑ፡የኃጥአንን፡ፍጻሜአቸውን፡ አየህን? |

በ፱፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘሠሉስ።

ብረነ፡ክብርክሙ፡እምላካዊ፡ውስተ፡ቤተ፡ክርስቲያን፡ቅድስት፡እንተ፡ኅቤነ፡ከመ፡ንዝክር፡ዘንተ፡በእምጣንነ፡ዘከመ፡ሥርዓተ፡ቀኖና።

፳፩፤ ወይእዜኒ፡ድልዋን፡ንሕነ፡ለገቢር፡ንብል፡ወነአምን፡በወልደ፡እግዚአብሔር፡ዋሕድ፡ዘተወልደ፡እምአብ፡እምቅድመ፡ኵሉ፡ዓለም፡ቀዳማዊ፡ምስለ፡አብ፡ወመንፈስ፡ቅዱስ፡ብርሃነ፡ጽድቅ፡ዘእምብርሃነ፡ጽድቅ፡አርአያ፡አካሉ፡ለአብ፡ዘኢይተዌለጥ።

፳፪፤ ወሶበ፡ተሣሃለ፡ፍጡራኒሁ፡እምነ፡መርገም፡ወሙስና፡ዘወድቀ፡ቦቱ፡አዳም፡በጌጋዩ፡ወፍትሐኒ፡ዘፈትሐ፡ላዕሌሁ፡እጽነነ፡ሰማያተ፡ወወረደ፡እንዘ፡ኢየዓርቅ፡እመንበረ፡ንግሡ፡እምላካዊ፡ወኀደረ፡ውስተ፡ከርሠ፡ድንግል፡ንጽሕት፡ማርያም፡ወተሠገወ፡እመንፈስ፡ቅዱስ፡ወእምኔሃ፡ለብሰ፡ድንግልናዊ፡ሥጋሃ፡ወረሰዮ፡አሐደ፡ምስሌሁ፡በአካሉ፡ወቦቱ፡ነፍስ፡ነባቢት፡ወለባዊት።

፳፫፤ ኢሀሎ፡እምቅድመ፡ኅድረቱ፡ወኢኮነ፡ተዋሕዶቱ፡ቦቱ፡ህልወ፡እምቅድመዝ፡በከመ፡ይቤ፡አምሳሊሆሙ፡ለሐዋርያት፡አትናቴዎስ፡ዐቢይ፡ወሥጋኒ፡አሚሃ፡ኮነ፡ሥጋ፡ቃለ፡እግዚአብሔር፡ሥጋ፡ዘቦቱ፡ነፍስ፡ነባቢት፡ወለባዊት፡ወአሚሃ፡ሥጋሁ፡ለእግዚእነ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ተሥዕለ፡በጥንተ፡አካል፡እንዘ፡ይትዋሐድ፡ምስለ፡ቃል።

፳፬፤ ወከመዝ፡ተፀገሠ፡መዋዕለ፡ልደቱ፡ተስዓተ፡አውራኀ፡ወአስተርአየ፡እምኔሃ። ሰብአ፡ዘበአማን፡ወኢፈትሐ፡ማኅተመ፡ድንግልናሃ፡ወእግዚአብሔር፡ቃል፡ዘወለደቶ፡ለሊሁ፡ያቀንት፡ኀይለ፡ለድኩማን፡ወከመዝ፡ወሰከ፡ኀቤሁ፡ሥጋ፡በተዋሕዶ፡አካል፡በዘ፡ኢይትረከብ፡ወበዘኢይትነገር።

፳፭፤ ወኢይክል፡ንባበ፡ዕጓለ፡እመሕያው፡ያእምሮ፡አው፡ይዝክር፡ክዋኔ፡ልደቱ፤ ወተፀገሠ፡

ማክሰኞ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

ብሔር፡ቃል፡የፈጸመው፡ሰው፡መሆን፡ነው፤ በእኛ፡ዘንድ፡ባለችው፡በምእመናን፡ጉባኤ፡እንደ፡አእምሮአችን፡መጠን፡የተወሰነ፡ሥርዓት፡እንደ፡መሆኑ፡ይህን፡ምሥጢረ፡ሥጋዌ፡እናስተምር፡ዘንድ፡አምላክ፡ያከበረው፡ሰውነታችሁ፡ያገብረናል።

፳፩፤ አሁንም፡እኛ፡ይኸን፡ለማድረግ፡ዝግጁዎች፡ነን፤ዓለም፡ሳይፈጠር፡ከአብ፡በተወለደ፡እንደ፡አብ፡እንደ፡መንፈስ፡ቅዱስ፡ቀዳማዊ፡በሚሆን፡ከእውነተኛ፡ብርሃን፡ከተገኘ፡በዕውነተኛ፡ብርሃን፡አብን፡በመልክ፡በሚመስለው፡በባሕርይ፡በሚተካከለው፡መለወጥ፡በሌለበት፡በአንድ፡በእግዚአብሔር፡ልጅ፡እናምናለን፡እንበል።

፳፪፤ አዳም፡በኃጢአቱ፡ተይዞበት፡ከነበረ፡ፍዳ፡መርገም፡ከፈረደበትም፡ፍርድ፡ፍጥረቶቹን፡ላድን፡ባለ፡ጊዜ፡ከባሕርይ፡ጌትነቱ፡ዙፋን፡ሳይለይ፡ከሰማየ፡ሰማያት፡ወርዶ፡በንጽሕት፡ማርያም፡ማኅፀን፡አደረ፤ በግብረ፡መንፈስ፡ቅዱስም፡ከዘር፡ከሩካቤ፡ንጹሕ፡የሆነ፡ሥጋዋን፡ከእርሷ፡ተዋሐደ፤ በተለየ፡አካሉም፡ከእርሱ፡ጋራ፡አንድ፡አደረገው። የምትጸውቅ፡የምትናገር፡ነፍስ፡አለችው።

፳፫፤ ሥጋ፡በቅድምና፡የነበረ፡አይደለም፤ ቃልም፡ሥጋን፡መዋሐዱ፡ከዚህ፡በፊት፡(ዕለተ፡ፅንስ)፡የነበረ፡አይደለም፤ ሐዋርያትን፡የሚመስላቸው፡ደገኛው፡አትናቴዎስ፡እንደተናገረ፡ሥጋም፡ያን፡ጊዜ፡የእግዚአብሔር፡ቃል፡ሥጋ፡ሆነ፤ የምታውቅ፡የምትናገር፡ነፍስ፡ያለችው፡ሥጋ፡ነው። ያን፡ጊዜም፡የጌታችን፡የኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ሥጋው፡ከቃል፡ጋር፡ተዋሕዶ፡የዕለት፡ፅንስ፡በመሆን፡ተቀረፀ።

፳፬፤ እንዲሁም፡ከመወለድ፡አስቀድሞ፡ያሉትን፡ቀኖች፡ዘጠኝ፡ወር፡ጠበቀ፤ ከእርሷም፡በእውነት፡ሰው፡ሁኖ፡ተገለጠ፤ ማኅተመ፡ድንግልናዋንም፡አልለወጠም፤ የወለደችው፡እግዚአብሔር፡ቃልም፡እርሱ፡የደከሙትን፡ያጸናቸዋል፤ በማይነገር፡በማይመረመር፡በአካል፡ተዋሕዶ፡ሥጋን፡ለራሱ፡ገንዘብ፡አደረገ።

፳፭፤ የልደቱን፡ነገር፡ሰው፡ሊአውቀው፡ሊናገረው፡አይችልም፤ የአካል፡ዕድገት፡ፍጻሜ፡እስከሚ

## በ፱፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሠሉስ።

፲፱፤ ወለእመ ፡ ትቤ ፡ እፎ ፡ ኮነ ፡ ዝንቱ ፡ ሀጕል ፡
እኩይ፡በእንተ፡ፍትወተ፡ዝሙት፡ባሕቲቱ።
፳፤ አወሥአከ ፡ እወ ፡ እስመ ፡ አንተ ፡ ትረክብ ፡
ዝሙተ ፡ ምክንያተ ፡ እከይ ፡ ብዙኀ ፡ እስመ ፡
ኀበ ፡ ሀሎ ፡ ስካር ፡ ወምርዐት ፡ ወእከይ ፡ ህየ ፡
ሀሎ፡ኵሉ፡ምግባረ፡እከይ።
፳፩፤ ወበእንተዝ፡ይቤ፡መጽሐፍ፡ሶበ፡ርእየ፡እግ
ዚአብሔር፡አምላክ፡ከመ፡በዝኀ፡እከዮሙ፡
ለሰብእ፡ላዕለ፡ምድር፡እስመ፡ዛቲ፡ኀሠሣ፡
እኪት፡ኢቆመት፡ላዕለ፡ወራዙት፡ባሕቲታ፤
ዳእሙ ፡ ወድቀት ፡ ኀበ ፡ ህመቀ ፡ አረጋዊ ፡
ወወሬዛ ፡ ወብእሲት ፡ ወደቂቅ ፡ ወባዕል ፡
ወነዳይ፡ወገብር፡ወእግዓዚ።
፳፪፤ ወበእንተዝ ፡ ይቤ ፡ መጽሐፍ ፡ እም
ላካዊ ፡ ወነስሐ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክ ፡
ላዕለ፡ኵሉ፡ፍጥረት፡ዘሥጋ፡ወኀለየ፡እንዘ፡
ይብል ፡ እደመስሶ ፡ ለሰብእ ፡ ዘገበርኩ ፡
እምታሕተ ፡ ሰማይ ፡ ወለእንስሳ ፡ ወለኵሉ ፡
ዘይትሐወስ ፡ ወሰራሪት ፡ ወሰገኖታት ፡
ወአዕዋፈ፡ሰማይ።
፳፫፤ ወፍካሬ፡ብሂሎቱሰ፡ለልዑል፡ከመዝ፡ብሂል፡
እስመ፡አነ፡ገበርኩ፡ዘይደሉ፡ኵሎ፡ወፈጠርኩ፡
ወአጣዕጣእኩ ፡ ወአምጻእኩ ፡ እምኀበ ፡
ኢሀልዎ፡ ኀበ ፡ ሀልዎ ፡ ወአብዛኀኩ ፡ ሠናያተ፡
ወአማዕቀብኩ፡ለፍጥረተ፡ዕጓለ፡እመሕያው፡
አእምሮ፡ለዘይደሉ፡በዘመፍትው።
፳፬፤ ወለዘኢይደሉ ፡ በዘኢመፍትው ፡ ወአ
ምለክዎ፡ በፈቃደ ፡ ሥጋሁ ፡ ወአሥለጥ
ክዎ ፡ መንግሥተ ፡ ወውእቱ ፡ ኀደገ ፡ ምክረ ፡
ልዑል ፡ ወወለጠ ፡ ግዕዘ ፡ በፍትወታት ፡
ዘሥጋ።
፳፭፤ ወበእንተ፡ዝንቱ፡እፈቅድ፡አንጽሓ፡ለኵላ፡
ምድር፡እምዐመፃሁ፡ወአህጕሎ፡እምኵሉ፡
ዘታሕተ ፡ ሰማይ ፡ ወእደመስሶ ፡ እምኔ ፡
ምድር፡ ወአማስኖ ፡ በኵነኔ ፡ ዘአልቦቱ ፡
መጠን።
፳፮፤ ወሶበ ፡ ጠየቀ ፡ ዘንተ ፡ ኀሠመ ፡ ምግባሮሙ ፡
ለኃጥአን ፡ ነጽር ፡ ኀበ ፡ ፍድፍድና ፡ ኄራን ፡

## ማከሰኞ፡መዓልት በ፱ ሰዓት።

፲፱፤ በዝሙት ፡ ፍላጎት ፡ ብቻ ፡ ይኸ ፡ ክፉ ፡ ጥፋት፡
እንዴት፡ሆነ፡ብትል።
፳፤ እመልስልሃለሁ፤ አወን፤ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ዝሙት፡
የክፉ ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ ምክንያት ፡ ሁኖ ፡ ታገኘ
ዋለህ፤ ስካር ፡ መዳራት ፡ ባለበት ፡ ቦታ ፡ ሁሉ፡
በዚህ፡የክፉ፡ሥራ፡ሁሉ፡መፈጸሚያ፡ነውና፡
፳፩፤ ስለዚህ፡መጽሐፍ፡እንዲህ፡አለ፤ የሰዎች፡ክፉ
ሥራ፡በምድር፡እንደ፡በዛ፡እግዚአብሔር፡ባየ፡
ጊዜ፡አለ፤ ይህቺ፡ክፉ፡ፍትወት፡(ፍላጐት)፡በጐ
ልማሶች፡ላይ፡ብቻ፡ጸንታ፡አልቀረችም፤ ከር
ግን ፡ በሽማግሎችና ፡ በጎልማሶች ፡ በሴቶችና፡
በልጆች ፡ በባለጠጋውና ፡ በደኃው ፡ በጌታውና፡
በሎሌው፡አደረች፡እንጂ።
፳፪፤ ስለዚህም፡ደግሞ፡አምላካዊ፡መጽሐፍ፡እግ
ዚአብሔር ፡ አምላክ ፡ በፈጠረው ፡ በሥጋዊ፡
ፍጥረት ፡ ላይ ፡ አዘነ ፤ ተጸጸተ ፡ አለ፤ የፈጠር
ኩትን ፡ ከሰማይ ፡ በታች ፡ ያለ ፡ ሰውን ፡ እንስ
ሳትን ፡ የሚንቀሳቀሰውን ፡ ሁሉ ፡ የሚበረ
ውንም፡ሰገኖዎችን፡የሰማይ፡ወፎችን፡ሁሉ፡
እደመስሰዋለሁ፡ብሎ፡አሰበ።
፳፫፤ ልዑል ፡ አምላክ ፡ ያለውም ፡ ምሥጢሩ፡
እንደዚህ ፡ ነው ። እርሱ ፡ ሁሉን ፡ ካለመኖር፡
ወደ ፡ መኖር ፡ አምጥቼ ፡ እንደሚገባ፡
አከናውኜ ፡ ፈጠርኩ ፤ መልካሙንም፡
አበዛሁ፤ ዕውቀት ፡ ለተገባው ፡ ለሰው፡
ፍጥረት፡በሚገባ፡አስጠበቅሁ።
፳፬፤ ለማይገባው ፡ ያለ ፡ አግባብ ፡ አስገዛቼው፡
ነበር፤ በሥጋዊ፡ፈቃድ፡የጸና፡ሲሆን፡በመን
ግሥት ፡ አሠልጥኜው ፡ ነበር ፤ እርሱ ፡ ግን፡
የልዑል ፡ አምላክን ፡ ምክር ፡ ትቶ ፡ በሥጋዊ፡
ፍትወት፡ጠባዩን፡ለወጠ።
፳፭፤ ስለዚህም ፡ መላዋን ፡ ምድር ፡ ከዐመፃው፡
ንጹሕ ፡ ላደርጋት ፡ ከሰማይ ፡ በታች ፡ ከሁሉ፡
አጠፋው፡ዘንድ፡እወዳለሁ፤ ከምድርም፡ላይ፡
እደመስሰዋለሁ ፤ መጠን ፡ በሌለው፡
ቅጣትም፡አጠፋዋለሁ፡አለ።
፳፮፤ የኃጥአንን ፡ የተበላሸ ፡ ሥራቸውን ፡ ከተረዳ፡
ወደ፡ደጋጎቹ፡ብልጫ፡ተመልክቶ፤ ወደ፡ማለ

Scanned by CamScanner

## በ፱፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘሠሉስ።

ወነዓ ፡ ኀበ ፡ ማእከል ፡ ወአልዕል ፡ ንጻሬክ ፡ ኀበ ፡ መልዕልት ፡ ከመ ፡ ታእምር ፡ ፍድፍድናሁ ፡ ለጻድቅ ፡ ኖኅ ፡ ከመ ፡ ኢወለጠ ፡ ፍቅረ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወኢ ፡ በፍትወት ፡ ወኢበተደልዎ ፡ ኢ ፡ ለበሊዕ ፡ ወኢ ፡ ለስካር ፡ ወኢ ፡ ለኵሉ ፡ ፍትወታት ፡ ዘሥጋ ፡ ዳእሙ ፡ ሖረ ፡ በማእከለ ፡ ምሩዓን ፡ ጽኑዐ ፡ ከመ ፡ አንበሳ ፡ ወልዑለ ፡ ከመ ፡ ንስር ፡ ወጽኑዐ ፡ ከመ ፡ እብነ ፡ አድማስ።

፳፯፤ ወተመይጠ ፡ ሎሙ ፡ ዐዋዴ ፡ ወመገሥጸ ፡ ለሀኬቶሙ ፡ ወዐቃቤ ፡ ለቀለምጺጸ ፡ ሠናያት ፡ እስከ ፡ ደለዎ ፡ ውዳሴ ፡ እምእግዚአብሔር ። ወድኅነ ፡ እማእከለ ፡ እለ፡ተሀጕሉ።

፳፰፤ አ ፡ መንክር ፡ እፎ ፡ አሐዱ ፡ ኄር ፡ ወጻድቅ ፡ ኀየሰ ፡ እምአእላፍ ፡ ዕልዋን ፡ እለ ፡ ኢይት ኃለቁ።

፳፱፤ ወእፎ ፡ በኃጢአተ ፡ ዘመደ ፡ ዕጓለ ፡ እመሕያው፡ ተሀጕሉ ፡ ዘመደ ፡ እንስሳ ፡ ወበኂሩተ፡አሐዱ፡ጻድቅ፡ተሐደሰ፡ፍጥረት፡ካልእ።

፴፤ አ ፡ ለዕበየ ፡ ኀይለ ፡ ሂሩት ፡ ዘአድኀኖ ፡ ለዐርክ፡እማእከለ፡ቅዱሳን፡ወሠወረቶ፡በመንጦላዕተ፡ምሕረት፡ወመጠቀቶ፡በሐፀረ፡ረድኤት።
ወከደነቶ ፡ በአልባሰ ፡ ፍቅር ፡ ወረሰየቶ ፡ አበ ፡ ለብዙኃን ፡ አሕዛብ ፡ ወይነውኅ ፡ ፍካሬሃ።

፴፩፤ ይደልወነኬ ፡ ከመ ፡ ንለቡ ፡ ዘንተ ፡ ነገረ ፡ ወንደዮ፡ውስተ፡እዘኒነ፡ሌሊተ፡ወመዐልተ፡ እመኒ ፡ ኖምነ ፡ ወእመኒ ፡ ተንሣእነ ፡ ከመ ፡ ይኩን፡መድኃኒተነ።
ወንትባላሕ ፡ በጸጋሁ ፡ ለመድኃኒነ ፡ እግዚአብሔር።
ዘሎቱ ፡ ስብሐት ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን።

## ማክሰኞ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

ላዊው ፡ ምርምር ፡ መጥተህ ፡ አመለካከትህን ፡ ወደ፡ ላይ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አድርግ፤የዕውነተኛውን፡ የኖኅን ፡ የማዕርጉን ፡ ብዛት ፡ ታውቅ ፡ ዘንድ ፡ እርሱ ፡ በመመኘትም ፡ ቢሆን ፡ በምቾትም ፡ ቢሆን፡በመብላት፡በመጠጣት፡ሁልጊዜ፡በመስከርም፡ቢሆን፡በሥጋዊ፡ፍትወትም፡ቢሆን፡ የእግዚአብሔርን፡ትእዛዝ፡እንዳልለወጠ፡ነገር፡ግን፡በርኩሳን፡ኃጥአን፡መካከል፡እንደ፡አንበሳ፡ ጠንክሮ፡እንደ፡ንስር፡መጥቆ፡እንደ፡አድማስ፡ ደንጊያ፡ጸንቶ፡ኖረ፡እንጂ።

፳፯፤ ዶ-ላቂን፡ለእነርሱ፡ዐዋጅ፡ነጋሪና፡ኃጢአታቸውን ፡ የሚዘልፍ ፡ የዕውቀት ፡ ብልጭታንም፡የሚጠብቅ፡ሁኖ፡ተመለሰ፤ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ መመስገንና ፡ ባለሟልነት ፡ እስከ ፡ ተገባው ፡ ድረስ ፡ ከተደመሰሱት ፡ መካከልም፡ተለይቶ፡ዳነ።

፳፰፤ ወዮ፡ለዚህ፡አንክሮ፡ይገባል፤ይህ፡ድንቅ፡ነገር፡ ነው ፤ አንዱ ፡ ደግ ፡ ዕውነተኛ ፡ ሰው ፡ ከማይ ቈጠሩ፡አእላፋት፡ከሀዲዎች፡እንዴት፡ተሻለ?

፳፱፤ የሰው ፡ ወገን ፡ በሠራው ፡ ኃጢአት ፡ የእንስሳ ወገኖች ፡ እንዴት ፡ ጠፉ ? በአንድ ፡ ጻድቅ ፡ ደግነትስ፡ፍጥረቱ፡ሁሉ፡እንዴት፡ሁለተኛ፡ ታደሰ?

፴፤ ወዮ ፡ ለመደምሰስ ፡ ከተለዩት ፡ መካከል ፡ የጌታ ፡ ወዳጅ ፡ የሆነውን ፡ ኖኅን ፡ ላዳነችው ፡ ለዚች ፡ የደግነት ፡ ኃይል ፡ ልዕልና ፡ አንክሮ ፡ ይገባል ፤ እርሷም ፡ በምሕረት ፡ መጋረጃ ፡ ሠወረችው ፤ በረድኤት ፡ ክንፍም ፡ መጠቀችው፤በፍቅር፡ልብስም፡ሸፈነችው፤ ለብዙ፡ወገኖችም፡አባት፡አደረገችው፤ትርጓሜዋም፡ይበዛል።

፴፩፤ ይህንንም፡ነገር፡እናስተውለው፡ዘንድ፡በቀንና፡ በሌሊትም፡ተኝተንም፡ቢሆን፡ተነሥተንም፡ ቢሆን፡ወደ፡ውሣጣዊ፡ልቡናችን፡እናስገባው፡ ዘንድ፡ይገባናል፤መድኃኒታችን፡ይሆን፡ዘንድ።
በመድኃኒታችን፡በእግዚአብሔር፡በጸጋው፡ እንድን፡ዘንድ።
በእርሱም ፡ ለዘላለሙ ፡ ክብር ፡ ምስጋና ፡ ይሁን፤አሜን።

Scanned by CamScanner

## በ፱፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሠሉስ።

### ምንተኑ፡በል።

ተአምሪሃ፡ለእግዝእትነ፡ቅድስት፡ድንግል፡ በክልኤ፡ማርያም፡ወላዲተ፡አምላክ፡ጸሎታ፡ ወበረከታ፡የሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡ አሜን።

፩፤ ወሀለወት፡አሐቲ፡ብእሲት፡ዘታፈቅራ፡ለእ ግዝእትነ፡ቅድስት፡ድንግል፡በክልኤ፡ ማርያም፡ወላዲተ፡አምላክ፡ወወለደት፡ ይእቲ፡ብእሲት፡ወለተ።

፪፤ ወወሰዳ፡ዝእብ፡ለይእቲ፡ወለት፡ወነገርዋ፡ ለይእቲ፡ብእሲት፡እንዘ፡ሀለወት፡በጊዜ፡ ማእድ፡ወአውየወት፡በዐቢይ፡ቃል፡እንዘ፡ ትብል፡እሙነኑ፡ወሰዳ፡ለወለትየ፡ዝእብ፡ ወኢአምነት፡ዘነገርዋ።

፫፤ ወሖረት፡ኀበ፡ቤተ፡ክርስቲያን፡ወጸለየት፡ ቅድመ፡ሥዕላ፡ለእግዝእትነ፡ቅድስት፡ ድንግል፡በክልኤ፡ማርያም፡ወላዲተ፡ አምላክ፡እንዘ፡ትብል፡እስከ፡አግባእኪ፡ ሊተ፡ወለትየ፡አነ፡እነሥእ፡ለወልድኪ፡እም ሕፅንኪ።

፬፤ ወእምዝ፡ነሥአቶ፡ለሕፃና፡እምውስተ፡ ሕፅና፡ለሥዕል፡ወአብአቶ፡ውስተ፡ቤታ፡ ወአንበረቶ፡በሣጹን፡ወነሥነሰት፡ላዕሌሁ፡ አፈዋተ፡ማየ፡ወርድ፡ወከደነቶ፡በአልባሰ፡ ሐሪር።

፭፤ ወበይእቲ፡ሌሊት፡አብርሀ፡ውስተ፡ቤታ፡ ከመ፡ብርሃነ፡መብረቅ፡ወበይእቲ፡ሰዓት፡ አምጽአት፡ወለታ፡ዘመሠጣ፡ዝእብ፡እግዝ እትነ፡ማርያም፡ወትቤላ፡ንሥኢ፡ወለተኪ፡ ወሊተኒ፡ሀብኒ፡ወልድየ፡ዘነሣእኪዮ፡እምሕ ፅንየ።

፮፤ ወትቤላ፡ይእቲ፡ብእሲት፡ለእግዝእትነ፡ ማርያም፡ንሥኢ፡ወልደኪ፡አ፡ንግሥተ፡ ሰማያት፡ወምድር፡ወአነ፡እገብር፡ ተዝካረኪ፡በዕጣን፡ወበማኅቶት።
ጸሎታ፡ወበረከታ፡የሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ ዓለም፡አሜን።

ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ጥዑመ፡ስም፡በል።
ተአምር፡ወመንክር፡ዘገብረ፡እግዚእነ፡ወአ ምላክነ፡ወመድኃኒነ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡

## ማክሰኞ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

### ምንተኑ፡በል።

ልመናዋ፡በረከቷ፡ለዘላለሙ፡ይደርብንና፡ አምላክን፡የወለደች፡በድንጋሌ፡ሥጋ፡ በድንጋሌ፡ነፍስ፡የጸናች፡ክብርት፡እመቤታችን፡ ማርያም፡ያደረገችው፡ተአምር፡ይህ፡ነው።

፩፤ በድንጋሌ፡ሥጋ፡በድንጋሌ፡ነፍስ፡የጸናች፡ አምላክን፡የወለደች፡ክብርት፡እመቤታችን፡ ማርያምን፡የምትወዳት፡አንዲት፡ሴት፡ ነበረች፤እርሱዋም፡ሴት፡ልጅን፡ወለደች።

፪፤ ያቺንም፡ልጅ፡ጅብ፡ወሰዳት፤እናቷም፡ በማእድ፡ላይ፡እያለች፡ነገሩዋት፤እርሷም፡ እውነት፡ነው፡? ልጄን፡ጅብ፡ወሰዳትን፡ እያለች፡በታላቅ፡ድምፅ፡ጮኸች።የነገሩዋ ትንም፡አላመነችም፡ነበር።

፫፤ ወደ፡ቤተ፡ክርስቲያንም፡ሄዳ፡በሁለት፡ወገን፡ ድንግል፡በሆነችና፡አምላክን፡በወለደች፡ በክብርት፡እመቤታችን፡ማርያም፡ሥዕል፡ ፊት፡ቆማ፡ልጄን፡እስከምትመልሽልኝ፡ ድረስ፡ልጅሽን፡እኔ፡ከክንድሽ፡ላይ፡እወስደ ዋለሁ፡እያለች፡ጸለየች።

፬፤ ከዚህም፡በኋላ፡ሕፃኑን፡ከክንዷ፡ ላይ፡ወሰደችው፤ወደቤቷም፡አስገብታ፡ በሣጥን፡ውስጥ፡አኖረችው፤የአበባና፡የሽቱ፡ ውኃን፡ነሥንሣ፡በሐር፡ልብሶች፡ሸፈ ነችው።

፭፤ በዚያችም፡ሌሊት፡በቤቷ፡ውስጥ፡እንደ፡ መብረቅ፡ያለ፡ብርሃን፡በራ፡ብሎ፡በራ፤ በዚያችም፡ሰዓት፡ጅብ፡ነጥቆ፡የወሰዳትን፡ ልጅ፡እመቤታችን፡ማርያም፡አምጥታ፡ ልጅሽን፡ውሰጂ፤የእኔንም፡ከብብቱ፡ውስጥ፡ የወሰድሽውን፡ልጄን፡ስጪኝ፡አለቻት።

፮፤ ያቺም፡ሴት፡እመቤታችን፡ማርያም፡ የሰማይና፡የምድር፡ንግሥት፡ሆይ፡ልጅሽን፡ ውሰጂ፤እኔም፡በመብራትና፡በማዕጠንት፡ መታሰቢያሽን፡አደርጋለሁ፡አለቻት።
ልመናዋ፡በረከቷ፡ከእኛ፡ጋር፡ለዘላለሙ፡ ይኑር፡አሜን።

ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ጥዑመ፡ስም፡በል።
ይቅርታውና፡ቸርነቱ፡ከእኛ፡ጋር፡ለዘላለሙ፡ ይኑርና፡ጌታችን፡አምላካችንና፡መድኃ

Scanned by CamScanner

## በ፱፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘሠሉስ።

ማህሉ፡ወምሕረቱ፡የሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡
ዓለም፡አሜን።
፩ ወሖረ፡እግዚእ፡ኢየሱስ፡በሳኒታሁ፡ደብረ፡
ዘይት ፡ ወምስሌሁ ፡ ያዕቆብ ፡ ወዮሐንስ ፡
ደቂቀ፡ዘብዴዎስ፡አርዳኢሁ።
፪ ወሶበ፡ርእይዎ፡ያዕቆብ፡ወዮሐንስ፡ውስተ፡
ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ይቤልዎ ፡ ምንት ፡ ይሤኒ ፡
ዝንቱ፡ቤተ፡መቅደስ።
፫ ወይቤሎሙ ፡ እግዚእ ፡ ኢየሱስ ፡ አማን ፡
እብለክሙ ፡ ኢይትረከብ ፡ ውስተ ፡ ዝንቱ ፡
ቤተ፡ መቅደስ ፡ እብን ፡ ዲበ ፡ እብን ፡ እስመ ፡
ይመጽኡ፡አሕዛብ፡እምሥራቀ፡ፀሐይ፡ወእ
ምዕራብ፡ወይነብሩ፡ዲበ፡ማእደ፡አብርሃም፡
ይሥሐቅ፡ወያዕቆብ።
፬ ወለደቂቀ፡መንግሥትሰ፡ይሰድድዎሙ፡ወያ
ወጽእዎሙ ፡ አፍአ ፡ ወይረክቦሙ ፡ ዐቢይ ፡
ሐዘን፡ወአሕዛብሰ፡ይትፌሥሑ።
፭ ወአንትሙሰ፡አርዳእ፡እስመ፡ይበጽሐክሙ፡
መዋዕል፡ዡሉ፡ዘኢ.ገብረ፡ላዕሌክሙ፡እኩየ፡
ወዘኢቀተለክሙ፡ከመ፡ዘኢ.ገብረ፡ምግባረ፡
ሠናይ። ወያገብኡክሙ፡ኀበ፡ነገሥት፡ወመ
ኳንንት ፡ ወይቀትሉክሙ ፡ በእንተ ፡ ስምየ ።
ወይጸልኡክሙ፡ዡሎሙ፡አሕዛብ።
፮ ወለእመ ፡ ቆምክሙ ፡ ኀበ ፡ ነገሥት ፡ ወመኳ
ንንት፡ኢተኀልዩ፡ዘትነብቡ፡ወዘትትናገሩ፡
እስመ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ዘኀዱር ፡ ውስቴ
ትክሙ፡ይነብብ፡በላዕሌክሙ፡ወይትናገር፡
በልሳንክሙ ፡ ወያስተኀፍሮሙ ፡ ለአሕዛብ ፡
በእንቲአክሙ።
፯ ወበውእቱ፡መዋዕል፡ያገብእ፡እኁ፡እኁዋሁ፡
ለሞት ፡ ወአብኒ ፡ ወልዶ ፡ ወውሉድኒ ፡
ይትነሥኡ ፡ ዲበ ፡ አዝማዲሆሙ ፡ ወይቀት
ልዎሙ።
ወዘሰ ፡ አዝለፈ ፡ ትዕግሥቶ ፡ ውእቱ ፡
ይድኀን።
፰ ተዐገሡ፡እንከ፡እስመ፡ከማሁ፡ሰደድዎሙ፡
ለነቢያት፡ቀደምትክሙ።
፱ ብፁዓን ፡ አንትሙ ፡ እለ ፡ ሰደዱክሙ ፡
አሕዛብ፡ ወአሕሰሩክሙ ፡ ወነበቡ ፡
ላዕሌክሙ፡ንባበ፡ሕስወ፡በእንተ፡ስምየ።

## ማክሰኞ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

ጌታችን፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ያደረገው፡ድንቅ፡
ተአምር፡ይህ፡ነው።
፩ ጌታ ፡ ኢየሱስም ፡ በማግሥቱ ፡ ወደ ፡ ደብረ ፡
ዘይት፡ ሄደ ፤ ደቀ ፡ መዛሙርቱም ፡ የዘብዴዎስ ፡
ልጆች፡ያዕቆብና፡ዮሐንስ፡ከእርሱ፡ጋራ፡ነበሩ።
፪ በቤተ ፡ መቅደስ ፡ ውስጥ ፡ ሁኖ ፡ ባዩት ፡
ጊዜ ፡ ይህ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ምን ፡ ያምር ፡
አሉት።
፫ ጌታ ፡ ኢየሱስም ፡ በዚህ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡
ውስጥ፡ደንጊያ፡በደንጊያ፡ላይ፡ሆኖ፡እንደማ
ይገኝ፤ በእውነት፡እነግራችኋለሁ፡ከፀሐይ፡
መውጫ ፡ እስከ ፡ ፀሐይ ፡ መግቢያ ፡ ያሉ ፡
አሕዛብ፡ይመጣሉና፤እነርሱም፡በአብርሃም፡
በይሥሐቅ፡በያዕቆብ፡ማእድ፡ይቀመጣሉ።
፬ የመንግሥትን ፡ ልጆች ፡ ግን ፡ አስወጥተው ፡
ወደ ፡ ውጭ ፡ ይሰዷቸዋል ፤ ታላቅ ፡ ሐዘንም ፡
ያገኛቸዋል፤አሕዛብ፡ግን፡ደስ፡ይላቸዋል።
፭ እናንተም፡ደቀ፡መዛሙርት፡በእናንተ፡ላይ፡ክፉ፡
ያልሠራና፡ያልገደላችሁ፡ሁሉ፡በጎ፡ሥራ፡እንዳ
ልሠራ፡የሚመስለው፡ጊዜ፡ይመጣል፤ወደ፡ነገሥ
ታቱና፡ወደ፡መኳንንቱ፡አደባባይ፡አሳልፈው፡
ይሰጡአችኋል ፤ ስለ ፡ ስሜም ፡ ይገድሏችኋል ፤
አሕዛብ፡ሁሉ፡ይጠሉአችኋል፡አላቸው።
፮ በነገሥታቱና ፡ በገዥዎች ፡ አደባባይ ፡
(በቆማችሁ ፡ ጊዜ) ፡ ብትቆሙ ፡ የምትናገሩ
ትንማ፡የምትመልሱትን፡አታስቡ፤በእናንት፡
አድሮ፡ያለ፡መንፈስ፡ቅዱስ፡በእናንተ፡ላይ፡
ይናገራልና ፤ ስለእናንተም ፡ በአንደበታችሁ ፡
ተናግሮ፡አሕዛብን፡ያሳፍራቸዋል።
፯ በዚያም፡ወራት፡ወንድም፡ወንድሙን፡ለሞት፡
አሳልፎ፡ይሰጣል ፤ አባት ፡ ልጁን ፡ ያሳልፋል ፤
ልጆችም ፡ በወላጆቻቸው ፡ ላይ ፡ በጠላትነት ፡
ይነሳሉ፤ይገድሉአቸውማል።
ትዕግሥቱን፡እዘውትሮ፡የያዘ፡ግን፡እርሱ፡
ይድናል።
፰ እንግዲህ ፡ ታገሡ ፤ እንዲሁ ፡ ከእናንተ ፡ አስ
ቀድሞ፡የነበሩ፡ነቢያትን፡አሳድደዋቸው፡ነበርና።
፱ አሕዛብ፡ያሳድዱአችሁ፡ያዋረዱአችሁ፡ስለ፡
ስሜም ፡ ሐሰት ፡ የተናገሩባችሁ ፡ እናንተ ፡
ብፁዓን፡ናችሁ።

Scanned by CamScanner

## በ፱፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሠሉስ።

፲፤ አእምሩ ፡ አ ፡ አኀውየ ፡ እስመ ፡ ቦ ፡ ምስሐ ፡ ከብካብ ፡ ዘይከውን ፡ ለሕዝብየ ፡ በውስተ ፡ ዛቲ፡ ዓለም ፡ ሠለስተ ፡ ምዕተ ፡ ዕለታተ ፡ እመዋዕል ፡ ዐበይት ፡ እስመ ፡ ይከውኑ ፡ ሕያዋነ፡በፍሥሓ፡ወበሐሤት፡ወበተድላ።

፲፩፤ አሜሃ ፡ ይትሐነጸ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናትየ ፡ እምሥራቀ ፡ ምድር ፡ እስከ ፡ ምዕራብ።

፲፪፤ ወይከውን ፡ ጉባኤየ ፡ በአሐቲ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንየ ፡ እንተ ፡ ሐዋርያት ፡ ቅድስት ፡ ወንጽሕት ፡ ወጽሪት ፡ ለስብሐትየ ፡ ምስለ ፡ አብ ፡ ወመንፈስ፡ ቅዱስ ፡ ጰራቅሊጦስ።

፲፫፤ ወይከውን ፡ መዋዕሊሁ ፡ ለጸላኢ ፡ በትረ ፡ መዐት፡ዘአጠየቁከሙ፡ዜናሁ፡ወፀአቶ፡እምነ ባብያን፡ሠለስተ፡ምዕተ፡ዕለታተ፡ንዑሳነ። ወባሕቱ ፡ አኅጽሮን ፡ ለእማንቱ ፡ መዋዕል ፡ በእንተ፡ኅሩያንየ።

፲፬፤ ወሶበ፡ኢያኀጸርክዎን፡ለእማንቱ፡መዋዕል፡ እምኢተርፈ፡አሐዱ፡ውስተ፡ምድር፡እምእመናንየ።

፲፭፤ ወለእመ ፡ ኢኀደጉ ፡ ሕዝብየ ፡ በውእቱ ፡ መዋዕል ፡ ገቢረ ፡ ኃጢአት ፡ ወኢነስሑ ፡ አመክዕብ ፡ መዋዕሊሁ ፡ ለጸላኢ።

ሣህሉ፡ወምሕረቱ፡የሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ ዓለም፡አሜን።

### ክፍል፡፫።

### ይ፡ዲ፡ቅድመ፡ወንጌል።

መዝ፡፳፬፡፩።

ኀቤከ ፡ እግዚኦ ፡ አንቃዕዶኩ ፡ ነፍስየ ፡ አምላኪየ ። ወኪያከ ፡ ተወከልኩ ፡ ወኢይትኀፈር ፡ ለዓለም ። ወኢይስሐቁኒ ፡ ጸላዕትየ።

### ወንጌል፡ዘማቴዎስ።

ምዕ፡፳፬፡፫–፴፭።

፫፤ ወእንዘ ፡ ይነብር ፡ እግዚእነ ፡ ውስተ ፡ ደብረ ፡ ዘይት ፡ ቀርቡ ፡ ኀቤሁ ፡ አርዳኢሁ ፡ ወይቤልዎ፡ እንተ ፡ ባሕቲቶሙ ፡ ንግረነ ፡ ማእዜ ፡ ይከውን ፡ ዝንቱ ፡ ወምንት ፡ ተአምሪሁ ፡ ለምጽአትከ ፡ ወለኅልቀተ፡ዓለም።

## ማክሰኞ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

፲፤ ወንድሞቼ ፡ ሆይ ፡ ከታላላቆቹ ፡ ቀኖች ፡ ውስጥ ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ቀን ፡ በዚህ ፡ ዓለም፡የሠርግ፡ምሳ፡የሚደረግበት፡እንዳለ፡ እወቁ ፤ በፍጹም ፡ ተድላ ፡ ደስታ ፡ ሕያዋን፡ ይሆናሉና።

፲፩፤ ያን ፡ ጊዜ ፡ ከፀሐይ ፡ መውጫ ፡ እስከ ፡ ፀሐይ፡ መግቢያ ፡ ድረስ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናቶቼ፡ ይታነጻሉ።

፲፪፤ ንጽሕት ፡ ጽሪት ፡ በሆነች ፡ ሐዋርያት ፡ በሰበሰቧት ፡ በከበረች ፡ በአንዲት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን፡የምእመናን፡አንድነት፡ሁኖ፡ከአብና፡ እጽናኝ ፡ ከሆነ ፡ ከመንፈስ፡ ቅዱስ ፡ ጋራ፡ ለጌትነቴ፡ምስጋና፡አንድ፡ይሆናሉ።

፲፫፤ የሐሳዌ፡መሲሕ፡ትንቢት፡ተናጋሪዎች፡እነዳ ንኤል፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ንዑሳን ፡ ዕለታት፡ እንደሆነ፡የአወጣጡንና፡የአመጣጡን፡ዜና፡ እንዳስረዱአቸሁ፡ዘመኑ፡የመከራ፡ይሆናል፤ ነገር፡ግን፡ስለ፡ተመረጡት፡ቀኖቹን፡አሳጥራ ቸዋለሁ።

፲፬፤ እነዚያንም፡ቀኖች፡ባላሳጥራቸው፡ከምእመ ናኖቼ፡በምድር፡ላይ፡አንድ፡ስንኳ፡ባልቀረ፡ ነበር።

፲፭፤ በዚያም ፡ ወራት ፡ ወገኖቼ ፡ ኃጢአት፡ መሥራትን ፡ ትተው ፡ ንስሐ ፡ ካልገቡ፡ የሐሳዌ፡ መሲሕን ፡ ዘመን ፡ ዕጽፍ ፡ አደር ጋለሁ፡አላቸው።

ይቅርታው፡ቸርነቱ፡ከእኛ፡ጋራ፡ለዘላለሙ፡ ይኑር፡አሜን።

### ክፍል፡፫።

### ዲያቆኑ፡ከወንጌል፡አስቀድሞ።

መዝ፡፳፬፡፩።

አቤቱ ፡ ፈጣሪዬ ፡ በአንቃዕድዎ ፡ ልቡና፡ ወዳንተ ፡ መልሼ ፡ ለመንሁ ። በመከራው፡ ለዘላለሙ ፡ እንዳላፍር ፡ ባንተ ፡ አመንሁ፡ ጠላቶቼም፡አይዘብቱብኝም፡ይበል።

### የማቴዎስ፡ወንጌል።

ምዕ፡፳፬፡፫–፴፭።

፫፤ ጌታችንም፡ በደብረ ፡ ዘይት ፡ ተቀምጦ ፡ ሳለ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ ቀረቡና፡ ለብቻቸው ፡ እንዲህ ፡ አሉት ፤ ይህ ፡ መቼ፡ ይሆናል?የመምጣትህስ፡ምልክቱ፡ምንድር፡ ነው ? የዓለሙ ፡ ፍጻሜስ ፡ መቼ ፡ ይሆናል! ንገረን፡አሉት።

### በ፱፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሠሉስ።

፬ ወአውሥአ፡እግዚእ፡ኢየሱስ፡ወይቤሎሙ፡
ዑቁ፡ኢያስሕቱክሙ።
፭ እስመ፡ብዙኃን፡ይመጽኡ፡በስምየ፡እንዘ፡
ይብሉ፡አነ፡ውእቱ፡ክርስቶስ፡ወያስሕ
ትዎሙ፡ለብዙኃን።
፮ ወአመ፡ሰማዕክሙ፡ቀትለ፡ወድምፀ፡
ጸባኢት፡ዑቁ፡ኢትደንግፁ፡እስመ፡ግብር፡
ይከውን፡ዝንቱ፡ኵሉ፡ወባሕቱ፡አኮ፡
በጊዜሃ፡ዘየሐልቅ።
፯ ወይትነሥኡ፡ሕዝብ፡ዲበ፡ሕዝብ፡
ወነገሥት፡ላዕለ፡ነገሥት፡ወይመጽእ፡
ረኃብ፡ወብድብድ፡ወድልቅልቅ፡ወሀከክ፡
በበብሔሩ።
፰ ወዝንቱ፡ኵሉ፡ቀዳሚሁ፡ለሕማም።
፱ አሜሃ፡ይትባጽሑክሙ፡ወይሜጥዉክሙ፡
ለምንዳቤ፡ወይቀሥፉክሙ፡ወይቀት
ሉክሙ፡ወትከውኑ፡ጽሉአነ፡በኀበ፡ኵሉ፡
ሰብእ፡በእንተ፡ስምየ።
፲ ወአሜሃ፡የዐልዉ፡ብዙኃን፡ሃይማኖ
ቶሙ፡ወይጻልኡ፡በበይናቲሆሙ፡ወይት
ቃተሉ፤
፲፩ ወይትነሥኡ፡ብዙኃን፡ሐሳውያን፡ነቢያት፡
ወለብዙኃን፡ያስሕትዎሙ።
፲፪ ወእምብዝኀ፡ዐመፃ፡ወእከይ፡ትሴኰስ፡
ፍቅር፡እምብዙኃን፡ወብዙኃን፡የዐልዉ፡ሃይ
ማኖቶሙ፡ወፍቅሮሙ።
፲፫ ወዘሰ፡አዝለፈ፡ትእግሥቶ፡ውእቱ፡
ይድኅን።
፲፬ ወይሰበክ፡ዝ፡ወንጌለ፡መንግሥት፡
ውስተ፡ኵሉ፡ዓለም፡ከመ፡ይኩን፡ስምዐ፡
ላዕለ፡ኵሉ፡አሕዛብ፡ወይእተ፡አሚረ፡
ይበጽሕ፡ኅልቀት።
፲፭ ወእምከመ፡ርኢክሙ፡ትእምርተ፡ርኵስ፡
ዘምዝባሬ፡ዘተብህለ፡በዳንኤል፡ነቢይ፡
ዘይቀውም፡ውስተ፡መካን፡ቅዱስ፡ዘያነብብ፡
ለይለቡ።
፲፮ አሜሃ፡እለ፡ውስተ፡ይሁዳ፡ይጐየዩ፡ውስተ፡
አድባር።
፲፯ ወዘሂ፡ሀሎ፡ውስተ፡ናሕስ፡ኢይረድ፡
ይንሣእ፡ዘውስተ፡ቤቱ።
፲፰ ወዘሂ፡ውስተ፡ገራኅት፡ሀሎ፡ኢይትመየጥ፡
ድኅሬሁ፡ይንሣእ፡ልብሶ።
፲፱ አሌ፡ሎን፡ለፅኑሳት፡ወለእለ፡የሐፅና፡
በውእቱ፡መዋዕል።

### ማክሰኞ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

፬ ጌታ፡ኢየሱስም፡መልሶ፡እንግዲህ፡እንዳስ
ቷችሁ፡ተጠንቀቁ፡አላቸው።
፭ ብዙዎች፡እኔ፡ክርስቶስ፡ነኝ፡እያሉ፡
በስሜ፡ይመጣሉና፡ብዙዎችንም፡
ያስታሉ።
፮ ጦርነቱን፡ሰልፉን፡የጦርነቱንም፡ዜና፡
በሰማችሁ፡ጊዜ፡እወቁ፤አትደንግጡ፤ይህ፡
ሁሉ፡ግድ፡ይደረጋልና፤ነገር፡ግን፡ወዲያው፡
የሚያልፍ፡አይደለም።
፯ ሕዝብ፡በሕዝብ፡ላይ፡ነገሥታት፡በነገ
ሥታት፡ላይ፡ይነሣሉ፤በየሀገሩ፡ረኃብ፡
ቸነፈር፡ንውጽውጽታ፡ፀብ፡ክርክርም፡
ይመጣል።
፰ ይህ፡ሁሉ፡የመከራው፡መጀመሪያ፡ነው።
፱ ያን፡ጊዜ፡ይከሱአችኋል፤ለመከራም፡
አሳልፈው፡ይሰጧችኋል።ይገርፉአችኋል፤ይገ
ድሏችኋል፤በስሜ፡ስለ፡አመናችሁ፡በሰው፡
ሁሉ፡ዘንድ፡የተጠላችሁ፡ትሆናላችሁ።
፲ ያን፡ጊዜ፡ብዙዎች፡ሃይማኖታቸውን፡
ይለውጣሉ፤እርስበርሳቸውም፡ይጣላሉ፤
ይጋደላሉ።
፲፩ ብዙዎች፡ሐሰተኞች፡መምህራን፡ይነሣሉ፤
ብዙዎችንም፡ያስታሉ።
፲፪ ከዐመፅና፡ከክፋት፡ብዛት፡የተነሣም፡ፍቅር፡
ከብዙዎች፡ትጠፋለች፤ብዙዎችም፡ሃይማኖ
ታቸውንና፡ፍቅራቸውን፡ይክዳሉ።
፲፫ ትዕግሥቱን፡አዘውትሮ፡የያዘ፡ግን፡እርሱ፡
ይድናል።
፲፬ ይህም፡የመንግሥት፡ወንጌል፡በዓለም፡
ሁሉ፡ይሰበካል።በአሕዛብ፡ሁሉ፡ላይ፡
ምስክር፡ሊሆን፡ያን፡ጊዜም፡እልቂት፡
ይደርሳል።
፲፭ በነቢዩ፡በዳንኤል፡የተነገረውን፡የመፍ
ረሱን፡ርኵሰት፡ምልክት፡ያያችሁ፡እንደሆነ፡
በተቀደሰው፡ቦታ፡የሚቆመው፡የሚአነ
በውን፡ያስተውል።
፲፮ ያን፡ጊዜ፡በይሁዳ፡ያሉ፡ወደ፡ተራሮች፡
ይሸሻሉ።
፲፯ በሰገነት፡ያለም፡በቤቱ፡ውስጥ፡ያለውን፡
ያነሣ፡ዘንድ፡አይውረድ።
፲፰ በእርሻም፡ያለ፡ልብሱን፡ሊያነሣ፡
ወደኋላው፡አይመለስ።
፲፱ ነገር፡ግን፡በዚያ፡ወራት፡ለፀነሱትና፡ለሚአ
ሳድጉ፡ወዮላቸው።

## በ፱፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘሠሉስ።

፳፥ ወጸልዩ፡ባሕቱ፡ከመ፡ኢይኩን፡ጕያክሙ፡ በክረምት፡ወበሰንበት።
፳፩፥ እስመ፡ይከውን፡ይእተ፡አሚረ፡ዐቢይ፡ ሕማም፡ ወምንዳቤ፡ ዘኢኮነ፡ ከማሁ፡ እምአመ፡ተፈጥረ፡ዓለም፡እስከ፡ዮም፡ወኢ ይከውንሂ።
፳፪፥ ወሶበ፡አኮ፡ዘአኅጸሮን፡ለእማንቱ፡መዋዕል፡ እምኢድኅነ፡መኑሂ፡ኵሉ፡ዘሥጋ፡ወባሕቱ፡ በእንተ፡ኅሩያን፡የሐፅሩ፡እማንቱ፡መዋዕል።
፳፫፥ አሜሃ፡እመቦ፡ዘይቤለክሙ፡ነዋ፡ዝየ፡ሀሎ፡ ክርስቶስ፡ወነዋ፡ከሐከ፡ኢትእመኑ።
፳፬፥ እስመ፡ ይመጽኡ፡ ሐሳውያን፡ መሲሕ፡ ወሐሳውያን፡ ነቢያት፡ ወይገብሩ፡ ተአምራተ፡ ወመንክራተ፡ ዐበይተ፡ ለአስሕቶ፡ሶበሰ፡ይትከሀሎሙ፡ለኅሩያንሂ፡ እምአስሐትዎሙ።
፳፭፥ ናሁ፡አቅደምኩ፡ነጊሮተክሙ።
፳፮፥ እመቦ፡ዘይቤለክሙ፡ነዋ፡ገዳመ፡ሀሎ፡ ኢትፃዑ፡ ወነዋ፡ ውስተ፡ አብያት፡ ኢትእመኑ።
፳፯፥ እስመ፡ከመ፡መብረቅ፡ዘይወፅእ፡እምጽባሕ፡ ወያስተርኢ፡እስከ፡ዐረብ፡ከማሁ፡ምጽአቱ፡ ለወልደ፡ዕጓለ፡እመሕያው።
፳፰፥ ኀበ፡ሀሎ፡ገደላ፡ህየ፡ይትጋብኡ፡አንስርት።
፳፱፥ ወእምድኅረ፡ሕማሞን፡ለእማንቱ፡መዋዕል፡ ፀሐይኒ፡ ይጸልም፡ ወወርኅኒ፡ ኢይሁብ፡ ብርሃኖ፡ወከዋክብትኒ፡ይወድቁ፡እምሰማይ፡ ወያንቀለቅል፡ኃይለ፡ሰማያት።
፴፥ ወይእተ፡ አሚረ፡ ያስተርኢ፡ ተአምሪሁ፡ ለወልደ፡ዕጓለ፡እመሕያው፡በሰማይ፡አሜሃ፡ ይበክዩ፡ ኵሎሙ፡ አሕዛበ፡ ምድር፡ ሶበ፡ ይሬእይዎ፡ ለወልደ፡ ዕጓለ፡ እመሕያው፡ እንዘ፡ ይመጽእ፡ በደመና፡ ሰማይ፡ ምስለ፡ ኃይል፡ወስብሐት፡ብዙኅ።
፴፩፥ ወይፌንዎሙ፡ለመላእክቲሁ፡ምስለ፡ቃለ፡ ቀርን፡ወስብሐት፡ዐቢይ፡ወያስተጋብእሙ፡ ለኅሩያኒሁ፡ እምአርባዕቱ፡ ነፋሳት፡ እምአ ጽናፈ፡ሰማይ፡እስከ፡አጽናፊሃ።
፴፪፥ ወእምበለስ፡አእምሩ፡አምሳሊሁ፡እምከመ፡ ለምለመ፡ አዕፁቂሁ፡ ወሠረጸ፡ ቈጽሉ፡ ተአምሩ፡ከመ፡ቀርበ፡ማእረር።

## ማክሰኞ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

፳፥ ነገር፡ ግን፡ ስደታችሁ፡ በሰንበትና፡ በክረምት፡እንዳይሆን፡ጸልዩ።
፳፩፥ ያን፡ ጊዜ፡ ዓለም፡ ከተፈጠረ፡ ጀምሮ፡ እስከ፡ ዛሬ፡ ያልተደረገ፡ ከእንግዲህም፡ ወዲያ፡የማይደረግ፡ጽኑ፡መከራና፡ጭንቅ፡ ይሆናል።
፳፪፥ እነዚያን፡ቀኖች፡ባያሳጥራቸው፡ኖሮ፡ሥጋዊ፡ ደማዊ፡ሁሉ፡ማንም፡ባልዳነም፡ነበር፤ነገር፡ግን ስለተመረጡት፡እነዚያ፡ቀኖች፡ያጥራሉ።
፳፫፥ ያን፡ጊዜ፡ክርስቶስ፡እነሆ፡ከዚህ፡አለ፤ወይም፡ ከዚያ፡አለ፡የሚላችሁ፡ቢኖር፡አትመኑ።
፳፬፥ ክርስቶስን፡ የሚክዱ፡ ነቢያትን፡ የሚአ ሳብሉ፡ ሐሰተኞች፡ መምህራን፡ ይነሣሉና፡ ለማሳትም፡ ታላቅ፡ ተአምራትንና፡ ድንቅ፡ ድንቅ፡ ሥራዎችንም፡ ይሠራሉና፡ ቢቻላ ቸውስ፡የተመረጡትንም፡ባሳቷቸው፡ነበር።
፳፭፥ እነሆ፡አስቀድሜ፡ነግሬአችሁአለሁ።
፳፮፥ በምድረ፡ በዳ፡ አለ፡ የሚላችሁ፡ ቢኖር፡ ወደዚያ፡አትውጡ፤በቤት፡ውስጥም፡ነው፡ ቢላችሁ፡አትመኑ።
፳፯፥ መብረቅ፡ ከምሥራቅ፡ ወጥቶ፡ እስከ፡ ምዕራብ፡ እንደሚታይ፡ የሰው፡ ልጅ፡ መምጣትም፡እንዲሁ፡ይሆናል።
፳፰፥ ገደላ፡(እርድ)፡ካለበት፡አሞሮች፡ይሰበሰባሉ።
፳፱፥ በእነዚያ፡ቀኖች፡ከሚደረገው፡መከራ፡በኋላ፡ ፀሐይ፡ ይጨልማል፤ ጨረቃም፡ ብርሃኑን፡ አይሰጥም፤ከዋክብትም፡ከሰማይ፡ይወድቃሉ፡ የሰማዮችም፡ኃይል፡ይናወጣል።
፴፥ በዚያ፡ ወራት፡ የሰው፡ ልጅ፡ ምልክት፡ በሰማይ፡ ይታያል፤ ያን፡ ጊዜም፡ በምድር፡ ያሉ፡አሕዛብ፡ሁሉ፡የሰው፡ልጅ፡በኃይልና፡ ከብዙ፡ ክብር፡ ጌትነት፡ ምስጋና፡ ጋር፡ በሰማይ፡ደመና፡ሁኖ፡ሲመጣ፡ባዩ፡ጊዜ፡ ያለቅሳሉ።
፴፩፥ መልዕክተኞቹን፡ ከመለከት፡ ድምፅ፡ ጋር፡ በታላቅ፡ ክብር፡ ይልካቸዋል። የተመረጡ ትንም፡ከዳር፡እስከ፡ዳር፡ከአራቱ፡ማዕዘን፡ ይሰበስባቸዋል።
፴፪፥ ምሳሌውንም፡ ከበለስ፡ እወቁ፤ ጫፉ፡ የለመለመ፡ ቅጠሉ፡ ያቈጠቈጠ፡ እንደሆነ፡ መከር፡እንደ፡ደረሰ፡ታውቃላችሁ።

Scanned by CamScanner

## በ፱፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘሠሉስ።

፴፫፤ ከማሁኬ ፡ አንትሙኒ ፡ እምከመ ፡ ርኢክሙ ፡ ዘንተ፡ኵሎ፡አእምሩ፡ከመ፡ቀርበ፡ወበጽሐ፡ ኀበ፡ኆኅት።
፴፬፤ አማን ፡ እብለክሙ ፡ ከመ ፡ ኢተኃልፍ ፡ ዛቲ ፡ ትውልድ፡እስከ፡ዝ፡ኵሉ፡ይትገበር።
፴፭፤ ሰማይ ፡ ወምድር ፡ የኀልፍ ፡ ወቃልየሰ ፡ ኢየኀልፍ።

ድኅረ፡ወንጌል፡በተሰዓቱ፡ሰዓት፡እምዕለተ፡ ሠሉስ ፡ ወውእቱ ፡ ድልው ፡ በዐሠርቱ ፡ ወአሐዱ፡ካዕበ።

፩፤ ለከ ፡ ዘዚአከ ፡ ለባሕቲትከ ኦ ፡ እግዚ አብሔር ፡ አኃዜ ፡ ኵሉ ፡ አበስኩ ፡ ስረይ ፡ ሊተ።
፪፤ ኦ ፡ እግዚእየ ፡ ወአምላኪየ ፡ እስመ ፡ አነ ፡ እገብር፡በድፍረት፡እኩየ፡ወአንዛህልል፡እም ትእዛዛቲከ፡እግዚኦ።
፫፤ አመ፡ትመጽእ፡በስብሐቲከ፡ወመላእክቲከ፡ ዐውድከ ፡ ትነብር ፡ አንተ ፡ ኦ ፡ መኰንን ፡ ዘበአማን፡ዲበ፡መንበረ፡ስብሐቲከ፡ወታስተ ጋብእ፡ኀቤከ፡ኵሎ፡አሕዛበ፡እምአርባዕቱ፡ ነፋሳት፡እምአጽናፈ፡ምድር።
፬፤ ወይፈልጥዎሙ ፡ እምካልእሙ ፡ ካልአ ፡ በየማን፡ወበፀጋም፡በአሐቲ፡ቃል።
፭፤ አባግዕ ፡ ይቀውሙ ፡ በየማንከ ፡ ወአጣሊ ፡ በፀጋምከ ፡ ወይትፌሥሑ ፡ እለ ፡ በየማንከ ፡ ምስሌከ፡እለ፡ገብሩ፡ፈቃደከ፡እልክቱ፡እለ፡ ተአንዙ፡በሕገጋቲከ፡ወዐቀብዎን፡እልክቱ፡ እለ፡አብልዑከ፡ጊዜ፡ርኅብከ፡ወአስተዩከ፡ አመ፡ጽምእከ፡ወአመ፡ንግደትከ፡ተወከፋከ፡ ውስተ፡አብያቲሆሙ።
፮፤ ወአመ ፡ ዐረቀ ፡ አልበሱከ ፡ ወአመ ፡ ተሞቃሕከ፡ ሐወጹከ ፡ ወአመ ፡ ደወይከ ፡ ተልእኩከ።
፯፤ አሚሃ ፡ ይትፌሥሑ ፡ በምግባራቲሆሙ ፡ ሠናያት ፡ ወይነሥኡ ፡ ዐስቦሙ ፡ ፈድፋደ ፡ እምአጣሊ።

ጻድቃንሰ ፡ የሐውሩ ፡ ውስተ ፡ ሕይወት ፡ ዘለዓለም፡ወኃጥአን፡ውስተ፡ኵነኔ።

## ማክሰኞ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

፴፫፤ እንዲሁ ፡ እናንተ ፡ ደግሞ ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ ያያችሁ፡እንደሆነ፡መከር፡እንደ፡ደረሰ፡ወደ፡ ደጃፍም፡እንደቀረበ፡ዕወቁ።
፴፬፤ ይኸ ፡ ሁሉ ፡ እስኪደረግ ፡ ድረስ ፡ ይኸች ፡ ትውልድ፡እንዳታልፍ፡እውነት፡እላችኋለሁ።
፴፭፤ ሰማይና ፡ ምድር ፡ ያልፉል ፤ ቃሌ ፡ ግን ፡ አያልፍም።

ማክሰኞ ፡ ቀን ፡ በዘጠኝ ፡ ሰዓት ፡ ከወንጌል ፡ በኋላ ፡ የሚነበብ ፤ ይህም ፡ ደግሞ ፡ ለአሥራ ፡ አንድ፡ሰዓት፡የተዘጋጀ፡ነው።

፩፤ ሁሉን ፡ የያዝክ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሆይ ፡ ያንተ ፡ ፍጥረት ፡ የሆንኩ ፡ እኔ ፡ አንተን ፡ ብቻ ፡ በደልኩ፤ይቅር፡በለኝ።
፪፤ ጌታዬ፡ፈጣሪዬ፡ሆይ፡አለል፡ዘለል፡በማለት፡ ከትእዛዝህ ፡ ወጥቼ ፡ በድፍረት ፡ ክፉ ፡ ሥራ ፡ ሠርቻለሁና።
፫፤ አንተ ፡ እውነተኛ ፡ ፈራጅ ፡ ሆይ ፡ መላእክት ፡ በዙሪያህ ፡ አጅበውህ ፡ በጌትነትህ ፡ በምትመጣ፡ ጊዜ ፡ በጌትነትህ ፡ ዙፋን ፡ ላይ ፡ ትቀመጣለህ፤አሕዛብንም፡ሁሉ፡ከዳር፡እስከ፡ ዳር፡ካራቱ፡ማዕዘን፡ወዳንተ፡ትሰበስባለህ።
፬፤ ባልንጀሮችን ፡ ከባልንጀሮች ፡ ወደ ፡ ሁለት ፡ ለያይተው ፡ በአንዲት ፡ ቃል ፡ በቀኝና ፡ በግራ ፡ ያደርጓቸዋል።
፭፤ አባግዕ ፡ የተባሉ ፡ ጻድቃን ፡ በቀኝህ ፤ ፍየ ሎች ፡ የተባሉ ፡ ኃጥአን ፡ በግራህ ፡ ይቆማሉ ፤ ፈቃድህን ፡ የፈጸሙ ፡ በቀኝህ ፡ ያሉት ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ ደስ ፡ ብሏቸው ፡ ይኖራሉ ፤ እነርሱም ፡ በሕጎችህ ፡ ተይዘው ፡ ሕጎችህንም ፡ ጠብቀው ፡ የኖሩ ፡ ናቸው ፤ እነርሱ ፡ በተራብክ ፡ ጊዜ ፡ ያበ ሉህ፡በተጠማህ፡ጊዜ፡ያጠጡህ፡እንግዳ፡በሆንህ፡ ጊዜ፡ተቀብለው፡በቤቶቻቸው፡ያሳደሩህ፡ናቸው።
፮፤ በተራቈትህ ፡ ጊዜ ፡ አለበሱህ ፤ በታሰርህ ፡ ጊዜ ፡ ጐበኙህ ፤ በታመምህ ፡ ጊዜ ፡ አገለ ገሉህ።
፯፤ ያን ፡ ጊዜ ፡ በበጎ ፡ ሥራቸው ፡ ደስ ፡ ይላቸዋል ፤ ከኃጥአንም ፡ ተለይተው ፡ ፍጹም ፡ የሆነ ፡ ዋጋቸውን፡ይቀበላሉ።

ጻድቃንም፡ወደ፡ዘላለም፡ሕይወት፡ይሄዳሉ፤ ኃጥአን፡ግን፡ወደ፡ዘላለም፡ሥቃይ፡ይገባሉ።

Scanned by CamScanner

### በ፱፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሠሉስ።

፰፤ ስምዑ፡አ፡አብዳን፡ወአእምሩ፡እለ፡የአምሩ፡ በምሕረት ፡ ይትፌሥሑ ፡ ባቲ ፡ ወይት ሜከሑ፡አመ፡ፍትሕ።

፱፤ ግበሩ ፡ ምሕረተ ፡ እምቅድመ ፡ ይምጻእ ፡ ላእሌክሙ፡ዠነኔሁ፡ለመኰንን።

፲፤ ወሶበ ፡ ፈጸመ ፡ መድኃኒነ ፡ ዘይትናገር ፡ ይቤሎሙ ፡ ለአርዳኢሁ ፡ ገሀደ ፡ ከመ ፡ እምድኅረ፡ ክልኤቱ ፡ መዋዕል ፡ ይከውን ፡ ፋሲካ።

፲፩፤ ስምዑ ፡ አ ፡ አኃው ፡ ዘኀረይኩክሙ ፡ እስመ ፡ ለወልደ ፡ ዕጓለ ፡ እመሕያው ፡ ይትፌጸም ፡ ላዕሌሁ፡ዘጽሑፍ፡ውስተ፡መጽሐፈ፡ነቢያት።

፲፪፤ ወውእቱ ፡ ይከውን ፡ በግዐ ፡ ጥቡሐ ፡ ወፍሡሐ ፡ ወፍጹመ ፡ እስከ ፡ ተፍጻሜተ ፡ ዓለም።

ክርስቶስ፡መድኃኒነ፡መጽአ፡ወሐመ፡ወበሕ ማማቲሁ፡ቤዘወነ።

ጸልዩ፡በእንተ፡ጽንዐ፡ዛቲ፡በል።
ወኵሉ፡ሥርዓቱ፡ከመ፡ቀዳሚ።

## ምዕራፍ፡፳፬።

ምንባብ ፡ ዘዐሠርቱ ፡ ወአሐዱ ፡ ሰዓተ ፡ መዐልት፡ዘሠሉስ፤

### ክፍል፡፩።

ዘኢሳይያስ፡ነቢይ፡በረከቱ፡ትኩን፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

ምዕ፤፳፱፤፮–፳፫።

፮፤ እስመ ፡ ይዋዒ ፡ በፀዓዕ ፡ ወበድልቅልቅ ፡ ወበዐቢይ፡ቃል፡ወበዐውሎ፡ዘይመጽእ፡ወበ ነበልባለ፡እሳት፡በላዒ።

፯፤ ወይከውን ፡ ብዕሎሙ ፡ ለኵሎሙ ፡ አሕዛብ ፡ ከመ፡ዘየሐልም፡ሕልመ።

፰፤ ወኵሎሙ ፡ እለ ፡ ጸብእዎሙ ፡ ለእስራኤል ፡ ወኵሎሙ ፡ እለ ፡ ጸብእዋ ፡ ለኢየሩሳሌም ፡ ወኵሎሙ፡እለ፡ተጋብኡ፡ላዕሌሃ፡ወሮድዋ፡ ይከውኑ ፡ ከመ ፡ እለ ፡ ይበልዑ ፡ ወይሰትዩ ፡ በሕልሞሙ ፡ ወሶበ ፡ ይነቅሑ ፡ ይሔስዎሙ ፡ ሕልሞሙ።

### ማክሰኞ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

፰፤ ሰነፎች፡ሆይ፡ሰምታችሁ፡ዕወቁ፤ርኅራኄን፡ ያወቁና፡የመጸወቱ፡በእርሷ፡ደስ፡ይላቸዋል፡ በፍርድ፡ቀን፡ይመኩባታል።

፱፤ በላያችሁ ፡ የጌታ ፡ ፍርድ ፡ ሳይመጣባችሁ፡ ርኅራኄን፡ምጽዋትን፡አድርጉ።

፲፤ መድኃኒታችንም ፡ የሚነግራቸውን ፡ በጨረሰ፡ ጊዜ ፡ ለደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ በግልጽ፡ ከሁለት ፡ ቀኖች ፡ በኋላ ፡ ፋሲካ ፡ ይሆናል፡ አላቸው።

፲፩፤ የመረጥኋችሁ፡ወንድሞች፡ሆይ፡ስሙ፡ለሰ፡ ሰው ፡ ልጅ ፡ በነቢያት ፡ የተጻፈው ፡ በእርሱ፡ ላይ፡ይፈጸማልና።

፲፪፤ እርሱም፡ያማረ፡የሠመረ፡የተወደደ፡ፍጹም፡ የሆነ ፡ ተድላ ፡ ነፍስ ፡ ያለው ፡ እስከ ፡ ዓለም፡ ፍጻሜ፡የሚሠዋ፡መሥዋዕት፡ይሆናል።

መድኃኒታችን፡ክርስቶስ፡ሰው፡ሆኖ፡መከራ፡ ተቀበለ፤በመከራውም፡አዳነን።

ጸልዩ፡በእንተ፡ጽንዐ፡ዛቲ፡በል።
ሥርዓቱ፡ሁሉ፡እንደ፡ፊተኛው፡ነው።

## ምዕራፍ፡፳፬።

ማክሰኞ ፡ ከቀኑ ፡ አሥራ ፡ አንድ ፡ ሰዓት፡ የሚነበብ።

### ክፍል፡፩።

የነቢዩ ፤ የኢሳይያስ ፡ ትንቢት ። በረከቱ፡ ከእኛ፡ጋር፡ለዘላለሙ፡ትኑር፡አሜን።

ምዕ፤፳፱፤፮–፳፫።

፮፤ በብልጭልጭታ፡በመብረቅና፡በነጐድጓድ፡ በሚአቃጥል ፡ በእሳት ፡ ነበልባልና ፡ በሚመጣ፡በጥቅል፡ነፋስም፡ይጐበኛልና።

፯፤ የአሕዛብ፡ሁሉ፡ባለጸግነታቸው፡ሕልም፡እን ደሚያልም፡ይሆናል።

፰፤ እስራኤልን ፡ የወጓቸው ፡ ሁሉ ፡ ኢየሩ ሳሌምን ፡ የወጓት ፡ ሁሉ ፡ በሱዋም ፡ ተሰብ ስበው፡የከበቧት፡ሁሉ፡በሕልማቸው፡እንደ ሚበሉ ፡ እንደሚጠጡ ፡ በነቁም ፡ ጊዜ ፡ ሕልማቸው ፡ ሐሰት ፡ እንደሚሆንባቸው ፡ ሰዎች፡ይሆናሉ።

Scanned by CamScanner

### በ፲ወ፩፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘሠሉስ።

፱፤ ወበከመ፡ጽሙእ፡ዘየሐልም፡እንዘ፡ይሰቲ፡ማየ፡ወነቂሖ፡ዓዲሃ፡ጽምእት፡ነፍሱ፡ወከንቶ፡ተሰፈወ፡ከማሁ፡ውእቱ፡ብዕሎሙ፡ለኵሎሙ፡አሕዛብ፡እለ፡ጸብእዋ፡ለደብረ፡ጽዮን።

፲፤ ደከሙ፡ወደንገፁ፡ወሰክሩ፡አኮ፡በወይን፡ወአኮ፡በሜስ።

፲፩፤ እስመ፡አስተዮሙ፡እግዚአብሔር፡ጋኔነ፡ዘያደነግፆሙ፡ወከደኖሙ፡አዕይንቲሆሙ፡ለነቢያቲሆሙ፡ወለመላእክቲሆሙ፡እለ፡ይሬእዩ፡ዘኅቡእ።

፲፪፤ ወይከውኖሙ፡ዝንቱ፡ኵሉ፡ነገር፡ከመ፡ነገረ፡መጽሐፍ፡ኅቱም፡ዘይሁብዎ፡መጽሐፈ፡ለብእሲ፡ዘየአምር፡መጽሐፈ፡ወይብልዎ፡አንብብ፡ዘንተ፡ወይብል፡ኢይክል፡አንብቦቶ፡እስመ፡ኅቱም፡ውእቱ።

፲፫፤ ወካዕበ፡ይሁብዎ፡መጽሐፈ፡ለብእሲ፡ዘኢየአምር፡መጽሐፈ፡ወይቤልዎ፡አንብብ፡ዘንተ፡ወይብል፡ኢየአምር፡መጽሐፈ።

፲፬፤ ወይቤ፡እግዚአብሔር፡እሉ፡ሕዝብ፡ይቀርቡኒ፡በከናፍሪሆሙ፡ወበልቦሙሰ፡ነዋኀ፡ይርኅቁ፡እምኔየ፡ወከንቶ፡ያመልኩኒ፡ወይሜህሩ፡ትምህርተ፡ትእዛዛተ፡ሰብእ።

፲፭፤ በእንተ፡ዝንቱ፡ናሁ፡እደግም፡እፍልሶቶሙ፡ለእሉ፡ሕዝብ፡ወእፈልሶሙ፡ወእሀጕሎሙ፡ጥበቦሙ፡ለጠቢባን፡ወአረስዮሙ፡ምክሮሙ፡ለመካርያን።

፲፮፤ አሌ፡ሎሙ፡ለእለ፡ይመክሩ፡ምክረ፡እኩየ፡ወዕሙቀ፡ከመ፡ይኅብኡ፡እምእግዚአብሔር፡ወአኮ፡እንበይነ፡እግዚአብሔር።

፲፯፤ አሌ፡ሎሙ፡ለእለ፡ይከብቱ፡ምክረ፡ወይገብሩ፡በጽልመት፡ግብሮሙ፡ወይብሉ፡አልቦ፡ዘይሬእየነ፡ወአልቦ፡ዘየአምር፡ዘንገብር።

፲፰፤ አኮኑ፡ከመ፡ፅቡረ፡ለብሐዊ፡አንትሙ፡ይክልኑ፡ልሕኵት፡ለለሐኩሁ፡ብሂሎቶ፡ኢተግበረኒ፡ከመዝ፡ይብሎኑ፡ግብር፡ለገባሪሁ፡ኢያሠነይከ፡ገቢሮትየ፡ወአልቦ፡እንከ፡

### ማክሰኞ፡መዓልት፡በ፲፩፡ሰዓት።

፱፤ የተጠማም፡ሰው፡በሕልሙ፡ውኃ፡እንዲጠጣ፤ በነቃም፡ጊዜ፡ሰውነቱ፡ገና፡ተጠምታ፡እንዲያገኛት፤ ያንን፡በከንቱ፡ተስፋ፡እንዲአደርግ፤ ደብረ፡ጽዮንን፡የወጓት፡የአሕዛብ፡ሁሉ፡ባለጠግነታቸው፡እንደዚያ፡ይሆናል።

፲፤ ደከሙ፤ደነገጡ፤ሰከሩ፤ነገር፡ግን፡በወይንና፡በጠጅ፡አይደለም።

፲፩፤ እግዚአብሔር፡የሚአስደነግጣቸው፡ጋኔንን፡አጠጥቷቸዋልና፡(አሳድሮባቸዋልና)፡የተሠወረውን፡እናውቃለን፡የሚሉ፡የካህናቶቻቸውንና፡የነቢያቶቻቸውን፡ዓይነ፡ልቡናቸውን፡ጋርዶባቸዋልና።

፲፪፤ ይህም፡ሁሉ፡ነገር፡እንደ፡ታጠፈ፡መጽሐፍ፡ይሆንባቸዋል፡መጽሐፍን፡ለሚአውቅ፡ሰው፡የታጠፈ፡መጽሐፍን፡እንዲሰጡት፡ይህንን፡አንብብ፡እንዲሉት፡ታጥፏልና፡ማንበብ፡አልችልም፡እንዲል፡እንደዚያ፡ይሆንባቸዋል።

፲፫፤ ዳግመኛም፡መጽሐፍ፡ለማያውቅ፡መጽሐፍ፡ገልጠው፡ሰጥተው፡ይህን፡መጽሐፍ፡አንብብ፡እንዲሉት፡እኔስ፡መጽሐፍ፡አላውቅም፡እንዲል፡እንደዚያ፡ይሆንባቸዋል።

፲፬፤ እግዚአብሔርም፡እነዚህ፡ወገኖቼ፡በአፋቸው፡ይቀርቡኛል፤ በከንቱም፡ያመልኩኛል። የሰው፡ሰራሽ፡ትምህርትንም፡ያስተምራሉ፡አለ።

፲፭፤ ስለዚህ፡እነዚህን፡ወገኖች፡እነሆ፡ዳግመኛ፡አስማርካቸዋለሁ፤ የብልሆችንም፡ዕውቀታቸውን፡እነርሱንም፡አጠፋቸዋለሁ። የመካሮችንም፡ምክራቸውን፡አስረሳቸዋለሁ።

፲፮፤ ምክራቸውን፡ከእግዚአብሔር፡ይሠውሩ፡ዘንድ፡ክፉ፡ጥልቅ፡ምክርን፡ለሚመክሩ፡ሰዎች፡ወዮላቸው፤ ነገር፡ግን፡ስለ፡እግዚአብሔር፡አይደለም።

፲፯፤ ምክርን፡ለሚሠውሩ፡ሥራቸውንም፡በጨለማ፡ለሚሠሩ፡የሚያየንም፡የምንሠራውንም፡የሚያውቅ፡የለም፡ለሚሉ፡ሰዎች፡ወዮላቸው።

፲፰፤ እናንተ፡እንደ፡ሸክላ፡ሠሪ፡ጭቃ፡አይደላችሁምን? ሸክላ፡ሠሪውን፡እንዲህ፡አድርገህ፡አትሥራኝ፡ይለው፡ዘንድ፡ይችላልን? ሥራስ፡ሠሪውን፡አከናውነህ፡አልሠራኸኝም፡

Scanned by CamScanner

## በ፲ወ፩፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሠሉስ።

ኅዳጥ።

፲፱፡ ወእምዝ ፡ ይከውን ፡ ዖም ፡ ከመ ፡ ከርሜል ፡ ወከርሜል፡ይከውን፡ከመ፡ዖም።

፳፡ ወይእተ፡አሚረ፡ይሰምዑ፡ጽሙማን፡ነገረ፡ መጽሐፍ ፡ ወእለሂ ፡ ውስተ ፡ ጽልመት ፡ ወእለሂ ፡ ውስተ ፡ ጊሜ ፡ ውእተ ፡ አሚረ ፡ ይሬእያ፡አዕይንተ፡ዕውራን።

፳፩፡ ወይትፌሥሑ ፡ ነዳያን ፡ በእግዚአብሔር ፡ በኑኄት ፡ ወይጸግቡ ፡ ትፍሥሕተ፡ ሰብእ ፡ ቅቡፃን ፡ በቅዱስ ፡ እሥራኤል።

፳፪፡ እስመ ፡ ኀልቀ ፡ ኃጥእ ፡ ወጠፍኡ ፡ ዕቡይ ፡ ወተሠረዉ ፡ እለ ፡ ይዔምፁ ፡ በእከይ።

፳፫፡ ወእለ ፡ ያስሕቱ ፡ ሰብአ ፡ በነገር ፡ ወኵሎሙ ፡ እለ፡ይትዋቀሡ፡በኆበ፡አናቅጽ፡ወያመጽኡ ፡ ማዕቅፈ ፡ ወይጠውይዋ ፡ ለጽድቅ ፡ በዓመፃሆሙ።

ዘኢሳይያስ፡ነቢይ፡በረከቱ፡ትኩን፡ምስሌነ፡ ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

ምዕ፡፳፰፡፲፮–፳፮።

፲፮፡ ወበእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ከመዝ ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር፡እግዚእ፡ናሁ፡አነ፡እሠይም፡ውስተ፡ ጽዮን፡እብነ፡ማእዘንተ፡ውስተ፡መሠረታ፡ ኅሪተ ፡ ወክብርተ ፡ እንተ፡ ብዙኅ ፡ ሤጣ ፡ ወዘአምነ፡ባቲ፡ኢይትኃፈር።

፲፯፡ ወእሬሲ ፡ ተስፋ ፡ በጽድቅ ፡ ወሣህልየኒ ፡ በመዳልው ፡ ወእለሰ ፡ ይትዌከሉ ፡ በከንቱ ፡ ወበሐሰት ፡ ኢያመሥጡ፡ እምዓውሎ።

፲፰፡ ወየዓልወክሙ ፡ መሐላክሙ ፡ ዘምስለ ፡ ሞት ፡ ወኪዳንክሙ ፡ ዘምስለ ፡ ሲኦል ፡ ኢይቀውም ፡ ወእመኒ ፡ መጽአ ፡ ዐውሎ ፡ ኀላፊ ፡ ይከይደክሙ ፡ ወትደክሙ።

፲፱፡ ወእምከመ፡መጽአ፡የሐፍሰክሙ፡ለለጽባሑ፡ ወትቀርበክሙ ፡ ዕለትክሙ ፡ ወሌሊታኒ ፡ ትሕዝብት፡እኪት።

፳፡ ተመሀሩ፡ሰሚዐ፡ቃለ፡ምንዱባን፡ኢትክሉ፡

## ማክሰኞ፡መዓልት፡በ፲፩፡ሰዓት።

ይለዋልን?ጥቂትስ፡ስንኳ፡እንዲህ፡የሚል፡የለም፡

፲፱፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ዛፉ ፡ እንደ ፡ ችፍርግ ፡ ችፍርጉ፡ እንደ፡ዛፍ፡ይሆናል።

፳፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ደንቆሮዎች ፡ የመጽሐፍን ፡ ቃል፡ ይሰማሉ፤በጨለማም፡ያሉ፡በጽጋግም፡(በድንቁርና) ፡ ያሉ ፡ ብርሃንን ፡ ያያሉ ፤ (ዕውቀትን፡ ያገኛሉ)፡ያን፡ጊዜ፡የዕውሮች፡ዓይኖች፡ያያሉ።

፳፩፡ ድሆችም ፡ በእግዚአብሔር ፡ አምነው ፡ ፈጽሞ፡ ደስ ፡ ይላቸዋል ፤ ተስፋ ፡ የቆረጡ፡ ሰዎችም ፡ እስራኤልን ፡ በሚያጸና ፡ በእግዚአብሔር፡ዘንድ፡ተድላ፡ደስታን፡ይጠግባሉ።

፳፪፡ ኃጢአተኛ ፡ ሰው ፡ አልቋልና ፡ ትዕቢተኛም፡ ሰው ጠፍቷልና ፡ በተንኰል ፡ የሚበድሉ፡ ሰዎችም፡ተደምስሰዋልና።

፳፫፡ በነገር ፡ ሰውን ፡ የሚያስቱ ፡ በአደባባይም፡ የሚከራከሩ ፡ ሁሉ ፡ በሰውም ፡ መሰናክልን፡ የሚያመጡ ፡ እውነትን ፡ የሚያጣምሙ፡ ሰዎች፡በበደላቸው፡ጠፍተዋልና።

የነቢዩ፡የኢሳይያስ፡ትንቢት፡በረከቱ፡ከእኛ፡ ጋራ፡ለዘላለሙ፡ትኑር፡አሜን።

ምዕ፡፳፰፡፲፮–፳፮።

፲፮፡ ስለዚህም ፡ ገዥ ፡ የሚሆን ፡ እግዚአብሔር፡ እንዲህ ፡ አለ ፤ እነሆ ፡ እኔ ፡ በኢየሩሳሌም፡ የተ መረጠች ፡ የከበረች ፡ ዋጋዋ ፡ ብዙ ፡ የሆነ፡ ድንጋይን፡በአራቱ፡ማእዘን፡አኖራለሁ፤የመ ነባትም፡ሰው፡አያፍርም፡አለ።

፲፯፡ ተስፋን፡በእውነት፡አደርጋለሁ፤ይቅርታዬንም፡ መጥኜ፡አደርጋለሁ፤በሐሰትና፡በከንቱ፡ጣዖት፡ የሚአምኑ፡ሰዎች፡ግን፡ከጥልቅ፡ነፋስ፡(ከመቅ ሠፍት)፡አያመልጡም።

፲፰፡ ከሞት ፡ ጋራ ፡ የተማማላችሁት ፡ መሐላችሁ፡ ይፈርስባችኋል ። ከመቃብርም ፡ ጋራ ፡ የተነጋ ራችሁት ፡ ቃል ፡ (ቃል ፡ ኪዳን) ፡ አይጸናም፡ ድንገተኛ ፡ ጥቅል ፡ ነፋስም ፡ (መከራ) ፡ ቢመጣ፡ ይወስዳችኋል፤በመከራውም፡ትደክማላችሁ።

፲፱፡ በመጣም ፡ ጊዜ ፡ እየዕለቱ ፡ ያጠፋችኋል ። የም ትማረኩባትም ፡ ቀን ፡ ትቀርባችኋለች ፤ ሌሊቷም፡የምታጠራጥር፡ክፉ፡ናት።

፳፡ በመከራው ፡ የተጨነቃችሁ ፡ እናንተ ፡ የነቢ

ላዒ፡ወጋዕዘ፡ምስለ፡እግዚአብሔር፡ለሊነ፡ ሠራጎነ፡ከመ፡ናስተጋብእክሙ፡ወከመ፡ ሕንጸ፡ደቂቅ።

፳፩፤ በእንተ፡ዝንቱ፡ይትነሣእ፡ፀር፡ወይሂሉ፡ ውስተ፡ቈላተ፡ገባእን፡ወይገብር፡ግብሮ፡ በመዐት፡መሪር፡መዐቱኒ፡ዕፁብ፡ይገብር፡ ወኀምዘኒ፡ነኪር፡አንትሙኒ፡ኢትት ፈሥሑ።

፳፪፤ ወኢይጸንዕ፡ቍጽርክሙ፡እስመ፡ ኀሉቀ፡ወምቱረ፡ነገረ፡ሰማዕኩ፡እምኀበ፡ እግዚአብሔር፡ጸባኦት፡ዘይገብር፡በኵሉ፡ ምድር።

፳፫፤ ስምዑ፡ቃልየ፡ወአጽምዑኒ፡ወለብዉ፡ ወስምዑ፡ነገርየ።

፳፬፤ ቦኑ፡ኵሎ፡አሚረ፡የሐርስ፡ዘየሐርስ፡ ወይቀድምኑ፡ዘሪዐ፡ዘእንበለ፡ይሕርስ፡ ምድሮ።

፳፭፤ አኮኑ፡አቀምጢዖ፡ገራህቶ፡አሜሃ፡ይዘርዕ፡ ኅዳጠ፡መለንሰ፡ወከሙነ፡ወካዕበ፡ይዘርዕ፡ ሥርናየ፡ወሰገመ።

፳፮፤ ወትትሜሃር፡ምድር፡ኵነኔ፡እግዚአብሔር፡ ወትትፌሣሕ።

ምሳሌያተ፡ሰሎሞን

በረከተ፡እምላኩ፡ትኩን፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ ዓለም፡አሜን።

ምዕ፤፳፯፤፳፩–፴፯።

፳፩፤ ዕቀብ፡ወልድየ፡ሕገገ፡አቡከ፡ወኢትት ኀየይ፡ትእዛዘ፡እምከ።

፳፪፤ ደዮ፡ውስተ፡ልብከ፡በኵሉ፡ጊዜ፡ ወጠብልሎ፡ውስተ፡ክሣድከ።

፳፫፤ ወሶበኒ፡ተሐውር፡ንሥኦ፡ምስሌከ፡ወየሀሉ፡ ወሶበኒ፡ትነውም፡የዐቅበከ፡ወሶበኒ፡ ትትነሣእ፡ይትናገረከ።

፳፬፤ እስመ፡ማኅቶት፡ትእዛዝ፡ወሕግ፡ብር ሃን፡ወፍኖተ፡ሕይወት፡ተግሣጽ፡ወትም ህርት።

፳፭፤ ወልድየ፡ዕቀብ፡ትዕዛዝየ፤ከመ፡ትቀብከ፡ እምብእሲት፡ብእሲ፡ወእምውዴተ፡ልሳነ፡ እኩይ።



ያትን፡ቃል፡መስማትን፡ተማሩ፤ከእግዚአ ብሔር፡ጋራ፤ጠብ፡ክርክርን፡አትችሉም፤ ለትምህርት፡እንሰበስባችሁ፡ዘንድ፡እኛ፡ ደከምን፤እንደ፡ልጆች፡ሕንጻም፡ሆናችሁ።

፳፩፤ ስለዚህ፡ጠላት፡ይነሣባችኋል፤በገባኦንም፡ አውራጃ፡ይሰፍራል፤ሥራውንም፡በጽኑ፡ ቁጣ፡ይሠራል፤ቁጣውም፡ጭንቅ፡ነገርን፡ ያደርጋል፤ጠሩም፡ልዩ፡ነው።እናንተም፡ ደስ፡አይበላችሁ።

፳፪፤ በአገሩ፡ሁሉ፡የሚአደርገውን፡ያለቀ፡ የተቈረጠ፡ነገርን፡አሸናፊ፡ከሚሆን፡ከእግዚ አብሔር፡ሰምቻለሁና፡ምክራችሁ፡ አይጸናም።

፳፫፤ ቃሌን፡ስሙኝ፡ልብ፡አድርጋችሁ፡ አድምጡኝ፤ነገሬንም፡ስሙ።

፳፬፤ በውኑ፡የሚአርስ፡ሰው፡ሁል፡ጊዜ፡ ያርሳልን? ምድሩንስ፡ሳያርስ፡አስቀድሞ፡ ዘርን፡ይዘራልን።

፳፭፤ እርሻውን፡(ትልሙን)፡ተልሞ፡የዚያን፡ ጊዜ፡ጥቂት፡ኑግ፡ጥቂት፡ተልባ፡የሚዘራ፡ አይደለምን ? ዳግመኛስ፡ሥንዴ፡ገብስ፡ የሚዘራ፡አይደለምን።

፳፮፤ ምድርም፡የእግዚአብሔርን፡ፍርድ፡ተምራ፡ ደስ፡ይላታል።

የሰሎሞን፡ምሳሌዎች።

የፈጣሪው፡በረከት፡ከሁላችን፡ጋራ፡ ለዘላለሙ፡ትሁን፡አሜን።

ምዕ፤፳፯፤፳፩–፴፯።

፳፩፤ ልጄ፡የአባትህን፡ሥርዓት፡ጠብቅ፤የእናት ህንም፡ትእዛዝ፡ቸል፡አትበል።

፳፪፤ በየጊዜው፡በልቡናህ፡አኑረው፤በአንገ ትህም፡ጠምጥመህ፡ያዘው።

፳፫፤ በሄድህም፡ጊዜ፡ይዘኸው፡ሂድ፤ከአንተ፡ ጋራ፡ይኑር፤በተኛህም፡ጊዜ፡ይጠብቅሃል፤ በተነሣህም፡ጊዜ፡ያነጋግርኻል።

፳፬፤ ትዕዛዝ፡መብራት፡ሕግም፡ብርሃን፡ነውና፡ ተግሣጽና፡ትምህርትም፡የሕይወት፡ጐዳና፡ ነውና።

፳፭፤ ልጄ፡ከጐልማሳ፡ሚስት፡ትጠበቅህ፡ዘንድ፡ከፉ፡ የሆነ፡የነገረ፡ሠሪ፡አንደበት፡ከሚያመጣው፡ ጡበም፡ትጠበቅህ፡ዘንድ፡ትእዛዜን፡ጠበቅ።

Scanned by CamScanner

፳፭፤ ኢይማዕከ ፡ ሥነ ፡ ፍትወታ ፡ ወኢትሠገር ፡ በአዕይንቲሃ ፡ ወኢትትመሠጥ ፡ በቀራንብቲሃ።

፳፮፤ ፍቅራ፡ለዘማ፡እስከ፡አሐቲ፡ኅብስት፡ወብእሲትስ ፡ ለእደው ፡ ክቡራን ፡ ታሀጕል ፡ ነፍሶሙ፡ወታሜግር።

፳፯፤ መኑ፡ዘየዐቍር፡እሳተ፡ውስተ፡ኅፅኑ፡ወአልባሲሁ፡ኢይውዕያ።

፳፰፤ ወመኑ ፡ ዘየሐውር ፡ ዲበ ፡ አፍሐመ ፡ እሳት ፡ ወእገሪሁ፡ኢይውዕያ።

፳፱፤ ከማሁ ፡ ዘይበውእ ፡ ቤተ ፡ ብእሲተ ፡ ብእሲ ፡ ኢይነጽሕ ፡ ወኵሉ ፡ ዘይለክፋ።

፴፤ አኮ ፡ መንክር ፡ እመ ፡ ተእኅዘ ፡ ሰራቂ ፡ ዘይሰርቅ፡ እስመ ፡ ይሰርቅ ፡ ከመ ፡ ያጽግብ ፡ ነፍሶ፡ርኅብተ።

፴፩፤ ወለእመ ፡ ተእኅዘ ፡ ይፈዲ ፡ ምስብዒተ ፡ ወኵሎ፡ ጥሪቶ ፡ ይሁብ ፡ ከመ ፡ ያድኅን፡ነፍሶ።

፴፪፤ ወመሐዝስ፡በንዴተ፡አእምሮ፡ኀጕለ፡ነፍሱ፡ይትጌበር።

፴፫፤ ሕማመ፡ወኅሣረ፡ይጼውዕ፡ወጽእለቱ፡ኢይደመሰስ፡ለዓለመ፡ዓለም።

፴፬፤ እስመ ፡ ምሉእ ፡ ምቃ ፡ ቅንዓተ ፡ ወመዐተ ፡ ወኢይምሕሮ፡በዕለተ፡ኵነኔ።

፴፭፤ ወኢይትዌለጥ፡በምንትኒ፡ቤዛ፡ጽልእ፡ወኢይትዓረቅ፡በብዙኅ፡ሀብት።

ምዕ፡፯፡፩-፭።

፩፤ ወልድየ ፡ ዕቀብ ፡ ነገረ ፡ ዚአየ ፡ ወትእዛዘ ፡ ዚአየ፡ይባእ፡ኅቤከ።

፪፤ ወልድየ ፡ አክብሮ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ወትጸንዕ፡ እምኵሉ ፡ ወዘእንበሌሁሰ ፡ ኢትፍራህ፡ባዕደ፡እስመ፡አልቦ፡ዘይቀትለከ፡ወአልቦ፡ዘያሐይወከ።

፫፤ ወልድየ ፡ ትእዛዘ ፡ ዚአየ ፡ ዕቀብ ፡ ወተሐዩ፡ወንባበ፡ዚአየ፡ዕቀብ፡ከመ፡ብንተ፡ዓይንከ።

፬፤ ደዮ ፡ ውስተ ፡ አፃብዒከ ፡ ወጸሐፎ ፡ ውስተ ፡ ራኅበ፡ልብከ።



፳፭፤ መወደድ ፡ ያለው ፡ ደም ፡ ግባቷ ፡ ድል ፡ አይንሣህ ፤ በዓይኗ ፡ አትጠመድ ፤ በቅን ድቧም፡ብትጠቅስህ፡ወደ፡እርሷ፡አትሳብ።

፳፮፤ የዘማ ፡ ፍቅርዋ ፡ እስከ ፡ አንዲት ፡ እንጀራ ድረስ ፡ ነው ። እንዲህ ፡ ያለቺቱ ፡ ሴት ፡ የክቡ ሩትን፡ወንዶች፡ሰውነት፡ታጠምዳለች።

፳፯፤ በልብሱ፡እሳትን፡የሚቋጥር፡ልብሶቹ፡የማ ይቃጠሉበት፡ማነው?

፳፰፤ በእሳት፡ፍም፡ላይ፡የሚሄድ፡እገሮቹ፡የማይ ቃጠሉ፡ማን፡ነው?

፳፱፤ እንደዚሁ ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ ጐልማሳ ፡ ሚስት ቤት፡የሚገባ፡ሰው፡ከፍዳ፡አይነጻም፤የሚቀ ርባትም፡ከዝሙት፡አይነጻም።

፴፤ የሚሰርቅ ፡ ሌባ ፡ ቢያዝ ፡ ድንቅ ፡ አይደለም፡ የተራበች፡ሰውነቱን፡ያጠግብ፡ዘንድ፡ይሰር ቃልና።

፴፩፤ ቢያዝም ፡ ሰባት ፡ እጅ ፡ ይከፍላልና ፤ ቢያ በትም ፡ ሰውነቱን ፡ ከሞት ፡ ያድን ፡ ዘንድ፡ ገንዘቡን፡ሁሉ፡ይሰጣልና።

፴፪፤ አመንዝራ፡ሰው፡ግን፡ከዕውቀት፡በመጕድ ሰውነቱ፡የሚጠፋበትን፡ሥራ፡ይሠራል።

፴፫፤ መከራውን ፤ ተዋርደውን ፡ ይጠራል ፤ ስድቡም ፡ ለዘላለም ፡ አይጠፋም ። (አመ ዝራ፡ሲባል፡ይኖራል)።

፴፬፤ ባሏ፡ቅንዓትን፡ቁጣን፡ተመልቷልና፡ስለ በፈረደለት፡ቀን፡አይምረውም።

፴፭፤ የጠቡም ፡ ካሣ ፡ በምንም ፡ በምን ፡ አይለወ ለትም፤በብዙ፡ገንዘብም፡አይታረቀውም።

ምዕ፡፯፡፩-፭።

፩፤ ልጄ ፡ የእኔን ፡ ነገር ፡ ጠብቅ ፤ የእኔንም፡ ትእዛዝ፡በልቡናህ፡ሸሽግ።

፪፤ ልጄ ፡ እግዚአብሔርን ፡ አክብረው ፡ ከሁሉ፡ይልቅ፡ትጸናለህ፤የሚአድንህና፡የሚ ገድልህ ፡ የለምና ፤ ያለሱ ፡ ሌላውን ፡ ሰው፡ አትፍራ።

፫፤ ልጄ ፡ ትእዛዜን ፡ ጠብቅ ፤ በሕይወት ፡ ትኖራለህ ፤ የኔንም ፡ ነገር ፡ እንደ ፡ ዓይንህ ብሌን፡አድርገህ፡ጠብቅ።

፬፤ በአፃብዐ፡ልቡናህ፡አኑረው፤በልቡናህ፡ሰሌ ነትም፡ጻፈው።

Scanned by CamScanner

## በ፲ወ፩፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሠሉስ።

፩፡ በላ ፡ ለጥበብ ፡ እኅተ ፡ ዚአየ ፡ አንቲ ፡ ወለአ
እምሮ፡ሀገሪተከ፡ረሲያ።

### ክፍል፡፪።
### ሃይማኖተ፡አበው።
ምዕ፡፺፩፡፲፪–፳፩።

ይቤ ፡ ቅዱስ ፡ ኪራኮስ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ዘአን ጾኪያ ፡ በጦማረ ፡ መልእክቱ ፡ ኀበ ፡ ንጹሕ ፡ አባ፡ ማርቆስ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ዘእለ ፡ እስክን ድርያ።

፲፪፡ ወኢንበል ፡ ከመ ፡ ሠለስቱ ፡ አካላት ፡ ተሠገዉ ፡ በሥጋ ፡ ወኢ/ሥላሲ ፡ በአሐዱ ፡ አካል ፡ ከመ ፡ ይሠገዉ ፡ አላ ፡ አሐዱ ፡ አካል ፡ እምሠለስቱ ፡ አካላት ፡ ዘውእቱ ፡ እግዚአ ብሔር ፡ ቃል ፡ ጥበቡ ፡ ለአብ ፡ ወኀይሉ ፡ ብርሃን ፡ ጽድቅ ፡ ዘያበርህ ፡ እምብርሃን ፡ አብ ፡ ብሩህ ፡ አምላክ ፡ ዘኢይትዌለጥ ፡ እም አምላክ ፡ ዘበአማን ፡ ዘተወልደ ፡ እመለኮተ ፡ አብ።

፲፫፡ ለሊሁ፡ተዋረደ፡በደኀሪ፡መዋዕል፡በእንተ፡ መድኃኒተ ፡ ዕጓለ ፡ እመሕያው ፡ ተሠገወ ፡ ወኮነ፡ሰብአ፡እምህላዌ፡ንጽሕት፡ድንግል፡ ማርያም ፡ እንተ ፡ ኢተአምር ፡ ብእሴ ፡ በሥምረተ ፡ አብ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ እለ ፡ ቦሙ ፡ ሥምረቱ ፡ ወኢያውረደ ፡ ሥጋ ፡ ምስሌሁ፡እምሰማይ፡በከመ፡ይቤሉ፡ሰብእ፡ በዐበዶሙ ፡ ወኢቦአ ፡ ውስተ ፡ ከርሠ ፡ ድንግል፡ ማርያም ፡ ከመ ፡ ማይ ፡ እምነ ፡ ውኂዝ፡ አላ ፡ ኮነ ፡ ሰብአ ፡ ዘበአማን ፡ ቃል ፡ ሕያው፡ለሊሁ፡ተሠገወ፡በከርሠ፡ድንግል፡ በሥጋ ፡ ዘቦቱ ፡ ነፍስ ፡ ነባቢት ፡ ወለባዊት ፡ በአሐዱ፡ህላዌ፡አካላዊ፡ዘኢይትነገር።

፲፬፡ ወእንዘ ፡ አሐዱ ፡ ውእቱ ፡ አካል ፡ ዘእግዚአ ብሔር ።ቃል ፡ ተሠገወ ፡ በሥጋ ፡ ፍጹም ፡ ወእንዘ፡ አሐዱ ፡ ግብር ፡ ወአሐዱ ፡ ሥምረት ፡ ዘእንበለ ፡ ትድምርት ፡ ወኢቱስሕት ፡ ወዘእ ንበለ፡ ፍልጠት ፡ ኀበ ፡ ክልኤቱ ፡ ሕላዌያት ፡ ወኢ፡ኀበ፡ክልኤቱ፡አካላት፡ከመዝ፡ተወልደ፡ እምኔሃ፡በመንክር፡ግብር፡ዘእንበለ፡ክልአት፡ ወበእንተ፡ዝንቱ፡ከሠተ፡ለነ፡ከመ፡ድንግል፡

## ማክሰኞ፡መዓልት፡በ፲፩፡ሰዓት።

፩፡ ጥበብን ፡ እኅቴ ፡ በላት ፤ ውደዳት ፤ እውቀ ትንም፡አገርህ፡አድርጋት።

### ክፍል፡፪።
### የአባቶች፡ሃይማኖት።
ምዕ፡፺፩፡፲፪–፳፩።

የአንጾኪያ፡ሊቀ፡ጳጳሳት፡ቅዱስ፡ኪራኮስ፡ ወደ ፡ እስክንድርያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ወደ ፡ ንጹሕ፡ አባ ፡ ማርቆስ ፡ በላከው ፡ መልእክቱ ፡ እንዲህ፡አለ።

፲፪፡ ሦስቱ ፡ አካላት ፡ ሥጋን ፡ እንደ ፡ ተዋሐዱ ፡ አንናገር፤ ወይም ፡ ሰው ፡ ይሆኑ ፡ ዘንድ ፡ ሥላሴ ፡ አንድ ፡ አካል ፡ ሆኑ ፡ አንበል ፤ ከሦስቱ ፡ አካላት፡ አንዱ፡አካል፡ሰው፡ሆነ፡እንበል፡እንጂ፡ይኸው፡ የአብ ፡ ጥበቡ ፡ ኃይሉ ፡ የሚሆን ፡ ከብሩህ ፡ አብ ፡ የተገኘ ፡ ብርሃን ፡ የሚአበራ፡ የእውነት ፡ ብርሃን ፡ ከባሕርይ ፡ አምላክ ፡ የተገኘ ፡ የማይለወጥ ፡ አምላክ፡ ከአብ ፡ አካል ፡ ዘእምአካል ፡ ባሕርይ ፡ ዘእ ምባሕርይ፡የተወለደ፡እግዚአብሔር፡ቃል፡ነው።

፲፫፡ እርሱ፡በኋላ፡ዘመን፡ሰውን፡ለማዳን፡ተዋርዶ፡ ወንድ ፡ ከማታውቅ ፡ ከቅድስት ፡ ድንግል ፡ ማርያም ፡ ባሕርይ ፡ ፈቃዱ ፡ ፈቃዳቸው ፡ በሚሆን፡ በአብ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ፈቃድ ፡ ነፍስን ፡ ሥጋን፡ ነሥቶ ፡ ሰው ፡ ሆነ ፤ ሰዎችም ፡ አእምሮ ፡ በማጣታቸው ፡ እንደሚናገሩት ፡ ከሰማይ፡ሥጋን፡ይዞ፡አልመጣም፡እንደመስኖ፡ ውኃም ፡ በድንግል ፡ ማኅፀን ፡ ገብቶ ፡ የወጣ ፡ አይደለም ፤ ነፍስን ፡ ሥጋን ፡ ነሥቶ ፡ በእውነት ፡ ሰው፡ሆነ፡እንጂ፡ሕያው፡ቃል፡እርሱ፡የማይመ ረመር፡አካል፡ያለው፡አንድ፡ባሕርይ፡በመሆን፡ የምትናገር፡የምታውቅ፡ነፍስ፡ያለችው፡ሥጋን፡ በድንግል፡ማሕፀን፤ነሥቶ፡ሰው፡ሆነ።

፲፬፡ የእግዚአብሔር፡ቃል፡አንድ፡ሲሆን፡ፍጹም፡ ሥጋን ፡ ተዋሐደ ፤ መቀላቀል ፡ መጠፋፋት ፡ ወደ ፡ ሁለት ፡ አካል ፡ ወደ ፡ ሁለት ፡ ባሕርይ ፡ መከፈል ፡ ሳይኖር ፡ አንድ ፡ ግብር ፡ አንድ ፡ ፈቃድ ፡ ሆኖ ፡ ድንግልና ፡ ልደትን ፡ ሳይከለ ክለው ፡ ልደት ፡ ድንግልናን ፡ ሳይለውጠው ፡ ድንቅ ፡ በሚያሰኝ ፡ ምሥጢር ፡ እንዲህ ፡ ከእርሷ ፡ ተወለደ ፤ ስለዚህም ፡ እግዚአብሔር፡

Scanned by CamScanner

## በ፲ወ፩፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘሠሉስ።

ማርያም፡ንጽሕት፡ወላዲተ፡አምላክ፡ይእቲ፡
እስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ተወልደ ፡
እምኔሃ፡ሥግወ፡ዘበአማን።
፳፡ ወኮነ ፡ ዝንቱ ፡ አሐዱ ፡ ብእሲ ፡ ፍጹመ ፡
ዘእንበለ ፡ ፍልጠት ፡ ወእኮ ፡ ለሊሁ ፡
ዘተፈጥረ፡ቅድመ፡ብእሲ፡ወእምዝ፡ኀደረ፡
ውስቴቱ፡አምላክ፡ዘከመ፡ኀለየ፡ተመክዐቢ፡
ክህደት፡ንስጥሮስ፡ወመምህራኒሁ፡ርኩሳን፡
ዘውእቶሙ ፡ ጳውሎስ፡ ሳምሳጢ ፡ ወድያ
ድርስ፡ ወትዮድርስ ፡ ዘፈጠሩ ፡ ነገረ ፡
በዕበዶሙ፡ወክህደቶሙ።
፳፩፡ ወይቤሉ፡ከመ፡ቃል፡ወልደ፡እግዚአብሔር፡
ቦአ፡ውስተ፡ድንግል፡ከመ፡ማይ፡ዘይውኅዝ፡
ወኢተሠገወ ፡ እሙነ ፡ እምሥጋሃ ፡ ወደማ ፡
ወዐፅማ፡አመ፡ኮነ፡ሰብአ፡በሥርዓት፡ወኢ፡
በግብረ፡ተፋልሶ፡ወባሕቱ፡ውእቱ፡እግዚአ
ብሔር ፡ ዘበአማን ፡ ወእሉሰ ፡ ይሬስይዎ ፡
ክልኤተ ፡ ሕላዌያተ ፡ ወክልኤተ ፡ አካላተ ፡
አምላክ ፡ በባሕቲቱ ፡ ወሰብአ ፡ በባሕቲቱ ፡
ወያበጽሑ ፡ ክልኤተ ፡ እግዚአ ፡ ወክልኤተ ፡
አካለ ፡ ወክልኤተ ፡ መሲሐ ፡ ወይሬስይዎ ፡
ለሥላሴ፡ርቡዐ፡ወይሰግዱ፡ለአሐዱ፡ፈጣሪ፡
ወለካልኡ፡ፍጡር።
፳፪፡ ንሕነሰ፡ናአትት፡ወናሴስል፡እምኔነ፡ዘንተ፡
ክህደተ ፡ ርኩሰ ፡ ዘውእቱ ፡ ከመዝ ፡ ወኢይደ
ልወነ፡ንበል፡ከመ፡ውእቱ፡ተፈጥረ፡ብእሲ፡
ወእምድኅረዝ ፡ ለብሰ ፡ እግዚአብሔርሃ ፡
ወኢኮነ፡ዝንቱ፡ልደት፡አላ፡ርሑቅ፡ውእቱ፡
እምልደት፡በከመ፡ይቤ፡ንጹሕ፡መምህር፡
ጎርጎርዮስ፡ኢጲስቆጶስ፡ዘእንዚናዙ።
፳፫፡ ወዳእሙ ፡ ንሕነ ፡ ንብል ፡ ምስለ ፡ ቢጸ
ሐዋርያት፡አትናቴዎስ፡ዘነበረ፡ዲበ፡መን
በረ ፡ ማርቆስ ፡ ወንጌላዊ ፡ ዘአብርሀ ፡
ኵሎ፡ሀገረ፡እንዘ፡ይብል፡ሥጋ፡እግዚአ
ብሔር፡ቃል፡ሥጋ፡ዘቦቱ፡ነፍስ፡ወዓዲ፡
ለሊሁ፡ሥጋ፡ነባቢ፡ሥጋ፡እግዚአብሔር፡
ቃል፡ዘቦቱ፡አካል፡ፍጹም፡ውእቱ፡በነፍሱ፡
ወበሥጋሁ።
፳፬፡ ወንሕነኒ፡ንነጽር፡ኀበ፡አሐዱ፡አካል፡ንቡር፡
ወአሐዱ፡ሕላዌ፡ሥግው፡መለኮት፡ወትሰ
ብእት፡ፍጹማን፡ዘዘዚአሆሙ፡ወንዕቀብ፡

## ማክሰኞ፡መዓልት፡በ፲፪፡ሰዓት።

ቃል፡በእውነት፡ሰው፡ሁኖ፡ከእርሷ፡ተወለ
ዶአልና ፡ ንጽሕት ፡ ድንግል ፡ ማርያም
አምላክን፡የወለደች፡እንደሆነች፡አስረዳን፡
፳፡ ይኸ፡አንዱ፡ያለ፡መከፈል፡ፍጹም፡ሰው፡ሆነ፡
እርሱ ፡ አስቀድሞ ፡ ዕሩቅ ፡ ብእሲ ፡ ሆኖ ፡
ተገኝቶ፡ኋላ፡አምላክ፡ያደረበት፡አይደለም፡
ክህደትን ፡ የሚያራባ ፡ ያ ፡ ንስጥሮስ፡እንደ፡
ተናገረ፡ርኩሳን፡መምህሮቹም፡እንደተናገሩ
እነዚህም ፡ በድንቁርናቸው ፡ በክህደታቸው፡
ልብ ፡ ወለድ ፡ ነገር ፡ የተናገሩ ፡ ጳውሎስ፡
ሳምሳጢ፡ድያድርስና፡ትዮድርስ፡ናቸው።
፳፩፡ የእግዚአብሔር፡ልጅ፡አካላዊ፡ቃል፡እንደ፡
መስኖ፡ውኃ፡ገብቶ፡ወጣ፡እንጂ፡በተዋሕዶ፡
ባለመለወጥ፡ሰው፡በሆነ፡ጊዜ፡በማሕፀኗ፡
ነፍስን፤ሥጋን፤ዐፅምን፡ነሥቶ፡በእውነት፡
ሰው ፡ አልሆነም ። ግን ፡ የባሕርይ፡አምላክ
ነው ፡ አሉ ። እነዚህ ፡ ግን ፡ አምላክን
ለብቻው፡ ሥጋን ፡ ለብቻው ፡ አድርገው፡
ሁለት፡አካል፡ሁለት፡ባሕርይ፡ያደርጉታል፡
ሁለት፡ጌታ፡ሁለት፡አካል፡ሁለት፡ክርስቶስ
እንደሆነ፡ይናገራሉ፤ሥላሴን፡አራት፡ያደር
ጉታል፤ አንዱን ፡ ፈጣሪ ፡ አንዱን ፡ ፍጡር፡
ብለው፡ይሰግዳሉ።
፳፪፡ እኛ፡ግን፡ይሕን፡የረከሰ፡ክህደት፡ከእኛ፡እና
ርቃለን፤ የኸውም ፡ እንዲህ ፡ ያለው ፡ ነው፡
ዕሩቅ፡ብእሲ፡ሆኖ፡ተፈጥሮ፡በኋላ፡እግዚአ
ብሔር፡ያደረበት፡ነው፡ልንል፡አይገባንም፡
ይህ፡ተወለደ፤አያሰኝም፤ተወለደ፡ከማለት፡
የራቀ፡ነው፡እንጂ፡የእንዚናዙ፡ኤጲስቆጶስ፡
ንጹሕ፡መምህር፡ጎርጎርዮስ፡እንደተናገረ፡
፳፫፡ ወንጌልን፡በጻፈ፡በማርቆስ፡ወንበር፡ከተሾመ፡
ሐዋርያትን፡ከመሰለ፡እግዚአብሔር፡ቃል፡የተ
ወሐደው፡ሥጋ፡ነፍስ፡ያለችው፡ሥጋ፡ነው፡
እንዲሁም፡እግዚአብሔር፡ቃል፡የተዋሐደው፡
የሚናገር ፡ ሥጋ ፡ በነፍሱ ፡ በሥጋ ፡ ፍጹም፡
አካል፡ያለው፡ነው፡ብሎ፡በማስተማር፡ሰውን፡
ሁሉ፡ዐዋቂ፡ካደረገ፡ከአትናቴዎስ፡ጋራ፡እኛ፡
እንናገራለን።
፳፬፡ እኛም ፡ በተዋሕዶ ፡ ጸንቶ ፡ ወደ ፡ አለ ፡ ወደ፡
አንድ፡አካል፡ሰው፡ወደ፡ሆነው፡ወደ፡አንድ፡
ባሕርይ፡እንደ፤መለኮትና፡ትስብእት፡በየገዛ

Scanned by CamScanner

### በ፲ወ፩፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘሠሉስ።

ተዋሕዶተ ፡ ህላዌ ፡ እንተ ፡ ትሜህረነ ፡
ኢ ፡ ኅብረተ ፡ ህላዌያት ፡ በአርአያ ፡ መለ
ኮት ፡ ዘእንበለ ፡ ዓቅም ፡ ወኢትልቍ ፡ እስመ
ኅበ ፡ ሀለዉ ፡ ክልኤቱ ፡ ህላዌያት ፡
ሀየ ፡ ይሄልዉ ፡ ክልኤቱ ፡ አካላት ፡ ወኢለ
በዉ ፡ ከመ ፡ ዝንቱ ፡ ይከውን ፡ ክፍላተ ፡
ለዘኢይቶሳሕ ፡ ወበእንተ ፡ ተራኅቆተ ፡
አካላትሰ ፡ ወህላዌያት ፡ ይከውን ፡ ፍል
ጠተ ፡ አሐዱ ፡ እምካልኡ ፡ ወናሁ ፡ ይከ
ውን፡በሀየ፡ኊልቍ።

፳፫፤ ንሕነሰ ፡ ንትአመን ፡ ከመ ፡ ዝንቱ ፡ ውእቱ ፡
አሐዱ ፡ ዋሕድ ፡ ዘነአምሮ ፡ ውእቱ ፡ ዘኢያስ
ተርኢ ፡ ወውእቱ ፡ ዘያስተርኢ ፡ ውእቱ ፡ ዘኢየ
ሐምም ፡ ወውእቱ ፡ ዘተወክፈ ፡ ሕማመ ፡
ውእቱ ፡ ዘሞተ ፡ በእንቲአነ ፡ ወውእቱ ፡ ዘኢይ
መውት፡እስመ፡ግዑዝ፡ውእቱ፡እምነ፡ሞት፡
ወሙስና ፡ ወዳእሙ ፡ ተወክፈ ፡ ሞተ ፡
በሥጋሁ፡ቢዛነ።

በረከቱ ፡ ለዝንቱ ፡ መምህር ፡ ተሃሉ ፡ ምስሌነ ፡
ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

#### ምንተኑ፡በል።

ተአምሪሃ ፡ ለእግዝእትነ ፡ ቅድስት ፡ ድንግል ፡
በክልኤ፡ማርያም፡ወላዲተ፡አምላክ፡ጸሎታ፡
ወበረከታ ፡ የሀሉ ፡ ምስሌነ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡
አሜን።

፩፤ ስምዑኬ ፡ አ ፡ አኃውየ ፡ ዘንተ ፡ ምሥጢረ ፡
መንክረ ፡ ወመድምመ ፡ ዘነገሩነ ፡ አበዊነ ፡
ቅዱሳን ፡ ዘረከብዎ ፡ ውስተ ፡ መጻሕፍት ፡
ቅዱሳት።

፪፤ ወይቤሉ ፡ አመ ፡ ይመጽእ ፡ እግዚእነ ፡ በዳግም ፡
ምጽአቱ ፡ በስብሐት ፡ ምስለ ፡ መላእክት ፡
ወኀይላት ፡ በንፍኅተ ፡ ቀርን ፡ አሜሃ ፡
ይትነሥኡ ፡ ምውታን ፡ ወይነብር ፡ እግዚእነ ፡
በመንበረ፡ስብሐቲሁ፡ውስተ፡ደብረ፡ጽዮን፡
ለኰንኖ፡ዓለም።

፫፤ ወትወርድ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ሰማያዊት ፡ ምስለ፡
ኵሎሙ፡ጻድቃን፡እለ፡ውስቴታ፡ወትተከል፡
ላዕለ ፡ ደብረ ፡ ጽዮን ፡ ወላዕለ ፡ ኢየሩሳሌም ፡
በአንጻረ፡ደብረ፡ዘይት።

፬፤ ወማእከሎሙ ፡ ዐቢይ ፡ ወግር ፡ ዕሙቅ ፡

### ማክሰኞ፡መዓልት፡በ፲፩፡ሰዓት።

ባቸው ፡ ፍፁማን ፡ ናቸው ። ሁለት ፡ ባሕርያት ፡
ካሉ ፡ ዘንድ ፡ ሁለት ፡ አካላት ፡ ይኖራሉና ፡
መወሰን ፡ መከፈል ፡ በሌለበት ፡ በመለኮት ፡
ግብር ፡ የባሕርያትን ፡ አለመቀላቀልን ፡ የምታስ
ተምረንን ፡ የባሕርይን ፡ ተዋሕዶ ፡ እንጠብቅ፤
ይህ ፡ ሁለት ፡ ማለት ፡ መቀላቀል ፡ በሌለበት ፡
በእርሱ ፡ መከፈልን ፡ እንደኢመጣ ፡ አላወቁም፤
በአካላትና ፡ በባሕርያት ፡ አለመዋሐድስ ፡
የአንዱ ፡ ከአንዱ ፡ መለየት ፡ ይሆናል ፤ እነሆ ፡
በዚህ፡ቍጥር፡(ሁለት፡ማለት)፡ይመጣል።

፳፫፤ እኛስ ፡ የምናውቀው ፡ ይህ ፡ አንዱ ፡ አንድ ፡
እንደሆነ ፡ እናምናለን ፤ የማይታየው ፡ እሱ ፡
ነው ። የሚታየውም ፡ እሱ ፡ ነው ። የማይታ
መመው ፡ እሱ ፡ ነው ። ሕማምን ፡ መከራን ፡
የተቀበለ ፡ እሱ ፡ ነው ፤ ስለእኛ ፡ የሞተ ፡ እሱ ፡
ነው ። ሞት ፡ የሌለበትም ፡ እሱ ፡ ነው ። ከሞት ፡
ከመለወጥ ፡ የራቀ ፡ ነውና ፡ ቢዛችን ፡ እርሱ ፡
በሥጋ፡ሞትን፡ተቀበለ፡እንጂ።

የዚህ ፡ መምህር ፡ በረከቱ ፡ ከእኛ ፡ ጋራ ፡
ለዘላለሙ፡ትኑር፡አሜን።

#### ምንተኑ፡በል።

ልመናዋ፡ክብርዋ፡በእኛ፡ለዘላለሙ፡ይደርብንና፡
አምላክን ፡ የወለደች ፡ በድንጋሌ ፡ ሥና ፡
በድንጋሌ፡ነፍስ፡የጸናች፡ክብርት፡እመቤታችን፡
ማርያም፡ያደረገችው፡ተአምር፡ይህ፡ነው።

፩፤ ወንድሞቼ ፡ ሆይ ፡ የከበሩ ፡ አባቶ
ቻችን ፡ ከቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ አግኝተው ፡
የነገሩንን ፡ ይህን ፡ ዕፁብ ፡ ድንቅ ፡ ምሥጢር ፡
ስሙ።

፪፤ እንዲህም ፡ አሉ ፤ ጌታችን ፡ ከኃይላት ፡
መላእክት ፡ ጋራ ፡ በመለከት ፡ ድምጽ ፡
ሁለተኛ፡ በጌትነት ፡ በሚመጣ ፡ ጊዜ ፡ ያን ፡
ጊዜ፡ ሙታን ፡ ይነሣሉ ፤ ጌታም ፡ ፍርድ ፡
ለመስጠት ፡ በደብረ ፡ ጽዮን ፡ በጌትነቱ ፡
ዙፋን፡ላይ፡ይቀመጣል፤(ይገለጣል)።

፫፤ ኢየሩሳሌም ፡ ሰማያዊት ፡ በውስጥዋ ፡ ካሉት ፡
ሁሉ ፡ ጻድቃን ፡ ጋራ ፡ ወርዳ ፡ በደብረ ፡ ዘይት ፡
አንጻር ፡ በኢየሩሳሌምና ፡ በደብረ ፡ ጽዮን ፡ ላይ ፡
ትተከላለች።

፬፤ በመካከላቸውም ፡ እጅግ ፡ ጥልቅ ፡ የሆነ ፡

Scanned by CamScanner

## በ፲ወ፩፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘሠሉስ።

ፈድፋደ፡ወይሰመይ፡ሐቅለ፡ዮሳፍጥ።

፰፡ ወሀለወት፡ህየ፡ቤተ፡ክርስቲያን፡ዘሕንጽት፡ መልዕልተ ፡ መቃብሪሃ ፡ ለእግዝእትነ ፡ ቅድስት ፡ ድንግል ፡ በክልኤ ፡ ማርያም ፡ ወላዲተ፡አምላክ።

፱፡ ወይቤሉ፡በደኅሪት፡ዕለት፡ትከውን፡ከመ፡ ሐመር፡ወታዐድዎሙ፡ለኵሎሙ፡ሕዝበ፡ ክርስቲያን፡እለ፡ይገብሩ፡ተዝካረ፡በዓላ፡ለእ ግዝእትነ ፡ ቅድስት ፡ ድንግል ፡ በክልኤ ፡ ማርያም፡ወላዲተ፡አምላክ።

፲፡ ወእለ፡መሐሩ፡ነዳያነ፡ወምስኪናነ፡በስማ፡ ታስተፌሥሐሙ ፡ ምስሌሃ ፡ በመንግሥተ ፡ ሰማያት፡ወታወርሶሙ፡ሕይወተ፡ዘለዓለም።

ጸሎታ፡ወበረከታ፡የሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ ዓለም፡አሜን።

ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ጥዑመ፡ስም፡በል።

ተአምር፡ወመንክር፡ዘገብረ፡እግዚእነ፡ወአ ምላክነ ፡ ወመድኀኒነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ዘከመ፡አስፈዎሙ፡ብፅዓነ፡ለአርዳኢሁ፡እለ፡ ሖሩ፡በፍናዊሁ። ሣህሉ፡ወምሕረቱ፡የሀሉ፡ ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

፩፡ ብፁዓን፡እሙንቱ፡እለ፡የአምኑ፡ብየ፡እስመ፡ ይከውን፡ርስቶሙ፡ምስሌክሙ፡አ፡አርዳእየ።

፪፡ ብፁዓን፡እሙንቱ፡እለ፡የአምኑ፡ብየ፡እስመ፡ ይነብሩ ፡ ውስተ ፡ ገነተ ፡ ተድላ ፡ ምስለ ፡ አብርሃም፡ይሥሐቅ፡ወያዕቆብ።

፫፡ ብፁዓን፡እሙንቱ፡እለ፡የአምኑ፡ብየ፡እስመ፡ ገጾሙ፡ይበርህ፡ከመ፡ብርሃነ፡ፀሐይ፡አመ፡ ዕለተ፡ፍዳ።

፬፡ ብፁዓን ፡ እለ ፡ አዝለፉ ፡ ትዕግሥቶሙ ፡ በምንዳቤ፡በእንቲአየ።

፭፡ ብፁዓን ፡ እለ ፡ ይጼዕልዎሙ ፡ ወይጸርፉ ፡ ላዕሌሆሙ፡ወላዕለ፡አበዊሆሙ፡በእንተ፡ሃይ ማኖትየ።

፮፡ ብፁዓን ፡ እለ ፡ ተጸፍዑ ፡ ገጾሙ ፡ ወመላት ሒሆሙ፡በእንተ፡ስምየ።

፯፡ ብፁዓን ፡ እለ ፡ ቀሠፍዎሙ ፡ በእንተ ፡ ሃይማኖትየ ፡ ብፁዓን እለ ተቀትሉ በእንተ ስምየ።

## ማክሰኞ፡መዓልት፡በ፲፩፡ሰዓት።

ሐይቅ፡ያለው፡ታላቅ፡ኮረብታ፡አለ፤ስሙም፡ የዮሳፍጥ፡በረኻ፡ይባላል።

፰፤ በዚያም፡በሁለት፡ወገን፡ድንግል፡በሆነች፡ አምላክን ፡ በወለደች ፡ በክብርት ፡ እመቤ ታችን፡ማርያም፡መቃብር፡ላይ፡የተሠራች፡ ቤተ፡ክርስቲያን፡አለች።

፱፤ በኋለኛይቱ ፡ ዕለት ፡ እንደ ፡ መርከብ ፡ ሁና፡ በሁለት፡ወገን፡ድንግል፡የሆነች፡አምላክን፡ የወለደች፡የክብርት፡እመቤታችን፡ማርያም፡ የበዓልዋን፡መታሰቢያ፡የሚያደርጉ፡የክርስቲ ያንን፡ወገኖች፡ሁሉ፡ታሻግራቸዋለች፡ይላሉ።

፲፤ በስሟ ፡ ለጦም ፡ አዳሪዎችና ፡ ለድኆች ፡ ምጽዋት፡በመስጠት፡የሚራሩትንም፡ሁሉ፡ በመንግሥተ፡ሰማያት፡ከእርስዋ፡ጋር፡ደስ፡ ታሰኛቸዋለች፤የዘላለም፡ሕይወትንም፡ታወ ርሳቸዋለች።

ልመናዋ፡በረከቷ፡ከእኛ፡ጋራ፡ለዘላለሙ፡ ይኑር፡አሜን።

ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ጥዑመ፡ስም፡በል።

ይቅርታውና፡ቸርነቱ፡ከእኛ፡ጋራ፡ለዘላለሙ፡ ይኑርና፡ጌታችን፡ፈጣሪያችን፡መድኃኒታችን፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በሕጉ ፡ ለጸኑ ፡ ደቀ፡ መዛሙርቱ፡ብፅዕናውን፡ተስፋ፡በማስደረግ፡ ያደረገው፡ድንቅ፡ተአምር፡ይህ፡ነው።

፩፤ የሚአምኑብኝ ፡ ብፁዓን ፡ ናቸው ፤ ወዳጆቼ፡ ሆይ፡ርስታቸው፡ከእናንተ፡ጋራ፡ይሆናልና።

፪፤ የሚአምኑብኝ፡ብፁዓን፡ናቸው፤ከአብርሃም፡ ከይሥሐቅና፡ከያዕቆብ፡ጋራ፡ተድላ፡ነፍስ፡ በሚደረግባት፡በገነት፡ይኖራሉና።

፫፤ የሚአምኑብኝ ፡ ብፁዓን ፡ ናቸው ፤ በፍርድ፡ ቀን ፡ ፊታቸው ፡ እንደ ፡ ፀሐይ ፡ ብርሃን፡ ይበራልና።

፬፤ ስለእኔ ፡ መከራ ፡ በመቀበል ፡ ትዕግሥታ ቸውን፡ያዘወተሩ፡ብፁዓን፡ናቸው።

፭፤ በእኔ፡ስለ፡አመኑ፡በእነሱና፡በወላጆቻቸው፡ ላይ ፡ የስድብና ፡ የዘለፋ ፡ ቃል ፡ የሚናገሩ ባቸው፡ብፁዓን፡ናቸው።

፮፤ ስለ፡ስሜ፡(በስሜ)፡ስለ፡አመኑ፡ፊታቸውንና፡ ጉንጫቸውን፡የተጸፉ፡ብፁዓን፡ናቸው።

፯፤ በእኔ ፡ ስለማመናቸው ፡ የሚገረፉ ፡ ብፁዓን፡ ናቸው ። በስሜ ፡ ስለ ፡ አስተማሩ ፡ የተገደሉ፡ ብፁዓን፡ናቸው።

Scanned by CamScanner

## በ፲ወ፩፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘሠሉስ።

፰፡ ብፁዓን ፡ እለ ፡ ዐመፅዎሙ ፡ በእንተ ፡ ሃይማኖትየ፡ከመ፡እነ፡ዕሩይ፡ምስለ፡አቡየ፡በመለኮትየ።

ብፁዓን ፡ እለ ፡ ተጼወዉ ፡ በእንተ ፡ ርትዕት ፡ ሃይማኖት።

፱፡ ብፁዓን ፡እለ ፡ ይሔስዉ ፡ ላዕሌሆሙ ፡ በእንቲአየ።

፲፡ ብፁዓን፡እለ፡አንደዩ፡ርእሶሙ፡በእንተ፡አፍቅሮቶሙ፡ኪያየ።

፲፩፡ ብፁዓን፡እለ፡ይሠየጡ፡በወርቅ፡ወበብሩር፡ለኀበ፡ነገሥት፡ወመኳንንት፡ጸኒዖሙ፡በሃይማኖት፡ርትዕት።

፲፪፡ ብፁዓን ፡ እለ ፡ ይሴስዩ ፡ አኀዊሆሙ ፡ ነዳያነ፡እስመ፡እሙንቱ፡ይከውኑ፡ቅሩባነ፡በኀቤየ።

፲፫፡ ብፁዓን ፡ እለ ፡ ያኀድርዎሙ ፡ ለአናግድ ፡ ውስተ፡አብያቲሆሙ።

፲፬፡ ብፁዓን ፡ እለ ፡ ያለብስዎሙ ፡ ለዕሩቃን ፡ ወይገብሩ፡ሠናየ፡ለኵሉ፡ፍጥረት።

፲፭፡ ብፁዓን፡እለ፡ይጐይዩ፡እመካን፡ውስተ፡መካን፡በእንተ፡ስምየ።

፲፮፡ ብፁዓን ፡ እለ ፡ ይነብሩ ፡ ውስተ ፡ ገዳም ፡ ወበድው፡ከመ፡ይትቀነዩ፡ሊተ።

፲፯፡ ብፁዓን፡እለ፡የኀድሩ፡ውስተ፡አድባር፡ነዋኃን፡በእንተ፡ስምየ።

፲፰፡ ብፁዕ ፡ ውእቱ ፡ ዘይጸልዕ ፡ ዘንተ ፡ ዓለመ ፡ ኀላፌ፡በእንተ፡አፍቅሮቱ፡ኪያየ።

፲፱፡ ብፁዓን ፡ እለ ፡ ረከቡ ፡ ኀሳረ ፡ በእንቲአየ ፡ ወእለ፡ ያከብርዎሙ ፡ ለእለ ፡ የአምኑ ፡ በስምየ።

፳፡ ብፁዓን፡እለ፡ይሔውጽዎሙ፡ለካህናትየ፡ወይሁብዎሙ፡መፍቅዶሙ፡በእንተ፡አፍቅሮትየ፡ወአወርሶሙ፡ገነተ፡ተድላ፡ወመንግሥተ፡ዘኢየኀልፍ።

፳፩፡ ብፁዓን ፡ እለ ፡ ይትለአኩ ፡ በፍርሐት ፡ ወበረዓድ ፡ በንጽሕ ፡ ወበጽድቅ ፡ እንዘ ፡ ይሴፈዉ ፡ ዐስቦሙ ፡ ዘእኤስዮሙ ፡ እነ ፡ በተድላየ፡ዕሴተ፡ሠናየ።

፳፪፡ ብፁዓን፡እለ፡ያበርሁ፡ውስተ፡አብያትየ፡መኃትወ።

ብፁዓን፡እለ፡ይረድኡ፡አኀዊሆሙ፡እለ፡

## ማክሰኞ፡መዓልት፡በ፲፩፡ሰዓት።

፰፡ እኔ፡ከአባቴ፡ጋራ፡በባሕርዩ፡አንድ፡እንደ ሆንኩ ፡ በማስተማራቸው ፡ በደል ፡ የደረሰባቸው፡ብፁዓን፡ናቸው።

ስለ፡ቀናች፡ሃይማኖት፡የተማረኩ፡ብፁዓን፡ናቸው።

፱፡ ስለ፡እኔ፡በላያቸው፡ሐሰት፡የሚናገሩባቸው፡ብፁዓን፡ናቸው።

፲፡ እኔን፡ስለ፡መውደዳቸው፡ራሳቸውን፡ድኃ፡ያደረጉ፡ብፁዓን፡ናቸው።

፲፩፡ በቀናች፡ሃይማኖት፡ጸንተው፡ለነገሥታቱና፡ለመኳንንቱ ፡ በወርቅ ፡ በብር ፡ የሚሸጡ ፡ ንዑዳን፡ክቡራን፡ናቸው።

፲፪፡ ድኆች ፡ ወንድሞቻቸውን ፡ የሚመግቡ ፡ ብፁዓን ፡ ናቸው ። እነርሱ ፡ በእኔ ፡ ዘንድ ፡ የቀረቡ፡ይሆናሉና።

፲፫፡ እንግዶችን ፡ በቤቶቻቸው ፡ የሚአሳድሩአቸው፡ብፁዓን፡ናቸው።

፲፬፡ የተራቈቱትን፡የሚያለብሱአቸውና፡ለሁሉ፡በጎ፡ሥራ፡የሚሠሩ፡ብፁዓን፡ናቸው።

፲፭፡ ስለ ፡ ስሜ ፡ ከቦታ ፡ ወደ ፡ ቦታ ፡ የሚሰደዱ ፡ ብፁዓን፡ናቸው።

፲፮፡ ያገለግሉኝ፡ዘንድ፡በዱር፡በበረኻ፡የሚኖሩ፡ንዑዳን፡ክቡራን፡ናቸው።

፲፯፡ ስለ ፡ ስሜ ፡ በረጃጅም ፡ ተራራዎች ፡ ውስጥ ፡ የሚያድሩ፡ብፁዓን፡ናቸው።

፲፰፡ እኔን፡በመውደዱ፡ይህን፡ኃላፊውን፡ዓለም፡የጠላ፡ንዑድ፡ክቡር፡ነው።

፲፱፡ በእኔ ፡ ምክንያት ፡ መጐሳቈል ፡ ያገኛቸውና ፡ በስሜ፡የሚአምኑትንም፡የሚአከብሩአቸው፡ብፁዓን፡ናቸው።

፳፡ ስለ፡እኔ፡ፍቅር፡ካህናቶቼን፡የሚጎበኙና፡የሚሹትንም፡የሚሰጡአቸው፡ብፁዓን፡ናቸው ። ተድላ ፡ ነፍስ ፡ ያለባትን ፡ ገነትንና ፡ የማያልፈውን፡መንግሥት፡አወርሳቸዋለሁ።

፳፩፡ እኔ፡በልግሥና፡የምሰጣቸውን፡በጎ፡ስጦታ፡ተስፋ ፡ አድርገው ፡ በመፍራትና ፡ በመንቀጥቀጥ፡በእውነት፡በንጽሕና፡የሚአገለግሉ፡ብፁዓን፡ናቸው።

፳፪፡ በቤቶቼ ፡ ውስጥ ፡ መብራቶችን ፡ የሚያበሩ ፡ ብፁዓን ፡ ናቸው ። በችግር ፡ ውስጥ ፡ ያሉትን ፡ ወንድሞቻቸውን፡የሚረዱ፡ለተጨነቁትም፡

| በ፲ወ፩፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘሠሉስ። | ማክሰኞ፡መዓልት፡በ፲፩፡ሰዓት። |
|---|---|
| ሀለዉ ፡ ውስተ ፡ ምንዳቤ ፡ ወያርሕቡ ፡ ለእለ ፡ ተጽዕቁ። | የሚያስፋላቸው፡ብፁዓን፡ናቸው። |
| ፳፫፤ ብፁዓን ፡ እለ ፡ ይሔውጹ ፡ ፍቁራንየ ፡ እለ ፡ ይቀርቡ ፡ ኀቤየ ፡ እስመ ፡ እሙንቱ ፡ ይከውኑ ፡ ኅሩያንየ። | ፳፫፤ ወደ ፡ እኔ ፡ የሚቀርቡትን ፡ ወዳጆቼን ፡ የሚጎበኙ ፡ ብፁዓን ፡ ናቸው ። እነርሱ ፡ ምርጦቼ፡ይሆናሉና። |
| ፳፬፤ ብፁዓን ፡ እለ ፡ ይነጽሑ ፡ እምነ ፡ ርኵስ ፡ ወይኄንኑ፡ሥጋሆሙ፡ከመ፡ያሥምሩኒ። | ፳፬፤ ደስ ፡ ያሰኙኝ ፡ ዘንድ ፡ ከርኵሰት ፡ የሚነጹ ፡ ሥጋቸውን፡የሚገዙ፡ብፁዓን፡ናቸው። |
| ፳፭፤ ብፁዓን ፡ እለ ፡ ይትዔገሡ ፡ ንዴተ ፡ ወጻማ ፡ ወዕርቃነ፡በእንተ፡ስምየ። | ፳፭፤ ስለ ፡ ስሜ ፡ ችግርን ፡ ድካምን ፡ መራቆትን ፡ የሚታገሡ፡ብፁዓን፡ናቸው። |
| ፳፮፤ ብፁዓን ፡ እለ ፡ የኀድጉ ፡ አበዊሆሙ ፡ ወእሞሙ፡በእንተ፡ስምየ። | ፳፮፤ ስለ ፡ ስሜ ፡ አባቶቻቸውንና ፡ እናቶቻቸውን ፡ የሚተዉ፡ብፁዓን፡ናቸው። |
| ፳፯፤ ብፁዓን፡እለ፡ተሌለዩ፡እምአኀዊሆሙ፡ወእምውሉዶሙ ፡ ወአዝማዲሆሙ ፡ በእንተ ፡ ስምየ። | ፳፯፤ ስለ ፡ ስሜ ፡ ከወንድሞቻቸው ፡ ከልጆቻቸው ፡ ከዘመዶቻቸው ፡ የተለዩ ፡ ብፁዓን፡ናቸው። |
| ፳፰፤ ብፁዓን ፡ እለ ፡ ይሰብኩ ፡ በእንተ ፡ ስምየ ፡ እስከ፡አጽናፈ፡ምድር። | ፳፰፤ በእኔ ፡ ስም ፡ እስከ ፡ ምድር ፡ ዳር ፡ የሚያስተምሩ፡ብፁዓን፡ናቸው። |
| ፳፱፤ ብፁዓን ፡ እለ ፡ ይሜህሩ ፡ ወንጌልየ ፡ ለእለ ፡ ይትሜህሩ፡ወይከሥቱ፡ትምህርትየ። | ፳፱፤ ለሚማሩ ፡ ወንጌሌን ፡ የሚያስተምሩ ፡ ትምህርቴንም፡ገልጠው፡የሚያስረዱ፡ብፁዓን፡ናቸው። |
| ፴፤ ብፁዕ ፡ ዘጸሐፈ ፡ ወንጌልየ ፡ ወአምነ ፡ ቦቱ፡ ወየዐቅብ፡ቅዱሳነ፡ቃላቲሁ። | ፴፤ ወንጌሌን ፡ የጻፈ ፡ የሚያምንበትም ፡ የከበሩ፡ ቃሎቹንም፡የሚጠብቅ፡ብፁዕ፡ነው። |
| ፴፩፤ ብፁዓን ፡ እለ ፡ ይዘክሩ ፡ ስምየ ፡ ዘልፈ ፡ በሌሊት፡ ወበመዐልት ፡ እስመ ፡ እሄሉ ፡ ምስሌሆሙ፡ለዝሉፉ። | ፴፩፤ በመዓልትና ፡ በሌሊት ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ስሜን፡ በጸሎት ፡ በምስጋና ፡ የሚያስታውሱ ፡ ብፁዓን፡ ናቸው።ለዘላለሙ፡አድሬባቸው፡እኖራለሁና፡ |
| ፴፪፤ ብፁዓን ፡ እለ ፡ ይትማሐፀኑ ፡ በንጽሕት ፡ ወቅድስት ፡ ድንግል ፡ በክልኤ ፡ ማርያም ፡ ወላዲትየ፡በሥጋ። | ፴፪፤ በሁለት ፡ ወገን ፡ ድንግል ፡ በሆነች ፡ በነጻችና፡ በከበረች ፡ በሥጋ ፡ በወለደችኝ ፡ በእናቴ፡ በማርያም፡የሚማፀኑ፡ብፁዓን፡ናቸው። |
| ፴፫፤ ወተዘከረ ፡ ስማ ፡ ጊዜ ፡ ስእለቱ ፡ ወእስተብቍዖቱ ፡ እስመ ፡ ይከውን ፡ ማኅደሩ ፡ ውስተ ፡ መንግሥተ፡ሰማያት። | ፴፫፤ በልመናውና ፡ በምልጃው ፡ ጊዜ ፡ ስሟን፡የሚያስታውስም ፡ ማደሪያው ፡ በመንግሥተ፡ ሰማይ፡ይሆናልና፡ብፁዕ፡ነው። |
| ፴፬፤ ብፁዓን ፡ እለ ፡ ያርኅቡ ፡ ሥጋሆሙ ፡ ወያጸምእዎ ፡ እስመ ፡ ይቀርቡ ፡ ኀቤየ ፡ ወአነሂ ፡ አጸግቦሙ ፡ እምጸጋየ ፡ ወአረውዮሙ ፡ ፍሥሓ፡ዘለዓለም። | ፴፬፤ ሥጋቸውን፡(በጾም)፡የሚያስርቡ፡የሚያስጠሙትም፡ብፁዓን፡ናቸው።እነርሱ፡ወደ፡እኔ፡ ይቀርባሉና፤እኔም፡ጸጋዬን፡ከብሬን፡አጠግባቸዋለሁ፤ዘላለማዊ፡ተድላ፡ደስታን፡አረካቸዋለሁ። |
| ፴፭፤ ብፁዓን፡እለ፡ይመጽውቱ፡ለነዳያን፡ወይም ሕርዎሙ፡ለሕሙማን፡እስመ፡ሎሙኒ፡ይም ሕርዎሙ። | ፴፭፤ ለድኆች ፡ የሚመጸውቱ ፡ ለታመሙትም፡ የሚራሩ ፡ ብፁዓን ፡ ናቸው ። ለእነርሱም፡ (ሥላሴ)፡ይራሩላቸዋልና። |
| ፴፮፤ ብፁዓን ፡ እለ ፡ ይጸልኡ ፡ ተድላሃ ፡ ለዛቲ ፡ ዓለም፡ እስመ ፡ እሙንቱ ፡ ይወርሱ ፡ ሐዳሰ ፡ ምድረ። | ፴፮፤ የዚችን ፡ ዓለም ፡ ተድላ ፡ የሚጠሉ ፡ ብፁዓን፡ ናቸው ፤ እርሳቸው ፡ አዲስ ፡ ዓለም ፡ መንግሥተ፡ሰማያትን፡ይወርሳሉና። |
| ፴፯፤ ብፁዓን ፡ ንጹሓነ ፡ ልብ ፡ እስመ ፡ እሙንቱ ፡ | ፴፯፤ ልቡናቸው ፡ ንጹሕ ፡ የሆነላቸው ፡ ብፁዓን፡ |

Scanned by CamScanner

ይሬእዩ ፡ ገጽየ ፡ ወይወርስዋ ፡ ለመንግሥተ ፡ ሰማያት።
፴፰፤ ብፁዓን ፡ እለ ፡ ይትቃተልዎሙ ፡ አሕዛብ ፡ ከሐድያን፡እስመ፡እሙንቱ፡ይሬእዩ፡ገጽየ፡ ወይወርስዋ፡ለመንግሥተ፡ሰማያት።
፴፱፤ ብፁዓን ፡ እለ ፡ ይትቃተሉ ፡ በእንቲአየ ፡ እስመ፡ እሙንቱ ፡ ይከውኑ ፡ ቍርባነ ፡ ንጹሐ ፡ ወይከውኑኒ ፡ ካህናተ ፡ ወፍቁራነ ፡ ወመላእክተ ፡ ሥጋውያነ ፡ ወእትቄከፍ ፡ ስእለቶሙ ፡ ወእኔጽር ፡ ኀበ ፡ ዘተማሕፀነ፡በሙ።
ሣህሉ፡ወምሕረቱ፡የሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

## ክፍል፡፫።

## ይ፡ዲ፡ቅድመ፡ወንጌል።

መዝ፤፵፬፥፮–፯።፵፥፩።

በትረ፡ጽድቅ፡ወበትረ፡መንግሥትከ።
አፍቀርከ፡ጽድቀ፡ወዐመፃ፡ጸላዕከ።
ብፁዕ ፡ ዘይሌቡ ፡ ላዕለ ፡ ነዳይ ፡ ወምስኪን።

## ወንጌል፡ዘማቴዎስ።

ምዕ፤፳፭፥፲፬–፴።

፲፬፤ እስመ ፡ ከመ ፡ ብእሲ ፡ ዘይነግድ ፡ ወጸውዐ ፡ አግብርቲሁ ፡ ወወሀቦሙ ፡ ንዋዮ ፡ ይትገበሩ፡ቦቱ።
፲፭፤ ቦ ፡ ለዘወሀቦ ፡ ኀምስተ ፡ መክሊተ ፤ ወቦ ፡ ለዘወሀቦ፡ክልኤተ፡መክሊተ፤ወቦ፡ለዘወሀቦ፡አሐደ፡መክሊተ፤ወለለ፡አሐዱ፡እምኔሆሙ፡በአምጣነ ፡ ይክሉ ፡ ወሀቦሙ ፡ ወነገደ ፡ በጊዜሃ።
፲፮፤ ወሖረ ፡ ዝኩ ፡ ዘኀምሰ ፡ መካልየ ፡ ነሥአ ፡ ወተገበረ፡ቦቶን፡ወረብሐ፡ካልአተ፡ኀምስተ፡መካልየ።
፲፯፤ ወከማሁ ፡ ዘሂ ፡ ክልኤተ ፡ መካልየ ፡ ነሥአ ፡ ረብሐ ፡ ካልአተ ፡ ክልኤተ ፡ መካልየ።
፲፰፤ ወዘአሐተሰ፡መክሊተ፡ነሥአ፡ሖረ፡ወከረየ፡ምድረ፡ወኀብአ፡ወርቀ፡እግዚኡ።
፲፱፤ ወእምድኅረ ፡ ብዙኅ ፡ መዋዕል ፡ አተወ ፡ እግዚአሙ፡ለእሉ፡አግብርት፡ወአኀዘ፡ይትሐሰቦሙ።



ናቸው፡እነርሱ፡ፊቴን፡ያያሉና፡መንግሥተ፡ሰማያትንም፡ይወርሷታልና።
፴፰፤ ከሐዲያን ፡ አሕዘብ ፡ የሚዋጉአቸው ፡ ብፁዓን፡ ናቸው ። ፊቴን ፡ ያያሉና ፡ መንግሥተ፡ሰማያትንም፡ይወርሱአታልና።
፴፱፤ ስለ ፡ እኔ ፡ የሚጋደሉ ፡ ብፁዓን ፡ ናቸው ። እነርሱ ፡ ንጹሕ ፡ ቍርባን ፡ ይሆናሉና ፡ ለእኔም፡ የተወደዱ ፡ ካህናቶች ፡ ይሆኑኛል ፤ ምድራውያን ፡ መላእክቶቼም ፡ ይሆኑኛል ፤ ልመናቸውንም ፡ እቀበላለሁ ፤ የተማጸነባቸውንም፡በምሕረት፡እመለከታለሁ።
ይቅርታው፡ቸርነቱ፡ከእኛ፡ጋራ፡ለዘላለሙ፡ይኑር፡አሜን።

## ክፍል፡፫።

## ዲያቆኑ፡ከወንጌል፡በፊት።

መዝ፤፵፬፥፮–፯።፵፥፩።

የመንግሥትህ፡በትር፡የጽድቅ፡በትር፡ነው፤ ጽድቅን ፡ ወደድህ ፤ አመፅንም ፡ ጠላህ ፤ ለድኃና፡ለጦም፡አዳሪ፡የሚያስብ፡ንዑድ፡ክቡር፡ነው፡ይበል።

## የማቴዎስ፡ወንጌል።

ምዕ፤፳፭፥፲፬–፴።

፲፬፤ መንገድ ፡ እንደሚሄድ ፡ ሰው ፡ ነውና ፡ ብላቴኖቹን ፡ ጠርቶ ፡ ሊያተርፉበት ፡ ገንዘቡን ፡ ሰጣቸው።
፲፭፤ አምስት ፡ መክሊት ፡ የሰጠው ፡ ሰው ፡ አለ ፤ ሁለት ፡ መክሊትም ፡ የሰጠው ፡ ሰው ፡ አለ ፤ አንድ ፡ መክሊት ፡ የሰጠውም ፡ አለ ፤ ከእርሱ ፡ ለእያንዳንዱ፡በሚችሉት፡መጠን፡ሰጣቸውና ፡ወዲያውኑ፡ሄደ።
፲፮፤ ያ ፡ አምስት ፡ መክሊት ፡ የተቀበለውም ፡ ወጥቶ፡ ወርዶ ፡ ሌላ ፡ አምስት ፡ መክሊትን ፡ አተረፈ።
፲፯፤ እንዲሁም ፡ ሁለቱንም ፡ መክሊት ፡ የተቀበለው ፡ ወጥቶ ፡ ወርዶ ፡ ሌላ ፡ ሁለት ፡ መክሊትን፡አተረፈ።
፲፰፤ አንዲት ፡ መክሊት ፡ የወሰደው ፡ ግን ፡ ሄዶ ፡ ምድርን፡ቆፈረና፡የጌታውን፡ወርቅ፡ቀበረ።
፲፱፤ ከብዙ ፡ ቀንም ፡ በኋላ ፡ የእነዚያ ፡ ባሮች ፡ ጌታ ፡ ተመልሶ ፡ መጥቶ ፡ ይተሳሰባቸው ፡ ጀመር።

Scanned by CamScanner

በ፲ወ፩፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሠሉስ።

፳፡ ወቀርበ ፡ ዘኀምሰ ፡ መካልየ ፡ ነሢአ ፡ ወአምጽአ፡ካልአተ፡ኀምሰ፡መካልየ፡እንዘ፡ ይብል ፡ እኮኑ ፡ እግዚእ ፡ ኃምሰ ፡ መካልየ ፡ ወሀብከኒ ፡ ወናሁ ፡ ኀምሰ ፡ መካልየ ፡ እለ ፡ ረባኅኩ፡ዲቤሆን።

፳፩፡ ወይቤሎ ፡ እግዚኡ ፡ አ ፡ ገብር ፡ ኄር ፡ ወምእመን ፡ ዘበውኁድ ፡ ምእመነ ፡ ኮንከ ፡ ዲበ፡ ብዙኅ ፡ እሥይመከ ፡ ባእ ፡ ውስተ ፡ ፍሥሐሁ፡ለእግዚእከ።

፳፪፡ ወመጽአ ፡ ዘክልኤተ ፡ መክሊተ ፡ ነሢአ ፡ ወይቤ ፡ እግዚእ ፡ አኮሁ ፡ ክልኤተ ፡ መካልየ ፡ ወሀብከኒ ፡ ወናሁ ፡ ካልአተ ፡ ክልኤተ ፡ መካልየ፡እለ፡ረባኅኩ፡ዲቤሆን።

፳፫፡ ወይቤሎ ፡ እግዚኡ ፡ አ ፡ ገብር ፡ ኄር ፡ ወምእመን ፡ ዘበውኁድ ፡ ምእመነ ፡ ኮንከ ፡ ዲበ፡ ብዙኅ ፡ እሠይመከ ፡ ባእ ፡ ውስተ ፡ ፍሥሐሁ፡ለእግዚእከ።

፳፬፡ ወመጽአ ፡ ዘአሐተኒ ፡ መክሊተ ፡ ነሢአ ፡ ወይቤሎ፡እግዚእ፡አአምረከ፡ከመ፡ድሩክ፡ ብእሲ፡አንተ፡ተአርር፡እምኀበ፡ኢዘራዕከ፡ ወታስተጋብእ፡እምኀበ፡ኢዘረውከ።

፳፭፡ ወፈሪህየ ፡ ሖርኩ ፡ ወከረይኩ ፡ ምድረ ፡ ወኀባእኩ፡መክሊተከ፡ውስተ፡ምድር፡ናሁ፡ እንከ፡መክሊተከ።

፳፮፡ ወአውሥአ፡እግዚኡ፡ወይቤሎ፡አ፡ገብር፡ ኃካይ፡ወእኩይ፡ተአምረኒኑ፡ከመ፡ብእሲ፡ ድሩክ፡አነ፡አአርር፡እምኀበ፡ኢዘራዕኩ፡ወእ ስተጋብእ፡እምኀበ፡ኢዘረውኩ።

፳፯፡ እምደለወከ ፡ ታግብእ ፡ ወርቅየ ፡ ውስተ ፡ ማዕድየ ፡ ወመጺእየ ፡ እምአስተገበርክዎ ፡ ለልየ፡በርዴ።

፳፰፡ ወይቤሎሙ፡ለእለ፡ይቀውሙ፡ህየ፡ንሥኡ፡ እምኔሁ፡ዘንተ፡መክሊተ፡ወሀብዎ፡ለዘቦቱ፡ ዐሠርቱ፡መክሊት።

፳፱፡ እስመ፡ለኵሉ፡ለዘቦ፡ይሁብዎ፡ወይዌስክዎ፡ ወለዘሰ፡አልቦ፡እለሂ፡ቦ፡የሀይድዎ።

፴፡ ወለገብርሰ ፡ እኩይ ፡ ወኃካይ ፡ አውፅእዎ ፡ አፍአ ፡ ወደይዎ ፡ ውስተ ፡ ጸናፌ ፡ ጽልመት ፡ ኀበ፡ሀሎ፡ብካይ፡ወሐቅየ፡ስነን።

፴፩፡ ወአመ፡ይመጽእ፡ወልደ፡ዕጓለ፡እመሕያው፡

ማክሰኞ፡መዓልት፡በ፲፩፡ሰዓት።

፳፡ አምስት፡መክሊት፡የተቀበለውም፡ቀረበና፡ አቤቱ፡አምስት፡መክሊቶችን፡ሰጥተኸኝ፡ ነበር ። በእነርሱ ፡ ላይ ፡ ያተረፍኳቸው ፡ መክሊቶች፡እነሆ!ብሎ፡ሌሎች፡አምስት፡ መክሊቶችን፡አመጣ።

፳፩፡ ጌታውም፡አንተ፡በጥቂቱ፡የታመንክ፡በጎ፡ አገልጋይ፡በብዙ፡ሀብት፡ላይ፡እሾምሃለሁ፤ ወደ፡ጌታህ፡ተድላ፡ደስታ፡ግባ፡አለው።

፳፪፡ ሁለት ፡ መክሊት ፡ የተቀበለውም ፡ መጥቶ፡ አቤቱ፡ሁለት፡መክሊቶች፡ሰጥተኸኝ፡ነበር፤ እነሆ፤ሌሎች፡ሁለት፡መክሊቶች፡አትርፌ፡ አለሁ፡አለ።

፳፫፡ ጌታውም፡አንተ፡የታመንክ፡በጎ፡አገልጋይ፡ በጥቂቱ፡የታመንክ፡ስለሆነ፡በብዙ፡ሀብት፡ ላይ፡እሾምሃለሁ፤ወደ፡ጌታህ፡ደስታ፡ግባ፡ አለው።

፳፬፡ አንዲት፡መክሊት፡የተቀበለውም፡መጣና፡ እንዲህ ፡ አለ ፤ አንተ ፡ ያልዘራኸውን ፡ የምታጭድ፡ያልበተንከውን፡የምትሰበስብ፡ ጨካኝ፡ሰው፡እንደሆንክ፡አውቃለሁና።

፳፭፡ ስለፈራሁ ፡ ሄድኩና ፡ መሬት ፡ ቆፍሬ ፡ ወርቅህን ፡ በምድር ፡ ውስጥ ፡ ቀበርኩ ፤ እነሆም፡ገንዘብህን፡ውሰድ፡አለ።

፳፮፡ ጌታውም ፡ መልሶ ፡ እንዲህ ፡ አለው ፤ አንተ ፡ ክፉ፡ሰነፍ፡ባሪያ፡እኔ፡ጨካኝ፡ሰው፡ያልዘራ ሁትን ፡ የማጭድ ፤ ያልበተንኩትን ፡ የምሰ በስብ፡መሆኔን፡ታውቃለህን?

፳፯፡ ወርቄን ፡ ወደ ፡ ግምጃ ፡ ቤቱ ፡ ልትመልስ ፡ በተገባህ ፡ ነበር ፤ እኔም ፡ ራሴ ፡ መጥቼ ፡ በትርፍ፡ባሠራሁት፡ነበር።

፳፰፡ ከዚያ ፡ የቆሙትንም ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ፤ ይህን፡መክሊት፡ከሱ፡ተቀብላችሁ፡ዐሥር፡ መክሊት፡ላለው፡ስጡት።

፳፱፡ ላለው ፡ ሁሉ ፡ ይሰጡታል ፤ ይጨምሩለታል ፤ ለሌለው ፡ ግን ፡ ያንኑ ፡ ያለውን ፡ ይወስዱበ ታልና።

፴፡ ክፉዉን ፡ ሰነፍ ፡ ባርያ ፡ ግን ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ አውጡና ፡ ልቅሶና ፡ ጥርስ ፡ ማፋጨት ፡ ወዳለበት፡ወደጽኑ፡ጨለማ፡አግዙት።

፴፩፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ቅዱሳን ፡ መላእክትን ፡

Scanned by CamScanner

## በ፲ወ፩፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘሠሉስ።

በስብሐቲሁ ፡ ወኵሎሙ ፡ መላእክቲሁ ፡ ቅዱሳን ፡ ምስሌሁ ፡ አሜሃ ፡ ይነብር ፡ ዲበ ፡ መንበረ፡ስብሐቲሁ።
፴፪፤ ወይትጋብኡ፡ኵሎሙ፡አሕዛብ፡ቅድሜሁ፡ ወይፈልጦሙ፡ዘዘ፡ዚአሆሙ፡ከመ፡እንተ፡ ይፈልጥ፡ኖላዊ፡አባግዐ፡እምአጣሊ።
፴፫፤ ወያቀውም ፡ አባግዐ ፡ በየማኑ ፡ ወአጣሌ ፡ በፀጋሙ።
፴፬፤ አሜሃ ፡ ይብሎሙ ፡ ንጉሥ ፡ ለእለ ፡ በየማኑ ፡ ንዑ ፡ ኀቤየ ፡ ብሩካኑ ፡ ለአቡየ ፡ ትረሱ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ዘድልው ፡ ለክሙ ፡ እምቅድመ፡ይትፈጠር፡ዓለም።
፴፭፤ እስመ፡ርኀብኩ፡ወአብላዕክሙኒ፤ጸማእኩ፡ወአ ስተይክሙኒ፤ነግደ፡ኮንኩ፡ወተወከፍክሙኒ።
፴፮፤ ዐረቁ ፡ ወአልበስክሙኒ ፡ ደወይኩ ፡ ወሐወጽ ክሙኒ ፡ ተሞቃሕኩ ፡ ወመጻእክሙ ፡ ኀቤየ ፡ ወነበብክሙኒ።
፴፯፤ አሜሃ ፡ ያወሥኡ ፡ ጻድቃን ፡ ወይብሉ ፡ እግዚኦ፡ማእዜኑ፡ርኢናከ፡ርኁበከ፡ወአብላ ዕናከ፡ወጽሙአከ፡ወአስተይናከ።
፴፰፤ ወማእዜ፡ርኢናከ፡እንግዳከ፡ወተወከፍናከ፡ ወዕሩቀከ፡ወአልበስናከ።
፴፱፤ ወድውየከኒ ፡ ወሐወፅናከ ፡ ወሙቁሐከኒ ፡ ወመጻእነ፡ኀቤከ፡ወነበብናከ።
፵፤ ወእምዝ፡ያወሥኦሙ፡ንጉሥ፡ለእለ፡በየማኑ፡ ወይብሎሙ፡አማን፡እብለክሙ፡ኵሎ፡ዘገበ ርክሙ፡ለአሐዱ፡እምእሉ፡ንዑሳን፡አኀውየ፡ እለ፡የአምኑ፡ብየ፡ሊተ፡ገበርክሙ።
፵፩፤ ወእምዝ፡ይብሎሙ፡ለእለ፡በፀጋሙ፡ሑሩ፡ እምኔየ፡ርጉማን፡ውስተ፡እሳት፡ዘለዓለም፡ ዘድልው፡ለሰይጣን፡ወለመላእክቲሁ።
፵፪፤ እስመ ፡ ርኅብኩ ፡ ወኢያብላዕክሙኒ ፡ ጸማእኩ፡ወኢያስተይክሙኒ።
፵፫፤ ነግደ ፡ ኮንኩ ፡ ወኢተወከፍክሙኒ ፡ ዐረቁ ፡ ወኢያልበስክሙኒ ፡ ደወይኩ ፡ ወኢሐወፅ ክሙኒ፡ተሞቃሕኩ፡ወኢመጻእክሙ፡ኀቤየ፡ ወኢነበብክሙኒ።
፵፬፤ አሜሃ፡ያወሥኡ፡እለ፡በፀጋሙ፡ወይብሉ፡ እግዚኦ፡ማእዜ፡ርኢናከ፡ርኁበከ፡ወኢያብላ

## ማክሰኞ፡መዓልት፡በ፲፩፡ሰዓት።

አስከትሎ ፡ በጌትነቱ ፡ በሚመጣበት ፡ ጊዜ ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ በጌትነቱ ፡ ዙፋን ፡ ላይ ፡ ይቀመጣል።
፴፪፤ አሕዛብ ፡ ሁሉ ፡ በፊቱ ፡ ይሰበሰባሉ ፤ እረኛ ፡ በጎችን ፡ ከፍየሎች ፡ እንደሚለያቸው ፡ እየራ ሳቸው፡ይለያቸዋል።
፴፫፤ በጎችን ፡ በቀኙ ፡ ፍየሎችን ፡ በግራው ፡ ያቆማል።
፴፬፤ ያን፡ጊዜ፡ንጉሡ፡በቀኙ፡ያሉትን፡አባቴ፡የባ ረካችሁ፡ዓለም፡ሳይፈጠር፡የተዘጋጀላችሁ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያትን ፡ ትወርሱ ፡ ዘንድ ፡ ወደ፡እኔ፡ኑ፡ይላቸዋል።
፴፭፤ ተርቤ ፡ አብልታችሁኛልና ፤ ተጠምቼ ፡ አጠጥ ታችሁኛልና፤እንግዳ፡ሆኜ፡ተቀብላችሁኛልና።
፴፮፤ ታርዤ ፡ አልብሳችሁኛልና ፡ ታምሜም ፡ ጐብ ኝታችሁኛልና ፡ ታሥሬም ፡ ወደኔ ፡ መጥታችሁ፡አነጋግራችሁኛልና።
፴፯፤ ያን ፡ ጊዜም ፡ ጻድቃን ፡ እንዲህ ፡ ብለው ፡ ይመልሳሉ ፤ አቤቱ ፡ መቼ ፡ ተርበህ ፡ አይተን ፡ አብልተንህ? ፡ መቼ ፡ ተጠምተህ ፡ አይተን ፡ አጠጥተንህ?
፴፰፤ መቼስ፡እንግዳ፡ሆነህ፡አይተን፡ተቀበልንህ? ታርዘህስ፡መቼ፡አለበስንህ?
፴፱፤ መቼ፡ታመህ፡አይተን፡ጐበኘንህ?ታስረህስ፡ ወደ፡አንተ፡መጥተን፡መቼ፡አነጋገርንህ።
፵፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ንጉሡ ፡ መልሶ ፡ በቀኙ ፡ ላሉት ፡ እውነት ፡ እላችኋለሁ ፤ በኔ ፡ ካመኑ ፡ ከእነዚህ ፡ ከታናናሾች ፡ ወንድሞቼ ፡ ለአንዱ ፡ ያደረጋ ችሁት፡ሁሉ፡ለኔ፡አደረጋችሁት፡ይላቸዋል።
፵፩፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በግራው ፡ ያሉትን ፡ እንዲህ ፡ ይላቸዋል ፤ እናንተ ፡ የተረገማችሁ ፡ ለሰይ ጣንና ፡ ለመልእክተኞቹ ፡ ወደ ፡ ተዘጋጀው ፡ ወደ፡ዘላለም፡እሳት፡ሂዱ።
፵፪፤ ተርቤ፡አላበላችሁኝምና፡ተጠምቼ፡አላጠጣ ችሁኝምና።
፵፫፤ እንግዳ ፡ ሆኜ ፡ አልተቀበላችሁኝምና ፡ ታርዤም ፡ አላለበሳችሁኝምና ፡ ታምሜም ፡ አልጎበኛችሁኝምና ፡ ታስሬም ፡ መጥታችሁ ፡ አላነጋገራችሁኝምና።
፵፬፤ ያን ፡ ጊዜም ፡ በግራው ፡ ያሉት ፡ መልሰው ፡ መቼ፡ተርበህ፡አይተንህ፡አናበላህም፡ብለን፤

## በ፲ወ፩፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘሠሉስ።

ዕናከ ፤ ወማዕዜ ፡ ርኢናከ ፡ ጽሙአከ ፡ ወኢያስተይናከ ፤ ወእንግዳከ ፡ ወኢተወከፍናከ ፡ ወዕሩቀከ ፡ ወኢያልበስናከ ፤ ወድውየከኒ ፡ ወኢሐወፅናከ ፡ ወሙቁሐከኒ ፡ ወኢነበብናከ።

፵፭፤ ወእምዝ፡ያወሥኦሙ፡ንጉሥ፡እንዘ፡ይብል፡ አማን፡እብለክሙ፡ዘኢገበርክሙ፡ለአሐዱ፡ እምእሉ ፡ ንዑሳን ፡ አኀውየ ፡ ሊተ ፡ ኢገበርክሙ።

፵፮፤ ወየሐውሩ፡እሉሂ፡ውስተ፡ኵነኔ፡ዘለዓለም፡ ወጻድቃንሰ፡ውስተ፡ሕይወት፡ዘለዓለም።

ምዕ፤፳፮፡፩-፪።

፩፤ ወኮነ ፡ እምዝ ፡ ፈጸመ ፡ እግዚእ ፡ ኢየሱስ ፡ ዘንተ፡ኵሎ፡ነገረ፡ይቤሎሙ፡ለአርዳኢሁ።

፪፤ ተአምሩሁ ፡ ከመ ፡ እምድኅረ ፡ ክልኤ ፡ መዋዕል፡ ይከውን ፡ ፋሲካ ፡ ወይእኅዝዎ ፡ ለወልደ፡ዕጓለእመሕያው፡ወይሰቅልዎ።

ድኅረ፡ወንጌል፡በዐውርቱ፡ወአሐዱ፡ሰዓት፡ መዓልት፡ዘሠሉስ።

፩፤ አ ፡ ለዛቲ ፡ ምሳሌ ፡ አምላካዊት ፡ ዘአንበራ ፡ ንጉሥ፡ስብሐት፡።

፪፤ ኢይትናገር፡በእንተ፡ብእሲ፡ዘፈቀደ፡ነጊደ፡ ወወሀበ ፡ ንዋዮ ፡ ለአግብርቲሁ ፡ ኃምስተ ፡ መክሊተ ፡ ዘወሀበ ፡ ለቀዳማዊ ፤ ወክልኤተ ፡ መክሊተ፡ለካልኡ፡ወአሐደ፡ለሣልሱ።

፫፤ ያኤምር ፡ ኪያሆሙ ፡ ኀበ ፡ ሊቃነ ፡ ካህናት ፡ ወእለ፡ ሥርዓታት ፡ እለ ፡ ተወከፉ ፡ ሀብታቲሁ።

፬፤ እስመ ፡ ዘየሐውር ፡ በሥምረተ ፡ መካልይ ፡ ዘነሥአሙ፡ይትካዐበቱ፡ሎቱ።

፭፤ ወዘይትኃከይ፡ወዘኢይገብር፡በከመ፡ትዕዛዘ፡ ቀኖና ፡ መክሊት ፡ ዘተወፈያ ፡ ትትነሣእ ፡ እምኔሁ፡ወትትወሀብ፡ለዘያረብሕ።

፮፤ ወለውእቱሰ፡ገብር፡ኃካይ፡ያወፅእዎ፡አፍአ፡ ወውስተ ፡ ሲኦል ፡ ይወድይዎ ፡ በእንተ ፡ ዘተረከበ፡ከዊኖ፡ኃካየ፡ወኢገብረ፡ምግባረ፡ ሠናይ፡በከመ፡ይደሉ።

## ማክሰኞ፡መዓልት፡በ፲፩፡ሰዓት።

መቼ ፡ ተጠምተህ ፡ አይተንህ ፡ አናጠጣህም፡ ብለን ፤ መቼ፡እንግዳ፡ሆነህ፡አይተንህ፡አንቀበልም፡ብለን ፤ መቼ፡ታርዘህስ፡አይተንህ፡አናለብስህም፡ብለን ፤ መቼ፡ታመህ፡አይተንህ፡አንጐበኝህም፡ብለን ፤ መቼ፡ታስረህስ፡አይተንህ፡ አናነጋግርህ፡ብለን፡ይሉታል።

፵፭፤ ከዚህ፡በኋላ፡ንጉሡ፡መልሶ፡እውነት፡እላችኋለሁ ፤ ከእነዚህ ፡ ከታናናሾቼ ፡ ወንድሞቼ፡ ላንዱ ፡ ያላደረጋችሁት ፡ ለኔ ፡ አላደረጋችሁትም፡ይላቸዋል።

፵፮፤ እነርሱም ፡ ወደ ፡ ዘላለም ፡ ቅጣት ፡ ይሄዳሉ፤ ጻድቃን፡ግን፡ወደ፡ዘላለም፡ሕይወት፡ይሄዳሉ።

ምዕ፤፳፮፡፩-፪።

፩፤ እንዲህም፡ሆነ ፤ ጌታ፡ኢየሱስ፡ይህን፡ሁሉ፡ ነገር፡ተናግሮ፡ከጨረሰ፡በኋላ፡ደቀ፡መዛሙርቱን፡እንዲህ፡አላቸው።

፪፤ ከሁለት፡ቀን፡በኋላ፡ፋሲካ፡እንዲሆን፡ታውቃላችሁ ፤ የሰውን ፡ ልጅም ፡ ይዘው ፡ ይሰቅሉታል።

ማክሰኞ ፡ ከቀኑ ፡ በአሥራ ፡ አንድ ፡ ሰዓት፡ ከወንጌል፡በኋላ፡የሚነበብ።

፩፤ የክብር፡ባለቤት፡ያስቀመጣት፡ለዚህች፡አምላካዊት፡ምሳሌ፡ወዮ!አንክሮ፡ይገባል።

፪፤ ንግድ፡ስለሚፈልግ፡ሰው፡ለባሮቹም፡ለመጀመሪያው፡አምስት፡መክሊት፡ለሁለተኛው፡ ሁለት ፡ ለሦስተኛው ፡ አንድ ፡ መክሊት ገንዘቡን፡ስለሰጣቸው፡ብቻ፡አይናገርም።

፫፤ ስጦታዎቹን ፡ ወደ ፡ ተቀበሉት ፡ ሥርዓት ወደ፡ተሠራላቸው፡የካህናት፡አለቆች፡የምስክታል፡እንጂ።

፬፤ መክሊቱን ፡ ለማትረፍ ፡ ወደ ፡ የሄደ ፡ የመክሊቶች፡ትርፍ፡እጥፍ፡ይሆንለታልና።

፭፤ በመክሊቱ፡ነግዶ፡ማትረፍ፡እንደሚገባው፡ ሥርዓት ፡ እንደታዘዘ ፡ የማይሠራ ፡ የሚሰፈውን፡ያችው፡ያለችው፡ከእርሱ፡ተወስዳ፡ ለሚያተርፍባት፡ትሰጣለች።

፮፤ ያንን ፡ ሰነፍ ፡ ባርያ ፡ ግን ፡ እንደሚገባ ፡ በጎ፡ ሥራ ፡ ስላልሠራና ፡ ሰነፍ ፡ ታካች ፡ ሆኖ፡ ስለተገኘ ፡ ወደ ፡ ወጭ ፡ ያስወጡታል ፡ ወደ ሲኦልም፡ያስገቡታል።

Scanned by CamScanner

በ፲፩፡ሰዓተ፡ሌሊት፡ዘረቡዕ።

ንሕነኒ፡ለንግበር፡ሠናያተ፡ወናሥምሮ፡ለአ
ምላክነ፡በምግባራቲነ፡ትሩፋት፡ወናእኵቶ፡
ለጸጋዊ፡በእንተ፡ብዝኁ፡ሀብታቲሁ።

ክርስቶስ፡መድኃኒነ፡መጽአ፡ወሐመ፡ወበሕ
ማማቲሁ፡አድኃነነ።

ጸልዩ፡በእንተ፡ጽንዐ፡ዛቲ፡በል።።
ማኅተመ፡ጸሎትሰ፡ከመ፡ቀዳሚ፡ፈጽም።

ረቡዕ፡ሌሊት፡በ፲፩፡ሰዓት።

፯፤ እኛም፡በጎ፡ሥራ፡እንሥራ፤ፍጹማን፡በሆኑ፡
ሥራዎችም፡ፈጣሪያችንን፡ደስ፡እናሰኘው።ስለ፡
ብዙ፡ስጦታዎቹም፡ሰጪውን፡እናመስግነው።

መድኃኒታችን ፡ ክርስቶስ ፡ ሰው ፡ ሁኖ ፡
መከራ፡ተቀበለ፡በመከራውም፡አዳነን።

ጸልዩ፡በእንተ፡ጽንዐ፡ዛቲ፡በል።
የጸሎቱ፡መፈጸሚያ፡እንደ፡ፊተኛው፡ነው።

Scanned by CamScanner